
ሕዝብና አስተዳደር



ሞ ራ ል

ከይድነቃቸው ተሰማ

FESSEHA ALEMAYEHU MULUGETA YOHANNES

በማርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት
ዘኢትዮጵያ በሠላሳ ሁለተኛው ዘመነ መንግሥት

አዲስ አበባ ፲፱፻፸፬ ዓ ም

በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ታተመ ቁ 7439



ግርማዊ ሆይ

ሕዝብና አስተዳደር የተባለችውን ይህችን መጽሐፍ ያዘጋጀሁት ዝቅተኛ አገልጋይዎ በተለምዶ ደራሲ አይደለሁም ። ምንም እንኳን ለልዩ ልዩ መሥሪያ ቤቶች ሥራቸውን ስለሚመለከቱ ጉዳዮች ብዙዎች መጽሐፎችና ደንቦች ባዘጋጅም ፥ በራሴ ስም ጠቅላላውን ጥቅም የሚመለከት መጽሐፍ አስካሁን አላዘጋጀሁም ነበረ ።

ሕዝብና አስተዳደር በተባለው አርዕስት ስር ለመጻፍ በሰሜያል ሳይንስ ፤ የበቃ ትምሕርት ማግኘት አስፈላጊ መሆኑን አውቃለሁ ። ቢሆንም ልዩ ልዩ መጽሐፍት በማንበብ ራሴ ለመረዳት የቻልኩትን ያህል ሌሎችም ቢያውቁ የሚጠቅም መሰሎ ስለታየኝ ለማዘጋጀት ደፍሬያለሁ ።

ኢትዮጵያ ከግርማዊነትዎ በተሰጣት ሕገ መንግሥት መሠረት የምትተዳደር መሆኗ ብዙ ጊዜ የተነገረና የተገ

ለጸ ቢሆንም ፤ አብዛኛው ሰው ሕገ መንግሥት ማግኘቱ ዋ ጋው የቱን ያህል እንደሆነ እንደሚበቃ ለማወቅና ለመገ ንዘብ ገና ባለመቻሉ ተገቢውን ግምት አልሰጠውም ፤ ስለ ዚህ ዋናው ዓላማዬ ሕዝቡ በሕገ መንግሥቱ የታወጀውን በዝርዝር ለመረዳት እንዲችልና ሕገ መንግሥቱ በሰጠው መብት እንዲሠራበት ፤ የተጣለበትን ተግባር እንዲፈጽ ምና የግርማዊነትዎ ውለታ የቱን ያህል እንደሆነ እንዲያ ውቀው ነው ።

በራሴ በኩል ግን መጽሐፉን ራሱን ሳዘጋጅ ምኞቴ የቀድሞዎቹ ነገሥታት ያላደረጉትን ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀረብኝ ብሎ ያላሳሰብዎትን ፥ ሊነሱት ችሎታ ሲኖርዎ በፈቃድዎ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሕዝብዎ ሕገ መንግሥት በ መስጠትዎ ፍጹም አድናቂና ባለውለታ መሆኔን ለመግለጽ ነው ።

ይድነቃቸው ተሰማ

ማስተዋወቂያ

አንባቢ ሆይ ፤

የዚህ መጽሐፍ ዓይነተኛ ዓላማ ምን እንደሆነ በመጀ መሪያው ገጽ ላይ አስረድቻለሁ ። ሕዝብና አስተዳደር ፥ ሕገ መንግሥት ፥ ለያንዳንዱ ሰው የሰጡት መብት ብቻ ሳይ ሆን ተግባርም ጭምር ነውና በተሰጠው መብት መጠቀም የሚመኝ ሁሉ ለውጡን የተጣለበትን ተግባር መፈጸምም መልመድ አለበት ።

የመጽሐፉ አቀራረብ ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ነው ።

መጽሐፉ በሁለት ላይ ተከፍሏል ፥ መጀመሪያው የሕዝብ ንና የአስተዳደርን ሁኔታ ሲይዝ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በተለይ ስለሞራል የተዘጋጀ ነው ።

ሃሳቤን በቂና እጥጋቢ በሆነ መንገድ ለመግለጽ በማሰብ ያልተሊመዱ ወይም አዳዲስ ቃላቶች በጽሑፉ ውስጥ ለማግ ባት ተገድጃለሁ ። ስለዚህ ከዚህ በሚከተለው ገጽ የነዚህን ቃላቶች ዝርዝር በፊደል ተራ ባማርኛ ፥ እጐኑ ተመዛኙን የውጭ ቃልና ፥ ሶስተኛ የቃሉን ፍች የሚያስረዳ ሰሌዳ አዘ ጋጅቼለታለሁ ።

የመጽሐፉ መጀመሪያ ክፍል በስድስት ምዕራፎች ተከፍ ሏል ።

እንደኛው ስለሕዝብና ስለ መንግሥት ፣ ሁለተኛው የኢትዮጵያን ሕገ መንግሥትና የሥልጣንን አከፋፈል ፤ ሶስተኛው ስለ ግዛቶች አከፋፈል ፣ አራተኛው ስለ ከተሞችና ስለማዘጋጃ ቤቶች ፣ አምስተኛው ስለሚኒስቴሮች ፣ ስድስተኛው ፣ ስለአገረ ሰብ መብትና ተግባሮች ያትታሉ ። በጠቅላላውም የነዚህን ድርጅቶች ዓላማ ፣ አቋቋማቸውንና ፣ የሕዝቡንም ተካፋይነት ጭምር ግልጽ በሆነ መንገድ ለማሰረዳት ሞክሬ ያለሁ ።

በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ፣ በሞራል ረገድ ሰው የሚመራባቸውን ፣ ሕጐች በዘጠኝ አንቀጾች በመክፈል ፣ ማለትም 1 ተጠያቂነት ወይም አላፊነት ፣ 2 (ግብረ ዋጋ) ቅጣት 3 ተባባሪነት 4 ግለ ሰብ 5 ቤተ ሰብ 6 ሕዝብ 7 አገር 8 መንግሥት 9 ኤኮኖሚካዊ ኑሮ በሚሉ አርዕስቶች ነጣ ጥዬ አዘጋጅቼዋለሁ ።

ኢትዮጵያውያን አንባቢዎች ፣ የሚያውቁትም በሃሳቡ እንዲ ስማሙበት ፣ ከዚህ ቀደም የማያውቁትም ፣ ጠቃሚ ነገሮች እንዲያገኙበት ተስፋ አደርጋለሁ ።

አ ዘ ጋ ጅ ው

መጽሐፉን ለማዘጋጀት የጠቀሙኝን የፈረንሣይ መጻሕፍት ለጠቅሙኝና ለረዱኝ ፣ ለሊሴ ገብረ ማርያም ዲሬክተር ለሙሴ ቤርላንና ለሙሴ ኩምባ ጥልቅ የሆነ ምስጋና አቀርባለሁ ፤

ማ ው ጫ

1 ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፣ ማቅረቢያ ።

2 ማስተዋወቂያ ።

3 ማውጫ ።

4 የቃሎች ፍች ።

5 ሰውና አስተዳደር ።

6 ምዕራፍ 1 ሕዝብና መንግሥት ።
ሕዝባዊ ጸጋዎች ።

7 ምዕራፍ 2 የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥትና የሥልጣኖች አከፋፈል ።
ሥልጣን የተለየበት ምክንያት ።
ሕግ አስፈጻሚ ሥልጣን ።
ሕግ አውጭ ሥልጣን ።
የዳኝነት ሥልጣን ።

8 ምዕራፍ 3 የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግዛት አከፋፈል ።

9 ምዕራፍ 4 ከተሞችና ማዘጋጃ ቤቶች ።
የካርታ ክፍል ።
በከተማ ውስጥ የጸጥታ ጥበቃ ።
ትምህርት በከተማ ውስጥ ።
ተራድኦ በከተማ ውስጥ ።
ስለ ማሕበሮች መቋቋም ።

10 ምዕራፍ 5 ሚኒስቴሮች ።
የመንግሥት መ/ቤቶች አስተዳደርና ተግባር ።
የውጭ ግንኙነት
መከላከያ ፣ ጸጥታና ዳኝነት ፣ ትምሕርት ፣
ጤና ጥበቃና ተራድኦ ፣ ገንዘብና አስተዳደር ።
ሕዝባዊ ዕድገት ፣ ንግድና ኢንዱስትሪ ፣ እርሻ ።
ሥራና መገናኛ ። የሚኒስቴሮች ተባባሪነት ።
ሕብረ ግብርና ። የጋራ ሃብትን ሕዝባዊ ስለማ
ድረግ ።

11 ምዕራፍ 6 የአገረሰብ መብትና ተግባሮች ።
ነጻነት ፣ እኩልነት ፣ ተባባሪነት

2ኛ ፣ ክፍል

12 ጥቂት የሞራል ገጾች
13 ምዕራፍ ፣ 1 አላፊነት ።
14 ምዕራፍ ፣ 2 ቅጣት ።
15 ምዕራፍ ፣ 3 ተባባሪነት ።
16 ምዕራፍ ፣ 4 ግላዊ ኑሮ ።
17 ምዕራፍ ፣ 5 ሞራልና የቤት ኑሮ ።
18 ምዕራፍ 6 ፣ ሞራልና ፖለቲካዊ ኑሮ ።
19 ምዕራፍ ፣ 7 ሕዝብ ።
20 ምዕራፍ ፣ 8 መንግሥት ።
21 ምዕራፍ ፣ 9 ሞራልና ኤኮኖሚካዊ ኑሮ ።

ያንዳንድ ቃላት ፍች ፣

ሀ

1. ሕልውና Existence

የመኖር ባሕርይ ፣ ያለ ነገር ፣ ለምሳሌ የእግዚአብሔር ሕልውና (መኖር)

2. ሕብረሰብ ፤ Society

በአንድ ዓይነት ሕጐች ስር የሚተዳደሩ ፍጥረቶች ፣ ሰዎች ፤

3. ሕብረ ግብርና Cooperative

በመተባበር የሚሠራ ሥራ ፤

4. ሕዝብ ፣ Nation

በአንድ አገር ውስጥና ባንድ ሕግ ሥር የሚኖሩ ፣ ነዋሪ የጋራ ጥቅም ያላቸው ሰዎች ባንድ ሲጠሩ ሕዝብ ይባላሉ ። ባንድ አገር አንድ ሕዝብ ብቻ ሲኖር ስለሚችል ፣ የኢትዮጵያ ሕዝቦች ማለት ስሕተት ነው ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ማለት ይገባል ። የኢትዮጵያና የሱዳን ሕዝቦች ለማለት ይቻላል ፣ የሁለት አገር ሕዝቦች ናቸውና ፤

5. ሕይወታዊ Vital

ለሕይወት አስፈላጊ የሆነ ሕዋስ ሕይወታዊ ይባላል ፤ ለምሳሌ ልብ ሕይወታዊ ሕዋስ ነው ፣ እግር ግን አይደለም ። ቃሉን በማስፋፋት እርሻ ለኢትዮጵያ ሕይወታዊ ግብርና ነው ለማለት ይቻላል ።

6. ሕገ መንግሥት Constitution

ሕዝብ የተመሠረተበት ሕግ ፤

7. ሕግ ፣ Lois

የሚደነግጉ ፣ የሚያዙ ፣ የሚፈቅዱ ፣ የሚከለክሉ ደንቦች ፤

ለ

8. ልዩ መብት Privilège
ላንዳንዶች ብቻ በተለይ የተሰጠ መብት ፤

መ

9. ማመንጨት Produire
ሠርቶ ማፍራት ፤ (ለመጽሐፍ)

10. ምዕታመት ፥ Siècle
አንድ መቶ ዓመት ፥ አሁን ያለነው በሃያኛው ምዕታመት ነው ። ክፍለ ዘመን ከማለት የተሻለ ቃል ነው ።

11. ምርጫ Election
ከብዙዎች መካከል በድምጽ ብልጫ መምረጥ ፤

12. ሞኖፖል Monopole
አንድ ዓይነት ነገር ለመሸጥ ላንድ ሰው ፥ ላንድ ማሕበር ወይም ላንድ መንግሥት የሚሰጥ መብት ፤

13. ሞያሕሊና Conscience Professionnelle
አንድ ሰው ተግባሩን በሚፈጽምበት ጊዜ የሚመረኰዝበት የሕሊናው ዳኝነት ነው ።

ሰ

14. ሳንሱር ፥ Censure
የጽሑፎችና የድርሰቶች ፥ የቲአትሮች ፥ የጋዜጦችና ፥ የመሳሰለው ንም ምርመራ ፤

15. ሳይንስ ፤ Science
የተወሰኑ ነገሮችን በትክክልና መረጃ ባለው መንገድ የሚያሳውቅ ጥ በብ ፤ ወይም በጥናት ላይ የተመሠረቱ እውቀቶች ፤

16. ሰንዲካ Syndicat
የጋራ ኤኮኖሚካዊ ጥቅምን ለመጠበቅ የሚቋቋም ማሕበር ፤

17. በስፍራና በጊዜ Espace - Temps
ምሳሌ ፤ አንድ የተወረወረ ድንጋይ እስኪያርፍ ድረስ ፥ በጉዞ ላይ ስ ላለ ፥ ጉዞውን እስከ ጨረሰ ድረስና የሚያርፍበት ስፍራና ጊዜ እስኪታ ወቅ ድረስ በስፍራና በጊዜ ውስጥ ነው ። የሰውም ዘር እንደዚሁ ነው ፤

ሸ

18. ሸማች Consommateur
የገዛውን ነገር በቀጥታ ራሱ በመመገብ በመልበስ የሚጠቀምበት ሰው ነው ፤

19. ሸቀጥ Produit
የአንድ ሰው ፥ ወይም የአንድ ፋብሪካ የሥራ ፍሬ ነው ፤

ቀ

20. ቆንስል Consul
በውጭ አገር የሚኖሩትን የአገሩን ሰዎች መብት የሚጠብቅ ባለሥ ልጣን ነው ፤

በ

21. ባለእጅ Artisan
በእጁቹ የሠራቸውን ሥራዎች የሚሸጥ ነጋዴ ፤

22. ባጀት Budget
ያንድ ድርጅት ወይም ያንድ መንግሥት የገቢና የወጭው ሁኔታ መገ መቻቻ ሂሳብ ፤

23. በይደር ቅጣት Sursis
በይደር የተቀጣ ሰው ፥ ቅጣት ተወስኖበት ፥ ላፈጸጸሙ ቀን ሲሰጥ ነው።

ተ

24. ተባባሪነት Solidarité

ሰው እንዱ ለሌላውና በሌላው እንደሚኖርና እኩሉ ተከፍቶ እኩሉ ሊደሰት የማይችል ፍጡር መሆኑን የሚያስገነዝበን ስሜት ነው ፤

25. ተራድኦ Assistance

ላልተመቻቸው ለመርዳት የተቋቋመ ድርጅት ነው ፤

26. ተግባር Devoir

ልንፈጽመው ግዴታ የሆነ ሥራ ፥ ግዳጅ ፤

27. ታህተምድር Sous - Sol

ከምድር ቅርፊት ሰታች ያለው ሁሉ ፤

28. ትረስት ፤ TRUST

ሰብስቦ በመያዝ ያንድን ገንዘብ አቅዋም ወይም ያንድን ሸቀጥ ዋጋ ከፍ ለማድረግ የሚቋቋሙ ፥ ድርጅቶች ናቸው ፤

ዓ

29. ዓለምአቀፍ Universel

በጠቅላላ ዓለምን የሚመለከት ፤

30. አሐዱነት Unité

አንድ የመሆን ባሕርይ ፤

31. አክባጅ Aggravant

ጥፋትን ይበልጥ ከባድ የሚያደርግ ሁኔታ ፤

32. አገረሰብ Citoyen

ያንድ አገር አባል የሆነ ሰው ፥ (መብትና ተግባር ያለው)

33. አቃላይ Atténuant

ጥፋትን ይበልጥ የሚያቃልል ሁኔታ ፤

34. አንድ ጋብቻ Monogamie

ወንድ ካንዲት ሴት በቀር ፥ ሴት ካንድ ወንድ በቀር ለማግባት የማይች ሉበት ሥርዓት ፤

ወ

35. ወግለበሰ Solennel

በታላቅ ክብርና ሥርዓት የሚፈጸም ነገር ፤

ዘ

36. ዘመንጓድ Contemporains

ባንድ ዘመን ውስጥ የሚኖሩ ፤

ደ

37. ዲክታተር ፤ Dictateur

ሥልጣንን ሁሉ በጁ የሚጨብጥ ፤

38. ዲፕሎማሲ Diplomatie

ኢንተርናሺናል ግንኙነቶችን የማወቅ ጥበብ ፤

39. ዲሞክራሲ Démocratie

በሕዝብ ፈቃድ የመተዳደር ዘዴ ፤

40. ድሕረሞት Outretombe

ከሞት በኋላ ፤

ግ

41. ግለሰብ Individu

ከተመሳሳይ ፍጥረቶች አንዱ ፥ በኛ መጽሐፍ ከሰዎች መካከል አንዱ ማለት ነው ።

42. ግብረኃይል Violence
ሙቢትንና ሕግን ፣ በኃይል መቃወም ፤

43. ግዛተዘውድ Monarchie
ባንድ ዘውድ ስር የመተዳደር ዘዴ ፤

ጸ

44. ጸጋ Vertu
ዘወትር ወደበጐ የሚያዘነብል የመንፈስ ሁኔታ ፤

45. ጽናት Persévérance
ተሥፋ ያለመቁረጥ ባሕርይ ፣

ጠ

46. ጥበት Restriction
መወሰን ፣ መገደብ ፤

ፈ

47. ፍኖተ ሕይወት Destinée
አስቀድሞ የተሰመረ እድል ፤

48. ፈቃደኛነት Volonté
የመንፈስ ብርታት ፣ በኃይል መሻት ፣

T

49. ፖለቲካ Politique
አገር የመምራት ዘዴ ፣ በአስተዋይነት የማከናወን ዘዴ

ሰውና አስተዳደር ፤

በዛሬው ጊዜ በምድር ላይ ፣ ቍጥራቸው ከሁለት ሚሊያርድ በላይ የሚሆኑ ሰዎች በልዩ ልዩ አገሮች ውስጥ ፣ በሕግና በሥርዓት ይተዳደራሉ ። ነገር ግን ሲጀመር ሰው እንደዛሬው በማሕበር እንዳልተቋቋመ የተረጋገጠ ነው ። እያንዳንዱ ሰው ለራሱ ተለይቶ ፣ አድኖ እየበላ በዋሻና ጥግ እየፈለገ እየተኛ ፣ የኖረበት ዘመን አለ ፣ ሰው በምድር ላይ ፣ ከሚኖሩት ፍጡሮች ሁሉ የተለየና የረቀቀ አእምሮ የተሰጠው ስለሆነ ፣ ረሐብን ፣ ብርድን ፣ እውሬውን ፣ ብቸኝነትን ብቻውን አሸንፎ ለመኖር የማይችል መሆኑን ተመራምሮ አውቆ መሰሉን ፍጡር እየፈለገ አብሮ መኖርን ለመደ ። አብረው የሚኖሩት ሰዎች ቍጥርም ከጊዜ ወደጊዜ እየበዛ ሰለሔደ ፤ ሰው ምግቡን እንዳውሬ እያደነና እየተዘዋወረ መፈለጉን ፣ ማለትም ዘላን መሆኑን ትቶ ባንድ በተወሰነ ስፍራ ላይ እያረሰና ከብት እያረባ መኖርን ለመደ ።

በዚያም በተወሰነ ስፍራ ምግቡን ፣ ልብሱን ፣ ምቾቱን ለማግኘት ሰለቻለ ፣ ያስፍራ አገሩ ሆነ ። በአገሩ ውስጥ አቅማቸውን አስተባብረው የሚኖሩት ሰዎች እንድ ሕዝብ ለመሆን ቻሉ ፤ እያንዳንዱም ሰው በሥራው ፍሬ ንብረት ለማበጀት ከመቻሉም በላይ ለማሕበሩም በሥራው ጠቃሚ ሆነ ። ነገር ግን ፣ ሰው ሁሉ እውቀቱ ፤ አቅሙ ፣ ጠባዩ የተለያየ ስለሆነ ብልጡ የዋሁን ፣ አዋቂው ደንቆሮውን ፣ ኃይለኛው ደካማውን ፣ እንዳያጠቃና እንዳይነጥቀው ፤ ሕዝቡ የሚተዳደርበት ሕግ አወጣ ። ሕጉንም የሚያስከብርለት መ

ንግሥት አቋቁሞ ፣ ሕጉን ያፈረሱትን ሰዎች የሚይዝ የፖ
ሊስ ኃይል ሰጠው ፤ ጥፋተኞችም ፣ እንደየጥፋታቸው መ
ጠን ቅጣታቸውን እንዲቀበሉ ፣ ንጹሕም ቢሆኑ እንዲሉ
ቀቁ የሚወሰን የዳኝነት ሥልጣን መሠረተ ፤ በዚህ አካሄን ፣
የሰው ማሕበር ፣ በአንድ አገር ፣ አንድ ሕዝብ ሆኖ ፣ ባንድ
ሕግ ስር ባንድ አስተዳደር ፣ ውስጥ መኖር ላይ ደረሰ ፤
ይህ መጽሐፍ እዚህ ሁኔታ ላይ የደረሰውን ሕዝብና አስተ
ዳደሩን የሚገልጽና የሚያስረዳ ነውና መጀመሪያውን ምዕ
ራፍ ከዚህ እናስከትላለን ።

ምዕራፍ ፤ 1 ፤

ሕዝብና መንግሥት ፣

የሕዝብ ፖሊቲካዊ አስተዳደርና የመንግሥቱ አመራር በታ
ሪክ ውስጥ እየተለዋወጠና እየተሻሻለ የመጣ ነገር ነው ።
በዛሬው ጊዜ ዴሞክራሲ የተባለው አስተዳደር በአብዛኛው
ክፍለ ዓለም ተዘርግቶ ይገኛል ።

በሚከተሉት መስመሮች በሕዝብ አስተዳደር ውስጥ ያሉ
ትን ዋና ዋና ቃሎች ፍቻቸውን እንሰጣለን ።

ሕዝብ ፤ ባንድ በተወሰነ ስፍራ ውስጥ የሚኖሩ ፣ ባንድ ዓይ
ነት አስተዳደር የሚመሩ ፤ አንድ ዓይነት ሕጐች የሚያከ
ብሩ ሰዎች ፣ በደፈናው ሲጠሩ ሕዝብ ይባላሉ ።

መንግሥት ፤ የሕዝቡ ሕጋዊ እንደራሴ ማለት ነው ።
አስተዳደር ፤ በመንግሥቱ ውስጥ ያሉትን ያገሩን ሥራ የሚ
ያከናውኑትን መሥሪያ ቤቶች የሚጠቀልል ስም ነው ።

ልዩ ልዩ ያስተዳደር ዓይነቶች ፤
አገሮችና ሕዝቦች በልዩ ልዩ ያስተዳደር ዘዴ ይመራሉ ።
ከነዚህም ዋና ዋናዎቹ ቀጥሎ የተመለከቱት ናቸው ።

1 ፍጹም ግዛተዘውድ ፤ ይህ አስተዳደር ሕገ መንግሥት
ከመሰጠቱ በፊት የነበረው ፤ የኢትዮጵያ አስተዳደር
ነው ፤ በዚህ መልክ በሚተዳደሩ አገሮች ፤ ንጉሡ ወይ
ም ንጉሠ ነገሥቱ ብቻውን ፍጹም ሥልጣኑን ይዘ ይገ
ዛል ማለት ነው ፤ ግዛተ ዘውድ ራሱ በዘውድ ስር የሚተ
ዳደር አገር ማለት ነው ፤

2 ሕገ መንግሥታዊ ግዛተ ዘውድ ፤ የዛሬው የኢትዮጵያ ፤
አስተዳደር ሕገ መንግሥታዊ ግዛተ ዘውድ ነው ። አገ
ሪቱ በዘውድ የምትገዛ ፣ ነገር ግን ያገዛዙንና ያስተዳደ
ሩን ሁኔታ የሕዝቡን መብትና ግዳጅ ፣ የሚወስኑ ሕ
ጐች አሏት ማለት ነው ። በ1924 ዓ ፡ ም ፡ ከግርማዊ
ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በተሰጠውና በ1948 ዓ ፡ ም ፡ በተ
ሻሻለው ሕገ መንግሥት ሥልጣኑ በዘመናዊ ዴሞክ
ራሲ ሥርዓት ፤ በሕግ አስፈጻሚ ፣ በሕግ አውጭና ፣ በዳ
ኝነት በነዚሁ በሰሱቱ ሥልጣኖች ፣ ተከፋፍልዋል ። የሰ
ውም መብትና ተግባር በሚለው ምዕራፍ የኢትዮጵያ
ሕዝብ ፤ ሰብዓዊ መብቱና ተግባሩ አስደናቂ በሆነ አኳ
ኋን ተጽፎለታል ።

3 ዲክታተራዊ ግዛት ፤ በትውልድና በውርስ ወይም በመ
መረጥ ሳይሆን ፤ ያስተዳደር ሥልጣን ፥ በኃይል በያ
ዘው ባንድ ሰው እጅ ብቻ ሲሆንና ፥ ያለተቆጣጣሪ ሊሠ
ራበት ሲችል ፤ አገሪቱ በዲክታተር ትገዛለች ማለት
ነው ።

4 ሪፐብሊክ ፤ በመሠረቱ ፥ ሕዝብ በመረጠው ፕሬዚዳ
ንት የማስተዳደር ዘዴ ነው ፤ በፕሬዚዳንትና በንጉሥ
መካከል ያለው ልዩነት ፥ ፕሬዚዳንቱ ሥልጣኑን የሚይ
ዘው በመመረጥና ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ሲሆን ፤ ንጉሡ
በውርስና ለዕድሜ ልኩ መሆኑ ብቻ ነው ። ዴሞክራቲ
ካዊ ግዛተ ዘውድና ዴሞክራቲካዊ ሪፐብሊክ ፤ በጣም
የተመሳሰሉ ያስተዳደር ዓይነቶች ናቸው ፤

ዴሞክራሲ ማለት ፤ ሕዝቡ በመንግሥቱ አስተዳደር ተካ
ፋይ የሚሆንበትና ፤ ባብዛኛው ክፍል ውሳኔ የሚተዳደር
በት ዘዴ ነው ። ሕዝቡም በቀጥታ ራሱ ፤ ተሰብሰቦ ውሳኔ
ለመስጠት ብዛቱ ስለማይፈቅድለት ፤ በሱ ስም ሆኖ ሃሳቡ
ንና ፤ እስተያየቱን የሚገልጽ እንደራሴ ፥ በድምጽ ብልጫ
መርጠ ይሾማል ፤ (የሕዝብ እንደራሴዎች)

ሕዝባዊ ጸጋዎች (ጤናነት)

በአገራችን የሕዝብ እንደራሴዎች መምረጥ በ1948 ዓ ፡ ም ፡
ተጀመረ ።

እንደራሴ መምረጥ ማለት ፤ በኔ ሰም ሆኖ ስለአገሪቱ አስተ

ዳደር ሕጐች በሚደረጉ ጥናት ላይ አስተያየት የሚሰጥና
መብቴን የሚጠብቅልኝ ሰው ማድረጌ ነው ፤

እንደራሴ መምረጥ ለአገረ ሰብ የተሰጠው ታላቅ መብት
ነው ። ነገር ግን ምርጫ ፥ በሚደረግበት ጊዜ ሁሉ ብዙዎቹ
ግዴታ የለብንም በማለት ድምጽ ሳይሰጡ ይቀራሉ ። ከ
ብዙ ሺ ዓመቶች በኋላ በተሰጠው በዚህ ታላቅ መብት አለ
መጠቀም ፤ አላዋቂ ያሰኛል ። ባይሆን ፥ ለመመረጥ ከቀረ
ቡት እጩዎች መካከል ፥ የምንፈቅደው አንድም ባይኖር ፤
በሳጥኑ ውስጥ ነጭ ወረቀት መጣል ይሻላል ።

እንደዚህ በምናደርግበትም ጊዜ በጉዳዩ ላይ ያለንን አስተያ
የት መሰጠታችን ነውና ድምጽ እንዳልሰጠን አይቆጠርብ
ንም ። የሚያሳዝ ነው ግድ የለሽ ሆኖ አስተያየት አለመስ
ጠቱ ነው ።

<u>ሕግን ማክበር</u> ፤ ሕግ አገርና ሕዝብ የሚተዳደሩበት ፥ የሰ
ላም ፥ የጸጥታ ፥ የእምነት ፥ መሠረት ስለሆነ ፤ እያንዳንዱ
ሰው ያለማመንታት ሊያስክብረው ይገባል ። ስለዚህ ማንኛ
ውም ሰው ፤ አንዱን ሕግ እኔ አልወደድኩትምና አልፈጽመ
ውም ሊል አይችልም ፤ አብዛኛው ክፍል የተስማማበት ከ
ሆነ ፥ ቢወዱትም ባይወዱትም ሕጉን መቀበልና ማክበር
የዴሞክራሲ ዋናው መሠረት ነው ።

ከሕዝባዊ ተግባሮችም መካከል በተለይ ሊታለፉ የማይ
ቻል ሶስት ነገሮች አሉ ።

— እያንዳንዱ አገረ ሰብ ልጆቹን ማስተማር ወይም
እንዲማሩ ማድረግ አለበት ።

— እያንዳንዱ አገረ ሰብ የሚደርስበትን ግብር ያለማ መንታት መክፈል አለበት ።

— እያንዳንዱ አገረ ሰብ አገሩን እንዳትደፈር በመከ ላከል ወይም ለመከላከል በማዘጋጀት ጊዜ ወደ ኋላ ሊል በፍጹም አይፈቀድለትም ።

ትምሕርት ፣ ግብር መክፈል ፣ ወታደራዊ አገልግሎት ፣ ለአ ገር መሠረታዊ ተፈላጊ ነገሮች ናቸው ።

ሕዝባዊ ንብረት ማክበር ፤ የሕዝብን ከፍተኛ ጥቅም ለማ ዳን ሲባል ፤ የራስን ጥቅም መዘንጋት ተየቀደሰ ተግባር ነው ። አገር በፖለቲካ ፣ በኤኮኖሚ ፣ ባስተዳደር ከፍ ያለ ችግር በገጠማት ጊዜ ፣ ለሕብረቱ ጥቅም ሲል የራሱን ጥ ቅም አላልፎ የማይሰጥና መቸገርን የማይፈቅድ አገረ ሰብ ፣ ከስሱቱ ይልቅ ገልቱነቱን መመስከሩ ነው ።

ዞሮ ዞሮ የራሱ ጥቅም ከአገረ ሰብ ጥቅም ጋር ፣ የተያያዘ መ ሆኑን ባለመገንዘብ ነውና ገልቱ ቢባል ቅር አያሰኝም ።

ም ዕ ራ ፍ 2

የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥትና የሥልጣኖች አከፋፈል፣

አገራችን ኢትዮጵያ ከብዙ ሺ ዓመታት በነጻነቷ ኩርታ የ ኖረች አገር ናት ። አስተዳደርዋም ፤ በፍጹም ግዛተ ዘውድ

ሆኖ እስከ 1923 ዓ ፣ ም ፣ ከቆየ በኋላ ፣ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃ ይለ ሥላሴ በፈቃዳቸው ሕገ መንግሥት ስለሰጡት ፤ ሕገ መንግሥታዊ ግዛተ ዘውድ ሆነች ፤ ሕገ መንግሥቱ ፣ በ1948 ዓ ፣ ም ፣ ተሻሽሎ በበለጠ አኳኋን ዘመናዊና አጥጋቢ ሆኖ ወጣ ።

ሕገ መንግሥቱ ፣ በሰምንት ታላላቅ ምዕራፎች የተከፈለ ነው ።

እንደኛው ምዕራፍ ፤ ስለንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ግዛትና ስለዘውድ አወራረስ ፤

ሁለተኛው ምዕራፍ ፤ ስለንጉሠ ነገሥቱ ሥልጣንና ሥራ ፤

ሶስተኛው ምዕራፍ ፤ ስለሕዝብ መብቶችና ተግባሮች ፤

አራተኛው ምዕራፍ ፤ ስለንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ሚኒስ ትሮች ፤

አምስተኛው ምዕራፍ ፤ ስለሁለቱ ምክር ቤቶች ፤

ስድስተኛው ምዕራፍ ፤ ስለዳኝነት ሥልጣን ፤

ሰባተኛው ምዕራፍ ፤ ስለመንግሥት ገንዘብ ፤

ስምንተኛው ምዕራፍ ፤ ስለጠቅላላ ውሳኔዎች ፤

በዚህ እኳኋን ተሟልቶ የተዘጋጀ ነውና ፣ ሁሉንም በምዕ ራፍ በምዕራፋቸው ፣ አድርገን በሚከተሉት ገጾች ዘርዝረና ቸዋል ።

ሶስት ሥልጣኖች

ከ1923 ዓ ፡ ም ማለትም ከ30 ዓመታት በፊት ፥ አገራችን ኢትዮጵያ ትተዳደርበት የነበረው ፥ ደንብና የገዥዎች ሥልጣን ፥ ዝክረ ነገር ፥ ተብሎ በተሰየመው ከቡር ባላምበራሰ ማሕተመ ሥላሴ ፤ ባዘጋጁት መጽሐፍ ተዘርዝሯል የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ፥ በ1948 ዓ ፡ ም ፡ በተሻሻለው ሕገ መንግሥት መሠረት ብቻ ያገራችንን አስተዳደር ዘርዝሮ መግለጽ ነው ።

ሥልጣን የተለየበት ምክንያት

— መብት መጠበቁን የሚያረጋግጥ ዋስትና የሌለበትና ፥ ሥልጣን በሕግ ያልተለየበት ግሕበር ፥ ሕገ መንግሥት አለው ለማለት አይቻልም ።

ምሳሌ ፤ የሕዝብ እንደራሴዎች ትምሕርት ግዴታ ነው የሚል ሕግ ያወጣሉ ፤

ይህ የሕግ አውጭ ሥልጣን አድራጐት ነው ።
የወጣውን ሕግ ማስፈጸም ፥ መከበሩን መቆጣጠር ፥ ሕግ የሚተላለፉትን ፤ መያዝ ፤ ያስፈልጋል ፥ ይህ በመንግሥቱ በኩል ይፈጸማል ፤

ስለዚህ አስፈጻሚ ሥልጣን ይባላል ፤

አስፈጻሚው ሥልጣን ፥ ጥፋተኞች ከያዘ በኋላ ፥ ራሱ ሊዳኛቸው አይችልም ፤

እፍርድ ፊት ያቀርባቸዋል ፤ ዳኛውም ተከሳሹ ሕግ መጣሱ አለመጣሱን ፤ አስቀድሞ ካረጋገጠ በኋላ ፤ ይበይንበታል ወይም ነጻ ያወጣዋል ፤ ይህ የዳኝነት ሥልጣን አድራጐት ነው ፤

እነዚህ ሶስቱ ሥልጣኖች ያልተለያዩ እንደሆነ ለምሳሌ ያህል ቀጥሎ የተመለከቱት ነገሮች ሊደርሱ ይችላሉ ፤

1 አስፈጻሚው ባለሥልጣን ፥ ትምሕርት ግዴታ ነው የሚል ሕግ ራሱ ያወጣል ። በጉዳዩ ላይ የሕዝቡን ፥ ማለትም በምክር ቤት የሕዝብ እንደራሴዎችን አሳብ አልጠየቀምና ሕጉ በሕዝቡ አብዛኛው ክፍል የተደገፈ ለመሆኑ ፤ እርግጠኛ ሊሆን አይችልም ። በዴሞክራሲ መንፈስ ይህ ሕግ ዋጋ ሊኖረው አይችልም ።

2 አስፈጻሚው ሥልጣን ፥ ሕግን በሚያስፈጽምበት ጊዜ፥ አንድ ሕግ ተላላፊ አግኝቶ ይይዛል ። ከዚያም በኋላ ጉዳዩ እንዲፋጠን በማለት ራሱ ቢዳኘውና ቢፈርድበት እራሱ ከሳሽ ፥ እራሱ ዳኛ መሆኑ ነውና ሕጋዊ ድርጊት ሊሆን አይችልም ፤

3 ሕግ አውጭው ሥልጣን ደግሞ ፥ ሕግን እራሴ አስከብራለሁ ብሎ ቢነሳ ፥ ሊያደርገው የሚችልበት ዘዴ የለውም ፤ የፖሊስ ኃይል ከሌለው ፥ እያንዳንዱ የፓርላሜንት አባል ፥ ራሱ ፖሊስ ሆኖ ወንጀለኞች ሊያሳድድ

አይችልም ። ስለዚህ የሕግ አስፈጻሚ ሥልጣን መኖር በግድ አስፈላጊ ነው ።

ይህ አጭር ምሳሌ የሶስቱ ሥልጣኖች መለየት ላንድ አገር ፍጹም አስፈላጊ መሆኑን ያሳይናል ።

ሕግ አስፈጻሚ ሥልጣን

በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ፥ የሕግ አስፈጻሚነት ሥልጣን የተሰጠው ፥ የሕዝቡ መሪ ለሆነው ለንጉሠ ነገሥቱና በሕጉ መሠረት ሥራውን ለሚያከናውኑ ሚኒስትሮች ነው ። የሚኒስትሮችን ምክር ቤት የሚቆጣጠረው ሕግ አውጭው ሥልጣን ነው ።

ንጉሠ ነገሥቱ ፣

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ ከንግሥት ሳባና ከሰሎሞን ከተወለደው ፥ ከቀዳማዊ ምኒልክ ነገድ ሳይቋረጥ ተያይዞ ከመጣው ከንጉሥ ዛህለ ሥላሴ ፥ ዘር ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፥ ትውልድ የማይወጣ ነው ።

የዘውድ አወራረስ ተራ መስመሩን ይከተላል ፤ ይኸውም ከሕጋዊ ጋብቻ የተወለደ ወንድ ብቻ ይወርሳል ማለት ነው ። ያቀዳደሙ ተራ በሕገ መንግሥቱ ተዘርዝርዋል።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ፥ በኢትዮጵያ አርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን እንዲያምን ግዴታ ነው ።

ንጉሠ ነገሥቱ በመንግሥቱ ላይ ሙሉ ገዥነትና የበላይም ሆኖ በአገሩ ጉዳዮች ላይ ፥ ከፍተኛ ሥልጣን አለው ።

የመሥሪያ ቤቶችን ባለሥልጣኖች መሾም ፥ በማዕረግ ማሳደግ ፥ ማዛወር ፥ መሻር የንጉሠ ነገሥቱ የተለየ መብት ነው ።

የማዘጋጃ ቤቶች ምክር ቤቶች መርጠው ከሚያቀርቡዋቸው ሶስት ሰዎች መካከል ፤ የከተማውን ማዘጋጃ ቤት ገዥ የሚሾም ንጉሠ ነገሥቱ ነው ።

ፓርላሜንቱ እየተሰማማበት ፥ ጦርነት ለማወጅ መብት አለው ።

የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥም እንደመሆኑ መጠን ፥ ለመኰንኖች ማዕረግ መሰጠትና ማሳደግ የንጉሠ ነገሥቱ መብት ነው ።

ከውጭ አገር ጋር የሚደረግን ግንኙነት የበላይ ሆኖ ይመራል ፤ አምባሳደሮችና ሚኒስትሮች እየሾመ የሚልክ ንጉሠ ነገሥቱ ነው ። እንዲሁም ከውጭ አገር የሚመጡትን መልክተኞች የሹመት ደብዳቤያቸውን የሚቀበል እሱ ነው ።

ኢትዮጵያ ከሌሎቹ አገሮች ጋር የምታደርገው ስምምነት ንጉሠ ነገሥቱ ካልፈቀደ ሊጸድቅ አይችልም ።

ይህን የመሳሰሉትን ስምምነቶች በጠቅላላው ሁለቱ ምክር ቤቶች ከተሰማሙባቸው በኋላ ፤ ለንጉሠ ነገሥቱ ይቀርባሉ ።

ንጉሠ ነገሥቱ የመሰናንትና ሌላም ክብር ለመስጠ ትም ፥ ለመንሣትም ፥ አዲስ ኒሻን ለማውጣትም መብት አ ለው ።

ገንዘብ እንዲቀረጽ ፥ እንዲታተምና እንዲወጣ ማድ ረግ የንጉሠ ነገሥቱ መብት ነው ።

የፓርላሜንቱን ሁለቱን ምክር ቤቶች ለማፍረስና ውሳ ኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በአራት ወር ውስጥ መማክር ቶች እንደገና እንዲሾሙ ፥ እንዲመረጡና እንዲሰበሰቡ ለማ ድረግ ይችላል ።

ንጉሠ ነገሥቱ የሕግ አሳቦች ለፓርላሜንቱ ለማቅረብ መ ብት አለው ።

ሕጐችና ድንጋጌዎች ዋጋ ኖሯቸውና ሊሠራባቸው የሚችለው ንጉሠ ነገሥቱ ተቀብሎ ካጠናቸውና ካሳወጃ ቸው በኋላ ነው ።

<u>መንግሥት ፤</u>

የመንግሥቱ ሥራ በንጉሠ ነገሥቱ የበላይ አዛዥነት ፥ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት ፥ በሚመራ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይካሄዳል ፤

የመንግሥቱ አባል ባለሥልጣን የሆነ ሰው ሌላ የግል የተለየ ሥራ ወይም ውክልና ሊኖረው አይችልም ፤ ለምሳሌ ባንድ ጊዜ የንግድ ሚኒስትርና ነጋዴ ለመሆን አይፈቀድም፤

የሚኒስትሮች ዓላማና ተግባር ፤ በምዕራፍ 5 ተዘርዝር ዋል ።

ሕግ አውጪ ሥልጣን

ሕግ የማውጣት ሥልጣን ለሁለት ምክር ቤቶች ተሰጥ ቷል ። አነርሱም ፥ ሕግ መወሰኛና ሕግ መምሪያ ይባላሉ ።

የሕግ መወሰኛ አማካሪዎች ከንጉሠ ነገሥቱ ይሾማሉ፤

የሕግ መምሪያ አማካሪዎች በሕዝብ ድምጽ ይመረ ጣሉ ።

አንድ ሰው ባንድ ጊዜ የሁለቱ ምክር ቤቶች አባል ሊሆን አይችልም ።

የፓርላሜንቱ አባሎች በሕግ የተወሰነላቸውን ደሞዝ ይቀበላሉ ። ፓርላሜንቱ ፥ የመማክርቶቹን ደሞዝ የሚያሳ ድግ ማናቸውንም ሕግ ያወጣ እንደሆነ ያሕግ ሊጸና የሚች ለው ቀጥሎ የሚመረጠው ፓርላሜንት ከተሰበሰበ በኋላ ነው ።

የምክር ቤቱ አባሎችና ሚኒስትሮች በምክር ቤቱ ው ስጥ ባቀረቡት ጽሑፍ ፥ ወይም ባደረጉት ንግግር ምክንያት እይወነጀሉም ፤ ይህ ውሳኔ አሳባቸውን ያለሰጋት ለመግለጽ የሚችሉበት መብት ሰጥቷቸዋል ።

<u>የሕግ አሳብ አቀራረብ ፤</u> ፓርላሜንቱ ለመከራከርና ይ ሁን ብሎ ለመወሰን ፤ የሚችለው አስቀድሞ የሕጉ አሳብ ሲቀርብለት ነው ። የሕግ አሳብም ፤ ማንኛውም ሰው እንዲ ያቀርብ አልተፈቀደለትም ፤ በተለይ ንጉሠ ነገሥቱና ከሁ

ለቱ ምክር ቤቶች አንደኛው አስር ወይም ከአስር በላይ በ ሆኑ ፥ አባሎች የተደገፈ ሲሆን የሕግ አሳብ ማቅረብ ይች ላሉ ።

<u>የድምጽ አሰጣጥ ፤</u> ምክር ቤቶቹ ውሳኔ የሚሰጡት በድ ምጽ ብልጫ ነው ። የድምጾቹ ቍጥር እኩል የሆነ እንደሆነ፥ ፕሬዚዳንቱ ያለበት ወገን ያመዝናል ።

<u>አስቸኳይ ሁኔታ ፤</u> አማካሪዎች በማይሰበሰቡበት ጊዜ፤ አስቸኳይጉዳይየተገኘ ወይምየቀረበእንደሆነንጉሠነገሥቱ ከሕገ መንግሥቱ ጋራየማይቃወሱ፥ሕግሆነው፤ የሚሠራባ ቸውን ድንጋጌዎች ለማወጅ ይችላል ። በዚህ ዓይነት አኳ ኋን የወጡ ሕጐች ፓርላሜንቱ በሚሰበሰብበት ጊዜ ፥ ቀር በውለት ፥ የተቀበላቸው እንደሆነ እንዳሉ ይጸናሉ አለዚያ ፓርላሜንቱ ሳይቀበለው ከቀረበት ቀን ጀምሮ የጸኑ መሆና ቸው ይቀራል ።

<u>የሕዝብ እንደራሴዎች አመራረጥ ፤</u>

አስቀድሞ የንጉሠ ነገሥቱ ግዛት ፥ ሁለት መቶ ሺ ሰው በሚገኝባቸው የምርጫ አውራጃዎች ፤ ይከፈላል ።

ከዚህም በቀር ሰላሳ ሺ የሚሆኑ ሰዎች የሚኖሩበት እያንዳንዱ ከተማ አንድ የሕዝብ እንደራሴ ይኖረዋል ።

ቍጥራቸው ከሰላሳ ሺ በላይ የሆነ እንደሆነ ፥ በተጨ ማሪው በየሃምሳው ሺ ሰው አንድ የሕዝብ እንደራሴ በተጨ ማሪ ይኖራቸዋል ።

ለምሳሌ ባንድ ከተማ 130.000 ሰዎች ቢኖሩ ፥ ለመጀ መሪያው 30.000 ፥ ሰው አንድ የሕዝብ እንደራሴ ፥ በተረፈ ለተጨማሪዎቹ መቶ ሺ ሰዎች በየሃምሳው ሺ አንድ በማ ሰብ ሁለት እንደራሴ ይጨመርና በጠቅላላው ከተማው ሶ ስት እንደራሴ ይኖረዋል ማለት ነው ።

የሕዝብ እንደራሴ ለመምረጥ ዕድሜ 21 ዓመት እንዲ ሞላ ፥ በምርጫው አውራጃ አዘወትሮ ነዋሪና የምርጫ ሕግ የሚጠይቀው ችሎታ ያለው ፥ በትውልድ ኢትዮጵያዊ መ ሆን ያሻል ።

የሕዝብ እንደራሴ ለመሆን ፥ ዕድሜው ከ25 ዓመት ያ ላነሰ ፥ የታመነ ያገር ነዋሪ የሆነ በምርጫው ሕግ ከሚወሰ ነው ያላነሰ ተንቀሳቃሽ ንብረት ወይም ርስት ያለው ፥ በም ርጫ ሕግ የተጠየቀው ፥ ለተመራጭነት የሚያስችለው መ ብት ያልተወሰደበት በትውልድ ኢትዮጵያዊ መሆንን ይጠ ይቃል ።

እሁለቱም ላይ በትውልድ ኢትዮጵያዊ ማለት ፥ ኢትዮ ዮጵያዊ ሆኖ የተወለደ ማለት ነው ።

ሲወለድ የሌላ አገር ዜጋ የነበረና ከተወለደ በኋላ የኢ ትዮጵያን ዜግነት ለማግኘት የቻለ ሰው ለመራጭነትም ለተ መራጭነትም ተገቢ አይደለም ማለት ነው ።

የሕዝብ እንደራሴዎች የሚመረጡት ለአራት ዓመት ነው ።

የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባሎች ፤

በሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ንጉሠ ነገሥቱ ለሰድስት ዓመት የሚሾማቸው የሕግ መወሰኛ ፥ ምክር ቤት አባሎች ይገኙበታል ።

የፓርላሜንቱ ደንቦችና አሠራሮች ባጭሩ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ናቸው ።

ይህ ድርጅት ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚተዳደርበትን ሕግ የሚያጠናና የሚያወጣው አቅዋም ነው ፤ ከ1948 ዓ፡ም፡ ጀምሮ ሕዝቡ የሚመራበት ሕግ በሚወጣበት ሥራ ተካፋይ እንዲሆን ፤ መብት ስለተሰጠው እንደራሴዎቹን ፥ መርጦ ፥ በምክር ቤቱ ተገኝተው በሚጠቅመውና በሚጐዳው ነገር ላይ ተከራክረው ሕጉ እንዲወጣ ወይም እንዳይወጣ ለማድረግ በመቻላቸው ፥ ያላወቀውንና ያልተስማማበትን ሕግ እንደጥንቱ እንዲያከብር መገደዱ ቀረለት ።

ፓርላሜንቱ ፥ ማለትም የሕግአውጭው ሥልጣን ፥ ዋ ናዎቹ ሥራዎች ፤ ሕግን ማውጣት ፤ አስፈጻሚውን ሥል ጣን መቆጣጠርና ፥ ባጀቱን ማጽደቅ ነው ።

ለባጀቱ የሚሆነው ገንዘብ ፥ አብዛኛው ፥ ሕዝብ ከሚከ ፍለው ግብርና ቀረጥ የሚሰበሰብ ስለሆነ ፤ አገባቡንና አወጣ ጡን ፥ ማለትም ባጀቱን ፥ የሕዝብ እንደራሴዎች መርምረው እንዲያጸድቁት መደረጉ ሕግን የተመረኰዘና ትክክለኛ አስ ተያየት ነው ።

የዳኝነት ሥልጣን

በኢትዮጵያ አስተዳደር ሶስተኛው ሥልጣን የዳኝነት ሥልጣን ነው ፤ በሕገ መንግሥቱ ፥ የተሰጠው ደንብ ባጭሩ ቀጥሎ የተመለከተው ነው ።

— የዳኝነት ሥልጣን በሕግ ለተቋቋሙት ፍርድ ቤቶች የ ተሰጠ ነው ።

— ዳኞች በሕግ መሠረት ሲያነጋግሩና ፍርድ ሲሰጡ ነጻ ናቸው ፥ የፍርድ ሥራን በሚሠሩበትም ፤ ጊዜ ከሕግ በቀር በሌላ ሥልጣን አይመሩም ፤

— ዳኞችን የሚሾም ንጉሠ ነገሥቱ ነው ፤

ዳኝነት በሠለጠነ ሕዝብ አስተዳደር እንደፖሊስ እ ቋም ፥ ለማሕበራዊ ኑሮ በቅድሚያ የታሰበበት ድርጅት ነው ። በዛሬ ዘመን ሰው በገዛ ኃይሉ እንዲበቀል ወይም እን ዲከስ አይፈቀድም ፥ በሰዎች መካከል የሚነሱ አከራካሪ ነገሮች ሁሉ በትክክለኛና በሰላማዊ መንገድ በዳኝነት እን ዲታዩ ሥልጣኔ ያስገድዳል ።

በጥንት ዘመናት ፥ ሕዝቡ ተሰብስቦ ራሱ ይፈርድ ነ በረ ፤ ባንዳንድ አገሮች ባላባቱ ወይም ዕድሚያቸውና አስተ ዋይነታቸው የታወቀ ሽማግሌዎች ፍርድ ይሰጡ የነበረበት ጊዜ አለ ።

ነገር ግን ከሮማውያን ሥልጣኔ ወዲህ የፍትሕ ነገር እ ጅግ ሰፊና አስቸጋሪ እየሆነ በመሄዱ ያንድ ወይም የብዙ ሰዎች መልካም ፈቃድ ብቻ ሊያከናውነው አልቻለም ።

ሕግ ብዙ ቅርንጫፍ ያለው ፣ የልዩ አዋቂዎችን ጥናት የሚጠይቅ ጥበብ ነው ። የደንቦችና የሕጐችም ማጠቃላያ እጅግ ሰለበዛ በተለይ ይህንኑ የተማሩና ፣ ያጠኑ ዳኞች ብቻ ሊያውቋቸውና ሊሠሩባቸው ቻሉ ። እፍርድ ፊት በማንኛውም ምክንያት የሚቀርብ አብዛኛው ሰውም እራሱ ለመሟገት የሕግ በቂ ችሎታ ሰላጣ ፣ በዚሁ ተዳዳሪ የሆነ ጠበቃ የተባለ ልዩ ሞያተኛ ፣ መግዛት ግዴታ ሆነበት ።

የፍትሕ ሁለቱ ዋና ክፍሎች ፣ ፍትሐ ብሔርና ፣ የወንጀል መቅጫ ሕግ ናቸው ፤ ፍትሐ ብሔር ፤ ከሰዎች መካከል የሚነሣ ክርክር የሚዳኝበት ሕግ ነው ፤

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ፣ በሕብረ ሰብና በወንጀለኞች መካከል ሰለሚነሳ ክርክር ያለው ዳኝነት ነው ፤

<u>የፍትሐ ብሔር ነገር</u> ፤ የዳኞች ቊጥር እንደፍርድ ቤቱ ከፍተኛነትና ዝቅተኛነት አንድ ወይም ከዚህ የበለጠ ይሆናል ፤ የድምጽ እኩልነት እንዳይኖር ቊጥራቸው ሁልጊዜ ጐዶሎ ይሆናል ።

ተሟጋቾቹ የቀረቡበትን ጉዳይ ያሰማሉ ፤ ጠያቂው ከሳሽ እየተባለ የሚጠራው ፤ በመጀመሪያ ያስረዳል ። ተጠያቂው ተከሳሽ እየተባለ የሚጠራው ለቀረበበት ክስ መልሱን ይሰጣል ፤ ዳኛው ሁለቱን ወገኖች ከሰማ በኋላ ፣ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ይሰጣል ፣ ይህም ውሳኔ <u>ብይን</u> ወይም <u>ፍርድ</u> ይበላል።

ዳኛው ወዲያው ለመበየን ፣ ወይም ጉዳዩን ለማጥናት በቀጠሮ ሊያስተላልፈው ይችላል ። የከሳሹን ሃሳብ በሙሉ ወይም በከፊል ሊቀበለው ወይም ጨርሶ ላይቀበለው ይችላል ።

በሙግቱ ተረቺ የሆነው ወገን ማንኛቸውንም የዳኝነትና የጠበቃ ወጭ ይችላል ፤

በሁለቱ ሰዎች መካከል የተነሳው ክርክር ፣ ለምሳሌ በቦታ ወሰን ፣ ወይም በገንዘብ ብድር አለመክፈል ምክንያት የተነሳ ይሆናል ፤ የዚህ ዓይነት ሙግቶች ሁሉ የፍትሐ ብሔር ነገር ፤ ይባላሉ ።

<u>የወንጀል ነገር</u> ፤ ባንድ ፍርድ ቤት ከተፈቀደው ፍጥነት በላይ መኪና የነዳ አንድ ሰው ወይም አንድ ጸጥታ ያሸበረ ሰው ተከሰዋል ። በዳኛው ፊት እንደ ፍትሐ ብሔር ሙግት ሁሉ ፣ ተከሳሹና አንድ ሌላ ሰው ተቋቁመዋል ፣ ይህ ሰው በተከሳሹ ላይ ቅጣት እንዲወሰንበት ይጠይቃል ፤ እንደ ፍትሐ ብሔር ክሰ ዳኛ ሁለቱንም ከሰማ በኋላ ፍርዱን ይሰጣል ።

ተከሳሹ የተረታ እንደሆነ ፣ ግን እንደ ፍትሐ ብሔር ክሰ የተበደረውን እንዲመልስ ወይም የቦታውን ድንበር እልፍ እንዲያደርግ ብቻ አይፈርድበትም ፤ መቀጫ ወይም እሥራት ፣ (ወይም ሁለቱም) ይጣልበታል ። የረታ እንደሆነ ግን ፣ ነጻ ይለቀቃል ፤ የዚህ አይነት ሙግት የወንጀል ክሰ ይባላል ።

<u>የሕዝብ ከሳሽነት</u> ፤ አውቶሞቢል ነጂውን ወይም አሽባሪውን ሰው ከሶ እዳኝነት ፊት ያቀረበው ሰው ፣ የሚሟገ

ተው በግል በራሱ ስም ሳይሆን ፥ በመንግሥት ሥራ የተቀ መጠ ሰው ነው ፤ አብዛኛውን ጊዜ እንደ የፖሊስ ባልደረባ ነው ። ይህ ሰው እራሱ በቀጥታ ሳይነካ ፥ በምን ምክንያት ፥ በየትኛው መብቱ ፥ በማንስ ስም ሊከስ ቻለ? ይህ ሰው ወን ጀል ሠራ ተብሎ የተከሰሰውን ሰው የሚሞግተው በሕዝብ ስም ሆኖ ነው ፤ ስሙም ሕግ አስከባሪ ይባላል ።

ሁለቱ ሰዎች በወሰን በተጣሉ ጊዜ መሬቱ የዚያም ይሁን የዚህ የራሳቸው ጉዳይ ነውና ሕዝብን የሚያገባው ነገር የለም ። ግን ጥፋተኛው ነጂና አሸባሪው ሰው በሕዝብ ላይ ጉዳት ስላደረሱ ወይም ሊያደርሱ ስለሚችሉ ፥ ሕዝብ በጉዳዩ የግድ መግባት ይኖርበታል ።

ስለዚህ ቀድሞ ለመሬቱ ቅራጭ የተሟገተው ሰው እንዳደረገው ሁሉ ሕዝብ ፥ ወንጀለኛውን በዳኛ ከሰሰው ፥ ተከታተለው ። በተለምዶ አነጋገር ፥ ዳኝነት ወንጀለኛውን ተከታተለው የሚለው አነጋገር ግን ስሕተት ነው ። በዘመ ናዊ ሕግ መሠረት ፤ ዳኝነት ማንንም አይከስም የሚከታተ ልና የሚከስ በሕዝብ ፥ ስም ሆኖ ፥ መንግሥት ነው ። በመሠ ረቱ ፥ መንግሥት ተሟጋችና ዳኛ ለመሆን አይችልም ፤ በዳ ኛው ፊት ከሳሹ መንግሥትና ተከሳሹ ወንጀለኛ እኩል ና ቸው ።

በሕገ መንግሥቱ ዳኝነት ከመንግሥት የተለየና በሕጉ መሠረት ብቻ የሚሠራ ሥልጣን እንዲሆን የተወሰነው ስለ ዚህ ነው ።

ሕጐች ፤ በፍትሐ ብሔርም ሆነ በወንጀል ነገር ፍርድ ቤቱና ዳኞች በተጻፉ ሕጐች መሠረት ነው እንጂ በየጊዜው እንደመሰላቸው ሊፈርዱ አይችሉም ።

ዛሬ በኢትዮጵያ ፤ የፍትሐ ብርሔና የወንጀለኛ መቅጫ ሕጐች በዘመናዊ አገሮች ሥርዓትና መልክ ተዘጋጅተው ይሠራባቸዋል ።

በዳኝነት ሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎች ፤ የአገሪሰቡ ፥ ክ ብር ፥ ንብረትና ፥ ሕይወት በእጃቸው ስለሆነ ፥ ከማንኛቸ ውም አመራር ነጻ መሆን አለባቸው ሲል ሕገ መንግሥቱ ወስኗል ።

ስለዚህ ዳኞችን መሾምና መሻር ፥ ተግባራቸውን በት ክክል እንዲፈጽሙ አስፈላጊውን ዋስትና መስጠት ለን ጉሠ ነገሥቱ ብቻ በተለይ የተሰጠ ሥልጣን ነው ።

ም ዕ ራ ፍ 3

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግዛት አከፋፈል

በኢትዮጵያ አስተዳደር ፥ በአገር ግዛት ሚኒስትር አማ ካይነት ሲከናወን ፤ አገሪቱ በ13 ጠቅላይ ግዛቶች ተከፍላ ለች ፥ አሰራ አራተኛ ኤርትራ ከ1945 ጀምሮ ፥ በፌዴሬሺን ከኢትዮጵያ ተቀላቅላለች ፤

ጠቅላይ ግዛቶች በአውራጃ ፣ አውራጆች በወረዳ ፣ ወረዳዎች በም/ ወረዳ ተከፍለዋል ፤ ጠቅላይ ግዛቶችን የሚያስተዳድር ከንጉሠ ነገሥቱ የተሾመ ፣ ማዕረጉ ከሚኒስትር ጋር ተመዛዛኝ የሆነ ጠቅላይ ገዥ ነው ፤

ጠቅላይ ገዥው ለጠቅላይ ግዛቱ የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ ነው ፤ እንዲሁም ፣ በጠቅላይ ግዛቱ ውስጥ የሚኒስቴሮቹ ወኪል በመሆን ፣ በዚያ የሚገኙትን የሚኒስቴሩን ቅርንጫፎች በበላይነት ይቆጣጠራል ።

የአውራጃ ፣ የወረዳ ፣ የም/ ወረዳ ገዥዎችም የሚሾሙ ከንጉሠ ነገሥቱ ነው ።

ነገር ግን ከም/ ወረዳ እስከ ጠቅላይ ግዛት ድረስ ፣ ዋናው ስፍራ ከተማ ስለሆነ ፤ በሚከተለው ምዕራፍ ስለከተሞችና ስለማዘጋጃ ቤቶች በተለይ እንገልጻለን ።

ም ዕ ራ ፍ 4

ከተሞችና ማዘጋጃ ቤቶች

በኢትዮጵያ ብዙ ትልቅም ትንሽም ከተሞች አሉ ፣ ነገር ግን እንደየአቅማቸው ማዘጋጃ ቤት ሊኖራቸው ይገባል፤

አንድ ከተማ ፣ በራሳቸው ለመተዳደርና የውስጥ ጉዳያቸውን እራሳቸው እንዲመሩ የተወሰነ መብት ያላቸው ሰዎች በአንድነት የሚኖሩበት ስፍራ ነው ፤

ማዘጋጃ ቤት ፤

ማዘጋጃ ቤት ያንድ ከተማ ሰዎች ከተማውን የሚያስተዳድሩበት አቅዋም ነው ፤ ባጀቱንም የሚወስንለት የከተማው ሕዝብ ነው ፤ በማሕበር የሚኖሩም ሰዎች ፤ የተወሰኑ ገቢዎችና ፤ የተወሰኑ ወጭዎች ስላሉዋቸው ሁለቱ የተመዛዘኑ እንዲሆኑ በተቻለ መጠን መድከም አለባቸው ። ስለዚህ የማዘጋጃ ቤቱ ባጀት ፣ በከተማው ሕዝብ ይወሰናል ፤ አብዛኛው ገንዘብ እራሳቸው ከሚከፍሉት የማዘጋጃ ቤት ቀረጥ የተገኘ ስለሆነ ለነሱ ጥቅም ፣ ማለትም ፤ ለከተማው ሕንጻዎች ፣ ለመንገዶች ፣ ለውሃ ሥራና ይህን ለመሳሰለው መውጣት አለበትና ፤ እወጣጡን መቆጣጠር መብታቸው ነው ። ነገር ግን ፤ የከተማው ሕዝብ ሁሉ በጉባዔ ተቀምጦ በጉዳዩ ለመከራከር ስለማይችል ፤ የመቆጣጠርና የማስተዳደር መብታቸውን ፣ ቍጥራቸው ለተወሰነ ሰዎች ወክለው ይሰጣሉ ፤ ማዘጋጃ ቤቱ በከተማው ውስጥ አንድ ድርጅት ያለ ሕንጻ ይይዛል ፤

በውስጡም ዘወትር ፣ ብዙ ሰዎች ሊሰበሰቡና ሊመካከሩ የሚችሉበት ፣ አንድ ሰፊ አዳራሽ ይኖረዋል ፤ የማዘጋጃ ቤት ምክር ቤት ነው ።

የማዘጋጃ ቤት አማካሪዎች ፤ የማዘጋጃ ቤት አማካሪዎች ፣ ብዛታቸው እንደ ከተማው ሰፋትና እንደ ሕዝቡ ፣ መጠን ፤ በተወሰነው ደንብ መሠረት ፣ የከተማው ሕዝብ የሚመርጣቸው ሰዎች ናቸው ፤ እነርሱም በደንበኛ ጉባዔ ፤ አስፈላጊም ሲሆን በልዩ ጉባዔ እየተሰበሰቡ ፤ የከተማውን ጉዳይ ፣ ያጠናሉ ፤ በተለይም ባጀቱን ይወስናሉ ።

በሕገ መንግሥቱ መሠረት ፥ ለክንቲባነት የሚገቡ የሶስት ሰዎች ስም መርጠው ፤ ለንጉሠ ነገሥቱ ያቀርቡና ንጉሠ ነገሥቱ ከሶስት አንዱን ይሾመዋል ።

የቀሩት ምክትል ከንቲባዎች ይሆኑና በተለይም ከንቲባው በሌለበት ጊዜ ፥ የሱን ሥራ ፥ ሊሠሩ ይችላሉ ።

የከንቲባው ተግባሮች ፤ የማዘጋጃ ቤት አማካሪዎች ፥ ተሰብስበው በቀረቡ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣሉ ፤ የሚያስፈጽመው ግን የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት የሆነው ፥ ከንቲባው ነው ።

ከዚህም በቀር ፓርላሜንት የሚያወጣቸው ሕጐች ፤ መንግሥት የሰጣቸው ትዛዞች ፤ በኢትዮጵያ ከተሞች ሁሉ መፈጸም ስላለባቸው ፤ ለሚያስተዳድረው ከተማ ሕዝብ ማስታወቅና ውሳኔው እንዲፈጸም መጠባበቅ የከንቲባው ተግባር ነው ። ለዚህ ሥራ እንዲመቸው ፥ መንግሥት የወጡትን ሕጐችና የመንግሥት ማስታወቂያዎች በየጊዜው ይል ከለታልና እያንዳንዱ የከተማው ሕዝብ እንዲያውቀው ግዴታ ስለሆነ ያስታውቃል ፥ ያስፈጽማልም ።

በማዘጋጃ ቤቱ የሕዝባዊ ሁኔታ መዝገብ እንዲያዝ ያደርጋል ፤

<u>የማዘጋጃ ቤቱ ጽ/ቤትና የገንዘብ አሰተዳደር</u>

ከተማው ትንሽም ይሁን እንደ ጽ/ቤት እንዲኖረው ግዴታ ነው ። በትልልቅ ከተሞች ከፍ ያለ ሕንጻና ሰፊ አሰተዳደር አለው ፤

ማዘጋጃ ቤቱ አንድ ባጀት እንዳለው ባለፉት መስመሮች ጠቅሰናል ፤ ማዘጋጃ ቤቱ ፥ ቀረጥን የመሳሰሉ ገቢዎች አሉት ፤ ለመንገዶች ጥበቃ ፥ ለተማሪ ቤቶች ፥ ለደሞዝ ፥ የሚያደርጋቸው ወጭዎች አሉ ፤ እንደ ከተማው መጠን የሂሳብ መዝገቦች የሚይዙ ሠራተኞች ይኖሩታል ።

ሕዝባዊ ሁኔታ

ሕዝባዊ ሁኔታን የሚከታተለው ክፍል ፥ የያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ፤ ሕይወትና ዋና ዋና ጉዳዮች ይይዛል ፤ ባንድ መሥሪያ ቤት በምንቀጠርበት ጊዜ ፥ ስም ፥ ያባት ስም ፥ እድሜና ይህን የመሳሰሉትን ነገሮች እንጠየቃለን ፤ በቃላችንም ስለምናውቃቸው ለመናገር እንችላለን ፤ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ግን ፥ በኛ ወይም በወላጆቻችን አሰተዋሽነት ብቻ መያዝ የለባቸውም ፤ ባንድ ደንበኛ ስፍራ ላይ እንዲመዘገቡ ያስፈልጋል ።

ያንድ ኢትዮጵያዊ የልደት ፥ የጋብቻ ፥ የሞት ፥ ሰነዶች ፥ ሕዝባዊ ሁኔታው ይባላሉ ፤ እነዚህ ሕዝባዊ ሁኔታን የሚገልጹ ሰነዶች በማያሻማ እኳኋን ተሞልተው እንዲገኙ፥ አስፈላጊ ነው ። እያንዳንዱን ሰው በትክክል ለማወቅ ይጠቅማሉ ። በሕዝባዊና ባስተዳደር ኑሮ በሚፈጸሙ ነገሮች ላይ ሁሉ ትክክለኛነትን ያስከትላሉ ።

የሕዝባዊ ሁኔታ አመዘጋገብ ሥራ በመላው ኢትዮጵያ አልተስፋፋም ፥ ቢሆንም ባንዳንዱ ከተሞች ተጀምረዋልና

በሙሉ እንዲሠራበት ማድረግ በዛሬው ዘመን ላንድ አገር በማዬታ አስፈላጊ ነገር ነው ።

የልደት ሰነድ ፤ አንድ ልጅ ሲወለድ ፥ አላፊው ሰው ፥ አብዛኛውን ጊዜ አባትዬው ። ለከተማው ማዘጋጃ ቤት ማስ ታወቅና ማስመዝገብ አለበት ። በዚህ ጊዜ ለዚሁ ሥራ በተ ቋቋመ ባንድ መዝገብ ላይ የልደቱ ሁኔታ ይሰፍራል ።

የጋብቻ ሰነድ ፤ አንድ ጋብቻ በተፈጸመ ጊዜ ፥ ጋብ ቻው በተፈጸመበት ከተማ ማዘጋጃ ቤት በልዩ መዝገብ ላይ ይመዘገባል ፤ ጋብቻው የተፈጸመበት ከተማ ማዘጋጃ ቤት ባልዬውም ሚስትዬዋም ለተወለዱባቸው ከተሞች ማ ዘጋጃ ቤቶች ያስታውቃሉ ፤ እነዚህም ማዘጋጃ ቤቶች በተጋ ቢዎቹ የልደት ሰነዶች ላይ ጋብቻቸውን ፤ ይመዘግባሉ ።

የቤተ ሰብ ሹም ለሚሆነውም ለባልዬው ፥ የሁለቱን ተጋቢዎች ሕዝባዊ ሁኔታ ፥ የጋብቻቸው ቀንና ስፍራ የተጸ ፈበት የቤተ ሰብ ደብተር የተባለ ይሰጠዋል ። በዚህ ደብ ተር ላይ ባዶ ያልተጻፈባቸው ሰንጠረዦች አሉ ፥ ልጆች በ ተወለዱ ጊዜ አባትዬው ሕዝባዊ ሁኔታቸውን ያሰፍርባቸ ዋል ።

የሞት ሰነድ ፤ አንድ ሰው ሲሞት ወዲያውኑ ሰውየው ለሞተበት ፥ ከተማ ማ/ቤት ማስታወቅ ያስፈልጋል ፥ ማ ዘጋጃ ቤቱ በሙቶች መዝገብ ላይ ሞቱን ያሰፍርና ፥ ሟቹ የተወለደበትን ከተማ ማ/ቤት ያስታውቀዋል ፤ ሟቹ ቤተ ሰብ ያለው የሆነ እንደሆነ ፥ በቤተ ሰብ ደብተር ላይ መሞቱ

ይጸፋል ፤ ሟቹ ሕጻን የሆነ እንደሆነ ፥ በወላጆቹ ደብተር ላይ ይመዘገባል ።

በዚህ ሁኔታ የአንድን ሰው የልደት ሰነድ ሲመለከቱ ፥
የተወለደበትን ጊዜ ፥
እግብቶ እንደሆነና ፥ መች እንደሆነ ፥ ማንንስ እንዳ ገባ ፥
የትስ እንደተዳረ ፥
ሞቶ እንደሆነና ፥ የትና ፥ መቼ እንደሞተ ፥
በቀላሉ ለማወቅ ይቻላል ።

ሕዝባዊ ሁኔታ መዝገቦች ፤

እላይ እንደ ተመለከትነው ፤ የአንድ ማዘጋጃ ቤት ሕዝ ባዊ ሁኔታ ጽ/ቤት ፥ የልደት ፥ የጋብቻ ፥ የሞት ፥ ማለትም ፤ ሶስት መዝገቦች መያዝ አለበት ፤

እነዚህ መዝገቦች ፥ ቅጥር ፥ ገጽና ፥ ምልክት ስለሚደ ረግባቸው ፥ ከውስጡ በድንገትም ሆነ በተንኰል አንድ ገጽ ቢጠፋ ወዲያው ይታወቃል ።

በተጨማሪም የመዝገቦቹ አንዳንድ ግልባጭ ለብሔ ራዊ ፍርድ ቤት ስለሚላክ ፥ አንዱ መዝገብ ቢጠፋ ፥ በዚያ ለመቆጣጠርና እንደገና ለማስተካከል ይቻላል ።

እነዚህ መዝገቦች ለሕዝብ ግልጽ ናቸው ፤ እያንዳንዱ ከተማ ነዋሪ እሱን የሚመለከተውን ሰነድ ግልባጭ ጠይቆ ለማግኘት መብት አለው ። እነዚህ ግልባጮች ፥ የመዝገቡ ትክክለኛ ቅጂ መሆን አለባቸው ።

የካርታ ክፍል

እንድ ከተማ የመሬቱ ፕላን በካርታ መነሳት አለበት ፤

ቤት የተሠራባቸውም ያልተሠራባቸውም ፤ የልዩ ልዩ ባለንብረቶች ሃብት የከተማ ቦታዎች በድንጋይ ፤ በግንብ ወይም በአጥር ተካለው ይገኛሉ ፤ ብዙ ጊዜ ደግሞ መለያ የሚሆኑ ፤ በመካከላቸው አንድም የሚታይ ነገር ሳይኖር ይቀራልና በመሸጥና በመለወጥ ጊዜ የሚደርሰው በወሰን ክርክር እጅግ ብዙ ነው ። በተለይ በአገራችን የሚያከራክረው ፥ የቦታው ስፋትና ዋጋ ሳይሆን ፥ አብዛኛው ሰው እስከ ሙግት የሚደርሰው ቦታዬ ለምን ተደፈረ ወይም ሲወርድ ሲዋረድ የመጣው ወሰኔ ተነካ በማለት ስለሆነ ፤ የወሰን ክርክር በብዛት ይገኛል ።

የካርታ ፕላን ማንሳት ሥራ ከዚህ ሁሉ ችግር ያድናል ፤ በካርታ ላይ ሁለት ዓይነት ነገሮች ይገኙበታል ፤ አንደኛው ዝርዝር ሁኔታ የተባለው ቦታው የሚገኝበትን ፥ በውስጡ ያለውን ሁሉ ፥ ደን ፥ እትክልት ይህን የመሳሰለ መለያ እንዳለው ያስረዳል ፤

ሁለተኛው ደግሞ ፕላኑ ፥ እንደ ጆግራፊ ካርታ ፥ ወይም እንደ ጦር ፕላን ፥ የተሳለ ሲሆን በአገሮቹ ወይም በስፍራዎቹ ስም ፋንታ ፥ የባለቤቶቹ ስም ይገኝበታል ፤ አንዳንዱ ቁራጭ መሬት ቍጥር ይሰጠዋል ፤

የካርታ ፕላን ሥራ ፥ በየቀኑ የሚሸጥ የሚለወጠውን በማስተካከል ፥ ዕለት በዕለት ፥ ሙሉ መግለጫ ሆኖ መገኘት አለበት ፤

የካርታው ግልባጭ ለባለቤቱ ይሰጠዋልና ፥ ለቦታው ባለቤት ለመሆኑም ምስክሩ ስለሆነ ፤ እሱን እሰይዞ ገንዘብ ሊበደርበት ይችላል ። ማዘጋጃ ቤት ባለርስት የሆነ ሰው ካርታ ጠፍቶበኛልና ዳግመኛ ግልባጭ ይሰጠኝ ሲል ፥ በዕዳ መያዝ አለመያዙን ሳያጣራ የማይሰጠው ባንድ ቦታ ሁለት እንድ ዓይነት ካርታና ሁለት ባለቤቶች ሊኖሩ ስለማይገባ ነው ።

ለወደፊቱ ካርታ ይዞ ፥ ገንዘብ ወይም ሌላም ሃብት የሚያበድር ሰው ሁሉ ከተበዳሪው ጋራ ማዘጋጃ ቤት ካርታ ክፍል ሄዶ ካርታውን ማስያዙን እንዲያስመዘግብ ግዴታ ሳይሆን አይቀርም ። በዚህ ሁኔታ በየጊዜው ካርታውን ይገዥ ዋለሁ የሚል እንዳለ ፥ እያሉ ማስታወቂያ ከማውጣት ካርታው ተይዞ እንደሆነ እዚያው መዝገብ ላይ መያዝ አለመያዙ ስለሚታወቅ በቀጥታ ለመስጠት ወይም ለመከልከል ይቻላል ።

በከተማ ውስጥ የጸጥታ ጥበቃ

<u>የፖሊስ ተግባር</u> ፥ በጥንታውያን የሰው ማኅበሮች ፥ ሥልጣን ኃይል ብቻ ነበረ ።

እንዲህም ማለት ኃይል ያለው ቅጣት ሳይፈራ ፥ መሰ
ረቅ ፥ መግደል ፥ ሲችል ለሱ መቃወሚያው የተሰራቂዎ
ቹና የተገዳዮቹ የመከላከል ፥ አቅም ብቻ ነበረ ። ተበዳ
ዮቹም ተባብረው የኃይለኛውን አድራጐት የሚቃወሙ
በት ዘዴ ካላገኙ ፥ ኑሮዋቸው የሚያሰተማምን ሊሆን
አይችልም ።

ስለዚህ ፥ ሰዎች ጊዜ ሳያባክኑ በመተባበር ፥ የተቀደሰ
ሃብታቸው ፥ ማለት ፥ ከሁሉ በፊት ፥ የራሳቸውና የቤተ ሰባ
ቸው ሕይወት ፥ ቀጥሎም ንብረታቸው እንዲከበር ለማድረግ
ፈለጉ ፤ ይህም ዓላማቸው እንዲፈጸም ፥ ከሕዝቡ መካከል
ቀጥራቸው የተወሰነ ሰዎች መርጠውና ፥ በተለይ አሠልጥ
ነው ደሞዝ እየከፈሉ ፥ የሕዝቡን ሕይወትና ሃብት እንዲጠ
ብቁ እደረጉ ፤

የፖሊስ ኃይል የተመሠረተው በዚህ ዓይነት መንገድ
መሆኑ የታመነ ነው ።

በዛሬው ዘመን የፖሊስ ኃይል ድርጅት እጅግ ሰለተሰ
ፋፋ ፥ ቅርንጫፉ ካገር ወሰን ውጭም ደርሷል ።

ፖሊስ ፤ ባንዳንድ አገሮች የከተማውን ጸጥታ የሚጠ
ብቀው ፥ በማዘጋጃ ቤቱ የሚታዘዝ ፖሊስ ነው ፤ በኢትዮ
ጵያ ፥ የጸጥታ ጥበቃ ሥራ ፥ በጸጥታ ሚኒስቴር ሰር በሚተ
ዳደር ፥ በፖሊስ ኃይል ፥ ይከናወናል ።

ባንድ ከተማ ውስጥ የሚገኙ መገናኛዎች

ባንድ ከተማ ውሰጥ ፥ የባቡር ጣቢያ ፥ የአውቶሞቢል
መንገዶች አብዛኛውን ጊዜ ሰለሚገኙ ፤ በተሽከርካሪ ለሚ
ደረገው ጉዞና ከተማዋ ካገሪቱ ልዩ ልዩ ክፍሎች ጋር ለምታ
ደርገው ግንኙነት ይጠቅማል ። እንዲሁም የፖሰታ አገልግ
ሎት ፥ የቴሌግራምና የሰልክ መገናኛዎች በጽሑፍና በቃል፥
ከወጭው ጋራ በመላላክ የከተማው ሕዝብ ይጠቀምበታል።

ሕዝቡ የሚዘዋወርበት የአውቶቡስ አገልግሎትና ታክ
ሲዎች በብዙዎቹ ከተሞች ውሰጥ ይገኛሉ ።

ከፍተኛ ከተሞች ደግሞ ፥ ከከተማው እልፍ ብሎ የአ
ይሮፕላን ማረፊያ ሰላላቸው ፥ መንገደኛ ፥ ፖስታና ፥ ዕቃ ፥
በፍጥነት ለመዘዋወርና ለማድረስ ምቾት ይሰጣሉ ፤ በከተ
ማ ውሰጥ የትራፊኩን ሥርዓት የሚያሰጠብቅ የተለየ ፖ
ሊስ አለ ።

ትምህርት በከተማ ውስጥ

የትምሕርት ግዴታ ፤ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ መሠ
ረተ ትምሕርት እንዲያገኝ በሕግ የተወሰነ ሰለሆነ ፥ ልጁን
የማያሰተምር ወላጅ ሕዝባዊ ግዳጁን እንዳልፈጸመ ይቆጠ
ራል ። በየከተማዎች ውስጥ የተማሪ ቤቶች አሉ ፤ ነገር ግን

ባለመብቃታቸው ምክንያት ብዙዎቹ ልጆች ያለ ትምህርት ይቀራሉ ።

ሕግ መሠረታዊ ትምህርት መማር ግዴታ ነው ሲል ፣ ልጆቹ ተማሪ ቤት መሄድ አለባቸው ማለቱ አይደለም ። ግዴታ መማሩ ብቻ ነውና ሕጉ እዚህ ላይ የፈለገው ፤ ማንኛውም ሕጻን መሠረታዊ ትምህርት ለመማር በሚፈቀድለት እድሜ ፣ መማር እንጂ ከትምህርት በቀር ቋሚ ሥራ መያዝና ተቀጥሮ መሥራት የለበትም ሲል ነው ፤ ስለዚህ ያንድ መንደር ወይም ወረዳ ሰዎች ተሰብስበው ፤ አዋጥተው ተማሪ ቤት ፣ በመሥራት ወይም አንድ መምህር ለብዙ ቤተ ሰብ ልጆች በመቅጠር ልጆቻቸው መሠረታዊ ትምህርት እንዲያገኙ ለማድረግ ይችላሉ ። ተማሪ ቤት አጣሁ ብሎ ልጅን አለማስተማር ታላቅ በደል ነው ።

ተራድኦ በከተማ ውስጥ

የከተማው ሕዝብና ማዘጋጃ ቤቱ ፣ በተፈጥሮ ጉድለት ወይም በአደጋ ምክንያት ስንኩል የሆኑትን ሁሉ ፣ ችግራቸውን ማቃለል ዓይነተኛ ተግባራቸው ነው ።

እርዳታ ፤ ሰው ሁሉ በደስታና በምቾት ላይ አይገኝም ። በልዩ ልዩ ምክንያቶች ፤ ለምሳሌ በበሽታ ፤ በቤተሰብ አባት መሞት ፣ በሥራ መፍታትና ይህን በመሳሰለ ነገር ፣ አቅም በማጣት ፣ ፍጹምና አሳዛኝ በሆነ ችግር ይጠመዳሉ ። እያንዳንዳችን ፣ እንደየ አቅማችን ፣ እንደዚህ ያሉትን ሰዎች ፣ መርዳት የማይታለፍ ግዴታችን ነው ። ነገር ግን የያንዳንዳችን እቅም እኩስተኛ ስለሆነ ፤ እርዳታው ጥቅም ሊሰጥ የሚችለው በማሕበር ቢደራጅ ነው ።

በጠቅላላው እላይ በተባለው ሁኔታ የሚገኙ ሰዎች ፣ እንዲረዱ በመንግሥት በኩል የተቋቋሙ ሰፊ ድርጅቶች አሉ ፤ ቢሆንም የከተማው ሕዝብ በበኩሉ ደግሞ የተራድኦ ማሕበሮች ማቋቋምና መረዳዳት አለበት ።

ለምሳሌ የበጐ አድራጐት ጽ/ቤት ተቋቁሞ ፣ ከልዩ ልዩ ሰዎች የሚሰጠውን ገንዘብ ፣ ከማዘጋጃ ቤቱ የሚያገኘውን እርዳታና ሌሎችም ስጦታዎች እያደላደሉ ፤ ለተቸገሩ ሰዎችና ፣ ቤተሰቦች በየመጠኑ ማከፋፈል ይችላል ።

ሆስፒታሎችና ፣ የጡረታ ቤቶች ፤ ማዘጋጃ ቤቱ ሆስፒታሎችና የጡረታ ቤቶች ማቋቋም አለበት በመሠረቱ ሁሉቱም ፣ ለችግረኞችና ፣ ለደካሞች የተዘጋጁ ስለሆነ ፣ እርዳታቸውን በነጻ መስጠት አለባቸው ፤ ሆስፒታሎቹ በሽተኞቹን እያስታመሙ ድነው እስኪወጡ ፣ ድረስ ብቻ ይረዷቸዋል ፤

የጡረታ ቤት ግን ደካሞችና ሽማግሌዎች ፣ ቀሪውን እድሜያቸውን ከረሃብ ፣ ከችግርና ከጉዳት ተጠግተው የሚያሳልፉበት ስፍራ ነው ።

የበጐ አድራጐት ጽ/ቤት ፣ ሆስፒታሎች ፣ የጡረታ ቤቶች በጠቅላላው ፣ ማሕበራዊ መረዳጃ ይባላሉ ።

በከተማ ውስጥ ሕዝባዊ ማኅበሮች ።

የተቋቋመውን ሕግ አይጣሱ እንጂ ፣ የሚፈቅዱትን ዓይነት ሥራ ለማከናወን ፣ ብዙዎች ሰዎች በሚመሰላቸው መንገድ ፣ በማሕበር መቋቋም ይችላሉ ።

እስካሁን ድረስ ያጠናነው በሕግ የተወሰኑትን ደን በኛ አቋሞች ፣ ሠራተኞችና ፣ ድርጅቶች ነው ። የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ፣ አገረሰቦች ፣ በሚመሰላቸው መንገድ በማ ሕበር እንዲቋቋሙ ፣ ይፈቅዳል ። ነገር ግን ፣ የማሕበሩ ዓ ላማ ግልጽ እንዲሆንና ፣ አድራጐቱም ሁሉ ፣ የሕብረሰብን ጥቅም የማይነካ እንዲሆን ግዴታ ነው ። ለምሳሌ ያህል ጥቂ ቶች እንጠቅሳለን ።

መንፈሳዊ ሕብረቶች ፤ የኢትዮጵያ መደበኛ ሃይማ ኖት ፣ አርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን መሆኗ በሕገ መንግ ሥቱ ሲነገር ፣ በሌላ ሃይማኖት ማመን ወይም አለማመን ለ ሕዝቡ መብት ሆኖ ተሰጥቷል ፤ ስለዚህ ባንድ ከተማ ውስጥ አርቶዶክሳዊ ፣ ካቶሊካዊ ፣ የፕሮቴስታንት (ወንጌላዊ) ቤተ ክርስቲያኖች ፣ እስላማዊ ፣ መስጊድ ፣ እሥራኤላዊ ፣ ሲና ጐግ ፣ ይታያሉ ፤ በነዚህ ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች የሚያምኑ ሁሉ ፣ በየቤተ ጸሎታቸው እየተሰበሰቡ ፣ የሃይማኖታቸውን ሥርዓት በፍጹም ነጻነት ለማክበር ይችላሉ ።

ፖለቲካዊ ሕብረቶች ፤ ፖለቲካዊ ሕብረቶች በኢትዮ ጵያ አልተቋቋሙም ። ነገር ግን ማንኛውም ሰው ፖለቲካ

ዊ አስተያየቱን ፣ ሕግን ሳይተላለፍ በንግግርም ቢጋዜጣም ለመስጠት ሙሉ መብት አግኝቷል ።

የሠራተኞች ማሕበር ፤ ሕብረት ኃይል ነው የተባለ እምነት አለ ፤ አንድ ዓይነት ሥራ የሚሠሩ ግለ ሰቦች ፣ መጠ በቅ የሚገባቸው የጋራ ጥቅሞች አሏቸው ፤ ለምሳሌ ፣ የሥራ ምኞታቸውን ገቢያቸውን (ደሞዝ ፣ አበል ፣ ትርፍ ፣ የድ ካም ፣ ዋጋ ፣) ለማሻሻል ፣ እንዲሁም ከነሱ መካከል በልዩ ልዩ ምክንያት የራሳቸውንና የቤተ ሰባቸውን ጥቅም ለመጠ በቅ ያልተመቻቸውን ለመርዳት ፣ ይጥራሉ ፤ ስለዚህ የሠራ ተኞች ማሕበር ማቋቋም ጠቃሚ ነው ፤ እነዚህ ማሕበሮች በእንግሊዘኛ ሲንዴኬት ይባላሉ ።

ሠራተኞቹ ራሳቸው ፣ ባለፋብሪካዎችም ፣ ሐኪሞች ፣ መሐንዲሶች ፣ ነጋዴዎች ፣ ጸሐፊዎች ፣ በየበኩላቸው በማ ሕበር ሊቋቋሙ ይችላሉ ፤

እነዚህ ድርጅቶች የሚሰጡት ጥቅም በጣም ከፍ ያለ ነው ፤ ለምሳሌ የግንበኞች ፣ ማሕበር የተቋቋመ እንደሆነ ፤

ሀ) ማንኛውም ግንበኛ ካንድ ከተወሰነ ደሞዝ በታች እንዳይቀጠር በመሰማማት ፤ ቤት ሠሪና ፣ ባለ ሃብት ፣ በአነ ስተኛ ደሞዝ እንዳያጉላላቸው ለማድረግ ይችላሉ ፣ የሥራ ውን ዋጋ በማስቀረት ቀጣሪ እንዳያጉላላውም በሕግ ፊት ተከራካሪ ሆኖ ይቆምለታል ።

ለ) ከሚያገኙት ገንዘብ ላይ የተወሰነ መቶኛ እያዋጡ በማኅበሩ ሣጥን በማኖር ፣ ሥራ በፈቱ ጊዜ ፣ በታመሙ ጊዜ

ወይም ሌላ ጉዳት በደረሰባቸው ጊዜ ፣ የሚተማመኑበት እር ዳታ ያደራጃሉ ፤

መ) የማንበን ሥራ ጥበብ የማሻሻል እርምጃ ለመው ሰድ ያመቻቸዋል ፤ በመሠረቱ ይህን የመሳሰሉ ብዙ ጥቅ ሞች ሊያገኙበት ይችላሉ ። ደግሞ በትልልቆች ከተሞች የሚገኙ የጢም ላጭዎች ሱቆች የጥቂት ሰዎች ንብረት ስለ ሆኑ ፣ ጠንር አሰተካካዮች ቀጥረው ይሠራሉ ፤ የሚከፍሏቸ ውም ጥቂቶች ባለንብረቶች ተሰማምተው የወሰኑትን ፣ ከ መቶ ይህን ያህል ብለው ነው ፤ ከተቀጣሪዎቹ አንዱ ይህን ዋጋ አልቀበልም ቢል ፣ ቀጣሪው ከሥራ ያሰናብተዋል ፤ አን ዱ ያሰናበተውንም ሌላው እንዳይቀጥር በቀጣሪዎች መካ ከል ልዩ ሰምምነት ሰላለ ፣ ይህ ሰው ወይም ሥራ ፈት መ ሆን ፣ ወይም የሠጡትን አበል ተቀብሎ መሥራት አለበት ፤ ነገር ግን ተቀጣሪዎቹ ማሕበር ቢያበጁና ጥቅምና መብታ ቸው በሱ አማካይነት እንዲጠበቅ ቢያደርጉ ተገቢ ደሞዝ ለማግኘትና ሰባዓዊ ያልሆነ በደል እንዳይፈጸምባቸው ለመ ከላከል በቻሉ ነበር ፤

በሥነ ፣ ጥበብ ረገድ ደግሞ ፣ ሙዚቀኞች ፣ ደራሲዮች እንደዚሁ በማሕበር እየተቋቋሙ ሥራቸውን ለማስፋፋት ችለዋል ፤

<u>ስፖርታዊ ማህበሮች ፤</u> በግለሰብ ሊደረጉ የሚችሉ ብዙ እስፖርቶች አሉ ፣ አብዛኞቹ ግን በብዙ ሰዎች መካ ከል የሚደረጉ ናቸው ፤ ስለዚህ የነዚህ ስፖርት አፍቃሪዎች፣ በግድ በማሕበር መቋቋም አለባቸው ። ለምሳሌ ቴኒስ ፣ ፉት

ቦል ወይም ቦክስ የሚያዘወትሩ ሰዎች መጫዋቻቸውን ስፍ ራና መለማመጃውን ቤት እያንዳንዳቸው ፣ ሊያሠሩ ያስቸ ግራልና ፣ ማሕበርተኞቹ ለሆኑት ሁሉ አስፈላጊውን ስፍ ራ በመግዛት ወይም በመከራየት በሚያቀርብላቸው ባንድ ማሕበር መመዝገብ ይኖርባቸዋል ። ይህም ማሕበር ስፖር ታዊ ማሕበር ይባላል ። የነዚህ ማሕበሮች መቋቋም ለማሕ በራዊ ኑሮ የሚሰጠው ጥቅም ፣ ከፍ ያለ ግምት አለው ፤ በተ ለይም በዛሬው የሥልጣኔ ዘመን ፤ ሰው በተፈጥሮ የተሰጠ ውን አካሉን ከድካም ለማዳን በቴክኒክና ፣ በመኪና አገል ግሎት እየተጠቀመ ፣ ጣትን እንኳን ሳያንቀሳቅስ ፣ ለመኖር የሚችልበትን መንገድ ይፈልጋል ። የሰው አካልም ፣ ሲፈ ጠር የተመደበለትን ፣ ሥራ ሲተው ፣ መቀጨጩና ፣ መድ ከሙ ፣ የተመረመረና የተረጋገጠ ስለሆነ ፣ በሥራ ምክን ያት ፣ ያገኘው የነበረውን አሁን ግን የተከለከለውን ቅስ ቃሴ ፣ በሌላ ዘዴ ለማግኘት እንዲችል ማድረግ ግዴታ ነው ደግሞም ሰው ዕውቀቱን እያራቀቀ በምድር ላይ ብቻ ሳይ ሆን ከምድርም ውጭ ያሉትን ኃይሎች በቴክኒኩ ሊገዛቸ ውና ሊጠቀምባቸው በብዙ ስለሚደክም ፣ ከፍ ያለ አእምሮ ያስፈልገዋል ። ይህም አእምሮ ሊኖር የሚችለው በጤናማና በብርቱ አካል ውስጥ ብቻ መሆኑ ከጥንት ጀምሮ የተነገረና የታመነ ስለሆነ ፣ አካሉን ችላ ሊለውና ለነፍሳቸው ያደሩ ሰዎች ያደርጉት እንደነበረ ሁሉ፣ሊያጐሳቅለው አይችልም።

ዳግመኛም እስፖርት የሰውን አካላዊ ጤንነትና ጥን ካሬ በመጠበቁ ፣ ለአገሪቱና ለሕብረ ሰብ ከፍ ያለ አገልግ ሎት ሊያቀዳጁ የሚችሉ ሰዎች ያተርፋል ። በስፖርት ውድ

ድሮችም ሰው በመወዳደር ድፍረትን ፣ መሸነፍን በሰላም በመቀበል ፣ ትግስትንና እውነተኛነትን ፣ ማሕበረተኛ መሆንና ሕጉንም በማክበር ፣ ሰልጡንነትንና የሕብረት መንፈስን ፣ እነዚህን የመሳሰሉ ሞራላዊ ባሕርዮችን ስለሚሳተፍ ፤ ስፖርት የአካል ብቻ ሳይሆን የመንፈስም መድህን ነው ። ስለዚህ ያንድ ከተማ ሕዝብ ፣ ልጆቹ ፣ ወንድሞቹ ፣ እሱ ራሱ ፣ በስፖርትና በሚያስከትለውም ጸጋ ለመጠቀምና ለሕብረሰብ ተገቢ ሰዎች በማግኘት ፣ ማሕበሩን ፣ ራሱን ለማጠንከር ፣ በከተማው ውስጥ ፣ የስፖርት ማሕበሮች ማቋቋም ፣ በገንዘብ መርዳትና ስታዲዮሞች መሥራት የማይዘነጋ ተግባሩ ነው ።

ስለማኅበሮች መቋቋም ከመንግሥት የሚጠየቀው ።

ማሕበር ማቋቋም በሕግ ያልተከለከለ መሆኑን ባለፉት መስመሮች ፣ ገልጸናል ። መንግሥት እንዲያመለክቱ ብቻ ይጠይቃል ። በማመልከቻው ላይ የማሕበሩን መጠሪያ ትክክለኛ ፣ ስም ፣ ዓላማውንና መሥሪያ ቤቱ የሚገኝበትን ሥፍራ ፣ መዘርዘር ያስፈልጋል ፤ ይህ ማመልከቻ ፤ ባዲስ አበባ ባገር ግዛት ሚኒስቴር ፣ በሌላ ከተማ ሲሆን ለግዛቱ ጽ/ቤት መድረስ አለበት ። ባለፉት ገጾች ባጭሩ ስለከተማና ስለማዘጋጃ ቤቱ አስተዳደር ጽፈናል ፣ ባጭሩም ስንመለከተው ፤ ከተማ በከተማ ሕዝብ ወኪሎች መመራቱን ፣ በውስጡ የሚፈጽማቸውን ዋና ዋና ተግባሮች ዘርዝረናል ፤

በተረፈ የከተማው ሕዝብ ፤ የተወለደበትን ወይም የሚኖርበትን ከተማ መውደድ ይገባዋል ። ይህ የራስ ከተማ ፍቅር ያገርን ፍቅር በምንም አኳኋን አይቀንሰውም ።

እንዲያውም ይህ ከሥር የተጀመረ ፍቅር ለታላቁ ለአገር ፍቅር በበለጠ አኳኋን ፤ ትምሕርትና መዘጋጃ ይሆናል።

ስለዚህ የከተማው ሕዝብ እያንዳንዱ ውበቷን መጠበቅና እየተሻሻለች እንድትሄድ ከተማውን መርዳት አይነተኛ ተግባሩ ነው ።

ም ዕ ራ ፍ 5 ፤

ሚኒስቴሮች ።

ባለፉት ገጾች የኢትዮጵያን አስተዳደር አከፋፈል ፣ የከተሞችን አኗኗርና የማዘጋጃ ቤቶችን ተግባሮች ገልጸናል ፣ ነገር ግን ጠቅላይ ግዛቶችና በውስጣቸው ያሉት መሥሪያ ቤቶች ፣ ተጠቃለው ፣ በዋናው ከተማ በአዲስ አበባ ላይ በሚገኙ ሚኒስቴሮች ይመራሉ ።

ለምሳሌ የወረዳ ገዥያችሁ አንድ አዋጅ ቢያሰማችሁ ፣ ይህ አዋጅ ፣ በመጀመሪያ ፣ ከአገር ግዛት ሚኒስቴሩ ፣ ለጠቅላይ ግዛቱ ፣ ከጠቅላይ ግዛቱ ፣ ለአውራጃው ለወረዳው ፣ ሲተላለፍ የመጣ ነው እንጂ ፣ በቀጥታ ከወረዳው የፈለቀ አይደለም ።

ጥበቃ ሚኒስትር በግዴታ ሐኪም መሆን የለበትም ፥ የሥራ ሚኒስትር በግዴታ መሐንዲስ እንዲሆን አያስፈልግም ፥ የሚኒስትሮች ተግባር ማስተዳደርና መምራት ስለሆነ ባንድ ዓይነት የትምሕርት ቅርንጫፍ የበቃ ብስለት ካላቸው ማንኛውንም ሚኒስቴር ለመምራት ይችላሉ ።

ሚኒስትሩ በቀጥታ ራሱ የሚቆጣጠረው ልዩ ጽሕፈት ቤት እንዲኖረው ያስፈልጋል ።

ባንድ ሚኒስቴር ውስጥ ልዩ ልዩ ድሬክሲዮኖችና ፥ የጽሕፈቱን ሥራ በጠቅላላ የሚያከናውን ፤ አንድ ዋና ጽሕፈት ቤት አለ ።

የሚኒስትሩ ትዕዛዝ በትክክል መፈጸማቸውን ፥ በስፍራው ላይ ሆኖ ለመመርመርና ፥ የምርመራውንም ፍሬና ፥ ያስተዳደሩን ሁኔታ ለሚኒስትሩ ለመግለጽ የተቋቋመ ፤ አንድ የኢንስፔክተሮች ጽ/ቤት አለ ።

ተግባራቸውም በየጠቅላይ ግዛቱ እየተዘዋወሩ የሚኒስቴሩን መ/ቤቶችና ሠራተኞቹን በመቆጣጠር ሥራው በምን አኳኋን እንደሚመራ ፥ የተገኘውን ጉድለት ፥ ለወደፊቱ ማድረግ የሚገባውን መሻሻል ሁሉ መግለጽ ነው ።

የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አስተዳደርና ተግባር ።

መንግሥት ፥ የሕዝቡን ጠቅላላ ጥቅሞች ለመጠበቅ ፥ ከአገረሰቡ በተሰጠው አደራ መሠረት የአገሪቱን መሬት አለ

ሚኒስቴር ማለት ምን ማለት ነው ? ፥ ሚኒስቴሮች የኢትዮጵያ ያንድ ክፍል ጉዳይ ሳይሆን ፤ መላ አገሩን የሚመለከቱት ጉዳዮች ሁሉ የሚፈጸሙባቸው አቋሞች ናቸው ።

የሚኒስቴሮች ዋና መሥሪያ ቤቶች ሁሉ የሚገኙት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ነው ፤ ነገር ግን በየጠቅላይ ግዛቱ የያንዳንዱ ሚኒስቴር አንድ ድሬክሲዮን ይገኛል ።

የሚኒስቴሮች ሕንጻዎች ታላላቅና በጥሩ አኳኋን የተሠሩ ናቸው፤በተለይም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብዙ የውጭ እንግዶች ስለሚቀበል ፥ ጥሩ፥ ጥሩ፥ ሳሎኖች ያስፈልጉታል።

ሚኒስትር ፤ ከላቲን ፥ ሚኒስተር ፥ ማለት አገልጋይ ከሚለው ቃል የፈለቀ ስም ነው ፤ ስለዚህ የመንግሥቱ አገልጋይ ነው ። ብዙዎቹ የሚኒስትር ሥራ ማዘዝ ብቻ እየመሰላቸው እንዴት አገልጋይ ይባላል የሚሉ አሉ ፤ ነገር ግን ፥ ትዕዛዝም ቢሰጥ በመንግሥት ስምና ፥ ለሕዝብ አገልግሎቶት ነው እንጂ በራሱ ስምና ለራሱ አገልግሎት አይደለም ፤ በዚህም የተነሳ ፥ የሕዝብ እንደራሴ የሆኑት የፓርላሜንት አባሎች ሥራውን ይቆጣጠሩታል ።

በዴሞክራቲክ አገሮች ለሚኒስትር ሕጋዊና ሞራላዊ ሥልጣኑን የሚሰጠው ይህ ሁኔታ ነው ።

ልዩ ልዩ ከፍያለ የሥራ ክፍል ባለባቸው ሚኒስቴሮች፥እያንዳንዱን ክፍል የሚመሩ፥ምክትል ሚኒስቴሮች አሏቸው።

ሚኒስትሮች እንደሚታሰበው ሁሉ የሚኒስቴራቸውን ሥራ በተለይ የተማሩ መሆን የለባቸውም ፥ ለምሳሌ ፥ የጤና

ማስደፈር ፤ ዳኝነትንና ፥ በአገሩ ውስጥ ጸጥታን ማስከበር ፥ የሕዝቡን አካላዊ ጤናና ፥ የአእምሮ ማጐልመሻ ፥ ማደራጀት ዓይነተኛ ግዳጁ ነው ። ባንድ አገር ውስጥ የሚቋቋሙትን ሚኒስቴሮች ቍጥር ለመወሰን አስቸጋሪ ነው ። አገሪቱ የምትገኝበት ሁኔታ ፥ አንዳንድ ጊዜ አዲስ ሚኒስቴሮች እንዲፈጠሩ ፥ ሲጠየቅ ፥ በሌላ ጊዜ ደግሞ ሁለት ሶስት ሚኒስቴሮች ባንድ እንዲጠቃለሉ አስፈላጊ ሆኖ ይገኛል ።

ስለዚህ አስቀድሞ መንግሥቱ የሚፈጽማቸውን የአስተዳደር ተግባሮችና የትኛው ሚኒስቴር ሊፈጽማቸው እንደሚገባ ፥ ለይቶ ማወቁ ይጠቅማልና ዋና ዋኖቹን በሚከተሉት መስመሮች እንገልጻለን ።

የመጀመሪያ ዋና ተግባር ፥ የአገሪቱን ምድር አንድነት አስከብሮ መኖር ነው ።

ይህም እንዲሆን ፥ መንግሥት ከሌሎች መንግሥታት ጋር የማይጸረጥ ግንኙነት ማድረግ ፥ ይኖርበታል ፤ ይህ የዲፕሎማሲና የውጭ ጉዳይ ሥራ ነው ።

የአገሪቱ መሬት በተጠቃ ጊዜ ፥ ለመንግሥት ፥ ገንዘቡን (ግብር) ፥ ጊዜውን (ወታደራዊ ግልጋሎት) አንዳንዴም ደሙን ፥ (በጦርነት ጊዜ) የሚሰጠው ፥ ሕዝቡ ፥ መንግሥትን ደግሞ በፋንታው ፥ በዚህ በተሰጠው ኃይል ፥ ያገሪቱን መሬት አንድነት ፥ የአገረሰቡንና የቤተ ሰቡን ሕይወትና ሐብት ፥ እንዲከላከልና እንዲያሰጥል ሊጠይቀው ይችላል ።

ይህ የመከላከያ ሚኒስቴር ሥራ ነው ፤ የጦር ጉዳት ካሣ መክፈል ደንብ የተመሠረተው ፥ ከዚህ በላይ በተጠቀሰው ውል መሠረት ነው ፤

በገንዘብና በአቅም የረዳውን ሕዝብ ፥ ሃብቱንና ሕይወቱን እንዲሁም የቤተ ሰቡን ሃብትና ሕይወት መንግሥት ጦርነትን በማራቅ ለማስከበር አላወቀበት ወይም አልቻለ እንደሆነ ፤ ጉዳት ለደረሰባቸው ሁሉ ፤ ካሣቸውን መክፈል ፥ ሕጋዊ ግዴታው ነው ።

— በአገር ውስጥ በግለ ሰብ መካከል ወይም በግለሰብና በሕብረሰብ መካከል ፤ ክርክር ቢነሳ ፤ በሰላማዊና በትክክለኛ መንገድ እንዲታይ አስፈላጊ ነው ፤ ይህም የዳኝነት ተግባር ይባላል ፤

— በሰላም ጊዜ የሚከናወን ሥራ ሁሉ ፥ ሥርዓትና ጸጥታ ይጠይቃል ፤

ይህን ሥራ ለማስፈጸም በቂ ኃይል ያለው መንግሥት ነውና ፥ የፖሊስ ተግባር ይባላል ፤ በመንግሥትና በሕዝብ መካከል ባለው ፥ በዚህ ሞራላዊ ውል መሠረት ፥ መንግሥት ሊያቆመው ይገባ የነበረ ሽብር ተነስቶ በሱ ሳቢያ በሰዎችና በሃብታቸው ላይ ፥ ጉዳት ቢደርስባቸው አስፈላጊውን እርዳታ ያደርግላቸዋል ።

— ሕዝቡ ያልተማረና ያላወቀ ሲሆን አገር ልትበለጽግና ልትኖር ስለማትችል ፤ መንግሥት ለአገረ ሰቡ ትምሕርትና መግለጫ መስጠት አለበት ፤ የትምሕርት ሚኒስቴር ተግባር ነው ።

— በዘመናዊ አገር ውስጥ ፤ እቅም ያላቸውና የተመቻቸው ፥ ያልታደሉትንና ደካማዎችን ፥ መርዳት አለባቸው ፥ ዝግጅቱ የመንግሥት ሥራ ነውና ፥ ተራድኦና ሕብረ ሰብዓዊ ሥራ መፈጸም የጡረታ ሚኒስቴር ተግባር ነው ።

— ሳገሪቱ የሚያስፈልገውን የገንዘብ ወጭ አገረ ሰቡ በማዋጣት መቻል አለበትና ፤ ይህን ገንዘብ መሰብሰብና ማከፋፈል የመንግሥት ፋንታ ነው ፥ የገንዘብ ሚኒስቴር ተግባር ነው ።

— ምንም እንኳን እያንዳንዱ ሰው የራሱን ጤና ቢጠብቅ ፤ ማኅበራዊ ኑሮ የጋራ ጤና አጠባበቅ ድርጅት ይጠይቃልና ፥ የጋራ ጤና አጠባበቅ ሥራ ካልተፈጸመም የያንዳንዱን ሰው ጤና መጠበቅ ፍሬ አይሰጥምና ፥ መንግሥት ይህን ሥራ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ያስፈጽመዋል ።

— በተረፈ የእርሻ ፥ የንግድ ፥ የኢንዱስትሪና ፥ የመሳሰሉም ሁሉ ሥራዎች ፥ አብዛኛውን ጊዜ በግለሰብ አማካይነት ቢከናወኑም ፤ ከጠቅላላው ያገሩ ጥቅም ጋራ የተያያዙ ናቸው ።

የመመላለሻና የመገናኛ ሥራዎችም መንግሥታዊ ድርጅቶች ናቸው ። የነዚህ ሥራ አመራር በጠቅላላው የአካላዊ ኑሮ ድርጅት ይባላል ። አካላዊ ኑሮ የተባሉበትም አገረ ሰቡ ለሕይወቱና ለኑሮው አስፈላጊ የሆኑትን ፥ ምግብ ፥ ልብስ ፥ መመላለሻና መገናኛ የሚያቀርቡለት ስለሆነ ነው ። ከዚህ በላይ የተዘረዘረው የሚኒስቴሮቹን የደረጃ አያያዝ ሳይሆን ፥ የመንግሥቱ ሥራ መዘርዘሪያ ልንለው ይገባል ።

በዚህ አኳኋን የመንግሥቱን ሥራ አሁለት ላይ ልንከፍለው እንችላለን ፤

1 ሞራላዊ ተግባር ፥ አገር መከላከያን ፥ ዳኝነትን ፥ ጸጥታን ፥ ትምህርትን ፤ ጡረታን ፥ መተዳደሪያ ገንዘብን ፥ ጤና ጥበቃን ፥ ይይዛል ፤

2 አካላዊ ድርጅት ፥ እርሻን ፥ ንግድን ፥ ኢንዱስትሪን ፥ መመላለሻን ፥ መገናኛን ይይዛል ፤ ከዚህ ቀጥሎ መንግሥት እነዚህን ሥራዎች እንደምን እንደሚያከናውን እንመልከት ፥

የውጭ ግንኙነት

የመንግሥቱ ፍጹምነት የሚታወቀው ከሌሎች አገሮች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ነው ።

የዲፕሎማሲ ሥራ ጠቃሚነት ፤ ጦርነት ከጥንት አባቶች ጀምሮ የቆየ ነገር ቢሆንም ፥ በስምምነትና በመመካከር ለማስቀረት የሚቻል መሆኑን ሰው ከብዙ ዘመን ጀምሮ አውቆት ተረድቶታል ። ቀጥሎም መንግሥታት በእንደራሴዎቻቸው ፥ አማካይነት ተነጋግረውበት በስምምነት የማይፈጸም ሲሆን ፤ ጦርነት ከመነሳቱ አስቀድሞ ፥ ማስታወቂያ መስጠት ግዴታ ሆነ ። በጦርነትም መካከል ፥ መልክተኛ

ያላንዳች መሣሪያ ጠላት ዘንድ ሄዶ ለመነጋገርና ለሕይወቱም ሳይሰጋ ለመመለስ እንዲችል መብት ነበረው ። የዲፕሎማሲ ሥራ ከዚህ ተያይዞ የመጣና በመንግሥታት መካከል ግንኙነትን ለማጥበቅ ፥ የአገርንም ምድር ለማስከበር የሚጠቅም ፥ ነገር ነው ። ይህ ሥራ የሚከናወነው ፥ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው ።

<u>የዲፕሎማሲ መልክተኞች ፤</u> የዲፕሎማሲ መልክተኞች አምባሳደሮችና ቆንሲሎች ናቸው ።

አምባሳደር ፥ በውጭ አገር የመንግሥቱ እንደራሴ ነው ። ባንድ አገርም ካንድ አምባሳደር የበለጠ ሊኖር አይችልም ። የሚኖረውም ፥ በተላከበት አገር ዋና ከተማ ነው ።

ከፍ ያለ ግንኙነት በሌለበት አገር ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ብቻ ማድረግ ይቻላል ።

ቆንሲል ግን ዓይነተኛ ተግባሩ ፤ በውጭ አገር የሚኖሩትን የኢትዮጵያ ተወላጆች የግል ጥቅማቸውን ማስከበር ነው ። ዳግመኛም በማዘጋጃ ቤቶች ምዕራፍ ፥ ላይ እንደገለጽነው ፥ በውጭ አገር የሚወለዱትን ኢትዮጵያውያን ሕዝባዊ ሁኔታ የሚመዘግብ እሱ ነው ። በውጭ አገር የሚጋቡትንም ኢትዮጵያውያን ጋብቻ እንደ ከተማ ከንቲባ ሆኖ ያስፈጽማል ፥ ይመዘግባል ።

ቆንሲሎች የሚቋቋሙት የኢትዮጵያ ተወላጆች በ ብዙ በሚገኙባቸው ፥ የውጭ አገር ከተሞች ነው ። ለም ሳሌ ፥ በጐረቤቶቻችን በጂቡቲና በናይሮቢ ከተሞች ቆንስላዎች አሉን ።

የመከላከያ ሚኒስቴር ፤

በዛሬ ጊዜ ፥ አገራቱን የመጠበቅ ተግባር የልዩ ልዩ መሣሪያዎችን ክፍሎች ፥ አጠቃሎ ለያዘ ሳንድ ጠቅላላ ድርጅት ተሰጥቷል ።

ስለዚህ የምድር ፥ የአየርና ፥ የባህር ኃይሎች ተጠቃለው በዚህ ሚኒስቴር ስር ፥ ይተዳደራሉ ።

<u>የጦርነት ሰንኩሎች ፤</u> በጦር ሜዳ በደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት ስንኩል የሆኑ ሰዎች ፥ በመከላከያ ሚኒስቴር አማካይነት ፥ ካሣቸውን ይቀበላሉ ። ይህም የካሣ እከፋፈል ፥ እንደተራድኦና እንደ በጐ አድራጐት አይቆጠርም፥ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች ፥ ጉዳት የደረሰባቸው ፥ መንግሥት ሊያስቀረው ባልቻለ ጦርነት ላይ ገብተው ተግባራቸውን ሲፈጽሙ ስለሆነ ከዚህ ጉዳት ሊያድናቸው ባለመቻሉ ከመንግሥት ካሣ እንጂ ፥ እርዳታ መቀበላቸው አይደለም ። ይህም በሕግ እንዳገኙት እንጂ እንደ ጡረታ አይቆጠርባቸውም ።

በአገራችን የወታደራዊ አገልግሎት ግዴታነት ገና ስላልተቋቋመ ፥ የወታደርነት ሕይወት ያልቀመሱ ብዙ ሰዎች አሉ ፤ ነገር ግን በአገሪቱ ላይ እንድ እደጋ በደረሰ ጊዜ በነጭ ለባሽ ሰም እየዘመቱ ሕዝባዊ ግዳጃቸውን ይፈጽማሉ ።

ጸጥታና ዳኝነት ፤

ኃይለኛ የሆነ የፖሊሰ ድርጅት ከሌለ ጸጥታ ባገር ውስጥ ሊኖር ያስቸግራል ። በሰዎች መካከል የሚነሳውንም ሙግት ያለ አደሎና ያለ ስጋት ለመዳኘት የሚችል አቅዋም ከሌለ ፤ ጸጥታና ሰላም ጨርሶ ለመኖር አይችልም ።

ስለ ጸጥታ አጠባበቅና ስለ ዳኝነት ተግባር ፥ በማዘጋጃ ቤቶችና በዳኝነት ሥልጣን ምዕራፍ ዘርዝረናል ።

ትምህርት ።

ከአርባና ሃምሳ ዓመት ከማይበልጥ ጊዜ በፊት ትምህርት በቤተ ክህነትና በቅዱሳን መጻሕፍት የተወሰነ ነበረና ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዘመናዊ ትምህርት ጋር ሳይተዋወቅ ፥ ብዙ ዓመታት ቆይቷል ። ፋሽስት ኢትዮጵያን ከመውረሩ በፊት ፥ እንዳንድ ሚሲዮኖች ፥ እንዲሁም መንግሥታዊ ት/ቤቶች ተቋቁመው የውጭ አገር ትምህርት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ ተከፈተለት ፥ ብዙዎች ወጣቶችም ወደ ውጭ አገር እየሔዱ ከፍተኛ ፥ ደረጃ ትምህርት በማግኘታቸው ፥ አገራችን ለዘመናዊ አስተዳደር የሚረዷት የመጀመሪያዎቹን ሰዎች አገኘች ፤

ኢትዮጵያ ነጻነቷን እንደገና ካገኘች በኋላ ግን ፤ መን ግሥት ፥ የባጀቱን አብዛኛ ክፍል ለትምህርት በማዋሉ ፤

ዛሬ ሐገራችን የራስዋ ሐኪሞች ፥ የራሷ መሐንዲሶች ፥ የራሷ የሕግ ሰዎች በመጠኑ አሏት ።

ትምህርት የሚመራው ፥ በትምህርት ሚኒስቴር ፥ በንጉሠ ነገሥቱ የበላይ አዛዥነት ነው ።

የአንደኛ ደረጃ ፥ የሁለተኛ ደረጃና የኰሌጅ ትምህርት በቀጥታ በአገራችን ለመስጠት ተችሏል ።

ዩኒቨርሲቲም ባሁኑ ዓመት ተከፈተ ፤ ብዙው ፥ ትምህርት ዛሬ ፥ በእንግሊዝኛና በፈረንሳይኛ ቋንቋ ይሰጣል ፥ ሆኖም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በአማርኛ ቋንቋ ሊሰጥ ተጀምርዋልና የከፍተኛ ደረጃም ትምህርትም ፥ በኛው ቋንቋ የሚሰጥበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ።

በተረፈ ፥ ወጣቶች ሞያ የሚማሩባቸው ተማሪ ቤቶች ተቋቁመው ፥ ብዙ ተማሪዎች ስለፈለቁ ዛሬ በልዩ ልዩ መ/ቤቶችና በባንክ ፥ በሌላም አቅዋሞች ኢትዮጵያውያኖች ከፍ ያለ የአላፊነት ቦታ በብዛት ይዘው ይገኛሉ ፤ ከነዚህም ተማሪ ቤቶች የንግድን ትምህርት ቤት ፥ ተግባረ እድን፥ ሕንጻ ኰሌጅን ፥ መጥቀስ እንችላለን ፤

እያንዳንዱ ሚኒስቴር ደግሞ ፥ ለራሱ ሥራ የሚያስፈልጉትን ሠራተኞች ለማሠልጠን ፥ ልዩ ልዩ ተማሪ ቤቶች ከፍተዋል ።

ለምሳሌ ፥ የእርሻ ኰሌጅ ፥ ለእርሻ ሚኒስቴር ፤
የአየር ፥ የባህርና ፥ የምድር ጦር አካዳሚዎች ለመከላከያ ሚኒስቴር ፤

ይህን የመሳሰሉ ይገኛሉ ።

የትምህርት ሚኒስቴር ፣ ጤነኛ አእምሮ በጤነኛ አካል የተባለውን ቃል በመከተል ፣ በውስጡ የስፖርትን ድር ጅት የሚመራ ሰፊ ክፍል አለው ፣ እንዲሁም የስፖርት ውድ ድሮችን በተማሪዎች መካከል የሚያዘጋጅ ፣ የተማሪ ቤ ቶች ስፖርት ማህበር የተባለ አቋም አለው ፤

የኰሌጆችም የስፖርት ማኅበር በዚሁ መልክ ተቋቁ ሚል ፤

ልዩ ማስታወሻ ።

በላይኞቹ መሰመሮች እንደገለጽኩት ፣ ዘመናዊ ትምህ ርት አገራችን ከገባ ፣ ብዙ ጊዜው አይደለም ። ስለዚህ ዛሬ አንድ ልጅ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ሲጨርስ ፣ ከወላጅ አባቱና እናቱ በትምህርት ይበልጣል ። ይህ ሁኔታ በቤተ ሰቦች መካከል ከፍ ያለ ችግርን ፈጥርዋል ፣ ልጅዬው አባ ትና እናቱ የማያነቡትን በማንበብ የማይጽፉትን በመጻፍ ፣ ከነሱ ይበልጥ ማወቁ ይሰማውና እንምከርህ ፣ ወይም እንዘ ዝህ ፣ ሲሉት ፣ እናንተ ምን ታውቃላችሁ ማለት አመጣ ፣ አባትና እናትም ፣ ምንም ቢሆን ካንተ ትምሕርት የኛ ከመ ቆየት የተገኘ ልምድ ይበልጣልና እንዳልህን እደር ሲባባሉ፣ እስከ መለያየት ይደርሳሉ ።

በውጭ አገር ከፍተኛ ደረጃ ተምረው የመጡትም ፣ ባንድ መ/ቤት ሲገቡ ፤ የበላዮቻቸው በትምሕርት ከነሱ

ያነሱ መሆናቸውን ስለሚገምቱ ፣ በምን ምክንያት በደረ ጃስ ፣ በደሞዝስ ይበልጠኛል ፣ ለምንስ ያዘኛል የማለት ሰ ሚት ያድርባቸዋል ። ያም የቆየ ሹም ፤ ባቀናሁት ቤትና ዘርዝሬ መንጥሬ በማውቀው ሥራ ዛሬ መጥቶ ከኔ ሊበልጥ ነው ወይ በማለት ፤ በሁለቱ ትውልድ መካከል ሰምምነት ርቋል ፤

ስለዚህ በኔ አስተያየት ለዚህ መድኃኒቱ ፤

1 ተማሪው ፤ አባትና እናት ያስተማሩት እንደነሱ አላዋቂ ሆኖ እንዳይቀር ፣ እውቀት ሽምቶ በአዲሱ ትውልድ ው ስጥ ተግቢውን ስፍራ ተሻምቶ ሊይዝ እንዲችል ፣ በማ ሰብ ስለሆነ ፣ ባያምንበትም እንኳን ውለታውን ለመመለ ስና ፣ ለክብራቸው ሲል ፣ ምክራቸውን ቢቀበል አይከ ፋም ፤

2 አባትና እናትም ፣ የሚመክሩትና የሚያዙት ልጅ ከተ ማሪ ቤት ፣ የቀሰመው የራሱ አስተያየት ያለው መሆኑን በመገንዘብ ፤ በቆየው ልምዳችን ዓይንህን ጨፍነህ ፣ አስ ተያየትህን አፍነህ እኛን ብቻ ሰማ ማለቱን ቢተው መግ ባባት ይፈጠራል ፤

3 ከፍተኛ ደረጃ ደርሰው በሥራ ላይ የተቀመጡትም ፤ የበ ላዮቻቸው ምንም እንኳ በመሠረቱ በትምሕርት ደረጃ ባይደርሱባቸው ፣ እነሱ እንዲማሩና እዚህ እንዲደርሱ ያ ደረጉ እነሱ መሆናቸውን አለመዘንጋትና ፣ ያስተማርዋ ቸውም ፣ እነሱ በሚደክማቸው ጊዜ እንዲተኳቸው ነው እንጂ እንዲነቅልዋቸው ስላልሆነ ፣ በምክር እየረዱ የመ

ተኪያውን ጊዜ ፥ በትእግሥት መጠበቅ አለባቸው ። የሥራና የባህል ልምድም የሚናቅ ፤ ነገር አይደለም ።

4 በውሰጣቸው ከፍተኛ ደረጃ የተማሩ ወጣቶች ያሉዋቸው ባለሥልጣኖች ደግሞ ፥ በምክራቸውና በእውቀታቸው መጠቀምና እንደ ልጆቻቸው መቁጠር ነው እንጂ ፥ ሊነጥቅ እንደመጣ አውሬ እነሱን ማራቅ አያስፈልግም ፤

በኢትዮጵያ ሁለት የተማሩ ትውልዶች እስኪ ድርሱ ድረስ በዚህ አኳኋን በመግባባት እየሠሩ መቆየት ፥ አሰፈላጊ ነው ።

ጤና ጥበቃና ተራድኦ ፤

መንግሥት የሕዝብን ጤና ለመጠበቅ የሚያሰፈልጉትን ጥንቃቄዎች ፥ አስቀድሞ ከመውሰዱም በላይ ፤ የተፈጥሮ መከራዎች በሕዝብ ዘንድ ለማድረስ የሚችሉትን ችግሮች ለማገድ ይታገላል ።

<u>የሕዝብ ጤና ፤</u> ያንድ አገር የመጀመሪያ ሃብቱ ፥ ሕዝቡ ነው ።

በሽተኛና አካለ ጐዶሎ የበዛበት አገር አንድም ፍሬ ነገር ሊሠራ አይችልም ፥ ስለዚህ መንግሥት በዚህ ጉዳይ ሊጨነቅበት በቂ ምክንያት አለው ።

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፥ የሕዝብን ጤና ለመጠበቅ የሚያገለግሉትን ነገሮች ሁሉ በማስተባበር ለምሳሌ ፥ እንደ

ሳንባ ነቀርሳና እንደ አልኩል ፥ ያሉትን መቅሰፍቶች ለማስወገድ ፥ አሰፈላጊውን ያደርጋል ።

ለምሳሌ መክተብን ፥ ግዴታ በማድረግ ፥ የያንዳንዱን ሰው ጤና እየጠበቀ መላውን ሕዝብ ደግሞ ከተላላፊ በሽታ ያስጥለዋል ።

አገራችን ኢትዮጵያ ሰፊ እንደመሆኗ መጠን ፥ በውስጢ የሚኖረው ሕዝብ ቁጥሩ አነስተኛ ነው ። በግል ጤናም ረገድ ብዙዎቹ የበቃ ጥንቃቄ አያደርጉም ፥ ስለዚህ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሕዝቡን ቁጥር ለማብዛት ብቻ ሳይሆን ጤናማ ሕዝብም እንዲሆን ጭምር ማሰብ ስላለበት ፤ የሚሞቱት ሰዎች ቁጥር እንዲቀነስ የሚወለዱት ቁጥር እየተጨመረ እንዲሄድ የሕክምና እርዳታ በሰፊው ያዘጋጃል ።

<u>ተ ራ ድ አ ፤</u> ያለው ፥ ለተቸገረው በመመጽወት ፥ አንዱ ያንዱን ትግር ማቃለል ከጀመረ አያሌ ጊዜ ነው ።

በዛሬ ጊዜ ግን ፥ የተቸገሩትንና የተጐዱትን መርዳት ብቻ ሳይሆን ፤ ችግርና ጉዳት ራሳቸው እየጠፉ እንዲሄዱ ማድረግ የመንግሥት ፥ ፋንታ ሆኖ ስለተገኘ ፥ የችግሮች ዝርዝር እየወጣ ከመድረሳቸው በፊት መድኃኒት እንዲፈለግላቸው ይደረጋል ። ለምሳሌ ፥ ሥራ መፍታት ፥ በሽታ ፥ አካለ ጐዶሎነት ፥ እርጅና ፥ የቤተ ሰብ አባት መሞት ፥ በነዚህ ውስጥ ይቆጠራሉ ፥ ለነዚህ ጉዳቶች ስታቲስቲክ በማብጀትና ከሕዝብ መዋጮ ወይም የተራድኦ ቀረጥ በመቀበል ሕዝባዊ መተማመኛ ፥ የተባለ ድርጅት ማቋቋም ይቻላል ።

ይህ ድርጅት በሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ውስጥ ፣ ወይም በጡረታ ሚኒስቴር ውስጥ ሊሆን ይችላል ።

የገንዘብ አስተዳደር ፤

የገንዘብ ሚኒስቴር ፣ ወጭና ገቢውን ለማስተካከል ከመደከሙም በላይ ፣ የመንግሥቱ ገንዘብ ለምን እንደሚ ውል በጥብቅ ይቆጣጠራል ።

ገንዘብ (ፊናንስ) ባላፉት ገጾች የዘረዘርናቸው ፤ መከላ ከል ፣ ዳኝነት ፣ ትምሕርት ፣ በጐ አድራጐት ፣ የሚያኰሩና አስፈላጊ ቢሆኑም ፣ ብዙ ገንዘብ የሚጠይቁ ተግባሮች ናቸ ውና ገንዘቡን ማግኘት ያስፈልጋል ።

ይህ ሁኔታ መጀመሪያ መንግሥት ገንዘብ እንዲኖረው ቀጥሎም ፣ ይህ ገንዘብ ፣ በሥርዓት እንዲተዳደር ይጠይ ቃል ፣ ከዚህም በቀር የመንግሥቱ ገቢው ወጭዎቹን እንዲ ችል ያስፈልጋል ።

እላይ እንዳልነው ሁሉ ሕዝቡ ከመንግሥቱ ፣ መከላ ከያ ኃይልን ፣ የውስጥ ጸጥታን ፣ ዳኝነትን ፣ ትምሕርትን ፣ ጤና ጥበቃን ፣ ጡረታን ፣ ይጠይቃል ።

መንግሥት ለሕዝቡ ይህን ሁሉ ለማዘጋጀት ፣ ገንዘብ ያስፈልገዋል ፤ ይህም ገንዘብ በነዚህ ፣ አቅዋሞች በቀጥታ ከሚጠቀምባቸው ፣ ከሕዝቡ እንዲመጡ ተገቢ ነው ። እንግ

ዲህ አንድ ሰው ለመንግሥት ቀረጥና ግብር ሲከፍል ፣ ከ ዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ድርጅቶች የሚፈልቀውን ፣ ጥቅም ተካፋይ ለመሆን ገንዘብ ማዋጣቱ ነው እንጂ ገንዘቡን አን ሰቶ ለሌላ ሰው መስጠቱ አለመሆኑን መረዳት አለበት ፤ ገንዘቡን የምንከፍለው ለራሳችን ስንል ከሆነ ለምን በሕግ ይዘው በግድ ያስከፍሉናል የሚሉ አይጠፉም ፣ እዚህ ላይ ማወቅ የሚገባ ፣ አንድ ሰው ባንድ አገር ውስጥና ባንድ ሕ ዝብ መካከል ሲኖር ፣ ያገሪቱን ፍሬ ሲመገብና በሌሎች ሰ ዎች ሥራ ሲጠቀም ፤ በማሕበሩ ውስጥ ውሉን ወዶ ገብ ቷል ማለት ነው ። ግብር ሲጠየቅ አልከፍልም ያለ በሕግ የሚገደደው ይህን ውል ስላፈረሰ ነው ። በቀጥታ ከግብር የሚመጡትን ሕዝባዊ ገቢዎችን የሚያስተዳድር የገንዘብ ሚኒስቴር ነውና ፣ የሚያጋጥመው ችግር እጅግ ከፍ ያለ ነው ፤ ሚኒስቴሮቹ በባጀታችን መሠረት ከፍ ያለ ገንዘብ ሰጠን ብለው በሚገባ ይጠይቁታል ፤ ግብር ከፋዩ ደግሞ በዝቶብኛልና ይነቀስልኝ ስለሚል በሁለቱ መካከል የሚዋ ጅቅ ገንዘብ ሚኒስቴሩ ነው ። ዳሩ ግን የግብሩን ልክና ፣ አወ ጣጡን ወሰኖ የሚሰጠው ፓርላሜንቱ ስለሆነና እሱም የን ጉሠ ነገሥቱና የሕዝብ እንደራሴዎችን ፈቃድ ፈጻሚ ስለ ሆነ ፤ ተጠያቂነቱ በዚሁ መጠን ይቃለልለታል ።

ይህም ሆኖ የገ/ሚኒስቴር ሥራ ፣ ልዩ ሞያቸው የሆነ ፣ ጥንቁቅ ሠራተኞች ይሹታል ።

ባጀትና ግምጃ ቤት ፤

በመሠረቱ እዝርዝር ጉዳይ ውስጥ ሳንገባ ፣ በባጀትና በግምጃ ቤት መካከል ፣ ያለውን ዓይነተኛ ልዩነት ማወቅ

ጠቃሚ ነገር ነው ። ለዚሁም ፥ ምሳሌ እንውሰድ ፥ አንድ ሰው በመስከረም አንድ ቀን በማጥኑ ውሰጥ ዜሮ ብር አላው (ምንም የለው ማለት ነው) ነገር ግን ፥ በመስከረም ወር ውሰጥ የሚቀበለው ገቢ ፥ 100 ብር እንዳለው አሰቦ አው ቋል ፤ በዚሁ ወር ውሰጥ ደግሞ ወጭው 80 ብር እንደሚሆን ገምቷል ፥ ይህን ሂሳብ ሲያደርግ ይህ ሰው ባጀቱን ወሰነ ማለት ነው ፤ በወሩ መጨረሻም 20 ብር ፥ ሰለሚተርፈው ባጀቱ አጥጋቢ ነው ።

ነገር ግን ገቢውን 100 ብር ባንድ ጊዜ ሳይሆን በከፊ ልና በየጊዜው የሚቀበል ፥ ሰለሆነ ገንዘብ የሚቀበልበትና ወጭ ፥ የሚያደርግበት ቀን ሳይገጣጠሙ ሊቀሩ ይችላሉ ። ይህን በመገንዘብ ሰውዬው የገንዘቡ አወጣጥ ከገቢው ጋራ በሚስማማ እኳኋንና ጊዜ እንዲፈጸም ለማድረግ ይሞክ ራል ፤ ይህን ሲያደርግ የግምጃ ቤቱን ሥራ አከናወነ ማለት ነው ።

ለምሳሌ በመስከረም 10 ቀን የ15 ብር ዕቃ መግዛት ቢኖርበት ፥ በመስከረም 8 ቀን ከሰው የሚቀበለው 20 ብር ሰላለው ግዥውን ሊያደርግ ይችላል ።

ይህ ሁኔታ ምን ያስረዳል ? ሰውዬው ምንም እንኳ ባጀቱ በቂና ተራፊ ቢሆንም ፥ በመስከረም ወር ውሰጥ ፥ ልዩ ልዩ የገንዘብ ሁኔታ ሊገጥመው እንደሚችል ፥ ያስረዳናል ፤ በወሩ መጀመሪያ አብዛኛውን ገንዘብ ገቢ ያደረገ እንደሆ ነና ፥ ከፍ ያለ ወጭም ያለበት በወሩ መጨረሻ ገደማ ሲሆን፥ ግምጃ ቤቱ ፥ በተመቸና በሰፊ ሁኔታ ላይ ሊገኝለት ነው ።

ነገር ግን ይህ ሰው በመስከረም 8 ቀን ይጠብቀው የነበረው ገንዘብ በከፋዩ ድንገተኛ ችግር ምክንያት ሳይገባለት ቢቀር፥ ላሰበው ግዥ ገንዘብ ሰለሚያጣ ፥ ምንም እንኳ ባጀቱ በቂ ቢሆን የግምጃ ቤት ፥ ችግር ገጠመው ማለት ነው ፤ የግምጃ ቤት ችግር ገንዘቡ ገቢ በሆነ ጊዜ ሊጠናቀቅ ፥ ሰለሚችል ፥ አላፊና የዕለት ችግር ነውና አዋኪነቱ እጅግም አይደለ ። የባጀቱ ፥ መዛነፍ ግን ይበልጥ አሶቸጋሪ ነው ፥ ለወጭው የገመተው 80 ብር ሳይበቃ ቀርቶ 120 ብር ቢያስፈልገውና ገቢው ከመቶ ብር የማይበልጥ ከሆነ ፥ መውጫ ከሌለው ች ግር ውሰጥ ይገባል ፥ እዚህ ላይ ወይም ትርፍ ሰዓት መሥ ራት ወይም ከጥቅምት ባጀት ላይ መበደር ሊያስፈልግ ነው ፤ የመንግሥትም ሁኔታ እንደዚሁ ነው ። በያመቱ በገን ዘብ ሚኒሶቴሩ አዘጋጂነት ፥ የታሰቡት የዓመት ገቢና ወጭ ዎች ፥ ለፓርላሜንቱ ቀርበው ፥ አዋጭው ሕዝብ እንደመ ሆኑ መጠን ፥ በሕዝብ እንደራሴዎች ይፈቀዳሉ ፤ የባጀቱም አፈቃቀድ በጠቅላላው ድምር ሳይሆን በአቀራረቡ ላይ በአ ርእሶቱ ሶለሆነ ፥ በዚሁ መሠረት አንድ በአንድ ይፈቀዳ ልና ፥ ላንድ ጉዳይ የተወሰነው ሂሳብ ለሌላ ጉዳይ ሊውል አይችልም።የባጀት ድሬክሲዮንና የጠቅላይ ግምጃ ቤት ድሬክሲዮን በገንዘብ ሚኒሶቴር ውሰጥ ከፍ ያሉ ክፍሎች የሆኑት ከዚህ በላይ በዘረዘርናቸው ምክንያቶች ናቸው ።

<u>የሂሳብ ኦመራመር ፤</u>

አዋጭዎች የከፈሉት ገንዘብ በተፈቀደውና በትክክ ለኛ መንገድ መውጣቱን ፥ መንግሥት በጥንቃቄ መቆጣ ጠር አለበት ። ለዚሁ ሥራ የተመደቡ የአውዲትና ፥ የሂሳብ

ኢንስፔክተሮች እየተዘዋወሩ ሂሳቡን በመመርመር ፣ የያን ዳንዱ ሚኒስቴር ወጭም ፣ ከባጀቱ ሕግ ጋራ ተስማሚ መሆ ኑን ይቆጠራሉ ።

የሕዝብ አካላዊ ኑሮ ድርጅት

ያንድ ሕዝብ አካላዊ ኑሮ እንዲረጋገጥ ምግብ ፣ ልብስ፣ መገናኛ መከላከያና ምቾት ያስፈልገዋል ፣ እነዚህን የማይ ታለፉ ነገሮች ለማግኘት ፣ ሰው እንዲሠራ ፣ እንዲያርስ ፣ እንዲነግድ ፣ እንዲዘዋወርና እንዲላላክ ስለሚያስፈልግ ፣ መንግሥት በልዩ ልዩ ሚኒስቴሮች አማካይነት ሕዝብን ይረዳዋል ።

1 <u>የሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር</u> ፤ የሥራውን ዘዴ በማስተማር ሠራተኞች የሚጠበቁባቸውን ማሕበራዊ ድር ጅቶች በማቋቋም ፣ ሕዝብን በሥራ ረገድና ማሕበራዊ ኑ ሮን ለማሻሻል ይረዳዋል ፣ (ስለ ሕብረ ግብርና በሌላ ገጽ ተመልከት)

2 <u>የንግድና የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር</u> ፤

የንግድ ሚኒስቴር ፣ በአገሩ ውስጥ የንግድን ሥራ እየ ተቆጣጠረ ያስፋፋል ፣ በተለይም የሸቀጦችን ዋጋ የሚወ ስን እሱ ነው ። በየጊዜው በሚያዘጋጀውም ስታቲስቲክ መ ሠረት አገሩ የሚያፈራውንና ለኑሮው የሚያስፈልገውን በማመዛዘን ይረዳል ። እንደጊዜው አስፈላጊነትም ፣ ከአ

ገር የሚወጣውንና ወደ አገር የሚገባውን ሸቀጥ የሚወስን እሱ ነው ፤ እንደዚሁም አገሪቱ ከውጭ አገሮች ጋር የምታ ደርገውን የንግድ ግንኙነት የሚያጠናቅቅ ፣ እሱ ነው ፤

በኢንዱስትሪ በኩል ደግሞ ፣ በመንግሥት የሚተዳደ ሩትን ልዩ ልዩ አቅዋሞች ፣ በቀጥታ ከማስተዳደሩ በቀር ፣ በአገር ውስጥ የፋብሪካዎችን ማቋቋም ያበረታታል ፣ ባለ ፋብሪካዎች የሚያስፈልጋቸውን መሣሪያ እንዲያገኙ ይረ ዳቸዋል ።

<u>ስለ ንግድ አጭር መግለጫ ፤</u>

<u>የችርቻሮ ንግድ</u> ፣ በሰፈርና በጊዜ ረገድ ፣ ሸቀጥን ለሸ ማቹ በዝርዝር ወዲያው የሚያስገኝለት ንግድ ነው ። የጅ ምላ ንግድ ደግሞ በባለፋብሪካውና በችርቻሪው ፣ መካከል ያለው አገናኚ ነው ። ደግሞም አንዳንድ ታላላቅ የንግድ ቤቶች የችርቻሮን ንግድ ራሳቸው አጠቃለው ይዘውታል ።

<u>ችርቻሮና ፍቹ ትንሽ ነጋዴ</u> ወይም ችርቻሪ ማለት ፣ በጥቂት በጥቂቱ ሸቀጡን በቀጥታ ለያንዳንዱ ሸማች የሚ ያቀርብና አብዛኛውን ጊዜ ብቻውን ወይም ቢበዛ ፣ ባንድ በሁለት ሰው እየተረዳ የሚሠራው ነጋዴ ነው ። ፍሬ ነጋዴ፣ ባለ ቡና ቤት ፣ ሸቀጣ ሸቀጥ (አረብ ቤት የምንለው) እነዚህ ሁሉ በዚህ ውስጥ ይቆጠራሉ ፤

<u>የጅምላ ንግድ</u> ፤ እንዳየነው ሁሉ ችርቻሮ ሸቀጥን ለሸ ማቹ ያቀርብለታል ፤ ሸቀጡ ፣ ወደ ችርቻሪው በምን አኳ

ኋን ደረሰ ? በባለፋብሪካውና (በሠሪው) በቸርቻሪው መካከል አማካይ የሆነው የጅምላ ነጋዴ ሥራ ነው ።

እንድ ቆርቆሮ ሰርዲን የሚሸጥልን ነጋዴ ፣ በቀጥታ ከፋብሪካው አልገዛውም ፣ ነገር ግን በጅምላ ሻጩ ፣ ከባለ ፋብሪካው ከፍ ያለ ቍጥር ይገዛና ይህንኑ ለቸርቻሪዎች ያከፋፍላቸዋል ፤ የባለፋብሪካው ተግባር ሸቀጡን መሥራት ብቻ ነው ። የሚጠቅመው ዕቃ በብዛት ላንድ ጅምላ ነጋዴ መሸጥ ነው እንጂ እራሴ እየዞርኩ ለቸርቻሪዎች ልሸጥ ቢል ገዥ እስኪያገኝ ድረስ ሸቀጥ እንደሚተኛበት የተረጋገጠ ነው ፤ እንዲሁም የጅምላ ነጋዴ ሥራ ሸቀጥን በብዛት ገዝቶ ለቸርቻሪዎች ማከፋፈል ነው እንጂ እራሱ መቸርቸር አይደለም ።

ትልልቅ የንግድ ቤቶችና ወኪሎቻቸው ፤

እንዳንድ ትልልቅ የንግድ ቤቶት ባንድ ሰፍራ ትልቅ ማጋዘን ይከፍቱና ብዙ ዓይነት ሸቀጦች ይሸጣሉ ፤ በተረፈ ደግሞ በየቀበሌው ትንንሽ ሱቆች ከፍተው ሠራተኛ ቀጥረው ለሰፈሩ ሰው ይሸጣሉ ፤ ይህ ዘዴ ብዙ ፣ ጠቃሚ ነት አለው ፣ ትልቁ የንግድ ቤት በቀጥታ ከፋብሪካው በብዛት ዕቃ ለመግዛት ስለሚችል በደህና ዋጋ ያገኛል ፣ እሱም በየሰፈሩ ለሚገኙት ሱቆች በቅናሽ ለመሸጥ ስለሚችል ለቸርቻሮች ኃይለኛ ተወዳዳሪ ነው ፤

የሆነ ሆኖ የዚህ ዓይነት ንግድ ባገራችን ገና በጣም አልተስፋፋም ።

ባለእጅና ኢንዱስትሪ ፤

የእጅ ጥበብና ፍቹ ፤

ባለእጅ ማለት በመሠረቱ በእጅ የሚሠራውን ዕቃ ሸጦ የሚኖር ነው ። በዛሬው ጊዜ ይኸው ሰው ራሱ የሠራቸውን ነገሮች በጥቂት ሰዎች ወይም በቤተ ሰቦች እየተረዳ ፣ ለደንበኞቹ ይሸጣል ። ደግሞም የሚሠራበትን ዕቃ ራሱን ሊሸጠው ይችላል ፣ ለምሳሌ ፣ እንድ ጫማ ሰፊ ፣ ቆዳውን ወይም ከቆዳው የተሠራውን ጫማ ሲሸጥ ። የባለእጅና የነጋዴ ሥራ መሥራቱ ነው ። ፎቶግራፍ አንሺም ፣ ፊልሙን ሸጦ ፣ መልሶ ደግሞ በማጠብና በመገልበጥ ሲያተርፍ ባለ እጅና ነጋዴ መሆኑ ነው ። ነጋዴ ተሠርቶ የቀረበለትን ይሸጣል ፣ ባለእጅ በእጅ የሠራውን ነገር ይሸጣል ።

ባለእጆች የሚሠሩት ሥራ በተሶይ አንድ ባንድ ስለሆነ ፣ ዕቃቸው በፋብሪካ ፣ በብዛት እንደሚሠራው ሊረከስ ስለማይችል የሚገዟቸው ሐብታሞች ሰዎች ብቻ ናቸው ። ተራው ሕዝብ ግን ለምሳሌ ጨርቅ ገዝቶ ከማሰፋት ይልቅ የተሰፋውን መግዛት ስለሚቀለው በብዛት የሚሠሩ ፋብሪካዎችም መኖራቸው ጠቃሚ ነው ።

ትልልቅ እንዱስትሪዎች ፤

እንደ አውቶሞቢል ፣ እንደ ባቡር ፣ እንደ ሱፍ ጨርቅ ፣ እንደ ብረት ፣ ያሉትን ነገሮች ባለእጅ ብቻውን ሊሠራቸው ስለማይችል ፣ ታላላቅ እንዱስትሪዎች ያከናውኑዋቸ

ዋል ። እነዚህ እንዱስትሪዎች ሥራቸው ፍሬ እንዲሰጥ በመ
ካከላቸው ልዩ ልዩ ስምምነቶች ያደርጋሉ ።

ለምሳሌ ፤ አንዳንድ ጊዜ ፋብሪካዎች በብዛት ዕቃ
ያወጡና ፥ ሽያጩ በዚያ መጠን ፥ አልከናወን ይላል ፤ ሸ
ቀጡ ከጠያቂው ፍላጐት ይበዛል ፥ ባለፋብሪካዎች ከፍ ያለ
የዋጋ መቀነስ ውድድር ያደርጋሉ ፤ ይህ ለሸማቾች በመሠ
ረቱ ጠቃሚ የሚመስለው ሁኔታ በሕብረሰብ ላይ ከፍ ያለ
ጉዳት ለማስከተል ይችላል ። ለምሳሌ አንዱ ባለፋብሪካ ፥
ውድድር እቅቶት የወደቀ እንደሆነ ሥራውን ይቀንሳል ወ
ይም ጨርሶ ያቆማል ፥ በዚህ ጊዜ ሠራተኞቹን ሁሉ ያሰናብ
ታልና ብዙ ሰው ሥራ ፈትነት ላይ ሊወድቅ ነው ።

ደግሞም ፥ በዚህ በዋጋ ውድድር አንዱ ፋብሪካ አሸ
ናፊ ሆኖ ሌሎቹን ሁሉ ፥ የጣለ እንደሆነ ፥ ብቻውን ገበያ
ውን ይይዝና የሚሻማው ሲያጣ ያሰኘውን ዋጋ ሊወስን
ሰለሚችል ፥ ዞሮ ዞሮ ሸማቹ እጉዳት ላይ ሊወድቅ ነው ።
ይህን የመሰለ ነገር እንዳይደርስ ለማድረግ ፥ ብዙ መንገድ
አለ ። ባለፋብሪካዎች በስምምነት አንድ ተገቢ የሆነ የሽ
ያጭ ዋጋ ይወስኑና ሁሉም በዚያ ዋጋ ብቻ ሊነግዱ ይዋዋ
ላሉ ፤ እንዲሁም ለያንዳንዳቸው የገበያ ቀበሌ ይመድባሉ
በተለይም ከየፋብሪካው ዕቃው ካንድ ከተወሰነ ቅጥር በ
ላይ እንዳይሠራና በገበያ የሚወጣው ሸማቾች ከሚፈልጉት
ጠቅላላ ድምር እንዳይበልጥ በመሰማማት ፥ ሸቀጥና ጠያቂ
ተመዛዛኝ እንዲሆን ያደርጋሉ ። ስምምነቱን በስሕተትም
ቢሆን ያፈረሰ ፋብሪካ ከፍ ያለ መቀጫ እንዲከፍል ግዴታ
ይገባል ።

ትረስት (ሰብሳቢዎች)

በላይኛው አንቀጽ ያየናቸው ተፈራራሚዎች በዋጋ ፥
በዕቃ ቅጥር ፥ በገበያ ቀበሌ ይወስኑ እንጂ ፥ ፋብሪካቸው
የሚሠራው ዕቃ ራሱ በመሰለውና በተስማማው ዓይነት
ብቻ ነው ።

የትረስት አባሎች ግን እንዲህ ያለ መብት የላቸውም ፤
ብዙዎች ባለኢንዱስትሪዎች ፥ በአንድ መምሪያ ፥ ሲዋሀ
ዱና ፥ ሥራቸው ፥ የሚያወጡትም ዕቃ መልክና ያሻሻጥ
መንገድ በሱ ብቻ ሲወሰን ፥ ትረስት ይባላሉ ። ለያንዳንዳ
ቸው አንድ የተለየ ዓይነት ሥራ ይመደብላቸዋል ፤ ለም
ሳሌ በአሜሪካን አገር ፥ አምስት የአቶሞቢል ፋብሪካዎች ፥
ካዲላክ ፥ ቡይክ ፥ ኦልድስሞቢል ፥ ፖንቲያክ ፥ ሸቭሮሌት ፥
ጥንት ለየራስ የነበሩት ዛሬ ጄኔራል ሞተርስ ተብለው በትረ
ስት መልክ ተቋቁመው ይሠራሉ ። ደግሞም ፥ ከታላላቅ
ፋብሪካዎች ለምሳሌ አውቶሞቢል ፋብሪካን እንውሰድ ፥
ባለፋብሪካው ፥ ማለትም አቶሞቢሉን የሚገጣጥመው ፥ በ
ልዩ ልዩ እቅራቢያዎች ፥ መጠቀም አለበት ። ብረትን ከብ
ረት ፋብሪካ ፥ መስቷቱን ከመስቷት ፋብሪካ ፥ እንዲሁም
ላስቲኩን ፥ መለኪያ መሣሪያዎችን ፥ ሰዓቶችን ፥ ፍጥነት ቆ
ጣሪዎችን ከየሠሪው ማግኘት ይኖርበታል ።

ነገር ግን አንዳንድ ታላላቅ ፋብሪካ በተለይም አሜሪ
ካኖች ፥ ከሌላ ገዝቶ ከመገጣጠም ፥ አስፈላጊውን ዕቃ ራሳ
ቸው ገዝተው ለመሥራት አቅደው ፥ ብረት መስቷትና ይ
ህን የመሳሰለውን ብቻ ሳይሆን ፥ የላስቲክ ዛፍና ሶእንጨት

የሚያስፈልጋቸውን ደን እስከ መትከልም ደርሰው ነበረ ። ይህ ዘዴ ለጊዜው ተስማሚ ይመስላል እንጂ ፣ ጠቃሚነቱ የተረጋገጠ አይደለም ።

ባለትልቁ ፋብሪካ ሰው ፣ ጉማውን ፣ መስታቱን ፣ ባትሪውን ፣ ራሱ የሠራ እንደሆነ ፣ ራሱ ለሚያወጣቸው መኪናዎች ብቻ ስለሆነ በብዛት ሊሠራ ካለመቻሉም በቀር ይህ የተወሰነ ሥራ ልዩ ሞያው ባለመሆኑ አጠናቆ ሊያዘጋጀው እይመቸውም ፤ በብዛትም ስለማይሠራው ፣ ዋጋው ከፍ ይል ብታል ፤ በተረፈ በዚህ ሥራ የሚኖሩትን ታናናሽ ኢንዱስትሪዎች ስለሚገድል ፣ በብዙ አገሮች መንግሥት በሕግ ይከለክለዋል ።

ባለትንሽ ኢንዱስትሪው ግን የሚሠራው ያችኑ ዕቃ ብቻ ስለሆነና ፣ ለልዩ ልዩዎቹም ፣ የአቶሞቢል ፋብሪካዎች ስለሚሸጥ ፣ በዓይነትም ጥሩ በዋጋም ርካሽ አድርጐ ሊያዘጋጅ ይችላል ።

<u>ሁኔታ የሚፈጥረው ሞኖፖል</u> ፤ አንድ ነጋዴ ተወዳዳሪዎቹን ሁሉ ሊያጠፋ የቻለ እንደሆነ ፣ ወይም ራሱ የሠራው ዓይነት ካንድ ከታላቅ ፋብሪካ በቀር ሌላ ሊያከናውነው የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ፣ መሥራቱና መሸጡ ያንድ ብቻ ልዩ መብት ይሆናል ፤ ይህም ሁኔታ ሞኖፖል ይባላል ፤ ይህ ሞኖፖል በሕግ ተፈቅዶ ወይም በውል ተሰጥቶ ሳይሆን ፤ የሌሎቹ ነጋዴዎች መውደቅ ያፈራው ስለሆነ ሁኔታው የፈጠረው ሞኖፖል ይባላል ።

ነጋዴዎች በልዩ ልዩ ዘዴ ይህ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋሉ ። ለምሳሌ ፣ ከፍ ያለ የገንዘብ ኃይል ያለው አንድ ታላቅ ፋብሪካ ፣ ዕቃውን ለጊዜው በከሣራና በዝቅተኛ ዋጋ በገበያ መሸጥ ይጀምራል ፤ እንደሱ ሃብት የሌላቸው ተወዳዳሪዎቹ በከሣራ እንደሱው እንዲሸጡ ወይም ዕቃቸውን ታቅፈው እንዲቀሩ በማድረግ ፣ ጨርሶ ያከሥራቸዋል ።

በዚህ አኳኋን ተወዳዳሪዎቹ ከሰረው ገበያውን ሲለቁለት ንግዱን በሞኖፖል ይይዝና ባሰኘው ዋጋ በመሸጥ ፣ በመጀመሪያ ደርሶበት የነበረውን ኪሣራ እጥፉን ለመመለስ ይችላል ።

ይህ አሠራር በእንግሊዝኛ ደምፒንግ ይባላል ። ደምፒንግ በመንግሥታት መካከልም ይደረጋል ፤ በዚህ ጊዜ በደምፒንግ ለመጠቀም የሚፈልገው መንግሥት ፣ ያገሩን ፋብሪካዎች በገንዘብ በመርዳት በውጭ አገር ገበያ ከተወዳዳሪዎቻቸው ባነሰ ዋጋ እንዲሸጡ ፣ ያደርጋል ። የቤንዚን ገበያ በዓለም ላይ በዚሁ ዘዴ ሰብስበው በያዙት በጥቂት ማሕበሮች እጅ ብቻ መገኘቱ የታወቀ ነው ።

የመንግሥት ሞኖፖሎች ፤ አንዳንድ ጊዜ ፣ መንግሥት ላገር ኤኮኖሚካዊ ጥቅም የሚበጅ መስሎ ሲታየው አንዱን ዓይነት ዕቃ ራሱ ብቻ ለማውጣትና ለመሸጥ የሚያስችለው መብት በሕግ ያስወስናል ፤ ይህም ሕጋዊ ወይም የመንግሥት ሞኖፖል ፣ ይባላል ።

ለምሳሌ የኢትዮጵያ መንግሥት የትምባሆን ሞኖፖል ይዟል ፤

ባለኦክሲዮን ማሕበሮች ፤ አንዳንድ የኢንዱስትሪና የንግድ ግብርናዎች ፣ ባንድ ግለሰብ ሃብት ብቻ ሊንቀሳቀሱ የማይቻልበት ጊዜ አለ ። የድርጅቱ ታላቅነት ፣ ያንድ ሰው ሃብት ብቻ ሊያንቀሳቅሰው ፣ የማይፈቅድ ይሆናል ። በዚህ ጊዜ ዋናውን ገንዘብ ብቻ ሰዎች ያዋጣሉ ። የሚያዋጡትም ገንዘብ እንደየችሎታቸው ሰለሆነ ጥቂትም ብቻ የሚያገቡ አሉ ። ባወጡትም ገንዘብ መጠን ፣ አንድ ወይም ብዙዎች አክሺን የተባሉ ሰነዶች ይሰጧቸዋል ። እያንዳንዱ አክሺን የዋናው ገንዘብ አንድ መቶኛ ወይም አንድ ሺየኛ ሊሆን ይችላል ። ለምሳሌ ዋናው ገንዘብ ሺ ብር ቢሆንና ለሁሉም መቶ አክሺኖች ቢመድቡለት እያንዳንዱ አክሺን አስር ብር ማውጣቱ ነው ።

አንዱ አክሺንም የዋናው ገንዘብ አንድ አሶረኛ መሆኑ ነው ። አክሲዮኖቹ ሊሸጡ ሊለወጡ የሚችሉ ፣ ከማሕበሩ ትርፍም ለመካፈል መብት የሚሰጡ ሰነዶች ናቸው ። አክሺኖቹ እንደ ቁጥራቸው መጠን ለባለቤቱ የሚያስገኙት ትርፍ ድርሻ ይባላል ።

በአክሺን የተቋቋሙ ማሕበሮች ባለፉት ገጾች የተነተናቸውን ፣ ታላላቅ ባለሃብት ኢንዱስትሪዎች ኃይላቸውን አላግባብ በመዘርጋት የሚያደርጉትን ሞኖፖል የሚያስታግሱ አቅዋሞች ናቸው ።

ሥራውም ያንድ ሰው ወይም ያንድ ቤተ ሰብ ልዩ መብት በመሆን ፈንታ አነስተኞች ቆጣቢዎች ገንዘባቸውን

ከመቅበር ይልቅ አክሺን ገዝተው ስለሚያሠሩት ፣ ለሕብረ ሰብ የሚሰጠው ጥቅም በጣም ከፍ ያለ ነው ።

በኢትዮጵያ የወንጂ ሱኳር ማሕበር ፣ የድሬዳዋ ጥጥ ማሕበር ፣ ሌሎችም በአክሺን የሚሠሩ ብዙ የንግድና የኢንዱስትሪ አቅዋሞች አሉ ።

የእርሻ ሚኒስቴር

የእርሻ ሚኒስቴር ዓይነተኛ ተግባሩ ፣ የኢትዮጵያ ምድር ፍሬ ለመሆ ጠት የምትችልበትን ዘዴ መፈለግና ማጠናቀቅ ፤ እንዲህ ም ያገሪቱን የወሃና የደን ሃብት የመጠበቅና የማሰፋፋት አደራ የተጣለበት አቅዋም ነው ፤ (ስለሕብረ ግብርና በተከታዮቹ ገጾች እንገልጻለን ።)

የሥራና የመገናኛ ሚኒስቴር

ባለፉት ገጾች የዘረዘርናቸው ፣ የንግድ ፣ የኢንዱስትሪ፣ የእርሻ ሥራዎች ሁሉ ተገቢ መገናኛ ከሌለ ደንበኛ ጥቅም ሊያገኙ ይችሉም ። መገናኛ ሲባልም ፤ መንገዶች ፣ ሐዲዶች ፣ ወሃዎች ፣ ናቸውና ባገልግሎት ላይ እንዲውሉ ፣ ድልድዮቹ ፣ ግደቦች ፣ ኤሌክትሪክ ሞተሮችና መሶመሮች ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው ። ስለዚህ ሥራንና መገናኛን ባንድ ሚኒ

ስቴር ማጠቃለሉ አሰፈላጊና ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል ። የን ግድ መርከቦችና የንግድ አየር መንገዶች የሚተዳደሩት በ ዚህ ሚኒስቴር ውስጥ ነው ።

ግንኙት ፣ መሸጥ ፣ መለወጥ ፣ መዋዋል ፣ ይህን የመሳ ሰሉት ነገሮች አሳብን በጽሑፍ ወይም በቃል ለማስተላ ለፍ የሚቻልበትን ዘዴ ስለሚጠይቁ ፣ ለሕዝብ አካላዊ ኑሮ አሰፈላጊ ከሆኑት አቅዋሞች ከዋኖቹ አንዱ ፣ የፖስታ ፣ የቴ ሌግራፍና ቴሌፎን ሚኒስቴር ነው ።

በኢትዮጵያ የሰልክና የሬዲዮ ግንኙነቶችን የሚያከና ውን ፣ የቴሌኮሙኒኬሺን ቦርድ ነው ፤ ፍቹም ፣ ቴሌ ሩቅ ማለት ሲሆን ፣ ኮሙኒኬሺን መገናኛ ነውና የሩቅ ማገናኛ (አቀራራቢ) ልንለው እንችላለን ። በተረፈ ፣ በልዩ ልዩ ከተ ሞች የሚኖሩ ሰዎች ገንዘብ በፖስታ ለመላክ የሚችሉበ ትን ሐዋላ እየተባለ የሚጠራውን አሰደናቂ የሆነ ዘዴ የሚ መራ ፖስታ ሚኒስቴር ነው ።

የሚኒስቴሮች ተባባሪነት ፤

ከዚህ በላይ የጠቀሰናቸው ሚኒስቴሮች ለየራሳቸው የተወሰነ ሥራ ቢኖራቸውም ፣ በአሠራር ረገድ በብዙ መን ገድ ይገናኛሉ ።

ለምሳሌ ፣ ስለቤንዚን እናስተውል ። ቤንዚን ለማስመ ጣት የውጭ አገር ገንዘብ ያስፈልጋል

(ገንዘብ ሚኒስቴር) እንዲሁም ከባለ ቤንዚኖቹ አገ ሮች ጋራ መስማማት ያስፈልጋል ፤ (ውጭ ጉዳይ ሚኒስ ቴር) ፣ ቤንዚኑን ለየሥራው ማከፋፈል ያስፈልጋል (መገ ናኛ ሚኒስቴር) ደግሞም የሚመጣውን ቤንዚን መጠን መወሰንና እንዲገባ መፍቀዱ የንግድሚኒስቴር ሥራ ሲ ሆን ቤንዚን በብዛት ባልተገኘ ጊዜ ፣ በከሰል ወይም በእ ንጨት እሳት መጠቀም ስለሚያስፈልግ እርሻ ሚኒስቴ ርን ያገባዋል ።

በተረፈም የቤንዚን ማነስና መብዛት ፣ በመንገድ ፣ በባሕር ፣ በአየር የሚደረገውን ግንኙነት ሊያበዛውና ሊያሳ ንሰው ስለሚችል ፣ የሥራና የመገናኛ ሚኒስቴርን ፣ ፖ ስታ ሚኒስቴርንም ጭምር ማሳሰቡ አይቀርም ፤

ይህ ባንድ ጉዳይ የብዙ ሚኒስቴሮችን መተባበር የሚጠይቅ ሁኔታ ለአርእስቱ በቂ ምሳሌ ነው ፤

በሕብረት የሚፈጸሙ ሥራዎች

ወ ይ ም ሕ ብ ረ ግ ብ ር ና

ለማመንጨትም ሆነ ፣ ለመግዛት ፣ ለመበደርም ሆነ ለማበደር ፣ እመንጭው ፣ ገዥው ፣ አበዳሪው ፣ ተበዳሪው ለማግኘት ከሚመኙት ትርፍ እያንዳንዱ ሰው ለመቆጠብ ፣ እንዲችል ፤ ሕብረ ግብርና ይፈቅድለታል ፤

የሕብረግብርና መሠረታዊ ፍች ፤ ቃሉ ራሱ እመ ጣጡ ሕብረ ፥ አብሮ ፥ ግብርና ሥራ ማለት ስለሆነ ፥ ተባ ብሮ መሥራትን የተመረኰዘ ነው ።

ለምሳሌ አንድ የሰርዲን ፋብሪካ እንውሰድ ፥ የሚሠ ራው ባለቤቱ ትርፍ ያገኝበታል ። ነገር ግን ፥ በውስጡ ያ ሉት ሠራተኞች ላንድ ባለቤት ከመሥራት ይልቅ እራሳ ቸው በማሕበር ተቋቁመው ያመነጩ እንደሆነ ፥ ትርፉን እራሳቸው ይካፈላሉ ።

ሰርዲኑ በቆርቆሮ ሆኖ ከተሠራ በኋላ ፥ ተመጋቢው ገዥ ከነጋዴ ዘንድ ይገዛል ። ነጋዴው ፥ ትርፍ ያገኝበታል ማለት ነው ። ነገር ግን ገዥዎቹ በማሕበር ተቋቁመው ፥ ሰርዲኑን ፥ በብዛት አንድ ጊዜ ገዝተው የተከፋፈሉ እንደ ሆነ ፥ አትራፊዎቹ እነሱ ይሆናሉ ፤ ቸርቻሪው ከነሱ ይበላ የነበረውን ትርፍ ያድናሉ ማለት ነው ። እነዚህ ሁለቱ እ ጭር ምሳሌዎች ፤ የሕብረ ግብርናን ሥራ በማመንጨትም ሆነ ፥ በመግዛት ሊፈጸም መቻሉን ያስረዱናል ፤ ስለዚህ ፥ የማመንጨት ሕብረ ግብርና ፥ የመግዛት ሕብረ ግብርና የተባሉ ሁለት ዓይነቶች አሉ ።

ደግሞም አንድ ቤት ሊማሠራት ገንዘብ ያስፈለገኝ እንደሆነ ፤ ከአንድ ባንክ ፥ በወለድ እበደራለሁ ። ግን ፥ ቤት መሥራት የምንመኝ ብዙዎች የሆንን እንደሆነ ፤ ተቀማጭ፤ ገንዘባችንን ፥ ባንድ እናደርግና ፥ ከተጠራቀመው ዋና ላይ ፥ ለያንዳንዳችን የቤት መሥራት ተራችን ሲደርስ የሚረዳን ገንዘብ በብድር ይሰጠንና በዝግታ እንከፍላለን ፥ የተበዳሪ

ዎቹ ሕብረ ግብርና ይባላል ፤ ያገራችን ዕቁብ በዚህ መልክ የተቋቋመ ነው ።

ልዩነቱ ሕብረግብርናው በየተራው ሲያከፋፍል ፥ ዕ ቁብ ግን በዕጣ ያድላል ፤ በመሠረቱ ግን ፥ የሁለቱም ዓላማ ጥቂት ገንዘብ በማዋጣት ከፍ ያለ ገንዘብ ማከማቸትና እያ ንዳንዱ ሰው ባንድ ጊዜ ጠርቀም ያለ ገንዘብ እግኝቶ በሥራ ላይ አውሎት በጥቂት በጥቂቱ እንዲከፍል ለማድረግ ነው ።

የማመንጨት ሕብረግብርና ፤ የዚህ ዓይነት ሕብረግብ ርና በብዙ መንገድ ሊዘጋጅ ይችላል ። ለምሳሌ ፤ የወይን ተክል ያላቸው ብዙ ገበሬዎች ፥ በሕብረግብርና ፥ ይቋቋ ሙና የወይን ፍሬያቸውን ባንድ ቀላቅለው ፥ ወይን ጠጅ በብዛት በማውጣት በጅምላ ፥ ለመሸጥና በቀጥታ ለማት ረፍ ይችላሉ ።

በተለይ ባገራችን የወተት ነጋዴዎች ሥራ በጣም ደካማ ነው ። እያንዳንዱ ሰው ፥ አንድ አስር ሊትር ወተት በቆርቆሮ ተሸክሞ ብዙ ኪሎ ሜትሮች አቋርጦ ይመጣና አንድ ሁለት ብር ያህል አትርፎ ይመለሳል ፤ በዚህ አኳኋን ምንም ፥ ጊዜ ቢሆን ኑሮውን ለማሻሻል አይችልም ። ባንድ አጠራቅመው ፥ የሚናጠውንም ንጠው ቅቤ በብዛት ቢያ ወጡ የቀረውንም በካሚዎን ፥ እያሰጫኑ ከተማ ሄዶ እንዲ ሸጥ ቢያደርጉ ፤

አንደኛ ፥ የመመላለሱን ሥራ ጥቂቶች ሰዎች ብቻ ስለሚፈጽሙት የቀሩት ከጧት እስከ ማታሥራ ከመፍታት ይድኑና ሌላ ተግባር ሊያከናውኑ ይችላሉ ።

ሁለተኛ ፥ ማሕበሩ ለሁሉም ደንበኛ ዋጋ ወሰኖስለሚ ሸጥ እርሰ በርሳቸው በዋጋ በመወዳደር በዝቅተኛ ዋጋ ከመ ልቀቅ ይድናሉና የበለጠ ጥቅም ያገኙበታል ።

ሶስተኛ ፥ እያንዳንዱ ወተት ሻጭ ወደከተማ ሲመጣ ፥ ለአቶቡስ ፥ ለምግብ ለመጠጥ ከሚያወጣው ወጭ ሁሉ ይድ ናል ፤ በጠቅላላው በሕብረግብርና ማመንጨት ፥ ለማሕበረ ተኞች ከፍ ያለ ጥቅምና በመተባበር ሰጋትን ከያንዳንዱ ላይ ለማራቅ ይጠቅማል ።

<u>የግዥ ሕብረግብርና</u> ፥ በላይኞቹ መሰመሮች የግዥ ሕብረግብርና የሚሰጠውን ፥ ጥቅም ዘርዝረናል ፤ በመሠ ረቱ እነዚህ ማሕበሮች ፥ በችርቻሮ የሚሸጥባቸው ሱቆች ናቸው ። አንዳንዶቹ አንድ ዓይነት ሸቀጥ ብቻ ይሸጣሉ ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ፤ ዳቦም ፥ ሥጋም ፥ የወጥቤት ዕቃም ፥ ልብስም ይሸጣሉ ፤

ድርጅታቸው ቀጥሎ እንደተመለከተው ነው ። ለም ሳሌ ባንድ መንደር የሚኖሩ ሰዎች ፥ የምግብ ዕቃ የሚሸጥ በት ሱቅ አዋጥተው ያቋቁማሉ ፤ ማሕበረተኞች ሁሉ አ ንድ የተወሰነ ገንዘብ ያወጡና ሱቁ ፥ አንድ ካፒታል እንዲ ኖረው ያደርጋሉ ፤ ሱቁ ከፋብሪካው በቀጥታና በጅምላ ፥ ልዩ ልዩ የምግብ ዓይነቶች በደህና ዋጋ ይገዛና ማሕበረተኛ ለሆኑት ሁሉ በተሰማሙበት ጥሩ ዋጋ ይሸጥላቸዋል ፤ በ ዚህ ጊዜ ችርቻሪ ከሚበላቸው ትርፍ ዳኑ ማለት ነው ፤ ደግ ሞም ፥ ሱቁ ለማሕበረተኞቹ በችርቻሪ ዋጋ ይሸጥላቸውና

የተገኘውን ትርፍ ባመቱ መጨረሻ በገዙት ሸቀጥ መጠን እየታሰበ ይከፋፈላሉ ።

ወይም ለማሕበረተኞቹ በዝቅተኛ ዋጋ ፥ ማሕበረተኛ ላልሆኑት በገበያ ዋጋ እየሸጡ የተገኘውን ትርፍ እላይ በተባለው ዘዴ ይከፋፈላሉ ፤ ለምሳሌ እንድ ቤተሰብ የሺ ብር ሸቀጥ ገዝቶ እንደሆነ ፥ መቶ ብር ትርፍ ቢደርሰው ፥ የአምስት መቶ ብር ሸቀጥ የገዛው ደግሞ ፥ ሃምሳ ብር ማለ ትም ግማሹ ይደርሰዋል ማለት ነው ።

በጠቅላላው ሰዎች በሕብረግብርና በማመንጨት ፥ በመግዛት ፥ በመበዳደር የኑሮአቸውን ደረጃ ለማሻሻል ስለ ሚያስችላቸው ጉዳዩ በቀጥታ ፥ የሕዝባዊ ኑሮ እድገትን የሚመለከት ነው ። ይህ ሚኒሰቴር ፥ በየስፍራው ሕብረግብ ርናን በማቋቋም ላይ እንደሚገኝ ሁላችንም እናውቃለን ።

የግል ሃብትን ሕዝባዊ ስለማድረግ

የንግድ ወይም የኢንዱስትሪ ኦቅዋሞችን ፥ ከግል ወይም ከማሕበራዊ ባለቤቶች ላይ አዛውሮ ሕዝባዊ ሃብት ማድረግን ብዙዎች ሲደግፉት አንዳንዶች የሚቃወሙት አሉ ።

ከሁሉ አስቀድመን ፥ በቃል ትርጉም እንዳንሳሳት ፥ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተውን እንወቅ ።

በአገራችን በተለመደ አነጋገር ፥ ምድር ባቡር የመንግሥት ነው ይባላል ፥ ይህ በመሠረቱ ስሕተት ነው ፥ መንግሥት አገርን ያስተዳድራል እንጂ ሃብት ወይም ንብረት የለውም ፥ ስለዚህ ፥ ምድር ባቡር ሕዝባዊ ሃብት ነው ፤

ይህ የሕዝባዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ነው ፥ ማለት ይገባናል ። ማንኛውም መንግሥት የያዘው ንብረት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲሆን ፥ በሕዝቡ ስም መንግሥት ያስተዳድራል፥ እንጂ የመንግሥት አይደለም ፥ አንድ ንብረት የመንግሥት ነው ከተባለ ፥ የመንግሥት ፥ ሠራተኞች ሃብት ነው እንደማለት ይሆናልና ፥ የመንግሥት ንብረት ሲባል መንግሥት የሚያስተዳድረው ሕዝባዊ ንብረት ማለት ነው ። ይህን ከገለጽን በኋላ ፥ ወደዋናው ጉዳይ እንመለስ ።

የጉዳዩ ሁኔታና መነሻው ፤ ለምሳሌ ለሕዝብ ጠቅላላ ሕይወት አስፈላጊ የሆነ ፥ አንድ አቅዋም አለ ። ይህ አቅዋም ፤ ያንድ ወይም የብዙ ነጋዴዎች ንብረት ፥ በመሆን ፈንታ የሕዝቡ የጋራ ንብረት መሆን አለበት ሲባል ፤ አቅዋሙን ሕዝባዊ ንብረት ማድረግ ነው ። የጥርስ ቡሩሽ ወይም የጠጉር ማበጠሪያ ፋብሪካዎች ፥ ለሕዝቡ ጠቅላላ ሕይወት ፥ የማይታለፍ አስፈላጊነት ስለሌላቸው ፤ ፋብሪካቸውን ማንም ሰው ቢይዘው ግድ የለም ። ነገር ግን የምድር ከሰል ፥ ኤሌትሪክ ፥ ምድር ባቡር ሕይወታዊ ድርጅቶች ስለሆኑ ፥ ሕዝባዊ መሆን አለባቸው ። በሞራልም ረገድ ፥ ከአገሪቱ ታሕተ ምድር የሚወጣውን ከሰልና ብረት ወይም ከፏፏቴዎችዋ ፥ የመነጨውን ኤሌትሪክ ፥ ለዝቅተኛዋም ጐጆ ቤ

ሆን ግድ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ፥ አንድ ወይም ብዙ ነጋዴዎች ሊነግዱባቸውና ሊያተርፉባቸው ፥ ተገቢ አይደለም ፤

በፖለቲካ ረገድ ደግሞ ፥ የምድር ከሰልን ፥ ኤልትሪክን ፥ ምድር ባቡርን ፥ የመሳሰሉ ፥ ኃይሎች በጥቂት ሰዎች እጅ ማድረግ ፥ እንደፈቀዱ ፥ ሊያቆሙት ፥ ሊቀንሱት ፥ ዋጋውን ሊያወጡትና ሊያወርዱት ስለሚችሉ ፥ የመንግሥትን ሥራ አመራር በኤኮኖሚ ጭቆና ሊያሰናክሉት ይችላሉ ማለት ነው ።

በሕዝባዊ አገልግሎት ረገድ ደግሞ ፥ እንደዚህ ያሉት አቅዋሞች የሚመሠረቱት ፥ ለጠቅላላው ሕዝብ አገልግሎት እንጂ ፥ ለአቋቋሚዎቹ ማትረፊያና መደሰቻ አይደለም።

ማንኛውም የግል ንግድ ፥ በትርፍ ሕግ ላይ የተመሠረተ ነው ። ትርፍ የሚጠብቅ ነጋዴም ፥ ሥራው የማያተርፈው ከሆነ ፥ ምንም እንኳ ለሕዝብ አስፈላጊ ፥ ቢሆን የግዴታ ማቆሙ አይቀርም ።

ሁለት ምሳሌዎች እንውሰድ ፥ አንድ ሐኪም ፥ የሰልክ መስመር ባለው መንገድ ዳር ከተማ ውስጥ ይኖራል ፥ ደግሞ አንድ ሌላ ሐኪም ከሰልኩ መስመር ሁለት ኪሎሚትር ርቆ ይኖራል ፥ ሁለቱም ሐኪሞች ለሕዝብ አገልጋዮች ናቸው ። የሰልኩ ባለቤት ነጋዴ ከሆነ ፥ በመስመሩ ዳር ለሚገኘው ሐኪም በርካሽ ዋጋ ሰልክ ሊያገባለት ነው ፤ ያኛው ግን ርቀቱ የሚያስከትለውን ፥ ወጭ በተጨማሪ ካልከፈለ ሰልክ ላያገኝ ነው ፥ በመሠረቱ ደንበኞቹ ሩቅ የሚገኙበት ፥

የዚህኛው ስለሆነ ስልክ ይበልጥ የሚያስፈልገው ለሱ ነው። ስልኩ ግን ፣ ሕዝባዊ ሃብት የሆነ እንደሆነ ፣ ለሕዝብ በሚ ያገለግሉ ነገሮች ላይ ልዩነት ስለማይደረግ ለሁለተኛው ሐኪም የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የፖስታ ሚኒስቴር ከባ ጅቱ አውጥቶ ፣ ይችልለታል። ሁለተኛው ምሳሌ ፤ ሁለተወ ረዳዎች በሕዝብም ብዛት በእርሻም ልማት እኩል ፣ የሆኑ አሉ ። ግን አንደኛው ወረዳ ለጥ ባለሜዳ ላይ ሲገኝ ሁለተ ኛው ደግሞ ፣ በኰረብታዎች ተከቦ ይገኛል ።

በትርፍ ሕግ የሚመራ ድርጅት ብዙ ወጭ ለማይጠይ ቀው በሜዳ ላይ ለሚገኘው ወረዳ ባቡር ሲያገባ ፣ ለሁለተ ኛው ግን ገንዘብ ለመቆጠብ ሲል ሳያገባለት ሊቀር ነው ።

የሕዝባዊ አገልግሎት መሠረታዊ ደንብ ግን ፣ በሁለ ቱም ወረዳ የሚገኙት ሕዝቦች በምድር ባቡር እኩል እንዲ ጠቀሙበት ያስገድዳልና የምድር ባቡር መሥሪያ ቤት ባጀ ቱን አቻችሎ ለሁለቱም ምድር ባቡር ማግባት አለበት ።

በመሠረቱ ያንዳንድ ኢንዱስትሪዎች ሕዝባዊ ሐብት መሆን ፣ በረከቱ ለአገረሰቡ በትክክል እንዲደርሰው የሚ ረዳ ዘዴ ነው ።

አንዳንድ ተቃዋሚዎች በሕገ መንግሥቱ የግል ንብ ረት እንዲጠበቅ ያዛልና ከግል ወስዶ ሕዝባዊ ማድረግ የ መሠረቱትን ሰዎች አላግባብ መጉዳት ነው ይላሉ ። ነገር ግን ሕገ መንግሥቱ ደግሞ ፣ ለጠቅላላው ሕዝብ ጥቅም ከሆነ ፣ የማንኛውንም ሰው ንብረት አስቀድሞ ትክክለኛ ግምት ከፍሎ ለመውሰድ መፍቀዱን የዘነጉት ይመስላል ።

ም ዕ ራ ፍ 6 ፤

የአገረሰብ መብትና ተግባሮች

በሕገ መንግሥቱ በሶስተኛው ምዕራፍ ስለሰው መብ ቶችና ተግባሮች ይመለከታል ፤ ያንድ አገር ሕዝብ በጠቅ ላላው በተለይም እያንዳንዱ አገረሰብ መብቱንና ተግባሩን ጠንቅቆ ካላወቀ ፣ ለሕብረሰብ ፣ ጠቃሚ ሆኖ ሊገኝ አይች ልም ፣ ምሳሌውም ገንዘብ ሳያገባ ባዶ እጁን በንግድ ማሕ በር ውስጥ ሊሻረክ እንደሚመኝ ሰው ነው ፤ ስለዚህ የሕገ መንግሥቱን ልዩ ልዩ አንቀጾች በተራ በመጻፍና ፍቻቸውን በመዘርዘር እንባቢው በበለጠ አኳኋን ሊረዳቸው እንዲ ችል ለማድረግ ሞክረናል ።

ሕገ መንግሥቱ ፣ በአንቀጽ በአንቀጹ የሰውን መብት ሲዘረዝር ፣ ስለነጻነትና ፣ ስለእኩልነት ፣ መብት ይናገራል ፤ እንዲሁም ስለተግባሩ ያሰረዳል ፤ ስለዚህ እኛ ምዕራፋችንን በሁለት ላይ ከፍለን ማለትም ፣ ነጻነትንና እኩልነትን ፣ አስ ፋፍተን እንገልጻለን ።

የሰውን መብት ለማሶገኘት የተደረገ ትግል ፣ ከሰው ታሪክ ጋራ የቆየና ያረጀ ነው ።

የሕግ ሁሉ መሠረት የሆነው ደካማን ከኃይለኛ ጭ ቆና የማስጣል ዓላማ ነው ።

የዚህኛው ስለሆነ ስልክ ይበልጥ የሚያስፈልገው ለሱ ነው። ስልኩ ግን ፣ ሕዝባዊ ሃብት የሆነ እንደሆነ ፣ ለሕዝብ በሚ ያገለግሉ ነገሮች ላይ ልዩነት ስለማይደረግ ለሁለተኛው ሐኪም የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የፖስታ ሚኒስቴር ከባ ጀቱ አውጥቶ ፣ ይችልለታል ። ሁለተኛው ምሳሌ ፤ ሁለት ወ ረዳዎች በሕዝብም ብዛት በእርሻም ልማት እኩል ፣ የሆኑ አሉ ። ግን አንደኛው ወረዳ ለጥ ባለሜዳ ላይ ሲገኝ ሁለተ ኛው ደግሞ ፣ በኰረብታዎች ተከቦ ይገኛል ።

በትርፍ ሕግ የሚመራ ድርጅት ብዙ ወጭ ለማይጠይ ቀው በሜዳ ላይ ለሚገኘው ወረዳ ባቡር ሲያገባ ፣ ለሁለተ ኛው ግን ገንዘብ ለመቆጠብ ሲል ሳያገባለት ሊቀር ነው ።

የሕዝባዊ አገልግሎት መሠረታዊ ደንብ ግን ፣ በሁለ ቱም ወረዳ የሚገኙት ሕዝቦች በምድር ባቡር እኩል እንዲ ጠቀሙበት ያስገድዳልና የምድር ባቡር መሥሪያ ቤት ባጀ ቱን አቻችሎ ለሁለቱም ምድር ባቡር ማግባት አለበት ።

በመሠረቱ ያንዳንድ ኢንዱስትሪዎች ሕዝባዊ ሐብት መሆን ፣ በረከቱ ለአገረሰቡ በትክክል እንዲደርሰው የሚ ረዳ ዘዴ ነው ።

አንዳንድ ተቃዋሚዎች በሕገ መንግሥቱ የግል ንብ ረት እንዲጠበቅ ያዛልና ከግል ወስዶ ሕዝባዊ ማድረግ የ መሠረቱትን ሰዎች አላግባብ መጉዳት ነው ይላሉ ። ነገር ግን ሕገ መንግሥቱ ደግሞ ፣ ለጠቅላላው ሕዝብ ጥቅም ከሆነ ፣ የማንኛውንም ሰው ንብረት አስቀድሞ ትክክለኛ ግምት ከፍሎ ለመውሰድ መፍቀዱን የዘነጉት ይመስላል ።

ም ዕ ራ ፍ 6 ፤

የአገረሰብ መብትና ተግባሮች

በሕገ መንግሥቱ በሶስተኛው ምዕራፍ ስለሰው መብ ቶችና ተግባሮች ይመለከታል ፤ ያንድ አገር ሕዝብ በጠቅ ላላው በተለይም እያንዳንዱ አገረሰብ መብቱንና ተግባሩን ጠንቅቆ ካላወቀ ፣ ለሕብረሰብ ፣ ጠቃሚ ሆኖ ሊገኝ አይች ልም ፣ ምሳሌውም ገንዘብ ሳያገባ ባዶ እጁን በንግድ ማሕ በር ውስጥ ሊሻረክ እንደሚመኝ ሰው ነው ፤ ስለዚህ የሕገ መንግሥቱን ልዩ ልዩ አንቀጾች በተራ በመጻፍና ፍቻቸውን በመዘርዘር እንባቢው በበለጠ አኳኋን ሊረዳቸው እንዲ ችል ለማድረግ ሞክረናል ።

ሕገ መንግሥቱ ፣ በአንቀጽ በአንቀጹ የሰውን መብት ሲዘረዝር ፣ ስለነጻነትና ፣ ስለእኩልነት ፣ መብት ይናገራል ፤ እንዲሁም ስለተግባሩ ያሰረዳል ፤ ስለዚህ እኛ ምዕራፋችንን በሁለት ላይ ከፍለን ማለትም ፣ ነጻነትንና እኩልነትን ፣ አስ ፋፍተን እንገልጻለን ።

<u>የሰውን መብት ለማስገኘት የተደረገ ትግል ፣ ከሰው ታሪክ ጋራ የቆየና ያረጀ ነው ።</u>

የሕግ ሁሉ መሠረት የሆነው ደካማን ከኃይለኛ ጭ ቆና የማስጣል ዓላማ ነው ።

በማንኛቸውም ሃይማኖት የተመሩ እምነቶች ሁሉ ፣ በሰው መካከል ወንደማማችነትን ፣ እኩልነትን መፋቀርን ያላሶ ተማሩ አይገኙም ፤ የታላላቅ ፈላስፎችም እምነት ፣ ሰው በተፈጥሮው ነጻ ነው የሚል ነበር ፤

ባለፉት ምዕታመቶች የዴሞክራሲ መንፈስ እየተዘ ረጋ ሲሄድ የሰው መብትም ጥናት በዚሁ መጠን እየተስፋፋ ሄደ ፣ ጥንት በ1215 ፣ ማኛ ካ ር ታ የተባለ ሕግ ፣ ቀጥሎም ፣ በቅርቡ በ1679 ሐቤአስ ኩርፑስ እክት የተባለው የእንግሊ ዞች ኦሶደናቂ የሆነው ሰበዓዊ ክብር መጠበቂያ ሕግ ፣ በ1776 ፣ የወጣው የአሜሪካን የነጻነት አዋጅ ፣ ፍጹምነትን ያገኘው ፣ የፈረንሣይ ፣ በ1789 የወጣው የሰው መብት አ ዋጅ ፣ ታሪካዊ ሰነዶች ናቸው ።

ኢትዮጵያ እ ኤ አ በ1949 የመንግሥታት ማኅበር ያወጣውን የሰው መብቶች ዓለምአቀፍ ጽሑፍ ተቀብላ ፣ በራሷ ሕገ መንግሥትም ፣ በተሚላ እኳኋን እጽድቃዋለች ፤

ነጻነት ።

ነጻነት ማለት የፈቀዱትን ነገር ሁሉ መሥራት ኦይደ ለም ፣ ያንዱ ሰው ነጻነት ፣ በሌሎቹ ሰዎች ነጻነትና በጋራ ጥቅም ይወሰናል ። ቢሆንም መንግሥት እጅግ አሶ ፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ ካልሆነ በቀር ለነጻነት ወሰን እንዳ ያደርግ ተግባሩ ነው ።

የነጻነት ፍች ፤ ነጻነት ማለት ሌሎችን የማይጐዳ ነገር ሁሉ ለመሥራት መቻል ነው ።

ሶለዚህ አንድ ሰው በነጻነቱ በሚጠቀምበት ጊዜ ፣ የሌሎቹን አገረሰቦች ነጻነት ፣ ካልተቃወመ በቀር ለነጻነቱ ወሰን የለውም ። እነዚህም ወሰኖች በሕግ ይታወጃሉ ።

ይህ ፍች የተሚላ ነው ፤ መብትና ዘመናዊ አእምሮ ፣ እላይ በተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልሆነ በቀር የሰው ነጻነት እንዲጣበብ አይፈቅዱም ። ባለቤቱ እራሱ እንኳን ቢፈ ቅድ ፣ ነጻነቱን በውል በጭራሽ ኦሳልፎ ሊሰጥ አይችልም ። ለሥራም ሲቀጠር ለእደሜ ልኩ መዋዋል የለበትም ። የራሴ ነጻነት ፣ ሊደፈር የማይገባ ቢሆንም፣የሌሎቹ የነጻነት መብት ሶኔ ነጻነት ወሰኑ ነው ፤ ለዚሁም አጭርና ቀላል ምሳሌ ቀጥሎ የተመለከተው ሊሆን ይችላል ።

እኔ በቤቴ ውሶ ጥ የሚመኖለኝን ነገር ለመሥራት ነጻ ነት ኦሪኝ ፣ ነገር ግን ጐረቤቴ ደግሞ በቤቱ ውሶ ጥ የመተ ኛት መብት ሶላለው ፣ ሰዓት ካለፈ በኋላ ራዲዮ በማሶ ጮህ እንቅልፉን ልነሳው አልችልም ። ጐረቤቴ ለመተኛት ያ ለው ነጻነት የኔን ነጻነት ወሰን አበጀለት ማለት ነው ።

የነጻነት መወሰን ፤ የነጻነት ወሰን በሕግ መታወጅ አ ለበት እንጂ ባለ ሥልጣን ፤ እንዳሰኘው ሊያዝበት ኦይች ልም ። ሶለዚህ ልዩ ልዩዎቹን የነጻነት መልኮች ለየብቻ ብናጠና የተሻለ ነው ።

ሀ) <u>የማሰብና የሃሳብ መግለጽ ነጻነት</u> ፥ ከነጻነት ሁሉ ቀላሉ የማሰብ ነጻነት ነው ፤ ሃሳቤን ማንም ሰው ሊያውቀው ስለማይችል የፈለግሁትን ማሰብ እችላለሁ ፤ ስለዚህ ሃሳቤን መግለጽ ካልቻልኩ የሃሳብ ነጻነት ምንም ዋጋ የለውም ። በዚህ መሠረት የተሰጠው መብት በሚቀጥለው አኳኋን ሊፈታ ይችላል ፤

በሕግ የተመሠረተውን ሕዝባዊ ጸጥታ የሚበጠብጥ ካልሆነ ፥ ማንኛውም ሰው በአስተያየቱና ባስተሳሰቡ የተ ነሳ ፥ በሃይማኖትም ረገድ ቢሆን ፥ ሊደፈር አይገባም ፤ ሃሳ ብንና አስተያየትን መለዋወጥ ከሰብአዊ መብቶች ከዋነ ኞቹ የሚቆጠር ስለሆነ ፤ እያንዳንዱ አገረሰብ ፥ በነጻ መና ገር ፥ መጻፍና ማሳተም ይችላል ። ግን ይህን በሚያደርግበት ጊዜ በሕግ የተጻፈውን ቢተላለፍ ተጠያቂ ይሆንበታል ።

እዚህ ላይ ሃሳቤና አስተያየቴ ፥ የመንግሥቱን ጸጥታ ከነኩ በቀስቃሽነት የምከሰስ መሆኑ ተገልጿል ።

በሕግ በተወሰነው መሠረት አሳብ መግለጽ ብዙ መ ልክ ሊኖረው ይችላል ፤ ሕገ መንግሥቱ ጸጥታን ሳያደፈርሱ መሰብሰብን ስለሚፈቅድ በሰብሰባው ላይ በንግግር አሳ ብን መግለጽ ይቻላል ።

ቢሆንም በሰብሰባው ብጥብጥ እንዳይነሳ ጸጥታ ፥ አስ ጠባቂ ባለሥልጣን እንዲኖር ያስፈልጋል ፤ እርሱም ስብሰ ባው ሰላማዊ መልኩን ሲተው ሲያይ ሊበትነው መብት አ ለው ፤

ለ) <u>የማሳተም ነጻነት</u> ፤ ማንኛውም ሰው ፥ ሃሳቡን በእ ትም ፥ በመጽሐፍ ፥ በማስታወቂያ ወይም በጋዜጣ ሊገልጽ ይችላል ፤ አገረ ሰብ ሃሳቡን ሊገልጽ ከሚችልበት ከማንኛ ቸውም ፥ መንገድ ሰፊ የሆነው የማሳተም ነጻነት ነው ። ነ ገር ግን በዚህ አይነቱ መግለጫ ብዙ እዋኪ ነገሮች ይፈጠ ራሉ ፤ አንዳንዶቹ ሰዎች ለማሳተም በተሰጣቸው ነጻነት ያለደንብ በመጠቀም ሌላውን ሊያዋርዱበትና ሊሰድቡበት ይችላሉ ።

በሕገ መንግሥቱ ውስጥ ፤ ሕግ የወሰነውን ሳይተላለፍ የተባለው እንደዚህ ያደረጉ እንደሆነ ፥ ተጠያቂ እንዲሆኑ ነው ። ሕግ ይህን በማሳሰብ ፥ የተበደለው አገረሰብ በወነጀ ለው ፥ ጋዜጣ ላይ መልስ ለመስጠት እንዲችል መብት ሰጥ ቶታል ፤ አለዚያም የጻፈውን ሰውና የጋዜጣውን ዲሬክተር በአባሪነቱ ፥ በስም አጥፊነት በዳኝነት ፊት ሊያቀርባቸው ፥ ይችላል ። ደግሞም ፥ ባለገንዘብ የሆኑ ሰዎች ጋዜጦችን በመግዛት የነሱን ሃሳብ እንዲደግፉ ለማድረግ ስለሚችሉ ፥ አንዳንድ አገሮች ጋዜጦች ፥ በዳረጎት ገንዘብ እንዳይተዳ ደሩ ይከለክላሉ ። በተረፈ በጦርነትና በአደገኛ ሁኔታ ጊዜ ፥ ለአገሪቱ አጠባበቅ የሚጐዱት እንቀጾች ሁሉ እንዲቆረጡ የሚያደርግ ወታደራዊ ሳንሱር ይቋቋማል ፤

መ) <u>የሃይማኖት ነጻነት</u> ፥ እያንዳንዱ ሰው የሃይማኖ ቱን ሥርዓት ፥ ጸጥታና ፖለቲካን ሳያውክ እንዲያከብር በሕገ መንግሥቱ መብት ተሰጥቶታል ፥ ሃይማኖት የግል ናት እገር ግን የጋራ ናት ፥ የሚለውን ንጉሠ ነገሥታዊ ቃል እናስታውስ ፤

ሠ) የራስ ነጻነት ፤ ከነጻነት ሁሉ ፤ ሰው ከፍ ያለ ዋጋ የሚሰጠው ፥ ሕግ በትክክል በወሰነው ፥ መንገድ ካልሆነ በቀር እንደማይታሰር እርግጠኛ መሆኑን ነው ።

የግል ነጻነት መሠረት ይህ ነው ። ዛሬ ይህ ነጻነት በሠለጠኑ አገሮች ሁሉ ታውጇአል ። የኢትዮጵያም ሕገ መን ግሥት በጥሩ አኳኋን እትቶታል ፥ ፍሬ ነገሩ ቀጥሎ እንደተ መለከተው ነው ።

— ማንኛውም ሰው ሕግ ባዘዘው መንገድና በወሰነው አኳኋን ካልሆነ ፥ በቀር ሊከሰስ ሊያዝና ሊታሠር አይች ልም ።

— ስለዚህ ከዚህ ደንብ ውጭ የሆነ ትእዛዝ እንዲፈጸም የሚጠይቁ ፥ የሚያስጠይቁ ወይም የሚፈጽሙ በሕግ ተላላ ፊነት ይጠየቃሉ ።

— ግን ይህ መብት የተሰጠው አገረ ሰብ ፥ በሕግ መሠ ረት ሲጠራ ወይም ሲያዝ ፥ ወዲያው መታዘዝ አለበት ፤ አለ ዚያ በእንቢተኛነት ይከሰሳል ።

— ማንኛውም ሰው ወንጀሉን ከመፈጸሙ በፊት ወጥቶ በታወጀ ሕግ መሠረት ካልሆነ በቀር ሊቀጣ አይቻልም ።

ይህ አንቀጽ ሕግ ወደኋላ ተመልሶ እንዳይሠራ የሚከ ለክል ነው ።

ለምሳሌ እኔ ዛሬ በሕግ የተፈቀደ አንድ ነገር ብሠራና፥ ነገ ይህን እድራጐት ወንጀል የሚያደርገው ሕግ ቢታወጅ ፤

እኔ በፈጸምኩት ጊዜ ገና ወንጀል ባልነበረ አድራጐት ልከ ሰስበት አይቻልም ።

እኔ በሕግ አውጭው አእምሮ ውስጥ ያለውን ለማወቅ ችሎታ አልነበረኝምና አድራጐቴ ትክክለኛ ነው ፤ አድራ ጐቴንም ዛሬ ባለው ሕግ ላይ ብቻ መመሥረት ሰላለብኝና ፥ ወደኋላ ተመልሶ የሚቀጣ ሕግ ይወጣል በማለት ከሚያድ ርብኝ ሰጋት ስለምድን ዋስትና አለኝ ማለት ነው ።

ነገር ግን የሕዝብና የአገር የበላይ ጥቅም በጠየቁ ጊዜ ፥ ለምሳሌ በጦር ሁኔታ ጊዜ ምንም የተቀደሰ መብት ቢሆን ግላዊ ነጻነትም ለጊዜው ሊታገድ ይቻላል ። ይህ አድራጐት፥ ተገቢነትን የሚያገኘው ፥ ዛሬ የግል ነጻነትን ለጊዜው በመ ወሰን ለወደፊቱ የጋራ ነጻነት እንዲጠበቅ ለማድረግ በማ ሰብ የተወጠነ መሆኑ ሲረጋገጥ ነው ። ይህ ሁኔታ በተፈጠ ረም ጊዜ ውሳኔው በሕግ መልክ መታወጅ አለበት ።

ረ) ከዚህ ራስጌ የዘረዘርነው ሁኔታ ሰባዓዊ ነጻነቶች ዋናዎቹም ቢሆኑ ፥ ዘወትርና በሁሉ ስፍራ ሊከበሩ የማይ ቻል መሆኑን ይገልጽልናል ። ነገር ግን ፥ መንግሥት ፥ በተ ለይም በኤኮኖሚ ረገድ ነጻነትን ሲያጠብ ፥ ለጊዜው የተደ ረገ ነገር መሆኑንና ለሰብዓዊ ነጻነት ሙሉ ተፈጸሚነት መሰጠት እሰፈላጊ መሆኑን ማመን አለበት ፤ ለምሳሌ ፥ አ ንድ ሐኪም በሽተኛውን ብዙ የምግብ ዓይነቶች እንዳይ በላ ፥ ሲከለክለው ፥ የተሻለው ያመጋገብ ዓይነት ይህ ነው ብሎ አይደለም ። ነገር ግን በሽተኛው ለጥቂት ጊዜ በዚህ ብተወሰነ አመጋገብ በመኖር እንደገና ጤናውን አግኝቶ

ያስኘውን መግብ የመብላት ነጻነቱን በሙሉ እንዲያገኝ ለማድረግ ነው ። ስለዚህ ያንድ አገር ነጻ ሕዝብ ሲቻ ለው የሚያቃልለለት መሆኑ ሲሰማው ፣ መንግሥት በነጻ ነቱ ላይ የሚያደርገውን አስፈላጊ ልጓም ፈቅዶ መቀበል ግድኛ ነው ።

ኤኩኖሚካዊ ነጻነቶች ፤

ከዋናዎቹ ነጻነቶች ሌላ ፣ ሰው ፣ በመሠረቱ የፈቀደ ውን ሥራ ለመያዝ ፣ የሥራውን ፍሬ ለማኖርና በሚሰማ ማው መንገድ ሲጠቀምበት መብት አለው ፤

ሀ) የሥራ ነጻነት ፤ በሕገ መንግሥቱ መሠረት ፣ ማናቸ ውም ሰው ያደረገው ውል ከፈቀደለትና ችሎታ ካለው ፣ የመሰለውን ሥራ ለማያዝ በገዛ አላፊነቱም ሥራ ለመለ ወጥ ፣ መብት አለው ፤ እንዲሁም ብቻውን ራሱ ወይም ከ ሥራ ጓደኞቹ ጋር በመተባበር ሥራውን ለመተው መብት አለው ፤ ስለዚህ አንድ ሰው የማይፈቅደውን ሥራ እንዲ ይዝ ለማስገደድ አይቻልም ።

ለ) የንግድና የኢንዱስትሪ ነጻነት ፤ እያንዳንዱ ሰው ሥራውን ለመምረጥ መብት አለው ተብሏልና ራሱ ደስ የሚለውን ዕቃ ሠርቶ ፣ ለመግዛት ፈቃደኛ ለሆኑ ሰዎች ለመሸጥ ነጻነት አለው ። ቢሆንም ፣ በጦርነት ወይም በው ጭ ኀንዘብ ፣ ችግር ምክንያት ፣ መንግሥት አንድ ዓይነት ዕቃ ከተወሰነ ቁጥር በላይ እንዳይሠራ ፣ ለመከልከል ይች ላል ፤

መ) የመዘዋወር ነጻነት ፤ ባገሩ ውስጥ ለመዘዋወርም ሆነ በውጭ አገር ለመሄድና ተመልሶ ለመግባት የሰው ጽኑ ፍላጐት ስለሆነ በሕግ አይከለከልም ።

ያንዳንድ አገር ሰዎች ወደሌላ አገሮች እየሄዱ ኑዋሪ በመሆን በተለይም ለአዲሶች አገሮች ያስገኙት ጥቅም በ ጣም ከፍ ያለ ነው ። በዛሬ ጊዜ በያንዳንዱ አገር ፣ የይለፍ ጽ/ቤት አለና በአገሩ የሚገቡትንና የሚወጡትን ሰዎች በ ፓስፖርታቸው አማካይነት ይቆጣጠራቸዋል ። ካንድ አገር ወደሌላ ጨርሶ ለመዛወር የሚፈቅድ አገረሰብ የትውልድ አገሩንና የመሄጃውን አገር ባለሥልጣኖች ፈቃድ ማግኘት አለበት ፤ ከአገሩ ውጭ የሚወጣ ሰው ፓስፖርት ያስፈል ገዋል ። በባእድ አገርም ሊገባ የሚችለው የዚህ አገር ቆን ሲል ፓስፖርቱ ላይ የቪዛ ፈቃድ ከሰጠው በኋላ ብቻ ነው ። እያንዳንዱ ሰው ወደ ውጭ አገር ይዞት ለሚሄድ የሚችለው ገንዘብ በሕግ የተወሰነ ነው ።

ሠ) ንብረት የማብጀት ነጻነት ፤ ለሰው ሊከለክሉ ከማ ይቻሉት መብቶች መካከል ንብረት ማብጀት ፤ ከዋኖቹ አንዱ ነው ፤ በሕገ መንግሥቱ ፤ ስለንብረት ማብጀት በተ ለይ አንድ አንቀጽ አለ ፤ ባጭሩ ቃሉ ቀጥሎ እንደተመለከ ተው ሊጠቃለል ይቻላል ።

— ማንኛውም ሰው ፣ ንብረት ማበጀት የተቀደሰና የማይ ደፈር መብቱ ነው ፣ ለሕዝባዊ አገልግሎት አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘና፤ የተወሰነና የተቆረጠ ትክክለኛ ግምት ፣ አስቀ

ድሞ ካልተከፈለ በቀር ማንም ሰው ንብረቱ አይወሰድበ ትም ። በግሞቱም ፥ ሰምምነት ባልተገኘ ጊዜ ፥ በዳኝነት ሥርዓት እንዲታይለት ለመጠየቅ ይችላል ፥

ይህ እንቀጽ ፍጹም የሆነና ፍቹ የማያሳስት ፥ በባለ ንብረትነት መብት ላይ ሊኖሩ የሚችሉትን ጥበቶች በተለ ይም ፥ ለሕዝባዊ አገልግሎት ሲባል ንብረቱን የሚለቅበ ትን ፥ ሁኔታ ያስረዳል ። ለምሳሌ ቦታው ለሆስፒታል ፥ ለመ ንገድ ፥ ለምድር ባቡርና ይህን ለመሳሰለው ነገር ሲያገለ ግል ፥ ማለት ነው ።

ንብረት ለማስለቀቅ ለሕዝባዊ አገልግሎት ጠቃሚ ነቱ ፥ በግልጽ መታወቅና መረጋገጥ አለበት እንጂ ፥ ያንዱ ኩባንያ ዲሬክተር ፥ ወይም አንድ የሥራ ሹም የሚያቀርበው ድፍን አሳብ አይበቃም ፤ ንብረት በማስለቀቅ ጊዜ ግምት እንዲከፈል ግዴታ ነው ። ግምቱም ትክክለኛ መሆን አለ በት ማለትም ንብረቱ ሊያወጣ የሚችለው ገንዘብ በማያሳ ስት ሁኔታ መታወቅ አለበት ፤ ሊያንስም ፥ ሊበዛም አይፈቀ ድም ፥ ለቃቂው ከዋጋው ያነሰ ዝቅተኛ ግምት ተቀብሎ እን ዲለቅ አይገደድም ፥ አቤት የማለትም መብት አለው ፤ እሱም በበኩሉ ፥ ለምሳሌ በሱ ርስት ላይ መንገድ የሚከ ፈት መሆኑን ሲያውቅ ፥ የሚጠይቀው ግምት ርስቱ ዛሬ የሚያወጣውን ግምት ነው እንጂ መንገድ ከተከፈተ በኋላ ሊያወጣ የሚችለውን ዋጋ አይደለም ። በማናቸውም መን ገድ የግምቱ አከፋፈል ፥ ባለንብረቱ እንዲለቅ ከመደረጉ በፊት መፈጸም አለበት ፤

እኩልነት ፤

የሰው አካላዊና አእምሯዊ እኩልነት ሕዝባዊ እኩል ነትና ፖለቲካዊ እኩልነት ሶስት የተለያዩ ነገሮች ናቸው፤ ሕዝባዊ እኩልነት ፥ ለሁሉም እኩል መብት የሚሰጥ ነው ። ፖለቲካዊ እኩልነት ለሁሉም በመንግሥት ማለትም በሕ ዝብ አስተዳደር ሥራ የመካፈልን መብት የሚሰጥ ነው ፤

ሀ) <u>የእኩልነት ጉዳይ አቀራረብ</u> ፥ የእኩልነት ጉዳይ ለክርክር ምቹ የሆነ ጉዳይ ይመስላል ። ብዙዎች ነገሩን መርምረው ያልተረዱትና ያላወቁት ፥ እኩልነት የለም በማ ለት ፥ የሚያቀርቡት ማሰረጃ ለጊዜው እውነት ከነሱ በኩል ያለ ያስመስላል ። ባገላለጻቸውም ላይ አንዳንዱ ሰው ጕበዝ፥ ውብ ፥ አዋቂ ፥ ንቁ ፥ ሲሆን ሌላው ደካማ ፥ ፉንጋ ፥ ገልቱ ፥ ወይም ሰነፍ ሊሆን ይችላልና ታላላቆቹን ፈላስፎች ከመን ደር ደንቆሮ ጋራ እኩል ለማድረግ አለመቻሉን ያስረዳሉ ፤ በዚህም የተነሳ ሰዎች እኩል ናቸው ማለትን እንደ ከንቱ ነገር ይቆጥሩታል ።

ይህ የነሱ አስተያየት ትክክለኛውን መንገድ ያልያ ዘና ፥ የአካልንና የማወቅን እኩልነት ከሕዝባዊ እኩልነት ጋራ በመቀላቀል የተሰጠ ነው ፤ የሰዎች ጠቅላላ ሁኔታዎች ለሁሉም እኩል ሊሆኑ አለመቻላቸው ግልጽ ነው ፤ ነገር ግን ሕጉ የሚናገረውና የሚያጸድቀው ፥ የሰዎችን የመብት እኩልነት ነው ።

በሕገ መንግሥቱ አነጋገር ፥ ማንም ሰው በሕግ እኩል ሆኖ ይጠበቃል ፥

በብሄራዊ መብቶች ረገድ በኢትዮጵያውያን መካከል ልዩነት አይደረግም ፥ ሲል ሰዎች ሲወለዱ ነጻና በሕግ ፊት እኩል መሆናቸውን ፥ ያስረዳል ፤ ፍቹም ፥ ማንም ሰው በተ ውልዱ ሰበብ ሕጋዊ የሆነ ልዩ መብት አይሰጠውም ፤ እንዲ ሁም ፥ ሕጋዊ መብቱ አይቀነስበትም ማለት ነው ። የዚህ እኩልነት መሠረተ አሳብ በልዩ ልዩ ረድፎች ይከፈላል ።

ለ) <u>የዘር እኩልነት ፤</u> ባንድ ሕዝብ ውስጥ የሚቆጠሩ አገረሰቦች ዘራቸውና ቀለማቸው ማንኛውም ቢሆን ፥ መብ ታቸው የሁሉም እኩል ነው ።

ላንድ ለተመረጠ ዘር ባአገሩም ውስጥ በሆነ በውጭ ሌሎቹን ዘሮች የመጨቆን መብት ይሰጥ የነበረው የዘር ልዩነት መብት ከሰው መብት ኢንተርናሺናላዊ አዋጆች ጋራ የተቃወሰ ነው ። ባለፉት ዓመታት ይህን ፍልስፍና ያጋ ነኑት ሰዎች ከሃሳቡ ጋራ አብረው እንደጠፉ ይታወሰናል ።

ዛሬም ባንዳንድ አገሮች የዚህ ፍልስፍና ደቀመዝሙ ሮቹ ስለሚገኙ የመምህሮቻቸውንና የገቢራቸውን እድል ይከተላሉ የማለት እምነት በሁሉም ዘንድ አለ ፤

መ) <u>በብሄራዊና በወንጀለኛ ሕግ ፊት እኩልነት ፤</u>

ሕግ ሲጠብቅም ሆነ ሲቀጣ ለሁሉም እኩል መሆን አለበት ፥ አገረሰቦች ሁሉ በአንድ ፍትሐ ብሔር ሕግ ጉዳያ

ቸው ይታያል ። ሁለት አገረ ሰቦች አንድ አይነት ወንጀል ሠርተው ቢገኙ ፥ ምንም እንኳ ደረጃቸውና ማዕረጋቸው የተለያየ ቢሆን ፥ ባንድ ወንጀለኛ መቅጫ በአንድ ዓይነት አንቀጽ ይጠየቃሉ ። ደግሞም ሥራቸው ወይም ሃብታቸው ማንኛውም ቢሆን ፥ የሚቀርቡት ባንድ ዓይነት የዳኝነት ሥልጣን ፊት ነው ።

ሠ) <u>የግብር አከፋፈል እኩልነት ፤</u> ሕዝባዊ ኃይል ተቋ ቁሞ እንዲኖር ፥ ላገሩም አስተዳደር ለሚሆነው ወጭ ፥ የሕ ብረት መዋጮ አስፈላጊ ነውና ፥ እንደየአቅማቸው መጠን የሚደርስባቸውን አገረ ሰቦች በሙሉ ማዋጣትና መስጠት አለባቸው ።

ይህ አንቀጽ ግልጽ ነው ፥ አገር ያለገንዘብ ሊተዳደር አይችልም ፥ ይህንንም ገንዘብ አገረሰቡ ካላዋጣ ከማንም ሊገኝ አይቻልም ። በመሠረቱም መዋጮው በያንዳንዱ ሰው ፥ እንደየችሎታው ፥ ማለትም እንደየሃብቱ መጠን እንጂ በማኅበራዊ ደረጃው አይወሰንም ማለት ነው ።

ነገር ግን ይህን ትክክለኛ ደንብ ለማስፈጸም ግብር አስገቢው ፥ በሚደክምበት ጊዜ አንዳንዶች ሰዎች ገቢያቸ ውን በመሰወርና አነስተኛ በማስመሰል ፥ በእርግጥ የሚደር ርስባቸውን ሳይከፍሉ ያመልጣሉ ። ይህ አድራጐት በሕብ ረሰብ ላይ የሚያስከትለውን ጉዳት በሞራል ክፍል እናትተ ዋለን ። ደግሞም ግብር በትክክለኛ መንገድ እንዲደርስ ሕግ አውጭዎች በሚያጠኑበት ጊዜ ልዩ ልዩ ችግር ስለ ገ ጠማቸው ፥ የአገረሰብን ገቢ ብቻ ሳይሆን የችግሩን መጠን

ማመዛዘን ፥ እንዲሁም ገቢ ከፍ ሲል በመቶ የሚከፍለውም ከፍ እያለ እንዲሄድ አድርገዋል ፤

ለምሳሌ ፥ ሁለት የቤተ ሰብ አባቶች እኩል ገቢ ቢኖ ራቸው ፥ ነገር ግን አንዱ አምስት ልጆች ሲኖሩት ሌላው አንድ ብቻ ቢኖረው ፥ ምንም እንኳን ገቢያቸው እኩል ቢ ሆን ፥ የሚደርሰባቸው ግብር እኩል ሊሆን አይችልም በ ሚል መንገድ ማሰብ ይኖራል ።

እንዲሁም አንድ አገረሰብ ፥ 100 ብር ቢኖረው ፥ አ ንዱ ደግሞ 10000 ብር ቢኖረው ፥ እያንዳንዳቸው የገቢያቸ ውን አንድ አሥረኛ ይከፍላሉ ብሎ መወሰን ስሕተት ነው ።

የመጀመሪያው ሰው 100 ብር ለኑሮው አስፈላጊ የሆነ ዋና እንደመሆኑ መጠን ፥ ከሱ ላይ አንድ አሥረኛ ግንሳት የማይችለው እዳ ሊሆንበት ነው ፤ ባለ 10000 ብር ግን ካ ንድ አሰረኛ በላይም ቢከፍል ጉዳት የለበትምና ፥ በእንደ ዚህ ያለ ጊዜ የገቢውን መጠን ብቻ በማየት መወሰን ትክክ ለኛ አስተያየት ነው ።

ረ) <u>በወታደርነት ተግባር ፊት እኩልነት ፤</u> በኢትዮ ጵያ የወታደራዊ አገልግሎት ግዴታ ለጊዜው አልተቋቋ መም ። ነገር ግን አገሪቱ በተጠቃች ቀጥር ወታደርም ሲሸ ልም ፥ ጐን ለጐን ተሰልፎና ተዋግቶ እስካለንበት ጊዜ ድ ረስ በነጻነት ያቆያት በመሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጀግንነት በዓለም ላይ የታወቀ ነው ። ቢሆንም በአገር አስተዳደር ላይ እኩልነት ለሁሉም ተሰጥቷልና በዚህ መብት የሚጠቀም

አገረሰብ ሁሉ ፥ አገሪቷን በየተራው በወታደርነት ፥ ግብል ገል ስላለበት የወታደርነት አገልግሎት ግዴታ ወደፊት መቋቋሙ አይቀርም ።

ጤናቸውና አቅማቸው የማይፈቅድላቸው ግን ይህን ተግባር ለመፈጸም ስለማይችሉ ፥ ሴቶችን ፥ እድሜያቸው የላቀን ወንዶች ፥ አካለ ጐዶሎዎችንና ደዌ የጐዳቸውን ሁሉ ፥ ከዚህ ግዴታ ውጭ ማድረግ ትክክለኛ አስተያየት ነው ።

ሸ) <u>በሥራና በማዕረግ ማግኘት የእኩልነት መብት ፤</u> ማኅበራዊ ደረጃ የሚለየው እያንዳንዱ ሰው ለማኅበሩ በሚ ያበረክተው ጠቃሚነት መጠን መሆን አለበት ። በኢትዮ ጵያ ፥ ንጉሠ ነገሥቱ ፥ ከንግሥት ሳባና ከንጉሥ ሰሎሞን ከተወለደው ከቀዳማዊ ምኒልክ ነገድ ሳይቋረጥ ተያይዞ ከ መጣው ከንጉሥ ዛህለ ሥላሴ ዘር ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ትውልድ ሳይወጣ እንዲኖር በሕገ መንግሥቱ የተወሰነ ነው ። በተረፈ ግን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ፥ የተጠቃሚ ዎቹ ምኞት ወይም በትውልድ የተላለፈለት ልዩ መብት ሳይታይ ፥ ለመንግሥቱ አገልጋይና ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ፥ በማንኛቸውም ሥልጣን ላይ ለመቀመጥ መብት አለው ። ስለዚህ ዛሬ አገረሰቦች ፥ ማዕረግ ፥ ሹመት ፥ ደሞዝ ፥ የክብር ሽልማት ፥ የሚያገኙት ፥ ለጋራ ጥቅምና ላገሪቱ ባበረከቱት አገልግሎት መጠን ብቻ ነው ።

ከትልቅ ወይም ከትንሽ መወለድ ሞያ አይደለም ራስን በታላቅ ታሪክ መውለድ ግን ሞያ ነው ። ሲሉ ግ ፥ ቀ ፥ ኃ ፥

ሥ ፣ በአዲሱ ዘመን መጀመሪያ ላይ የተናገሩትን እናስታውስ ፤

በሰው መብት አንቀጾች ፍች ፣ አገረሰቦች በሙሉ በሕግ ፊት እኩል ስለሆኑ ፣ አኩሪ ባሕሪያቸውና ሞያቸው ብቻ እየተመዛዘነ ፣ እንደየችሎታቸው ሕዝባዊ ማዕረግ ፣ ሹመትና ሥራ ሊሳተፉ ይችላሉ ማለት ነው ።

የዴሞክራሲ እውነተኛ አስተዳደር ይህ ነው ፤ በዚህ አኳኋን ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ፣ ሞራላዊ ባሕርዩና ፣ የዕውቀት ደረጃው ከፈቀደለት ከፍ ያለ ማዕረግና ሥራ ለማግኘት ሊሞክርና ሊያገኝም ይችላል ማለት ነው ። ነገር ግን ከሌሎቹ ፣ በችሎታው በልጦ መገኘት አለበት ። ለዚህም የመወዳደር እድል ይሰጠዋል ።

ለዚህ ምሳሌ አንድ የሩጫ ውድድር እንመልከት ተሽቀዳዳሚዎቹ የአስነሺውን ምልክት በመጠባበቅ እመነሻው መስመር ላይ ሲሰለፉ ኃይላቸው እኩል አይደለም በማለት የውድድሩን ትክክለኛነት ለመንቀፍ ፣ የሚችል የለም ። ኃይላቸው የተመጣጠነና እኩል ቢሆኑ ኖሮ በውድድሩ ስፍራ መሰለፍ ባልነበረባቸው ነበረ ፣ ነገር ግን ለሁሉም ተሽቀዳዳሚዎች ፣ የመንገዱ ርዝመት ፣ የውድድሩ ሕግ ፣ ሰዓት አቆጣጠሩ እኩል ነው ። የቀደመውም ሰው ከተመልካቹ ሕዝብ አድናቆትን ጭብጨባን ያተርፋል ፣ እዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባ ፣ ሁሉም ተሽቀዳዳሚዎች ፣ ለሁሉም እኩል ሆኖ በተዘጋጀ ውድድር ተካፋይ ሆነው እኩል ፣ እድላቸውን መሞከራቸውን ነው ።

በሕብረሰብ ኑሮም አገረ ሰቡ በሙሉ ሚኒስትር ወይም የፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ያንድ አቁዋም ዲሬክተር ለመሆን በቀጥታ መብት አለው ማለት ታላቅ ስሕተት ነው ።

ማለት የሚገባው ፈቃዳቸው ከሆነ አገረሰቦች በሙሉ ከፍ ያለ ባለሥልጣን ለመሆን የመወዳደር መብት ዘወትር አላቸው ነው ። ከውድድሩ በኋላ ግን ከመካከላቸው ፣ በእውቀቱ በችሎታው የበለጠውና ተገቢ ሆኖ የተገኘው የተባለውን ሥልጣን እንዲይዝ ትክክለኛ ውሳኔ ነው ።

—

ዋናው ጉዳይ የመወዳደሩ እድል እኩል ለሁሉም መሰጠቱ ነው ።

በትምሕርትም ጊዜ እንደዚሁ ነው ፤ ዝቅተኛ ደረጃ ትምሕርት ጨርሰው ብዙዎቹ ተማሪዎች ወደከፍተኛ ደረጃ ለመቀጠል ፣ ቤተሰቦቻቸው አቅም ያጡ እንደሆነ ፣ ከመካከላቸው ፣ በችሎታቸው ፣ በጠባያቸው በእውቀታቸውና በሞያቸው ብልጫ ላሳዩትና ወደፊትም ለሕዝብ ይጠቅማሉ ለተባሉት ፣ አገሪቱ ለትምሕርታቸው መጨረሻ ገንዘብ ታበድራቸዋለች ፤ በዚህ አኳኋን ተምሮ በሕይወቱ ዘመን አገሪቱ ከሱ ትጠብቅ የነበረውን ግልጋሎት ያበረከተላት ሰው ፣ ያበደረችውን ገንዘብ እንደከፈላት ፣ ይቆጠራልና ገንዘቡን ቁም ነገር ላይ አዋላቸው ማለት ነው ። መንግሥት ፣ ተሥፋ ፣ ያላቸው ወጣት አገረሰቦች ፣ ሃብታቸውንና ትውልዳቸውን ሳይመለከት ፣ በሰላማዊ ፈተና ላገራቸው ሊሠሩ የሚችሉትን ሁሉም የሚያሳዩበት እድል ሲሰጣ

ቸው ፥ በሕዝባዊ እኩልነት ረገድም መብታቸው ፥ ተጠበቀ ማለት ነው ።

ቀ) ፖለቲካዊ እኩልነት ፤ እሰካሁን የዘረዘርናቸው የእ ኩልነትን ዓይነቶች ፥ ሕዝባዊ እኩልነት በተባለው ፥ ለአገረ ሰቦች በሙሉ ፥ በሕዝባዊ መብት እኩልነት በሚሰጣቸው ደንብ ውስጥ የሚቆጠሩ ናቸው ፤ ነገር ግን በአገሪቱ ያስተ ዳደር ሥራ ውስጥ ሕዝቡ ባይገባበት ኖሮ ይህ እኩልነት ፍ ጹም ሊሆን ባልቻለ ነበረና ፥ ሕገ መንግሥቱ ለምክር ቤቱ ማለትም ለሕግ አውጭው ሥልጣን ፥ የሕዝብ እንደራሴ ዎች የመምረጥ መብት ፥ ከ21 ዓመት በላይ ላላቸው ሴትና ወንድ ኢትዮጵያን ፥ በመስጠቱ ፖለቲካዊ እኩልነትም ተጠበቀ ማለት ነው ።

ተባባሪነት

ተባባሪነት ፥ ሞራላዊ ስሜት ብቻ አይደለም ፥ ነገር ግን ሰዎች በአገርም ውስጥ ሆነ በጠቅላላው በሰው ዘር መካ ከል በሚደርሰው ጥቅምም ሆነ ጉዳት ተባባሪ ስለሆኑ ፥ አካላዊ ስሜት ነው ።

ተባባሪነትን በአካላዊ መንገድ በመውሰድ ዘርዝረን በማጥናት ለመረዳት እንሞክር ፤ ለምሳሌ ፥ የኢትዮጵያ ሕ ዝብ በሁለት ቤተሰብ እንወስነው ፤ የበቀለ ቤተሰብ ፥ በሐ ረር ፥ የእሸቱ ቤተሰብ በድሬዳዋ ይኖራሉ ፤ ሁለቱም ቤት

ሰቦች አንድ ዓይነት የሆኑ ሁለት ቤቶች አሏቸው ። በቀ ለ ለእሸቴ ፥ ከሰል ፥ ኤሌትሪክ ፥ ጨርቅ ያቀርብለታል ። እ ሸቴ ደግሞ በበኩሉ ፥ ለበቀለ ፥ እህልና አትክልት ያቀርብ ለታል ።

በቀለም እሸቴም በቅርብ ጊዜ የተዳሩ ሁለት ወንድ ልጆች አሏቸው ። ሁለቱም ለሙሽሮቹ ልጆቻቸው በየራሳ ቸው መሬት ላይ የየራሳቸውን ቤት ግማሽ የሚያህል ቤት ሊሠሩላቸው ይዘጋጃሉ ።

ለዚህም ሥራ ቆጥበው ያኖሩት በቂ ገንዘብ አላቸው ። በመካከሉ ጦርነት ተነስቶ ሐረር ላይ ቦምብ ወደቀና የበቀ ለን ቤት አፈረሰበት ፤ ድሬዳዋ ያለው የእሸቴ ቤት ግን ም ንም ሳይሆን ተረፈ ።

ማንኛውም ሰው በነገሩ ሲያስብ ፥ አዬ ጉድ በቀለ ቤቱ ፈረሰበት እድል የለውም ፥ እሸቴ ግን ንብረቱ ዳነለት ዕድለ ኛ ነው ይላል ፤

ይህ ግምት የተሳሳተ ነው ። እጥልቀው ቢመለከቱት ፤ ቦምቡ የበቀለን ቤት ግማሽ ፥ የእሸቴን ቤት ግማሽ ነው ያፈ ረሰው ።

ማስረጃ ፤ ጦርነቱ ሲፈጸም ፥ የበቀለ ዋናው አሳብ የፈ ረሰውን ቤቱን እንደገና ፥ ለመሥራት ነው ። እሸቴም በቀ ለን እዳህን እንዳሻህ ተወጣው ብሎ ሊተወው ነው ። በዚህ ጊዜ ምን ይፈጠራል ? በቀለ ለልጁ አስቦት የነበረውን አነ ስተኛ ቤት መሥራቱን ይተዋል ። በዚህ ገንዘብ የፈረሰውን

ቤቱን ማማሸ መልሶ ሊሠራበት ይችላል ። ለማሸ ግን ከ ሚያገኘው ገንዘብ ፣ ማለትም ከሥራው ገቢ ላይ ማንሳት ይኖርበታል ። ከጦርነቱ በፊት ፣ የሥራው ፍሬ የሚውለው ለራሱና ለእሸቱ የኢንዱስትሪ ዕቃ ለማቅረብ ነበረ ፤ አሁን ግን ለቤቱ መሥሪያም ማግኘት ስላለበት የሥራው ፍሬ ለ ሱና ለእሸቱ ፣ ማለትም ለሁለቱ ብቻ ሳይሆን እሶስት ላይ ሊከፈል ነው ።

ስለዚህ ለራሱና ለእሸቱ ያፈራው ከነበረው ዕቃ ላይ በግዴታ መቀነስ ሊኖርበት ነው ።

እሸቱም ፣ በስስታምነት መንፈሱ እየተመራ ፣ በቀለ በቀነሰው ዕቃ መጠን ፣ እሱም ከሚያቀርብለት እህል ላይ ይቀንሰበታል ። በዚህ ሁኔታ እሸቱ ምንም ዓይነት ጥቅም ፤ አያገኝም ምክንያቱም ፤ ከበቀለ ላይ ያስቀረውን ትርፍ እ ህል ከጥጋብ በላይ እራሱ መብላት ፣ ወይም የእርሻ ሥራ ውን መቀነስ ስለሚኖርበት ነው ። ይህ የአሠራር ዘዴ ሂ ሳብ ሲያስተውሉት እያደር የባሰ ችግር የሚያመጣ ነው ።

በቀለ በቂ እህል ባለማግኘቱ ምክንያት ይራብና የሥራ አቅሙ ይቀነሳል ፤ በዚህም የተነሣ ለእሸቱ የሚያቀርበው ዕቃ እያደር እያነሰ ስለሚሄድ ፣ እሸቱም ሊቸገር ነው ።

ለዚህ ችግር ምን ዓይነት መውጫ ይገኝለታል ?

እሸቱ በኤኮኖሚ ረገድ እንድ መውጫ መንገድ ሊያገ ኝለት ፣ ይችላል ፤ ከበቀለ ከጦርነቱ በፊት ይቀበለው የነበረ ውን የዕቃ መጠን እንደገና ለማግኘት የሚችለው ፤ በቀለ እንደወትሮው ለራሱና ለእሸቱ ብቻ የሠራ እንደሆነ ነውና

የሥራው ፍሬ እሶስት ላይ እንዲከፈል ያደረገውን ፣ ማለ ትም የቤት መሥራቱን ሸክም እንዲያቃልለት ያስፈልጋል። ስለዚህ እሸቱ ለልጁ ቤት ፣ መሥሪያ አስቀምጦ የነበረውን ገንዘብ ለበቀለ ለውጥ ሳይጠይቅ ቢሰጠው ፣ መጠኑ የቤቱን ማማሸ ለመጨረስ በቀለ ከጐደለው መጠን ጋራ እኩል ስለ ሆነ ፣ በቀለ የፈረሰውን ቤቱን ለመሥራት ቻለ ማለት ነው ። በገንዘብና በሞራል ረገድ ችግሩ የተቃለለለት በቀለ የሥራ ውን ፍሬ እንደወትሮው እሁለት ላይ ብቻ ስለሚከፍለው ለእሸቱ ፣ የሚያስፈልገውን ዕቃ በቀድሞው መጠን ሊያቀ ርብለትና እሱም ለውጡን እህል በመጠኑ ሊቀበል ነው ።

ሁለቱም ከቀድሞው ያላነሰ ወይም ያልበዛ ፣ እንድ እንድ ቤት ይኖራቸዋል ፤ ግን ሁለቱም ለልጆቻቸው ሊሠሩ እሰበዋቸው የነበሩት ቤቶች ሳይሠሩ ቀሩ ፤

በዚህ ሁኔታ ፣ በኢትዮጵያ ሕዝብ የመሰልናቸው እነ ዚህ ሁለቱ ቤተ ሰቦች ሁለት ግማሽ ቤቶች ማለትም እንድ ቤት ስለከሠሩ ያች ሐረር ላይ የበቀለን ቤት ያፈረሰችቦ ምብ እሸቴንም ልክ እንደ በቀለ እክስራዋለች ማለት ነው ።

ማጠቃለያ ፤ ያንድ አገር ሰዎች ጥቅም የተያያዘ ለመ ሆኑ ይህ ማስረጃ በቂ ነው ፣ ግን ይህ የጥቅም ተባባሪነት በጠቅላላው ነው እንጂ ባንዳንድ ሰዎች ብቻ አይደለም ። የኢትዮጵያ አገረሰቦች ሁሉ ተባባሪና የማይነጣጠሉ ፣ ጥቅ ምና ጉዳታቸውም የማይነጣጠል ነው ። የጂማ ቡና ነጋዴ ኪሣራ ቢደርስበት ፣ በዚሁ የተነሳ አንዳንድ ጊዜ ወዲያ ውኑ አንዳንድም ጊዜ በዝግታና ሳይታወቅ የአዲስ አበባ

ውን ጸሐፊ ወይም የጐጃሙን ማር ነጋዴ ሳይጐዳው አይቀርም ።

*

የጅማው ቡና ነጋዴ መክሰር ፣ የአዲሱ አበባው ላኪና አሰመጭ ሠራተኛ እንዲቀንስ ያስገድደዋል ፤ ሥራ የፈታው ሠራተኛ እንደወትሮ ጠጅ ለመጠጣት አይችልምና መሸታ ሻጭም ፣ የሚገዛውን ማር መጠን ስለሚቀንስ የጐጃም ማር ነጋዴ ሊጐዳ ነው ።

እነዚህ ሁኔታዎች አብዛኛውን ጊዜ ወዲያውኑ አይሰሙምና ፣ አንድ አንድ ስስታሞችና አርቀው ለማየት የማይችሉ ሰዎች ፣ የወደፊቱን እግዚአብሔር ያውቃል እያሉ ተባባሪነትን ይዘነጋሉ ። ያገር ፍቅር ፍች ጐድሏቸው ፣ በሕዝብ ላይ በደረሰ ችግር ሳቢያ አትራፊዎች የሆኑ ሁሉ ፣ ዛሬም ሆነ ቆይቶ ፣ ስስታቸው ይጥላቸዋል ። ለምሳሌ ለጊዜው በማይገኝ ሸቀጥ ገንዘብ የሚሰበሰብ ፣ ሰው ሁሉ አደሮ በዚያ በሰበሰበው ገንዘብ የሚገዛው ነገር ሲያጣ ገንዘቡ ራሱ ዋጋ ስለሚያጣ ያገርንም ገንዘብ የምንዛሪ አቅም እሰከ ማዋረድ ይደርሳል ።

ለጊዜው ለሰው ዓይን ይመስላል እንጂ ፣ የኤኮኖሚ አዋቂዎች እንዳጠኑት ሁሉ ፤ ባንድ አገረሰብ ወይም በሕዝቡ አንድ ክፍል ላይ የሚደርስ ኪሣራ የጠቅላላውን ሕዝብ ኤኮኖሚ የሚያናጋ መሆኑ ተረጋግጧል ።

ይህ የተባባሪነት ሁኔታ በአንድ አገር ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ፣ በልዩ ልዩ አገሮችም መካከል ያለ ነው ።

ለምሳሌ እኔ በኢትዮጵያ አንድ መሐንዲስ ነኝ ፣ አንድ ትልቅ ቡና ነጋዴ ቤት እንድሠራለት አዞኝ ፕላን በማዘጋጀት ላይ ሳለሁ ፣ ነጋዴው ቡናውን ይልክበት በነበረው አንድ የኤውሮፓ አገር ችጋር ገባና ፣ ቡናውን የሚወስድለት አጣ ፣ በዚህም የተነሣ ጉዳት ስለደረሰበት የታቀደውን ቤት ማሠራቱን ስለተወው ፣ ጉዳቱ ቤቱን በመሥራት ፣ እንጠቀም በነበርነው ፣ በኔ በመሐንዲሱ ፣ በኩሊዎቹ ፣ በድንጋይ አቅራቢው ላይ ፣ በቆርቆሮው ነጋዴ ላይ ሁሉ አሰተጋባ ማለት ነው ። በኢትዮጵያ አንድ ሰው የሃብቱን መደርጀት ሲያወራ ዘወትር የምንሰማው እህል አልሸምትም ከር ስቴ ይመጣልኛል ፤ ቤት ኪራይ አልከፍል ፣ ጐጆዬን ቀልሻለሁ ፣ መኪና ሰፌ አያሳስበኝ ሚስቴ ለራሷና ለልጆቿ በደንብ ትሰፋለች ፤ ስለዚህ ወጭዬ በጣም ተቀንሶልኝ ብዙ ገንዘብ ለመቆጠብ ችያለሁ ሲል ነው ፤ በእርግጥም ያገራችን ሰው ጥረት እዚህ ላይ ለመድረስ ነው ፣ በብዙዎቹም እስተያየት ይህ ሰው ፍጹም የኑሮን ዓይነት የተቀዳጀ ይመስላቸዋል ፤ ለምሳሌ የዚህ ሰው ግብርና ጫማ ሰፊነት ቢሆን ፣ ጫማውን ለማን ሊሸጠው ነው ? እህል በመሸመት ፣ ቤት በማከራየት ፣ ልብስ በማሰፋት ፣ እሱ ከሚያገኘው ገንዘብ ላይ ለገበሬው ፣ ለቤት ኪራይ ፣ ለልብስ ሰፊው ካላደረሳቸው ጫማውን በምናቸው ሊገዙት ነው ? ስለዚህ የዓለም ሕዝቦች ኤኮኖሚካዊ ተባባሪነት ፣ የማይዘነጋና የማይምር ፣ ሁኔታ መሆኑን ማስታወስ ያሻል ።

የተባባሪነት እውነተኛው መልክ ይህ ነው ፤ እሱንም ማክበር ከአእምሮ የሚፈልቅ ጸጋ ነው ። በተለይ ያገሬ

ሰው ፥ በጠቅላላም የሰው ዘር ሁሉ ተባባሪዬ (ወንድሜ) ነው ማለት ያስፈልጋል ፤

ባንድ ቤተ ሰብ ውስጥ ወንድማማቾች የማይስማሙበት ጊዜ አለ ፥ ግን ፥ የጋራ ጥቅማቸውና ተባባሪነታቸው አንድ ጊዜም ሊነጣጠል የማይችል ነው ።

እንዲሁም የሰው ዘር ጥቅም ፤
ስለዚህ በአገረሰቦቻችንና በሰዎች ላይ ጉዳት በደረሰ ጊዜ ፥ ተባባሪነታችንን መግለጽ ፥ የዓለምን ኤኮኖሚካዊ ድልድል ፥ እንደመገንዘብ የሚቆጠር ሰብዓዊ ጸጋ ነው ።

መ ጀ መ ሪ ያ ክ ፍ ል ተ ፈ ጸ መ

2 ኛ ክ ፍ ል

ጥቂት የሞራል ገጾች ፤

በመጽሐፉ በአንደኛው ክፍል በጠቅላላው ስለሕዝብና ስለአስተዳደር ጉዳይ ጽፌያለሁ ፤ ነገር ግን ሰው እናኗኗሩንና አስተዳደሩን ተንትኖ ቢያውቅና ቢረዳም የሕይወቱ መስመር በሞራላዊ ግዳጆች ካልተመራ ፍጹምነትን ሊያገኝ አይችልም ።

ሞራል ማለት ባጭሩ ፦—
«በጐ ሥራ ለመሥራትና ከክፉ ሥራ ለመራቅ እንድንችል ልንከተለው የሚገባንን ሥርዓት የሚያስተምረን ጥበብ ነው ።»

የሞራል ትምህርት ልዩ ልዩ ቅርንጫፎች አሉት ፤ ከነዚህ መካከል ፥ ለአንባቢውና ሊደረስ ለተፈለገበት ግብ ጠቃሚ መስለው የታዩኝን ክፍሎች ብቻ እውጥቼ በሚከተሉት መስመሮች አስፍሬያቸዋለሁና የታሰበውን ፍሬ በተቻለ መጠን እንዲሰጡ እመኛለሁ ።

ጽሑፉ ቀጥሎ በተመለከቱት ዘጠኝ ምዕራፎች ተከፍሏል ፦—

1. አላፊነት (ተጠያቂነት) — 2. ቅጣት — 3. ተባባሪነት — 4. ግላዊ ኑሮ — 5. ቤተሰብ — 6. ሕዝብ — 7. አገር — 8. መንግሥት (ወይም አስተዳደር) — 9. ኤኮ

ኖሚካዊ ኑሮ ። በውስጡ አንዳንድ አዳዲስ ቃላት ቢያጋ ጥማችሁ ፥ የቃሎች ፍች በሚለው ገጽ ላይ ትርጉሙን ለ ማግኘት ሞክሩ ።

ም ዕ ራ ፍ 1 ፤

አላፊነት (ተጠያቂነት) ፡—

አላፊነት የተባለው ፥ እያንዳንዱ ሰው በሠራው ሥራ ተጠያቂ መሆኑን የሚያስማው ቃል ነው ። አላፊነት በሶስት ረድፍ ይከፈላል ፤ ብሔራዊ አላፊነት ፥ ወንጀላዊ አላፊነት፥ ሞራላዊ አላፊነት ፤

ከሁሉም ሞራላዊ አላፊነት ይበልጥ ከባድ ነው ። የአ ላፊነትም ስሜት ከፍ ያለ ሕብረሰባዊና ሞራላዊ ዋጋ ሰላ ለው ፥ በሙሉ በሰዎች ዘንድ በተለይም በሕጻናት መንፈስ እንዲደረጅ ማድረግ ያስፈልጋል ።

አንድ ሰው አላፊነት ሲሰማው በመንፈሱ ውስጥ ሁ ለት ሁኔታዎች ይፈጠራሉ ።

ሕብረሰባዊ ሁኔታ ፡—

ሰው አላፊነት በተሰማው ጊዜ ያጠፋውን እንዲክስ ወይም ቅጣት እንዲወሰንበት የሚጠየቅ መሆኑ ይሰማዋል ። ለምሳሌ ፥ የሌላ ንብረት ቢያጠፋ ወይም ግብር ሳይከፍል ቢ ቀር ፥ የሚከሰስ ወይም የሚቀጣ መሆኑ ይሰማዋል ።

በዚህ ሁኔታ ቢያጐድልና ቢያጠፋ ለሚያስከትለው ካሣና ቅጣት መንፈሱን አዘጋጅቶ ይገኛል ።

ሞራላዊ ሁኔታ ፡—

ባንድ በኩል ደግሞ አድራጊው እሱ መሆኑ ፥ በጣም ጠልቆ ይሰማዋል ፤ በዚህም ስሜት የተነሣ ድርጊቱን የፈጸ መበትን እንዲገልጽ እንደምክንያቶቹም ሚዛን ፥ ወቀሳን ወይም ምስጋናን ለመቀበል ፥ አእምሮ ያለውን ፍጡር ሁሉ አላፊነት ያስገድደዋል ።

አላፊነትና ተባባሪነት ፡—

በዘመናዊ ሕብረ ሰቦች ውስጥ ያለው ተባባሪነት ፥ የ ዚህ ዓይነቱን አላፊነት አስፋፍቶታል ። ያንድ ሕብረ ሰብ አባሎች ሁሉ (መንግሥታቸው) አስተዳዳሪዎቻቸው በገቡ በት ውል ተጠያቂ መሆናቸውን ፈቅደው እንዲቀበሉ ያስፈ ልጋል ። የሕብረ ሰብ ውል መሠረት ይህ ነው ። እንዲሁም ጊዜና ስፍራ ሳይወስናቸው በሕብረት አላፊነትን በመቀ በል ቀደምቶቻቸው (አባቶቻቸው) የገቡትን ዕዳ ለመክፈል ፈቃደኛ ሆነው እንዲገኙ ያስፈልጋል ።

ስለዚህ አላፊነት ከተባባሪነት ሊነጠል አይችልም ።

የአላፊነት ዓይነቶች ፡—

ብሔራዊ አላፊነት ፡—

ብሔራዊ አላፊነት ማለት ፥ በቀጥታም ሆነ በሌላ በ ኩል የተፈጸመ ጉዳት እንዲካስና እንዲበጅ ሕግ የመሠረ

ተው ግዴታ ነው ። በሕጉ እንደተመለከተው የተፈጸመው ጉዳት እንዲካስ አስፈላጊ ነው ። ይህ ከሁሉ ይቀድማል ። ስለዚህ በቀጥታ አድራጊውን በመፈለግ ፈንታ፥ በአላፊነቱ ተጠቃሚው ካሣውን እንዲከፍል ይደረጋል ፤ ለምሳሌ ፥ የም ድር ባቡር አደጋ ሲደርስ ኩባንያው አላፊ ነው ። የአቶሞ ቢል አደጋ ሲደርስ የሚነዳው ሳይሆን አላፊው የአቶሞቢ ሉ ባለቤት ነው ። አብዛኛውን ጊዜ በተፈጸመው ጉዳትና አ ላፊ እንዲሆን በተወሰነው ሰው መካከል ብዙ ርቀት አለ ፤ ለምሳሌ ፥ ያንድ ቤተሰብ አለቃ ፥ ለአቅመ አዳም ባልደረሱ ልጆቹ ፤ በሠራተኞቹ ፥ በእንስሶቹ ንብረቱ በሆኑት ነገሮች አላፊ ነው ። በሕጉም ውስጥ ያሉ አንዳንድ እንቀጾች እን ዲህ ይላሉ ፡—

— ማንኛውም የሰው አድራጐት በሌሎቹ ላይ ጉዳት ሲያደርስ ፥ ጥፋተኛ የሆነው ጉዳቱን እንዲያበጅ ፥ እንዲክስ ግዴታው ነው ።

— እያንዳንዱ ሰው በአድራጐቱ ብቻ ሳይሆን በቸል ተኛነቱ ወይም ባለመጠንቀቁ ምክንያት በደረሰ ጉዳት አላፊ ነው ።—

— በራሰ እድራጐት ብቻ ሳይሆን በአላፊነቱ ስር የሚ ኖሩ ሰዎች ፤ በጠባቂነቱ ስር በሚኖሩ ነገሮች ምክ ንያት በሚደርሱ ጉዳቶችም አላፊነት አለ ።—

አእምሮው ትክክል ያልሆነ ሰው ፥ በብሔራዊም ሕግ በኩል ፥ ባድራጐቱ በሌሎቹ ላይ ጉዳት ቢያመጣም ተጠ ያቂ አይደለም ፡— ይኸውም አላፊ ለመሆን ጥፋት እንዲ

ገኘበት ሰለሚያስፈልግና ፈቃደኛነት (የአእምሮ ትክክለኛ ነት) ከሌለ ደግሞ ጥፋት ሊኖር ስለማይችል ነው ።

እላይ በጠቀስነው የምድር ባቡር ነጂ ጥፋት ጊዜ አላ ፊነቱ እሁለት ላይ ይከፈላል ፤ ብሔራዊ አላፊነት ፥ ማለ ትም የማብጀቱና የመካሱ አላፊነት ለኩባንያው ሲሰጥ የመ ንጂሉ አላፊነት ደግሞ በነጂው ላይ ያርፋል ።

የወንጀል አላፊነት ፡—

የወንጀል አላፊነት ፥ በሕግ የተወሰነውንና ለማሕበራ ዊ ኑሮ አስፈላጊ የሆነውን ሥርዓት በመጣሱ ቅጣት ሊወሰ ንበት የሚችለውን ሰው አላፊነት የሚያስረዳ ነው ። የወን ጀል አላፊነት ፥ ለኑሮው መጠበቂያ አስፈላጊ የሆነው ሥር ዓት እንዳይጣስ በተለይም ተደግሞ እንዳይደፈር ሕብረ ሰብ የሚመክትበት ሁኔታ ነው ።

የወንጀል አላፊነት ወደ ሞራላዊ አላፊነት ይመራል ፡—

ሕብረ ሰብን ከፍ ያለ ጉዳት ላይ ለመጣል የሚችል የጥ ፋቶች ዓይነት ነው ፤ በደካማነት ከተደረገ ይልቅ በተንኰል የተደረገ ጥፋት እደገኛ ነው ። ታስቦ የተሠራ አመጽ ባለመ ጠንቀቅ ከተሠራ አመጽ የከበደ ነው ። ስለዚህ ዳኛ ጥፋትን ዘርዝሮ መመርመርና የተከሳሹን ሕሊና አጥልቆ ማጥናት ይኖርበታል ። በዚህ አኳኋን የወንጀል አላፊነት ወደ ሞራ ላዊ አላፊነት ይመራናል ።

ሞራላዊ አላፊነት ፡—

ከዘረዘርናቸው የአላፊነት ዓይነቶች ሁሉ ፥ የሞራል አላፊነት ፥ እውነተኛው የአላፊነት መልክ ሆኖ ይገኛል ።

አድራጊው ከአድራጐቱ ጋር ተባባሪነቱን በሙሉ የሚ
ረዳው በሞራላዊ አላፊነት ነው ።

ደግሞም የሚቀርበው አድራጐቱን ብቻ በሚለየው
በውጭ ዳኛ ፊት ሳይሆን ፥ የልቡን አሳብም ጭምር ተንትኖ
በመረዳት ይበልጥ አሰተዋይና ጨካኝ በሆነ ውስጣዊ ዳኛ
ማለትም በራሱ ሕሊና ፊት ነው ።

ከውጭ ዳኛ በመማትም በምስክርም ብርታት ለማም
ለጥ ይችላል ፤ ከሕሊና ዳኝነት ግን ለማምለጥ ከቶ የማይሞ
ክር ነገር ነው ። ዘወትር ሥራችንን ሕሊናችን ፊት አቅር
በን ምስጋናውን ወይም ወቀሳውን ለመቀበል እንገደዳለን ።

ሞራላዊ አላፊነት ሙሉ ሆኖ የሚገኘው አድራጊው
የማወቅ ችሎታ ሲኖረው ነው ፤ አድራጊው ሞራላዊ ደንበ
ችንና ሥራውን የሚመሩትን ሕጐች ጠንቅቆ ሲያውቅና
ሙሉ ነጻነት ያለው ሲሆን ፥ ማለትም በፈቃዱብቻሲመራ፤
ያጠፋ እንደሆነ ያዋቂ አጥፊ ነውና ጥፋቱ የከበደ ነው ።

በሞራላዊ አላፊነት አድራጊው ማወቅ አለማወቁ እን
ዲጣራ ያስፈልጋል ። በሕብረ ሰባዊ አላፊነት ግን ማንም
ሰው ሕግን አላውቅም ነበር ብሎ ጥፋቱ ከሚያስከትለው ቅ
ጣት ሊመዳን ስለማይችል ሕጉን ያውቅ ነበር ወይም አያ
ውቅም ነበር የሚል ነገር አይገባበትም ።

የጥፋት ነዋሪነት ፡—

ሞራላዊ አላፊነት አሁን ለምናደርገው ብቻ ሳይሆን
ቀድሞም ላደረግነው ነገር ሁሉ የሚጸና ነው ፤ የቀድሞ ጥፋ

ታችን እይሠረዝም ፥ ጊዜም እንዴ ካለፈ ሊጠፋና ሊሻር
ስለማይችል የአድራጐታችን ምስል ዘወትር ይከታተለናል።
መጸጸት ስሕተታችንን አያስረሳንም ፥ ቢበዛ ጽሑፍ የመደ
ለዝ ያህል ይጋርድልን ይሆናል ።

ሰው ሁለ ሕግን በሥርዓት ያውቃል ፥ ወይም በሙሉ
በራሱ የሚመራ ነው ለማለት አስቸጋሪ ነው ። ስለዚህ
አላፊነት ልዩ ልዩ ደረጃዎች ሊሰጡት ይገባልና ባንድ ሰው
ጥፋት ፥ ዳኞች ፍርድ ከመስጠታቸው በፊት አላፊነቱን የ
ሚያቃልሉለት ሁኔታዎች እንዳሉ ይመረምራሉ ። አቃላይ
ሁኔታዎች ቢኖሩም ጠቃሚነታቸው ዳኛው በቂ አድርጐ
ሲቀበላቸው ብቻ ነው ።

የነጻነት መወሰን ፡—

የአድራጐት ነጻነት ልዩ ልዩ እንቅፋት ባጋጠመው
ጊዜ አላፊነትም በዚሁ መጠን ይቃለላል ። አንዳንድ ጊዜም
የበለጠ ኃይል ሲያጋጥም ሰው በአድራጐቱ በፍጹም አላፊ
መሆኑ ይቀርለታል ። ለምሳሌ ፥ የመጀመሪያዎቹ የክርስትና
ስማዕታቶች ከሥቃይ የተነሣ ወደመካድና ወደመጉደፍ ቢ
ደርሱ ሊያስጠይቃቸው የሚችል ሁኔታ አይደለም ። ቢሆ
ንም እዚህ ላይ የያንዳንዱን ሰው ጉዳይ በተለይ ማጥናት
እንጂ ለሁሉም የሚጸና ሕግ ለማድረግ አይቻልም ። እንዲ
ያውም የሞራላዊ አስተዳደግ ጥረት ፥ ሰው በመሰናክል ምክ
ንያት ከተግባሩ የማይሸሽበትን መንፈስ በሕሊናው ለማሳ
ደር ነው ። ለምሳሌ ፥ የንስሐን ሚስጢር የተቀበለ ቄስ ም
ንም ቢደረግ ሚስጢሩን ማውጣት የለበትም ። እንዲሁም

ባንድ ሰፍራ ላይ የተመደበ ወታደር የበለጠ ኃይል መጣ ብኝ ብሎ እንዲሄድ አይፈቀድለትም ።

ለይቶ የማወቅ ችሎታም ሊቀነስ ይችላል ፡—

ሊገነዘብ የማይችልንም ሰው ለምሳሌ ፣ አንድ ሕጻን ፣ እንቅልፍ የወሰደው ሰው ፣ አንድ ዕብድ ፣ አላፊ ለማድረግ በፍጹም የማይቻል ነገር ነው ። ሕግም አንድ ሰው ጥፋቱን በፈጸመበት ጊዜ፣አእምሮው ትክክል ካልነበረ አመጽ ወይም ወንጀል ተፈጸመ አያሰኝም ይላል ፤ ስለዚህ ዳኞች አጥፊው አብዛኛውን ጊዜ በሐኪሞች እንዲመረመር በማድረግ የሕሊና መሳቱን ደረጃ ለማወቅና አላፊነቱ የቱን ያህል እንደ ሆነ ለመገመት ይጥራሉ ።

ኃይለኛ ሰሚት ይቅርታ ሊሆን አይችልም ፡—

ባንዳንድ አገሮች በኃይለኛ ፍቅር የተነሣ ያመጹን ሰዎች ሰሚታቸው የበደላቸው ናቸው በማለት ይቅርታ ይደረግላቸው ነበረ ። ይህ አሰተያየት በፍጹም የተሳሳተ ነው ። ሰው አእምሮው ጤነኛ ከሆነ ሰሚቱን መግታት አለበት ። ደግሞም በሰካር መንፈስ ያጠፋ ከአእምሮ ውጭ ነበረና በ ማለት ይቅርታ የሚያደርጉለት አሉ ። እዚህ ላይ ማሰታወስ የሚገባ ሰካር ፣ አክባጅ ሁኔታ እንጂ አቃላይ ሁኔታ ለ መሆን አለመቻሉን ነው ። ማንኛውም ሰው በሚጠጣበት ጊዜ መጠጥ ሰካርን እንደሚያሰከትል ስካርም አእምሮ እን ደሚነሳ ማወቅ አለበትና ማጥፋት የጀመረው ይህን እያወቀ መጠጣት ገና ሲጀምር ነው ። ስለዚህ ጠጥቶ ጥፋት ያደረገ ፣ አስቀድሞ ወደክፉ መንገድ እንደሚመራው እያወቀ መጠ

ጣቱ አንድ ጥፋት ፣ ከሰከረ በኋላ ማመጹ ሁለት ጥፋት ሆኖ ጥፋቱ ይከብድበታል እንጂ ሊቃለልለት አይገባም ።

አላፊነት ለሞራል አስፈላጊ ቅመም ነው ፡—

ሰው ራሱንም ሆነ ሌሎችን በሚያሰተዳድርበት ጊዜ ፣ ሊደረግ የሚገባውን ነገር ተደራጊ ማድረጉ ያስችግረዋል ።

ሕዝብን በማስተማር በማሳደግ ጊዜ ፣ ሕግን ማክበር የተለመደ አመል እስኪሆንበት ድረስ መጫን ያስፈልጋል።

አላፊነቱ የሚሰማው ሰው በሚሠራው ሁሉ የሚጠየቅ ራሱ እንጂ ሌላ የሚያልፍለት እንደሌለ ይረዳል ፤ ይህን በማወቁም ሊፈጽመው የሚገባው ተግባር ፣ ጥፋቱ የሚያስከትለው ቅጣት ፣ ቢሳካለት የሚሰማው ደስታና ሲያቅተው የሚሰማው ሐፍረት በመንፈሱ ተዋሕደው ይገኛሉ ፤ በዚህ አኳኋን ተግባሩ ፣ ጥቅሙና ክብሩ ተባብረው ስለሚገኙ ሕብረ ሰብን የሚያድን ሁኔታ ይፈጠራል ።

አላፊነት አእምሮን ያፋፋል ፡—

ብዙዎቻችን እንደምናስታውሰው በትምህርት ቤት በነበርንበት ጊዜ ሰነፍ ይባሉ የነበሩ ተማሪዎች አድገው በአላፊነት ቦታ ላይ ሲቀመጡ እውቀታቸው እየተራቀቀና እየተስፋፋ መገኘቱን አይተናል ፤ ማንኛውም ሰው በሥራው ክልል ውስጥ ጥሩ ጥሩ አስተያየቶች ሊሰጥ ይችላል ። በተለይም እውቀት ከምንጩ ጀምሮ የሚንቀሳቀሰውና ፍሬ የሚሰጠው ችግር ሲገጥም ፣ መሰናክል ሲደቀንና መውጫ ሲጠብ ነው ። ስለዚህ አላፊነት መንፈስ ያብራራል ለማ ለት እንችላለን ።

አላፊነት ፈቃደኛነትን ያሳድጋል ፡—

አላፊነት በተሰማ ጊዜ ደካም ፥ ድካም እይመስልም ፤ ሰውም ተግባሩን ለመፈጸም አቅሙን ፥ ሃብቱን ሕይወቱን ሳይቆጥብ በሙሉ ይሰጣል ።

የማይሻሻሉ ዋዘኞች ፥ ይመስሉ የነበሩ ሰዎች የቤተ ሰብ አላፊነት ሲደርስባቸው ቁም ነገረኛና ጠንቃቃ ሆነው ይገኛሉ ። ወስላቶችና ግድየለሽ የነበሩ አንዳንድ ተራ ወታደሮች ማዕረግና አላፊነት ሲቀበሉ ፥ ጉበዝ እስተዳዳሪና መሪዎች እየሆኑ ተገኝተዋል ፤ አላፊነትን መግንዘብ ራሱ ሁኔታው ሥራን ሁሉ አቃሎ ያሳያል ፤ አይከብድም ።

አላፊነቱን በቁም ነገር የተቀበለ ሰው ከፍ ወዳለው የጸጋ ደረጃ ይደርሳል ። የሥራ ሕሊናውም እየመራው ተግባሩን በትክክል ስለሚፈጽም የሕብረ ሰብን መብት በሚገባ መጠበቁ ነው ።

አላፊነት መንፈስን ያረጋጋል ፡—

የአላፊነት ሰሜት መንፈስን ከፍ ስለሚያደርግ ወራዳ የሆነውን የምቀኝነትንና የጥላቻን ሰሜት ያጠፋዋል ።

ለዚህም ምሳሌ ፥ እንድ ታላቅ የመንግሥት ባለሥልጣን ያለውን መጥቀስ በቂ ነው ፡— የመሞቻው ጊዜ ሲቃረብ ፥ ሰዎች ጠላቶችህና ወዳጆችህ እነማን ነበሩ ብለው ጠየቁት ፥ እርሱም ፥ ያገሬ ጠላት ሁሉ የኔም ጠላት ነው ፥ ያገሬ ወዳጅ የሆነ የኔም ወዳጅ ነው ፥ ምንም እንኳን የኔ የግል ወዳጄ ቢሆን የአገሬ ጠላት ከሆነ ወዳጄ ሊሆን አይችልም ፡— ምንም እንኳን የግል ጠላቴ ቢሆን ያገሬ ወዳጅ

ከሆነ ጠላቴ ልለው አልችልም ፤ ሲል መለሰ ። በተለይም በመጨረሻው እነጋገሩ ይህ ሰው ከፍ ያለ መግለጫ ሰጥቶናል ። በመንግሥቱ ውስጥ ባለሥልጣን ሆኖ አላፊነት ስለነበረበት የግል ጠላቱን ለአገሩ ሲል ወደደው ፤ አላፊነት የግል የጥላቻ ስሜቱን እስተወው ፥ መንፈሱን ሰላማዊ አደረገለት ማለት ነው ።

አላፊነትና ሥልጣን ፡—

ማዘዝ ከምን የመጣ ነው ? ፥ በሥልጣንና በነጻነት መካከል ያለውስ ግንኙነት እንደምንድነው ? የአላፊነት ጉዳይ ሥልጣን ለምን እንደሚሠራበት ወሰኑስ እስከየት እንደ ሆነ ያስረዳናል ።

ማዘዝ በመሠረቱ የሌላውን ሰው ነጻነት መወሰን ነው ። ነገር ግን ይህ መብት በሕብረሰብ ግብርናንና ሃብትን ከሚከፋፍለው ሕግ የመነጨ ነው ። ሥልጣን ከጥቅምና ከመጨቆን መንፈስ የመነጨ ሲሆን የማይሆንና የማይታገሱት ነው ። አላፊነት ያስከተለው ሲሆን ግን ሕጋዊ ነው ። ቢሆንም ሥልጣን ከአላፊነት ጋር ተመዛዛኝ ማለትም ለሥራው በሚያስፈልገው መጠን መሆን አለበት ፥ ከዚህ ሲያልፍ ግን ግፍ ይሆናል ።

ለማዘዝ ፤ የበታች ባለሥልጣኖች ያስፈልጋሉ ። ነገር ግን አንዳንድ አዲስ ሹሞች በበታቾቸው ሥራ እንግባ ይሉና ችግር ያጋጥማቸዋል ፤ በገዛ እጃቸውም ጊዜያቸውንና ሥልጣናቸውን ያባክናሉ ። የበታቾችም እንደዚህ ያለ ሹም ሲያገኙ ሆን ብለው ያደነጋግሩትና የሥልጣን ኃይል ሲያጣ

ሊያዛቸውና ሊገስጻቸው በማይችልበት ሁኔታ ውስጥ ይጨምሩታል ።

አስተዋይ የሆኑ ሹማምንቶች የሥራውን ውጤት በጥብቅ ይቆጣጠራሉ እንጂ ባፈጻጸሙ ውስጥ አይቀለቀሉም ።

ሰው አላፊነት ሲሰጠው ከሥራው ጋር አንድ አካል ይሆናል ፤ ንቃት ያድርበታል አዳዲስ አሳቦች ከአእምሮው ይመነጫሉ ። ይህን ሁሉ ነገር በማስገደድ ለማግኘት አይቻልም ። በአላፊነት የመሩት ሥራ ፍሬ ሲሰጥ ማየትን የመሰለ ደስታ በሰው መንፈስ ሊያድር አስቸጋሪ ነው ።

<u>የአላፊነት ስሜት በሕጻናት ዘንድ ፦—</u>

ሕጻናት፤አዋቂዎች ችላ ሲሏቸው በመናቃቸው ምክን ያት የሚሰማቸው ሃዘን ብርቱ ነው ። ብዙዎቹ ይለምዱትና ልጆች ሆነው ይቀራሉ ። ሌሎቹ ደግሞ አቅማቸውን ለማሳ የት ሲሉ አመጽና ወንጀል እስከ መሥራት ይደርሳሉ ። ነ ገር ግን አላፊነት የተሰጣቸው እንደሆነና እምነት ሲጣልባ ቸው በጣም ይሻሻላሉ ። በቤተ ሰብ ምዕራፍ እንደርስበታ ለን ።

<u>በሕይወት ፊት አላፊነት ፦—</u>

በአላፊነት ስሜት ኃይል ላይ ሙሉ እምነት መጣል አለብን ። ይህን ስሜት ማጐልመስም ከሞራል ዋና እም ዶች አንደኛው ነው ። አብዛኛውንም ጊዜ ከሞራል እንዳን ሸሽ የሚያደርገን የአላፊነት ስሜት ነው ።

ይህች በእምነት የተሰጠችን ሕይወት ፥ በቶሎ የምታ ልፍና ዳግመኛም የማትገኝ ስለሆነች ፥ እስካለን ድረስ ላንድ

ቁም ነገር እንድናውላት ያስፈልጋል፤አለዚያ በከንቱ ቀረች ማለት ነው ።

በፍኖተ ሕይወታችን ላይ ያለንን ተጠያቂነት በጥልቅ ከተገነዘብነው ሕሊናችን ጥሩ መሪ ያገኛል ።

እያንዳንዱ ሰው ፥ እያንዳንዱ ሕጻን ፥ የሰው ዘር አባል ሁሉ ፥ ስንፈጠር ለያንዳችን አንዳንድ ጥቅል ድር እንደሚ ሰጠን ፥ እሱንም እንደየችሎታችን ማጠንጠን እንዳለብንና ስለኛ ሆኖ የሚያጠነጥንልን ማንም እንደሌለ መገንዘብ አለብን ።

እግዚአብሔር ንጹሕ መሆኑ በመጻሕፍቶች ተነግሮ ናል ፤ ስለዚህ ፍኖተ ሕይወቱን መምረጥና ፥ ስፍራ ማስያዝ ለያንዳንዱ ሰው የተሰጠ አላፊነት ነው ።

የሰው ዓይነተኛ ባሕርይ ይህን አላፊነት መገንዘብና ፥ በሰጠህ ሕይወት ምን እደረግህበት ብሎ በሚጠይቅ ዳኛ ፊት መቅረብ እንደማይቀር በማሰብ ኑሮውን መም ራት አለበት ።

ም ዕ ራ ፍ 2 ፤

ቅጣት

የአላፊነትን ጉዳይ ካጠናን በኋላ በቀጥታ ወደ ቅጣት ጉዳይ ማለፍ ደንበኛው መንገድ ነው ። በአላፊነት ገጽ እን

ደተመለከትነው ፤ አላፊነትን መገንዘብ የሚያስከትለውንም ቅጣት ለመቀበል ዝግጁ ሆኖ መገኘት ነው ። አድራጊው ለጥሩ ተግባሩ ሽልማት ለመቀበል ምኞት ካለው በጥፋቱ ጊዜ ደግሞ ካሣ መክፈል ፤ መቀጣት አለበት ። እዚህ ላይ ብዙ ከባድ የሆኑ አሳሳቢ ነገሮች ይፈጠራሉ ።

1. ድርጊቱና ቅጣቱ የሚገኙበት ሁኔታ ፤ 2. ቅጣቱን የሚወስነው ባለሥልጣን ባሕርይና ለመቅጣት ያለው መብት ፤ 3. የቅጣት ጠቃሚነትና በሞራላዊ ሕይወት ላይ ያለው አመዛኝነት ።

የኖረ የቅጣት ዘዴ ፦—

በጥንት ዘመናት ፥ በዳዩ በተበዳዩ ላይ በፈጸመው በደል ዓይነት ይቀጣ ነበረ ፤ ዓይን ያወጣ ዓይኑ ይወጣል ፥ ጥርስ የሰበረ ጥርሱ ይሰበራል ። ይህ አደራረግ ከፍርድ ይልቅ ወደሰባዊ የመበቀል ስሜት ይቃረባል ። ከዚህ ከጥሬ አሰተያየት አንዳንድ መሠረታዊ ነገሮች መውሰድ እንችላለን ።

1. ማንኛውም ክፉ ድርጊት ፥ ዕዳን እንደሚያስከት ልና መካስ እንዳለበት ያስረዳል ፤

2. በመሠረቱ ደግሞ ጥፋትና ቅጣት ፥ ኪሣራና ካሣ መመጣጠን እንዳለባቸው ያስተምረናል ።

ቢሆንም ይህ የኖረ ልምድ ፥ የሰውን እንሰሳዊና ተበቃይ ባሕርይ የሚያነቃቃ ፥ ሕብረ ሰባዊ ሥርዓትንም በማፍረስ ራሱ እንዲበቀል የሚገፋፋው ስለሆነ ፥ ልንደግፈው አንችልም ።

ለሕብረሰብ ጥበቃ ፦—

የሕብረሰብን ኑሮና ድርጅቱን የሚነካ ድርጊት ሲፈጸም ሕብረ ሰብ አጥፊውን በመቅጣት ይከላከላል ። ነፍሰ ያለው አካል ሁሉ ቅስቃሴውን የሚያሰናክል ባዕድ አካል ባገኘ ጊዜ እንደሚያስወጣው ወይም እንዳያውክ እንደሚያደርግ ሁሉ ፥ ሕብረ ሰብም ለኑሮው አሰጊ የሆነውን ወንጀለኛ በዚሁ መንገድ ይቃወመዋል ። ስለዚህ እንድ ሰው ሕግን በጣሰ ቁጥር ሕብረ ሰብ በመያዝ ፥ በማሰር ፥ በመደምሰስ ዳግመኛ እንዳያውክ ያደርገዋል ።

ቅጣት ማስፈራሪያም ነው ፦—

ቅጣት ሌላ መልክ አለው ። ሕብረ ሰብ ሲቀጣ ለዛሬም ለወደፊትም በመመልከት ነው ። ዛሬ ጥፋትን ለማቆም ሲሆን በተለይ ደግሞ እንዳይደገምና እንዳይወራረስ ለማድረግም ጭምር ነው ። ቅጣቱ ለሌሎቹ አርዓያ በመሆን እንዲያስፈራራቸውና እንዲገታቸው በማሰብ ነው ። በዚህ አኳኋን ቅጣት ማስፈራሪያና ዛቻ ይሆናል ፤ ለወንጀለኛ መቅጫ ሕጐች መኖራቸውንና እንደማያዋዙም ያስታውሳል ። ሕብረ ሰብም ቅጣት የሚወስነው እንደየጥፋቱ መጠን ተመሳሳዩ ቅጣት የተመለከተበት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በሚያዘው መሠረት ብቻ ነው ።

የቅጣት ግለሰብዓዊነት ፦—

ባለፈው ምዕራፍ እንደተመለከትነው ሕብረ ሰብ ወንጀሉን ብቻ ሳይሆን ወንጀለኛውንም መመልከት አለበት ፤ በመልክ ተመሳሳይ የሚመስሉ አመጸች ጐጂነታቸው የተ

ለያየ ሊሆን ይችላል ። ደንበኛ ወንጀለኛ ከልማደኛ ወንጀለኛ ይብስ ያስጋል ። ልማደኛ ወንጀለኛ ከዕለት ወንጀለኛ ይብሳል ። ስለዚህ ጥፋቱን ብቻ ሳይሆን ጥፋተኛውን አጥርቶ ማወቅ ያሻል ። ቅጣቱ ከተከሳሹ የአመጸኝነት ደረጃ ጋር ተመሳሳይ መሆንና የአጥፊውን የተፈጥሮና ሕብረ ሰባዊ ባሕርይ የተመለከተ መሆን አለበት ፤ ቅጣት ግለሰብዓዊነት አለው ያልነው ስለዚህ ነው ። አመጸኛው ዘወትር የሕብረ ሰብ ባልደረባ መሆኑ ስለማይቀርና መንፈሱም ከሕግ ሥርዓት ጋር የተጣለ መሆኑ በአድራጐቱ ስለተመሰከረ ፥ የሰው ማሕበር የአጥፊውን አመል ማቅናትና ሕግ እክባሪ ማድረግ ዓይነተኛ ተግባሩ ነው ። ቅጣት ለሕብረ ሰብ መከላከያ መድኃኒት ሲሆን ለአጥፊው ደግሞ ማዳኛ መድኃኒት ነው ።

ሞራላዊ ሥርዓት በቅጣት ይታደሳል ፦—

ቅጣት ፥ ማሻሻያም ፥ ምሳሌም ፥ ካሣም ሊሆን ይችላል ። ዋና ባሕርዩ ግን ለአጥፊው የሚሰጠው የሞራል ጥቅም ነው ። ለምሳሌ ፥ ጥፋት የሠራ ሰው በመንፈሱ ውስጥ የሕሊና ብጥብጥ ስለሚፈጠርበት ፥ ካልካሰ ወይም ካልተቀጣ ሰላምና እርጋታ ለማግኘት ያቅተዋል ። ሲቀጣ ግን ዕዳውን መክፈሉ ይሰማውና ሕሊናው ንጽሕናን ይጐናጸፋል ። ብጥብጥን መጥላትና የልብን አሳብ ሁሉ በሥርዓት ላይ መመሥረት ፥ ሥርዓትም በፈረሰ ጊዜ ራስን በመቅጣት የሥርዓትን ክብር መካስ ያስፈልጋል ።

የመቅጣት መብት ፥ ምክንያቱና ሰፋቱ ፦—

ሕብረ ሰብ የመቅጣት መብት የተሰጠው በምን የተነሣ

ነው ? መቅጣት ራሱ ከባድ መብት ነው ፤ ነገር ግን ይህ መብት ባይኖረው ሕብረ ሰብ ራሱን ከጥፋት ለማዳን ባለ ቻለ ነበረ ። መከላከያውና ምሽጉ የሆኑትን ሕጐች ካላስከበረ ማሕበር ሊኖር አይችልም ።

መቅጣትን መሣሪያ አድርጐ መነሳት ሕግ እንዲከበር ለማድረግ ነው ። ስለዚህ ቅጣት የሕግ ማስከበሪያ ዋስትና ነው ለማለት እንችላለን ፤ ሕጐች ከተጣሱ ፥ የከተማው ግንቦች ተናዱ ፥ ሕዝባዊ ሥርዓት ፈረሰ ማለት ነው ። ለቤተ ሰቦችና ለሰዎች ጸጥታ ፥ ሰላምና የመኖርም ችሎታ ጠፋ ማለት ነው ። ሕብረ ሰብ ሕግ ተላላፊዎቹን በሚቀጣበት ጊዜ ከዋናዎቹ ተግባሮች አንዱን መፈጸሙ ነው ። መብቱንም የሰጡት በውስጡ የሚተዳደሩት ሰዎች ናቸው ፤ እያንዳንዱ ሰው ፥ ብኀድል ሞት ይፈረድብኝ የሚለው ፥ ራሱን ከነ ፍሰ ገዳይ ለማዳን ሲል አይደለምን ?

ሆኖም ይህ መብት ሕብረ ሰብን በሰው ላይ ስለሚያነግሠውና ባለፉት ምዕታመቶች በምድር ላይ በፍርድ ሰም ይፈጸም የነበረውን ስቃይ ስንመለከተው ፥ መብቱ ራሱ አሰፈሪ ይሆናል ። ስለዚህ የመቅጣት መብት ፥ ግለሰብን ከግፍ በሚጠብቅ አኳኋን የተወሰነና በጥንቃቄ የተገደበ መሆን አለበት ። በዘመናዊ የሰው መብት ሕግ ፥ የሚከተሉት ቃሎች የገቡበት ስለዚህ ነው ። «ማንኛውም ሰው በሕግ በተወሰነው መሠረትና ሕግ ባዘዘው መንገድ ካልሆነ በቀር ሊከሰስ ሊያዝና ሊታሰር አይችልም ።»

«ሕግ የሚወስነው ቅጣት ሁሉ አስፈላጊነቱ በሚጠይቀው መጠን መሆን አለበት ፤ ወንጀሉ ከመፈጸሙ በፊት

ታውጆ በወጣ ሕግ መሠረት ካልሆነ በቀር ሰው ሊቀጣ አይ ችልም ።»

«ማንኛውም ሰው ጥፋተኛነቱ እስኪረጋገጥ ድረስ ን ጹህ ስለሆነ በሚያዝበት ጊዜ እንዳይጉላላና እንዳይጐዳ በ ሕግ መጠበቅ አለበት ።»

የመቅጣት ሥልጣን የተሰጣቸው ሰዎች ይህን ሁሉ ማስታወስና የሥልጣናቸውን ከባድነት መገንዘብ ፥ ውሳኔ በሚሰጡበትም ጊዜ ሁሉ ዋዛንና ችልታን ከሕሊናቸው ማስወገድ አለባቸው ። የመቅጣት መብት ሕብረ ሰብን በመጠበቅ መንፈስ ብቻ አይወሰንም ፤ ሕብረ ሰብ አጥፊ ውን እንደአደጋ ብቻ አይቆጥረውም ፥ ይዳኘዋል ። ሳይዳ ኝም ሊቀጣው አይችልም ። ለመቀጣቱም በቂ ምክንያት ለማግኘት የአጥፊውን ሕሊና ፥ ልቡን ፥ ምኞቱን ሁሉ ተን ትኖ ይመረምረዋል ፤ ከዚያም በቀላሉ ሊፋቅ የማይቻል ማ ሕተም በሕይወቱ ሰሌዳ ላይ ያኖርበታል ። የሰውን ባሕ ርይ መመዘን ፥ ሥርዓትን ማቃናት ሕብረ ሰብ የተቀዳጀው ከባድ መብት ስለሆነ ከመለኰታዊ ሥልጣን ጋር የሚያጐራ ብተው ሁኔታ ተፈጥርዋል ።

የሞት ፍርድ ፦—

በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሰው ከተቀዳጀው መብቶች ከሁሉም ከባድ የሞት ፍርድ ነው ። የሞት ፍርድ ሊመለስ ወይም ሊታደስ በማይቻል መንገድ የሚደመስስ ነው ። ም ንም እንኳን አንዳንድ ጊዜ የዳኝነት ስሕተት ሊኖር ቢች ልም ፥ አንድ ጊዜ ከተፈጸመ መመለሻ የለውም ፤ የሞት ፍ

ርድ እንደሕይወት ፥ እንደ እድል ፥ ባንድ አፍታ ይቀመጥ ላል ። ከእግዚአብሔርና ከሰው ሕጐች የሚቃወስ ፥ የመሰ ሉን ሕይወት መጠበቅ ተግባሩ ከሆነው ከሰው ሞራላዊ ተፈ ጥሮ ጋር የሚያጣላ ውሳኔ ይመስላል ።

ብዙዎች አገሮች ለምሳሌ ፥ ኢጣሊያ ፥ ሰዊስ ፥ ሆላ ንድ ፥ ፖርቱጋል ፥ ቤልጅክ የሞትን ፍርድ ሰርዘውት ነበረ ወይም ሰርዘውታል ። ነገር ግን በኛ አስተያየት የሕግ ዋና ዓላማው ፥ የዳኛ ዓይነተኛ ተግባሩ ፥ የሰው ሕይወት በአገሩ በሙሉ እንዲጠበቅ ማድረጉ ነውና የሞትን ፍርድ በሕግ ውስጥም ማግባት አስፈላጊ ሲሆን እንዲፈጸምም መጠየቅ ተገቢ ነገር ነው ። የሞት ፍርድ በተሰረዘባቸው አገሮች ነፍ ስ ግድያ መብዛቱ የተረጋገጠ ነገር ነው ።

የመቅጣትን መብት ማለስለስ ፦—

ባንድ በኩል ደግሞ ቅጣትን ማቃለልና ማለስለስ የ ሚቻልበትን መንገድ ማጥናት አለ ፤ ረጅምና አሰቃይ የሆኑ ትን ምርመራዎች በማስቀረት ፥ በይደር መቅጣት ፥ ማቃ ለያ ሁኔታዎችን መቀበል ፥ ምሕረት ፥ በዚህ ውስጥ ይቆጠ ራሉ ። የወንጀለኛ መቅጣት መንፈስ ራሱ እየተራቀቀ ፥ ሄ ድዋል ፤ በአጥፊው አድራጐት የሕብረ ሰብንም አላፊነት ያ መዛዝናል ። ለምሳሌ ፥ እናት አባት በማጣት ከልጅነት ብቻ ውን ያደገ ሰው ፥ ጥፋት አድርጐ ሲገኝ ፥ ሕብረሰብ እሱን ወደ በጐ መንገድ ለመመለስ ፥ ሞክሮ እንደሆነ ፥ አስተም ሮት እንደሆነ ፥ ከችግር አደኖት እንደሆነ ከመፍረዱ በፊት ዳኛው ይጠይቃል ።

የቅጣት አሳጭነት ፡—

ወንጀለኛው የሚደርሰበት ጉዳት በሕግ በተመለከተው ቅጣት ብቻ አይደለም ፤ በተለይም በሠለጠኑ ሕዝቦች ዘንድ የተሰፋፋው ሕዝባዊ ትዝብት የተባለው ነገር ያሰቃየዋል ።

ወንጀለኛውን ፥ አመጸኛውን የውርደት ምልክት እንዳረፈባቸው አድርጐ ሕብረሰብ ያርቃቸዋል ፥ ይሸሻቸዋል ። ቅጣቱንም ጨርሶ ከወጣ በኋላ ይህ ትዝብት ይከታተለዋል ፥ ያሳጣዋል ።

ብዙ ዳኞች ባንድ ሰው ላይ ለመጀመሪያው ጊዜ ቅጣት ሲፈርዱበት በዚህ የተነሣ በጣም ይቸገራሉ ፤ ባንዳንድ አገሮች እንዲያውም ከሕግ ፍራቻ የትዝብት ፍራቻ ከጥፋት የሚገታበት ጊዜ አለ ።

ቅጣትና ድርጊት የተያያዙ ናቸው ፡—

ጥፋተኛ ዞሮ ዞሮ ራሱን ነው የሚቀጣው ። ድርጊቱን እንደፈጸመ ቅጣትን ይሸምታል ፤ በመንፈሱ መታወርን ፥ በልቡ ሽብርን ሲያስገባ የራሱን ሰብዓዊ ባሕርይ ማፍረሱ ነው ። ድርጊቱ እንደተፈጸመ ወደኋላው ይቀራል ማለትም ተደረገ ፥ በጊዜ ላይ ዋለ ፥ ሊሠረዝ አይችልም ፤ ያለፈ እንጂ መጭ አይደለምና ትውስቱ እንደጥላው ይከታተለዋል ፥ መጥፎ ሕሊናውም አይለየውም ። ጥቂት ሞራላዊ ስሜት የቀረው ሰው መጥፎ ድርጊቱን ሲያስታውስ ሊኖር አይችልም ። በራሱ ይፈርዳል ፥ ቅጣትን ይሻል ፥ ቅጣቱንም ከተቀበለ በኋላ በንስሐ እንደነጻ ይሰማዋል ። ቅጣቱን በሚቀበል

በትም ጊዜ ዕዳውን በመክፈል ላይ መሆኑ ይታወቀዋል ። የሚያየውም መከራ ዳግመኛ እንዳያጠፋ ይመክረዋል ፤ ጥፋትንም ይጠላል ። ነገር ግን እውነተኛው ሥርየት የሚገኘው በመንፈሱ የሚፈጠረው የጥፋት ጥላቻ በሚያስከትላቸው ስሜቶች ነው ። እነዚህም ፥ ሐዘን ፥ ጸጸትና መቆጨት ናቸው ፤ በሠራው ሥራ ሲከፋና ምነው እንዲህ ባልሆነ ሲል ሐዘን ይሰማዋል ።

በሰብዓዊ ሥልጣኑና በፈቃዱ የማይደመሰስ ጥፋት በመሥራቱ ነፍሱን የሚያስጨንቀው ስቃይ ፥ ጸጸትን ያስማዋል ። የሠራው ሥራ በመንፈሱ ላይ የሚያሳድረው ሐዘንና ሁለተኛ እንዳይመለስበት የሚገባው ቃለሕሊና መቆጨትን ያሰማዋል ።

እነዚህ ሶስት ስሜቶች በመሠረቱ ሰው ክፉ አለመሆኑንና በጐ መመኘቱን በልቡ ውስጥ በጥፋቱ መጸጸቱንና ለመካስ ዝግጁ መሆኑን ፥ ጊዜ የማይገለበጥ በመሆኑ ያለፈንና የተደረገን ነገር ለመሠረዝ አለመቻሉን ያስረዱናል ።

ድሕረ ሞት ቅጣት ፡—

ከሞት በኋላ በሠራው ሥራ የሚጠየቅ መሆኑ በሰው መንፈስ የተቀረጸ እምነት ነው ፤ ሰው መጭው የሚያልቅ መሆኑን ሰለማያምንና ዘወትር በወደፊቱ ተስፋ ስለሚኖር ይህ አሳብ ከልቡ አይነቀልም ። ድሕረሞት የሚቆየን ቅጣት ብርቱ ቢሆንም በሕይወታችን ጊዜ ሊደርስብን የሚችለውም የሚናቅ አይደለም ፤ እግዚአብሔር በሰፊ ችሮታው ምሕረት ሊያደርግልን ይችላል ። ነገር ግን እራሱ የፈ

ጠረውን የጊዜን ሕግ ሊሽረው ስለማይፈቅድ የተደረገን እንዳልተደረገ ፥ የሆነን እንዳልሆነ እያደርግምና ሥርየት እንደ ንጽሕና አይሆንም ፥ ቅጣትም ጐዶሎ መድኃኒት ነው ።

ም ዕ ራ ፍ 3 ፡—

ተባባሪነት ፡—

ተባባሪነት የተፈጥሮ ምግባር ነው ። ሰዎች በብዙ ማሰሪያዎች የተዋሃዱ ናቸው ። እያንዳንዱ ሰብዓዊ ፍጡር ለሕብረ ሰብ ባለዕዳ ነው ። ዕዳውንም ለመክፈል የሚችለው ተባባሪነቱ የሚጠይቀውን ተግባር በመፈጸም ብቻ ነው ።

<u>የተባባሪነት ሁኔታና ከባድነቱ ፡—</u>

ሰብዓዊ ተባባሪነትን የሚያስተዳድሩ ትክክለኝነትና ርሕራሄ ናቸው ፤ ዓለም የሚመራው በተባባሪነት ሕግ ነው ። ሰው የማይነጣጠል መሆኑንና ተነጥሎ ለመኖር አለመቻሉን እናውቃለን ። ይህንንም ሰንል ኑሮና ጥቅም ብቻ ያገናኛቸዋል ማለት ሳይሆን ሰዎች የማይነጣጠሉ ፥ የተዋሃዱ አንድ አካል መሆናቸውን ለማስገንዘብ ጭምር ነው ።

<u>ሰዎችን የሚያዋህዱ ማሰሪያዎች ፡—</u>

ተባባሪነትን ጥሩ እድርጐ ለመገመት ሰዎችን ዘወትር የሚያስተባብሯቸውን ነገሮች መዘርዘር ጠቃሚ ነው ።

1. በዓለም ላይ በሚገኙት አንድ ዓይነት መቅኖችና ፊዚካዊ አካሎች በመጠቀም ፥ በተፈጥሮ ተባባሪነት ፡—
2. በተፈጥሮ አንድ በመሆንና ሕይወትን በመወራረስ ፤
3. ሰዎችን በጊዜና በስፍራ የሚያዋህዳቸው ማሕበራዊ ተባባሪነት ፥ በስፍራ ውስጥ የተባለው በማሕበር መኖር ራሱ ዘመን ጓዶቹን የማያቋርጥ ግንኙነት እንዲያደርጉ ስለሚጠይቃቸው ነው ፤ በጊዜ ውስጥ የተባለው ደግሞ ሰው ከአባቶቹም ከልጆቹም (ከተከታዮቹ) የሚነጠል ስላልሆነ ነው ።
4. በመፈቃቀርና ደስታን ፥ ሕመምን ፥ ጭንቀትን ባንድ ዓይነትመ ልክ በመቀበል ያለው ተባባሪነት ፤
5. በመወለድና ሕብረ ሰባዊን ኑሮ በመጋራት ብቻ ፥ በምንገባው ዕዳ ያለን ተባባሪነት ፥ ይህ የተፈጥሮ ተባባሪነት ፥ የሰው ማሕበር ሊከናወን የሚችልበት ስለሆነ ማንም ሰው ሊሸሸው የማይችል ነው ።

<u>እያንዳንዱ ሰባዊ ፍጡር ለሕብረ ሰብ ባለዕዳ ነው ፡—</u>

በመኖራችን ብቻና እንዲሁም ሕብረሰባዊን ኑሮ በመጋራታችን ፥ የምንገባው ዕዳ በጣም ከፍ ያለ ነው ። ሰውነታችን ፥ ቋንቋችን ፥ ሃሳቦቻችን ፥ አቅዋሞቻችን ፥ እውቀታችን ሁሉ አባቶች በትእግሥትና በድካም አከማችተው ያቆዩን ቅርስ ነው ።

ግለሰብ ከማሕበሩ ተለይቶ ሊኖር አይችልም ፤ አንድ ምግብ ሲጐርስ ፥ ባንድ መሣሪያ ሲጠቀም ፥ አንድ መጽሐፍ ሲገልጽ ፥ አንድ ሃሳብ ሲያመነጭ ፥ በዘመንጻዶቹ ሳይረዳ ፥ ወይም ያለፉት ትውልዶች ባከማቹት ማሕበራዊ ሃብት ሳይጠቀም አይሆንለትም ። ይህ ሁሉ ሃብት ብድሩ እስከተከፈለ ድረስ አላግባብ የተያዘና ዕዳው ያልወጣለት ሃብት ነው ። ባንድ ዕቃ ስንጠቀም ፥ በዚያ በዕቃ የተነሣ የዘመንጻዶቻችንና የተከታዮቻችን ባለዕዳ መሆናችን ነው ።

የጊዜ ሕግ ሰው ከአባቶች የተበደረውን ፥ ለተከታዮቹ እንዲከፍል ያዛልና የተከታዮቹም ባለዕዳ ያልነው ስለዚህ ነው ። ደግሞም የሕብረ ሰብ ሃብቶች እንዲደረጁ እያንዳንዱ ሰው ችሎታው በሚፈቅድለት መጠን እንዲጥር ይኸው ሕግ ያዛል ። በአንድ ዘመን የሚኖሩ ሰዎች (ዘመንጻዶች) ተጠቃቃሚ እንዲሆኑና አገልግሎትንም እኩል ለመከፋፈል ውል እንደሚያደርጉ ሁሉ የጋራ ሃብትን ማደራጀት ደግሞ በተከታታይ ትውልዶች መካከል ያለ ውል ነው ። ሰው ዕዳውን ካመነና ከተቀበለ በኋላ ለዘመንጻዶቹና ለተከታዮቹ እንዲከፍል በግዴታ ውስጥ ይገኛል ፤ ስለዚህ ሰዎች በውላቸው ተመሳሳይነትና ለሰው ዘር ሊከፍሉ የሚገባቸውን በመገንዘብ ተባባሪዎች ናቸው ። ማንም ሰው ሊሽረው የማይችለውና ሊሽረው የማይገባው የተባባሪነት ሕግ ይህ ነው ።

የተባባሪነት ተግባር ፡—

ሰው ሕብረ ሰባዊ ኑሮ ከሚያስገኘው ጥቅም በመካፈሉ ምክንያት ወዶ የተቀበለው ስለሆነ የተባባሪነት ግ

ዴታ ከተፈጥሮ ባሕርይ የፈለቀ ነው ። ይህም የውል ያህል ያስራል ። ነገር ግን ይህ ውል ተፈጻሚነት እንዲያገኝ የተባባሪነት ሕግ በትክክለኝነትና በርሕራሄ (በመተዛዘን) እንዲተዳደር ያስፈልጋል ። በዚህ ሁኔታ የተፈጥሮ ሕግ የነበረው ሞራላዊ ሕግ ይሆንና የያንዳንዱ ሰው መብትና ተግባር እንዲሁም የጋራን የተባባሪነት መንፈስ የሚወስኑ ትክክለኛ ደንቦች ለማውጣት ይቻላል ። የተፈጥሮን ሕግ ሞራላዊ ለማድረግ ፥ ግለ ሰብ ፥ ሕብረ ሰብ ፥ ዶረጀ መድረስና ይህ ሁኔታ የሚያስከትለውንም ተግባር ለመፈጸም ዝግጁ ሆኖ መገኘት አለበት ።

ተባባሪነት የትክክለኝነትንና የርሕራሄን ተግባር ያብራራል ፡—

በዚህ አኳኋን የተባባሪነት አሳብ ፥ የትክክለኝነትንና የርሕራሄ ተግባራችንን ብሩሕ አድርጉ ያሳየናል ። አንዱ ለሌላው ጠቃሚ በመሆን ፥ የሰው ዘር በኛ ላይ ያለውን ዕዳ በማመን ፥ ብድር ከፋይ ባለዕዳ ሆነን ለመገኘት በመዘጋጀት ትክክለኞች እንሆናለን ። ከሌሎቹ ተነጥሎ መኖርን በመጥላት ፥ መሰሎቻችን የሆኑትን ፍጡሮች ለመርዳትና በነሱም ለመረዳት ዝግጁ ሆኖ መገኘት ፥ በተከታታይ ትውልዶች መካከል ያለውን ውል በማክበር የጋራ ሃብታችንን ለማደርጀት በመጣር ርሕራሄን እንሳተፋለን ።

ተባባሪነት ሕግ አውጭን ይመራዋል ፡—

የሰው ዘር ያከማቸው የጋራ ሃብት የጥቂቶች ንብረት ብቻ[ሊሆን አለመቻሉን ለሕግ አውጭው ያሳየዋል ። ግ

ብር በትክክል እንዲደለደል ፥ አስፈላጊ ከሆነው ላይ ከመ
ቀነስ በፊት ከትርፍ ላይ እንዲነሳ ፥ በዚህም አኳኋን የተገ
ኘው ገንዘብ ለሕዝባዊ ጥቅም እንዲውልና እያንዳንዱም
ሰው ከማሕበሩ ሽርክና የሚደርሰውን እንዲያገኝ ይወሰን
ለታል ።

እንዲሁም ለራሳቸው መብቃት ለማይችሉት ለሕጻ
ናት ፥ ለድውያን ፥ ለበሽተኞች ፥ ለሽማግሌዎች የኑሮ ማሸን
ፊያ እንዲሰጣቸው ፤ ያረጁ ሠራተኞችም ከሕብረ ሰብ ሃ
ብት ላይ በሚነሳ ድርሻ እንዲጠሩ ይደረጋል ። በተረፈም
ሕብረ ሰብ አባሎቹ ለሆኑት ከኑሮ ጠንቆች ፥ ከሥራ ፈት
ነት ፥ ከበሽታ ፥ ከቃጠሎ ፥ ከውሃ ሙላትና ከመሳሰለውም
ነገር ሁሉ የሚጠበቁበት መተማመኛ እንዲያዘጋጅላቸው
ተባባሪነት ያስገድዳል ።

<u>የተባባሪነት ታላቅ ሞራላዊ አቅም ፡—</u>

ተባባሪነት ታላቅ ሞራላዊ ኃይል አለው ። ሰዎች እድ
ላቸው የጋራ መሆኑንና ተነጣጥለው ለመኖር እንደማይ
ችሉ ያስረዳቸዋል ። ትክክለኛነትና ርሕራሄ ሲዘረጋ ለዚህ
ስሜት ወሰን ሊኖረው እንደማይገባ ያስገነዝባቸዋል ። ነ
ገር ግን ተባባሪነት የስነ ፍጥረትን ሕግብቻ ተከትሎ ይፈጸማ
ል ብሎ ማመን አይገባም ፤ ሰው በተፈጥሮ ከሕብረ ሰብ ጋር
የተሳሰረ ቢሆንም የሞራላዊ አድራጐቱ ባለቤት ራሱ ነው ።
የተባባሪነት ሕግ ወደክፉም ወደበጐም ሊወሰድ ይችላል ፤
መምረጡ የሰው ፈንታ ነው ። በስስትና በግላዊ ስሜቱ
ብቻ የተመራ እንደሆነ ፥ በመሰሎቹ ላይ ግፍ ይውላል ፤ በዚ
ህም ክፉ ሥራን ያነግሥና ያስተላልፋል ። ግን በገዛ ፈቃዱ

በተፈጥሮ ጠባይ ላይ የአእምሮን ጠባይ ማለትም ትክክለኝ
ነትና ርሕራሄን ጨምሮ በዚህ የተመራ እንደሆነ የተፈጥሮ
ተባባሪነትን ከሞራላዊ ተባባሪነት ጋር በማዋሃድ ፍጹምነ
ትን ያገኛል ።

በዚህ ጊዜ በጐ ሥራ ይደረጅና ይወረሳል ። ይህ አሳብ
የአላፊነት ስሜታችንን በማንቃት አድራጐታችንንና በ
ሰው ዘር መካከል ያሉትን ግንኙነቶች በማንኛውም ጊዜ
በጥንቃቄ እንድናጠና ያደርገናል ። በተባባሪነት መንፈስ
የሠራን እንደሆነ ፥ በግላዊ ኑሮአችን አለመታጠራችንና በጊ
ዜም ሆነ በሶፍራ ያልተነጣጠልን መሆናችን ይሰማናል ። በ
ማንኛውም ጊዜ ከመሰሎቻችንና ከሰው ዘር ጋር መተሳሰ
ራችን በዘራችን ሕይወት ውስጥ መዋሃዳችንን ያሰማናል ።

ም ዕ ራ ፍ 4 ፡

ግላዊ ኑሮ ፡—

ሰው ለራሱ ሊፈጽመው የሚገባ ተግባር አለው ። ስለአ
ካሉ ኑሮ ለምሳሌ ፥ ራስ መግደልን መጥላትና ጤናውን
የመጠበቅ ግዴታ አለበት ፤ ከልክ ማለፍንና በተለይ ሰካርን
ማስወገድ አለበት ፤ አንድ ዓይነት የጤና ጥበቃ ደንብ ማብ
ጀትና ስፓርትንም በመጠኑ እንዲያዘወትር ያሻል ፥ ለመን
ፈሳዊ ኑሮው ደግሞ የልብን ስሜት ፥ እውቀትን ፥ ፈቃደኛ
ነትን ማጐልመስ ይኖርበታል ።

የተግባሮቹ ክባድነት ፡—

ሞራልና ሕብረሰባዊ ኑሮ እጅግ የተሳሰሩ ከመሆና ቸው የተነሳ ዓይነተኛ ተግባራችን ለሌሎች ማገልገል ብቻ ይመስለናል ። በእርግጥም የሕብረትን ኑሮ ዋናነት ለመ ካድ አይቻልም ፤ ቢሆንም እያንዳንዱ ሰው ደግሞ የራሱ ሕይወት እንዲኖረው ያስፈልጋል ። ሌሎችን እንዳከበረ ሌሎችም እኔን እንዲያከብሩኝ የሚያዘው የትክክለኝነት ተግባር ፡ ግለሰብ ላራሱም ሊፈጽመው የሚገባ ተግባር እን ዳለበት ያረጋግጥልናል ። በዚህ አኳኋን ሞራላዊ ሕይወት እያንዳንዱ ሰው በራሱ ፍኖት ሕይወት ላይ ያለውን ስሜት ከፍ ያለ ደረጃ እድርሶ ያሳየናል ። ሰው መድህኑ የሚሆኑ ትን ብርሃንና ኃይሎች ለማግኘት የሚችለው በራሱ ነው ። ስለዚህ ሰው ፡ የሕሊና ማሕደርና የሞራል ምሰሶ ነው ።

የአካላዊ'ኑሮ ጥበቃ ተግባሮች ፡—

ከተግባሮቹ ዋናው ፡ አካላዊ ኑሮውን የሚመለከቱት ናቸው ፤ ባጭሩም ሕይወቱን ማለት ነው ። በሰዎች ዘንድ ያለው የመኖር ፍቅር እጅግ ብርቱ በመሆኑ በሕይወታቸው መኖራቸውንና ዓለም በርግጥ መኖሩን የሚያምኑት በሱ ሳቢያ ነው ። ይህም ስሜት በጽኑ አኳኋን ፡ የተቀረጸብን ስለሆነ በሽታ ፡ ታላላቅ ፈተናዎች ሊያሸንፉት አይችሉ ምና እስከ መጨረሻው የሕይወታችን ደቂቃ ድረስ አይለየ ንም ። ያረጁ ሰዎች ፡ ለመሞት የተቃረቡም ሁሉ ከሕይወት ጋር እንደሚቆናጠጡ በማየት ፈላስፋው እንዲህ ብሏል ፡— «እያንዳንዱ ሰው በመጨረሻው ሰዓት ነፍሱ ስትወጣ ገና ዛሬ የተወለደ እንደመሰለው ነው የሚሞተው ።»

ራስን መግደል ፡—

ይህም ሆኖ ችግርን ፡ ድህነትን ፡ ውርደትን ባለመ ቻል ወይም ፈጽሞ ተስፋ በመቁረጥ ሕይወታቸውን የሚ ያጠፉ አንዳንድ ሰዎች አሉ ። ያንድ መምህር ደቀመዝሙ ሮችም ፡ «በጭስ ከታፈነ ቤት እንደምንሸሽ ሁሉ ፡ አንዳ ንድ ጊዜም ሕይወትን ትቶ መሄድ ተገቢ ነው» ። የሚሉ ነበሩ ። ባንዳንድ ሁኔታዎች ለምሳሌ ፡ መርከቤን ጥዬ አልሄ ድም በማለት አብሮ የሚሰምጥ ካፒቴን ወይም ድል የመሆ ንን ኃፍረት ባለመቻል ራሱ ሕይወቱን የሚያሳልፍ ወታ ደር ፡ ራስ መግደልን ጀግንነት የሚያስመስሉበት ጊዜ አለ ፤ ነገር ግን ልብ አድርገን ስንመለከተው ፡ ራስን መግደል የዋ ህነት ፡ ከጂነት ፡ ወንጀል ነው ።

የዋህነት ነው የተባለበት ፤ ሕይወት ራሷ ከምናስበውና ከምንጠብቀው የበለጠ ተለዋዋጭና ችግርንም የምናሸንፍ በት ኃይል የምትሰጠን ስለሆነች መታገስ ባለመቻላችን ነው ፤ ለምሳሌ ፡ አንዳንድ ሰዎች በኃይለኛ ደዌ ሲሰቃዩ ባ የን ጊዜ እንሳቀቃለን ፤ በራሳችንም ቢደርስብን እንዴት እንችለው ይሆን ብለን እንጨነቃለን ። ነገር ግን እንዳጋ ጣሚ ቢደርስብን ፡ ከመንፈሳችን አንድ አዲስ የማናውቀው ኃይል ይመነጭና መከራችንን አቃሎ የምንችልበት አቅም ይሰጠናል ፤ መታገሥና መቆየት የማያሸንፈው ችግር የ ለም ።

ከጂነት ነው የተባለበት ፤ እኛ በሕብረሰብ ውስጥ ማሕበረተኛ እንደመሆናችን መጠን የሰው ዘር ፋንታችንን

እንድናገለግልና እንድንሠራ ሲጠብቀን ራሳችንን ፥ በመግ
ደል ሰናመልጠው ከዳነው ማለት ነው ።

ወንጀል ነው የተባለበት ፡— ሞራላዊ ሕግ የተጐናጸፈ
ውን አካልና ሕይወት መደምሰስ ሌላ ሰው እንደመግደል
ያህል የሚቆጠር የአመጸች ሁሉ ታላቅ ስለሆነ ነው ። ሕይ
ወትን መቀበልና መጋፈጥ ፥ የሰው ቀዳሚ ተግባሩ ነው ።
እዚህ ላይ የፈላስፋውን የስቅራጥስን ቃል ማስታወስ እንች
ላለን ። «አንድ ወታደር የተመደበበትን ሰፍራ ያለመኰንኑ
ትእዛዝ ሊለቅ እንደማይችል ሁሉ ግንም ሰው አለፈጣሪው
ና አለጌታው ፈቃድ ሕይወትን ትቶ ሊሄድ አይገባውም ።»

በጤና ረገድ ያለ ተግባር ፡—

ሕይወትን መጠበቅ ተግባር መሆኑ ከታመነ ፥ በሞራ
ላዊና በአእምሯዊ ኑሮ ላይ ከፍ ያለ አመዛኝነት ያለውን ጤ
ናን ተጠንቅቆ መጠበቅ ያስፈልጋል ። በተለይ ባንዳንድ ሁ
ኔታ ካልሆነ በቀር የጤና አጠባበቅ በመጠን መኖርን ሲጠ
ይቅ ፥ተፈጥሮደግሞበዚህመንገድአይረዳም፤ሰውእንስሳዊ
ባሕርዩእያሸነፈውአብዛኛውን ጊዜመጠንን መጠበቅያቅተ
ዋል ። ሆዳምነት ብዙ ሰዎች ገድሏል ። ስካርም የበለጠ አጥ
ፍቷል ። ስካር የዘመናዊ ሕብረሰብ ኑሮ ቁስል ሆኖ ተገኝ
ቷል ። ጤናን ይመርዛል ፤ አእምሮን ያዋርዳል ፥ ዘርን
ያበላሻል ። (አንድ ሕዝብ በአልኰል ከብዙ ጊዜ ዝምሮ የተ
መረዘ ሲሆን ፥ አትሌቶቹ በኢንተርናሺናል ውድድር ጊዜ
ዝቅተኞች ሆነው ይገኛሉ) ። ስካር ቤተ ሰብን ያበጣብጣል ፥
ሰብዓዊ ስሜቶችንም ይቀጫል ፤ እንደዚሁም እያንዳንዱ

ሰው ለመጠጥ ፥ ከደሞዙ ግማሽ በላይ ስለሚያወጣ ፥ የሕ
ዝብ ኤኰኖሚካዊ ሁኔታ በጣም ይወድቃል ።

ዘማዊነት ደግሞ ፥ በሰው ዘር ላይ ከሚያሰፍረው ጉዳ
ትና በሽታ በላይ እጅግ ድንቅ የሆኑትን ልባዊ ስሜቶች ያረ
ግፋቸዋል ። በማንኛውም በኩል ከመጠን ማለፍ መንፈ
ስን ያረክሳል ያጨልማል ፤ በዚህ ዓይነት አኳኋን የሚኖሩ
ሰዎች ሁሉ ፥ የርሕራሄና የአእምሮ ደሆች መሆናቸው የተረ
ጋገጠ ነው ። እያንዳንዱ ሰው ለጤናው አንድ ደንብ ማብ
ጀት አለበት ፤ ጽዳትን መጠበቅ ፥ አመጋገብን ፥ መቆጣ
ጠር ፥ ሰውነትን ከመጠን በላይ አለማሰለመድ ከጥንት ጀ
ምሮ የታወቀ መድኃኒት ነው ። ጤና በመንቀሳቀስ ማለትም
በስፖርትም ሊጠበቅ ይቻላል ።

ስፖርቶች ፡—

በዘመናዊ ኑሮ እጅግ የተስፋፋው ስፖርት ለአካልና
ለሞራል ከፍ ያለ ጥቅም የሚሰጥ መሆኑ በፍጹም ታምኗል ።
አካልና ነፍስ ፥ ከተፈጥሮ ሃብት ታላቅ ከሆኑት ፥ ከብርሃን ፥
ከአየርና ከውሃ በመገናኘት ጥራትንና መታደስን ይሳተ
ፋሉ ። ደስታና ተድላን የሚያመነጭ መንፈስ ሰውነትን በ
ሙሉ ይወርሳል ። ስፖርትን ለማዘወተርና ቅርጽን ለመጠ
በቅ በመጠን እንዲኖሩ ያስገድዳል ። አትሌቶች ሰውነታ
ቸውን ለማጠንከርና ውጤታቸውን ለማሻሻል ሥጋዊ ቅብ
ጠትን ይሸሻሉ ። ስፖርት አቅምን በመገመት ትክክለኛ
መንፈስን ፥ አቅም እስከፈቀደ ድረስ ለመታገልም በመፍ
ቀድ ደፋርነትን ፥ አሰቡት ግብ ለመድረስ ቆራጥነትና
ጽኑነትን ያበረክታል ። በተለይም የቡድን ስፖርቶች የሥ

ርዓት ጠባቂነትን መንፈስ ያጐለምሳሉ ። ቢሆንም ስፖ
ርት ሊጠቅም የሚችለው በመጠኑ ሲይዙት ነውና የኑሮ
ዓላማ አድርጐ እሱን መያዝ ከልክ ማለፍን ስለሚያስከ
ትል የጉዳት ምንጭም ሊሆን ይችላል ።

ልባዊ ስሜቶችና ተግባሮች ፡—

ልባዊ ስሜቶችን ማስፋፋትና መኰትኰት ለመንፈ
ሳችን ከፍ ያለ እርዳታ ነው ። ሰውን ደራሲ ፣ ሙዚቀኛ ፣ ገ
ጣሚ ፣ ፈላስፋ የሚያደርገው ከፍ ያለ ልባዊ ስሜት ሲኖ
ረው ነውና መለኰታዊ ምልክት ነው ብለን ልናምንበት
ይገባል ። በሕብረሰባዊ ግንኙነት መንገድ ብንሔድ ፣ ሰብ
ዓዊነት ፣ ከሁሉ አስቀድሞ የሌሎችን ደስታና ሐዘን ለመካ
ፈል ዝግጁ መሆን ነው ። ሰውን ከሁሉ ይበልጥ ተስፋ የሚ
ያስቆርጠው ብጤዎቹ ግድየለሽ ሲሆኑበትና ችላ ሲሉት
ነው ። ታማኝነትና ታላላቅ አድራጐቶች የሚመነጩት ል
ባዊ ስሜት ሲኖር ነው ።

የእናቶችና የሚስቶች ልባዊ ስሜት በሰውር ያደረገው
መስዋዕትነት ባይኖር ሕብረሰብ ሊቆይና ሊዘልቅ ባልቻለ
ነበረ ። የጀግንነት ሁሉ እባት ፍቅር ነው ። የእግዚአብሔር
ፍቅር ባይኖር ስማዕታት ባልታዩ ነበረ ፤ ያገር ፍቅር ባይ
ኖር ጅግና ወታደር ባልተገኘ ነበረ ።

ልባዊ ስሜት በሰው መንፈስ አይዘራም ፣ ከተፈጥሮ
የሚወረስ ጸጋ ነው ። ቢሆንም ቢኰተኰቱትና ቢጠብቁት ፣
ትርምስንና የተሳሳተ መንገድን ትቶ ወደቁም ነገሩ ያመ
ራል ። ኃይለኛ ስሜት በተሰማ ጊዜ ግብርናን ካላስከተሉ መ

ሰማቱ ብቻ ዋጋ የለውም ። ያገርን መዝሙር ሲሰሙ ልብ
ቢባባ ጀግና አያሰኝም ፤ አሳዛኝ ሙዚቃ ስምተው ቢያለ
ቅሱ ሩሕሩሕ አያሰኝም ።

የመማርና የማወቅ ግዴታነት ፣ ፈቃደኝነት ፡—

መማርና ማወቅ በሕብረሰብ መካከል ለሚኖር ላንድ
ሰው ከፍ ያለ ግዴታ ነው ። ሰው ሲፈጠር በአንጐሉ አንድ
የተመጠነ የእውቀት ስፍር አለው ። እውቀቱም ለያንዳንዱ
በመጠን የተሰጠው ስለሆነ ፣ ትምህርትን እኩሉ በዝግታ ፣
እኩሉ በፍጥነት ይቀበለዋል ፤ ዋናው ነገር በተለይም ሕጻ
ናት አንዱ ዓይነት ትምህርት አይገባንም ብለው ተስፋ ቆር
ጠው እንዳይተውት ማድረጉ ነው ። በዘመናዊ ሕብረሰብ ፣
ለራስም ፣ ለቤተ ሰብም ፣ ለአገርም ጠቃሚ ሆኖ መገኘት
የሚቻለው በትምህርት የተኰተኰተ አእምሮ ይዘው ሲቀ
ርቡ ነው ።

እውቀት ያለ ትግል አይፋፋም ፤ በሚያንቀላፋ መን
ፈስ ውስጥ ሲኖር አብሮ ያንቀላፋል ። የሚያንቀላፋ መን
ፈስ ፣ የፈዘዘ አካልና ስሜት ይፈጥራል ። ሰውዬውም ማሰ
ብና ማወቅ የተሳነው ይመስላል ፤ ለምሳሌ ፣ የሂሳብ ትምህ
ርት ዋናዎቹ መስመሮች ከብዙ ሺ ዓመታት ጀምሮ የተዘረ
ጉና የማይለወጡ ሲሆኑ ፣ እያንዳንዱ ትውልድ ሊያውቃ
ቸው የሚቻለው ሃሳቡን አጣምሮ ፤ መንፈሱን አንቅቶእንደ
አዲስነገር በየተራው ታግሎ ካጠናቸው በኋላ ነው ። እያን
ዳንዳችን ዘወትር አዲስ ነገር ያጋጥመናል ፤ እንግዳ ይሆንብ
ናል ፣ መንፈሳችንም ግራ ይገባዋል ፤ ግን ጉዳዩን በፈቃደኝ
ነት ኃይል ከተዳፈርነው ልክ ልናገባውና በአእምሮአችን

ውስጥ ተገዢ ልናደርገው እንችላለን ። ይህ የፈቃደኝነት ኃይል የሚያገለግለን እውቀትን ለማንቃት ብቻ ሳይሆን እንዳለ ለማቆየትም ጭምር ነው ። መልካም ፈቃድ ካልደገፈው እውቀትም ዝቅ እያለ ይሄዳል ፤ ያወቀ ፡ እውቀቱን ላዲስ እውቀት መፍጠሪያ ካላደረገው እርምጃ አይገኝም ። ዘወትር ወደፊት መሄድ ያስፈልጋል ። ዛሬ የሚያምኑበት ጽኑ ነገር ነገ አጠራጣሪ ሆኖ ይገኛል ። የዛሬው እውነት ወደ ፍጹሙ እውነት መወጣጫ ነው እንጂ እራሱ መድረሻ አይደለም ። ያመነውን አምኖ የተኛ ሰው ሲነቃ ሁሉን ተለዋውጦ ነው የሚያገኘው ። የወጣት ታላቅ ጸጋ የአእምሮ ኃይል ነው ። መልካም ውጤት የሚገኝም ከፈቃደኝነት ነው ። ስለዚህ የፈቃደኝነት ኃይልንም መኰትኰት ያስፈልጋል ። ከተፈጥሮ ለመታገልና እድልንም ለማሸነፍ የሚያገለግል ሞራላዊ ባሕርይ ፈቃደኝነት ነው ።

የግለሰብ አስተዳደግ (አመራር) ፡—

አንድ ሰው ከሌሎቹ ጋር ያለውን ግንኙነት ደንብ ለማስያዝ የተፈጥሮ ስሜቱን ያለማቋረጥ መጠባበቅ አለበት ። በሕጻናት ዘንድ በተለይ ፡ ሕጻኑ አድራጐቱን ፡ አቀራረቡን አነጋገሩን በማንኛቸውም ጊዜ እንዲጠብቅ መቆጣጠር የወላጆችና የመምሕራን ተግባር ነው ። ይህ ሁሉ በሕጻንነት ጊዜ ሥርዓት ካልያዘ እንሰሳዊ ባሕርዩ ሰውን ያሸንፈዋል ። የእንስሳ ፡ የሕጻን ባሕርይ የሆነው እንስሳዊ ዝንባሌ ሁሉን ከሁሉ የሚያታግል ስለሆነ በሠለጠነ ሕብረ ሰብ ውስጥ ሊኖር አይገባም ።

አስተዳደግ ማለት ፡ አድራጐትን በትሕትና ላይ መመሥረት ፡ አምሮትን ፡ ስሜትን ሃሳብን በተለይም በሌሎች ሰዎች ላይ ያለንን ግምት አለማወጅ ነው ፤ አንድ አመለ ቢስ ሰው አንዱን ጓደ ሙሉ ይረብሻል ፤ አንድ የደነገጠ ፈሪ አንድ ሻለቃ ያሸሻል ፤ አንድ ችኩል ብዙዎችን ገደል ይጨምራል ።

ትሕትና ፡ (ጭምትነት) ፡—

ትሕትና የመጀመሪያ ደረጃ የሚሰጠው ጸጋ ነው ። ቻይናዎች ትሕትና የልባዊ ስሜቶች ጌጥ ነው ይላሉ ። ስሜታችንን በማስታገስ ፡ ሌሎችንም እንድናከብር በማድረግ ትሕትና ካንዱ ወደሌላው የሚተላለፍ የሰላም አብነት ነው። መቼም ቢሆን ሰው እንዳናስቀይምና ውለታ እንድንውል ስለሚያሳስበን ትሕትና የትክክል አስተያየትና የርሕራሔ ግምባር ቀደም ነው ። ብዙ ወታደሮች በተኩስ ፊት እየተጋፈጡ ግዳጃቸውን የሚፈጽሙት በድፍረት ብቻ ሳይሆን ፡ መልካም አስተዳደግም እየመራቸው ነው ።

ራስን ማክበር ፡—

ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸው ተግባሮች በመሠረቱ ራስን በማክበር ጠባይ የሚጠቃለሉ ናቸው ፤ ራሱን የሚያከብር ሰው በማንም ፊት የሚያፍርበት ምክንያት አይኖረውም ። የሞራላዊ ሕይወት መሠረት የሚገኘው ይህ ተግባር ሲፈጸም ነው ። ስለዚህ ሰው በሌሎቹም ፊት ሆነ ፡ ብቻውንም ባለበት ጊዜ ፡ ተገቢ በሆነ መንገድ መኖርና መሥራት አለበት ። ለምሳሌ ፡ ፖሊስ ወይም ሌላ ሰው አያየኝም

ብሎ በተከለከለ አቅጣጫ መኪና የሚነዳ ሰው ፣ ራሱን ማዋ ረዱ ነው ። ፖሊስም ሌላ ሰውም ባያየኝ ጥፋቱን በምፈጽም በት ጊዜ የራሴ ሕሊና ይመለከተኛል ፤ የሱም ታዛቢነትና ፍርድ ከሌሎቹ ታዛቢነትና ፍርድ የማያንስ ስለሆነ ሕሊና ዬን ፈርቼ ከጥፋት መታገድ አለብኝ የማይል ሰው ሕሊና ውን ናቀ ፣ ራሱን ዝቅ አደረገ ፤ አዋረደ ማለት ነው ።

ራስን ማክበርና ሌሎችን ማክበር ተባባሪ ናቸው ፡—

ግላዊ ተግባር ያልናቸው ነገሮች ሁሉ ዞሮ ዞሮ ማሕ በራዊነትም አላቸው ። የትሕትና ተግባሩን በመፈጸም ራ ሱን የሚያከብር ሰው ሌሎችንም የግዴታ ያከብራል ። ል ባዊ ስሜት ለሌሎች አገልጋይነትን ያስከትላል ። እውቀት መሸመት ለሌሎች ጠቃሚ ያደርጋል ፤ መንፈስን ማጠን ከር ለሌሎች ብርቱ ድጋፍ እስከ መሆን ያደርሳል ። ስለዚህ ግለሰብ ለራሱ የሚፈጽመው ተግባር ለሕብረሰብም ጠ ቃሚ ነው ማለት እንችላለን ።

ሞራላዊ ሰው መሆን ፡—

ሰው በብዙዎች መካከል አንድ አሐዱነት ነው ። አእ ምሮ ያለውም አሐዱነት ስለሆነ መሰሎቹ ከሆኑት ፍጡ ሮች ጋር የሚገናኝበትን ሥርዓት በሕጋዊ መንገድ ለማስተ ዋል የሚችል ነው ፤ ሞራላዊ አካል የሚሆነውም ከዚህ በ ኋላ ነው ። በዚህ አኳኋን በእንስሶች ዓለም ያለው ሁኔታ ይፈርስና ፣ ሰዎች የሚያገናኛቸውን ሕግ ለማውጣት ሁ ሉም እኩል መብትና ተግባር ስለሚኖራቸው ተባባሪነትን ለመቀዳጀት ችሎታ ያገኛሉ ። የሕሊና እውቀት እያደገ ሲሄ ድም ፣ ሰብዓዊ ማሕበርን የመመሥረት ተስፋ እያደረ ይደ

ረጃል ፤ የዚህም አፈጻጸም ብዙ ፈተናና እንቅፋት ቢያጋጥ መውም ፣ በጥቅምና በውድድር ሕግ ፈንታ ፣ የአእምሮንና የርሕራሄን ሕግ በመተካት ሰብዓዊ ማሕበር የተፈጥሮን ማ ሕበር ይሽረዋል ። ስለዚህ ሞራላዊ ሰውነት በድካማችን ልናገኘው የሚገባን ሁኔታ እንጂ ተፈጥሮ እንካችሁ ብሎ ያበረከተልን አለመሆኑን መግንዘብ አለብን ።

ም ዕ ራ ፍ 5

ሞራልና የቤት ኑሮ ፡—ቤተ ሰብ ፡—

የሕብረሰብ መሠረት ቤተ ሰብ ነው ፤ የቤተ ሰብ ዘመና ዊና ፍጹም መልክ የአንድ ጋብቻ ነው ፤ ቤተሰብ የብዙ ተግ ባሮች ምንጭ ነው ፤ ባልና ሚስት እርስ በርስ ፣ ወላጆች ለልጆቻቸው ልጆች ለወላጆቻቸው ፣ ልጆች እርስ በርሳቸው ሊፈጽሟቸው የሚገባ ተግባሮች አሉ ።

ቤተሰብ ከፍ ያለ ሕብረሰባዊና ሞራላዊ ዋጋ ያለው አቅዋም ነው ። ሆኖም ቤተሰባዊን ስሜቶች መኰትኰት አስፈላጊ ነገር ነው ።

ቤተሰብ የሕብረሰብ መሠረት ነው ፡—

ለግለሰብ የሚሰጠው ግምት ማንኛውም ቢሆን ቀድሞ የተነጠለ ወደፊትም የሚነጠል ነገር አለመሆኑ የተረጋገጠ ነው ። በሰፍራ ውስጥ ከመሰሎቹ ጋር በብዙ መንገድ የተሳ

ሰረ ነው ፤ በጊዜ ውስጥ የሕይወት ተላላፊነት (ተወራራሽ ነት) ከወላጆቹና ከልጆቹ ጋር ያስተሳስረዋል ። የሰው የተፈጥሮ ሞራላዊ ዝንባሌው ከሕብረሰባዊ ሁኔታው ሊነጠል የማይችል ነው ።

ይህም ሕብረሰባዊ ሁኔታ ከተፈጥሮ የሚወረሰው በቤተሰብ አማካይነት ነው ። ስለዚህ ሕብረሰብ በቤተሰቦች የተቋቋመ አንድነት ነውና በግለሰብ እንነጣጥልህ ቢሉት እንደ አዋራ ይበናል ። ለምሳሌ ፥ አንድ የመኪና ሞተር የሚፈታታ ሰው ባይነት ባይነቱ መለያየቱን ትቶ ፥ ቢፈጭና ቢያደቀው መልሶ ሊገጥመው ከቶ የማይቻል ነው ። የሰው ዘር ዘላለማዊ ቋሚነት የሚፈጸመው በቤተሰብ አካማይ ነት ነው ። የሕይወት ምንጭ የሆኑት አብነቶች ከቤተሰብ አገናኚነት የፈለቁ ናቸው ። በመሠረቱ የሰው ዘር ሰብዓዊ ወግን ጠብቆ ሕይወትን ለማስተላለፍና እንዳትቋረጥም የሚያደርግበት የተከበረ አብነት ቤተሰብ ነው ።

የቤተሰብ መልክ ፡—

የቤተሰብ መልክ በየጊዜው እየተሻሻለና እየተለወጠ የመጣ ነው ። እኛ የምናምንበትና በነዚህ መስመሮች ልናሰ ፍረው የምንፈቅደው ፥ የአንድ ጋብቻን ቤተሰብ ነው ። የ ዚህ ዓይነቱ የጋብቻ መልክ ፥ ከማንኛቸውም የጋብቻ ዓይነ ቶች ይልቅ የሰውን ክብር ፥ የባልና ሚስትን ፍቅርና የወላ ጆችን ፍቅር የመሰሉትን ቤተሰባዊ ስሜቶች ከነዚህ ስሜ ቶች የሚፈልቁትንም ሞራላዊ ጸጋዎች የሚያስፋፉና የሚያ ደረጅ መሆኑ የታወቀ ነው ።

ቤተሰብ ከጠቅላላ ሞራላዊ ተግባሮች ሌላ የልዩ ልዩ ተግባሮች ምንጭ ነው ። ለምሳሌ ፥ ሰብዓዊ ተግባር አለ ብን ፥ እንዲሁም የባልነት ተግባር ፥ ያባትነት ተግባር ፥ የል ጅነት ተግባር ፥ የወንድምነት ተግባር ፥ የሚስትነት ተግ ባር ፥ የእናትነት ተግባር ፥ የእህትነት ተግባር ፥ ከቤተሰብ መኖር የመነጩ ናቸው ።

ጋብቻና አሳሳቢነቱ ፡—

ጋብቻ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ትዳር ለመመሥ ረት የሚዋሃዱበት ደንበኛና ወግለበስ ሥርዓት ስለሆነ የቤ ተሰብም ማቋቋሚያ ሕግ ነው ። አፈጻጸሙም እጅግ ከባድ የሆነዋጋ ስላለው ከፍ ያለ ጥንቃቄና ማሰላሰልን ይጠይቃል፤ ጋብቻም እንዲቆይ ፥ እንዲደረጅና ፍሬ እንዲሰጥ አንዳንድ ሁኔታዎች በግዴታ አስፈላጊ ናቸው ።

1. አካላዊ ሁኔታ ፡— ከሁሉ አስቀድሞ የሕይወትን ግዳጅ ለመፈጸምና ለወገን ሸክም እንዳይሆኑ በቂ ጤና እን ዲኖር ያስፈልጋል ። ጤናው ደካማ የሆነ ወይም ተላላፊ በ ሽታ ያለበት ሰው ጋብቻን መድፈር የለበትም ። ደግሞም በሕይወታችን ውጤት ላይ እምነት ቢኖረንም ቅሉ አስተዋ ይነትንም መጨመር አስፈላጊ ነው ። ብዙዎች ወጣቶች ለኑሮዋቸው ማሸነፊያ በቂ ሃብት ሳያደራጁ ይጋቡና አካ ላዊ ኑሮአቸውን እንኳን የሚያረጋጡበት አቅም እስከ ማጣት ይደርሳሉ ። ይህን የመሰለው ችግርም የባልና ሚስ ትን የመፈቃቀር ስሜት እየቀነሰው ይሄዳል ።

2. የመፈቃቀር ሁኔታ ፡— ባልና ሚስት ከሁሉ አስቀ ድሞ በጋራ ፍቅር እንዲሳሳቡ አስፈላጊና በተፈጥሮ አስገ ዳጅ ሁኔታ ነው ። ይህም ፍቅር በሰፊው የታሰበበትና የተረ ጋገጠ መሆን አለበት ፤ በባልና በሚስት መካከል ሊኖር የ ሚገባው ፍቅር ፥ ከመልከ ቀናነትና ከአካል ውበት ብቻ የመነጨ ወይም በወጣቶች ዘንድ አብዛኛው ጊዜ እንደሚ ታየው ሁሉ በአጋጣሚ ስሜት የመጣ መሆን የለበትም ፤ ኃይለኛና የማይፈታ ስሜት እንዲሆን ያሻል ። የሚወድ ሰው በቀጥታ የሚፈልገው ከስሜቱ በሚፈልቀው ደስታ ራሱ ተድላን ለመሸመት ሲሆን የሚወደውንም ፍጡር በተ ድላው ውስጥ ለመጠቅለል ነው ። የሚያፈቅረው ሰው ደስ ካላለው እሱን ደስ ሊለው አይችልም ። በዚህም የተነሣ የሚያፈቅረውን ፍጡር ይጠብቀዋል ፤ ያከብረዋል ። ስለ ዚህ በራሱ ላይ ያደረውን ፍቅር ሰውዬውን ከሚወድበት ፍቅር ሊለየው አይችልም ። እኔና አንተ መባባል ይቀርና እ ኛ የሚሉት ቃል ይተካል ። በዚህ ጊዜ ፍቅር ፍጹም የደ ስታ ምንጭ ይሆናል ፤ መንፈስም ሳይቆጠብ ወደዚያው ያ መራል ።

3. ሕብረሰባዊ ሁኔታ ፡— ነገር ግን የስሜት ኃይል ማንኛውም ቢሆን ፥ ወሳዋይነትን ስለማያጣ የቤተሰብን እ ድል በሱ ላይ ብቻ ለመመሥረት አያስተማምንም ። ስለ ዚህ ጋብቻ በሕብረሰብ እንዲመዘገብና በሕዝባዊ ሥልጣ ንም እንዲታሸግ ያስፈልጋል ። ማንኛውም ሰው ከራሱ (ከደካማነቱ) የሚጠብቀው መተማመኛ ማዘጋጀት አለ በት ፤ ማንኛውም አቅዋም በተለይም ቤተሰብን ያህል ነገር

በመልካም ፈቃድ ላይ ብቻ ሊገነባ አይችልም ። ለቤተሰብ ደንበኛ ኑሮውን የሚያረጋግጥለት ሁኔታ ጋብቻ በሕዝባዊና በሥርዓታዊ ሥልጣን ፊት ሲመዘገብና ምሕላን ግዴታ ሲያስረው ነው ። ደግሞም ከፍ ያለ ከባድነት ባለው በዚህ ውል አፈጻጸም ሕብረሰብ ዳር ሆኖ ሊመለከት አይችልም ። እንዲያውም በተለይም ለክርስቲያናዊ ሕሊና ፥ ሕብረ ሰብ ዓዊ ውሳኔ በቂ መስሎ አይታየውምና በሕዝባዊ ሥርዓት ላይ መንፈሳዊ ሥርዓት በማከል ጋብቻን የማይደመስስ ያደ ርገዋል ።

4. ሞራላዊ ሁኔታዎች ፡— ያለፉት ሁኔታዎች የተቻ ላቸውን ያህል የሚያስተማምኑ ቢሆኑም ፥ ሞራላዊ ግዳጆች ካልተጨመሩባቸው በቂ ሆነው አይገኙም ። የቤተሰብን ሥርዓት ለሰብዓዊ ወግ የሚያበቃው ሞራላዊነትና ፥ ሞራ ላዊ ጸጋዎች ናቸው ፤ በዚህ መሠረት ጋብቻ የተማማኝነትን ምህላ ፥ ተግባር የመከፋፈልን ቃልኪዳን ፥ በጐና ክፉ እድ ልን የመጋራትንና ኑሮ የተባለውን ከባድ ሸክም ፥ እመል ካም ፍጻሜ የማድረስን ሞያ ፥ ሁለቱም ወገኖች እንዲቀበሉ ያስገድዳል ፤ ማለትም አንዱ ከአንደኛው ሁሉን ይሰጠኛል ብሎ በመጠበቅ ፈንታ ፥ በማንኛውም ጊዜ ለማገልገል ፥ ለማክበርና ለማስደሰት በአደራ እንደተቀበለው ነገር ሊቆ ጥረው ይገባል ፤ ጋብቻ ተዘጋጅቶ የሚገኝ ነገር አይደለምና ትዳራቸውን ማደራጀት የተጋቢዎቹ ፈንታ ነው ። ዝናብን እንደሚጠብቅ ሰው ሁሉ ከጋብቻ የሚፈልቀውን የተድላ ኑሮ ፥ እጅን አጣምረው ቢጠብቁ አንድ ጠብታም አይደ ርስ ። ተድላን በጸጋ ማግኘት ያስፈልጋል ።

ጋብቻ የማይፈርስ መሆን አለበት ፡—

በመጨረሻዎቹ መስመሮች የተዘረዘረው ጋብቻ ዕድሜን በሙሉ እንዲያበረክቱለት የሚጠይቅ መሆኑንና ከሞትም በቀር ሌላ ነገር ሊፈታው እንደማይችል ያስገነዝበናል ። ስምምነት በታጣ ጊዜ ከሚፈርስ የንግድ ውል ጋር ልናመሳስለው አይገባም ፤ ጋብቻ ነዋሪና የማይፈታ ሲሆን ፍሬ ሊያስገኝና ወደ ተመደቡለት ዓላሞች ሊደርስ ይችላል ። የሁለቱን አማኞች ጋብቻ የሚያሸገው ቡራኬ የማይጠፋ ስለሆነ መንፈሳዊ ግቡ ይደርሳል ፤ ፈቅዶ ራሱን የሰጠው ሰው ክብርና በፈቃዱ የገባው ግዴታ ሊጠበቁ የሚችሉት በመቆየቱና ለመሠረዝ ባለመቻሉ ስለሆነ ጋብቻ ሞራላዊ ዓላማው ይደርሳል ።

የጋብቻ ሕያውነት ለሰው ማሕበር ኃይልና ሥርዓታዊ መሠረት ስለሚሆን ሕብረሰባዊ ዓላማ በዚህ ይፈጸማል ። ጋብቻ ራሱ ብዙ የሥጋ ዝምድናዎችና ፥ ሕጋዊ ሁኔታዎች ስለሚፈጥርና ፥ ማፍረሱም የተገነባውን ወግ ፥ በሙሉ ስለሚያናውጸው የጋብቻ ሕያውነት ሕጋዊ ዓላማውን በሚገባ ያስፈጽመናል ። በተረፈ የሕብረሰብ ጤናማ አቅዋም የሚገኘው በጋብቻ ቋሚነት መሆኑ የማይጠረጠር ነው ።

መፋታትና ጉዳቱ ፡—

መፋታት ዘወትር ታላቅ ጉዳት የሚያመጣ ድርጊት ነው ። የሚፋታ ሰው ቤተሰብ ለማቋቋም ፈቅዶ የጀመረውን ግብርና በማፍረሱ ራሱን ከዳ ማለት ነው ። ልጆቹንም በሥርዓት ሊያድጉ ከሚችሉበት አካባቢ በማራቁ በመከራ

ውስጥ ይጥላቸዋል ። የገባውን ቃልኪዳን ባለማክበሩ በሕብረሰብ መሠረታዊ ግብ ላይ ብጥብጥን ይፈጥራል ። መፋታት በሚበዛበት አገር ሕብረሰባዊ በሽታ ለመግባቱ ምልክት ነው ።

ጋብቻና ሕግ ፡—

ይህን ሁኔታ ስንመለከትና መፋታት የሚያስከትለውን ጉዳት ስናስተውል ፥ ሕግ ጋብቻን ጽኑ ማድረግና የመፋታትን መንገዶች ሁሉ መዝጋት እንዳለበት ይሰማናል ። አብዛኛውን ጊዜ አንድ ነገር የተከለከለ መሆኑ ሲታወቅ የማድረጉም ሃሳብ ከመንፈስ ይርቃል ። መፋታት በቤተሰብ ልብ የሚያድረው የተፈቀደ ነገር መሆኑ ሲታወቅ ነው ። ለመፋታት ምቹ የሆነ ሕግ የሰውን መንፈስ ያታልላል ። የመፋታት ችሎታ መኖሩን የሚያውቁ እጮኞች ለጋብቻ የሚያስፈልገው ሁኔታ ሁሉ ሳያድርባቸው ፥ ባይሳካ እንኩ ታለን በሚል መንፈስ አጥልቀው ሳያሰላስሉ ይጋባሉ ፤ የዚህ ዓይነቱ ጋብቻም ፍሬ እንደማይሰጥ የተረጋገጠ ነው ። በየትንንሹ ምክንያት የመፋታት አሳብ በፊታቸው ይደቀናል ። ከሁሉም ይልቅ የሚያሳዝነው የመፋታት መብት መኖሩ ሲታወቅ ፥ የጋብቻ ወግና ክብር እየተዋረደ መሄዱ ነው ። እጮኞች ጋብቻን እድሜ ልክ እንደሚያስር ታላቅ ሥርዓት በመቁጠር ፋንታ ፥ ተፈትኖ በፈለጉ ጊዜ ሊተውት እንደሚቻል ሙከራ ይቆጥሩታል ። እርግጥ ነው ማንኛውም መንግሥት ፥ እጅግ ከባድ ሁኔታዎች በተፈጠሩ ጊዜ (ለምሳሌ ታማኝነት ማጉደል) የመፋታት ችሎታ ጨርሶ እንዲከለከል አያደርጉም ፤ ቢሆንም ይህ ፈቃድ ታስቦበትና በጥን

ቃቄ ተጠንቶ ነው እንጂ እንዲሁ በቀላሉ መሰጠት የለበትም ። መፋታት የተለመደ እንደሆነ ጋብቻና ቤተሰብ የሰው ማሕበር ከነሱ የሚጠብቀውን ግዳጅ ሊፈጽሙ አይችሉም ።

የሴት ግዳጅ ፡—

በሞራላዊ አካልነት ወንድና ሴት እኩል መሆናቸው ግልጽ ቢሆንም ተፈጥሮ አንድ ዓይነት ሕብረሰባዊ ዓላማ አልሰጣቸውም ። ወንዱ ቤተሰብን መጠበቅና ሉኑሮው የሚያስፈልገውን ሁሉ ማቅረብ አለበት ፤ ሴቲቱ ፥ የእናትነት ተግባርና ጕጆን የማስተዳደር ተግባር አለባት ። በቀድሞ ጊዜ የወንድዬው ሥልጣን እጅግ ከፍ ያለ ነበረ ። ዛሬም የቤተሰቡ ሹም ነው ። በሴቲቱና በልጆቹ ላይ ሥልጣን አለው ፤ የቤተሰቡን መኖሪያ የሚወስንእሱ ነው ፤ ሃብቱን የሚያስተዳድርና በሕግ ፊትም ተጠሪ ወንዱ ነው ። ነገር ግን ሴት በየጊዜው መብቷ እየተሻሻለላት በመሄዱ ልዩ ልዩ ሥልጣን ተቀዳጅታለች ።

ለምሳሌ ፥ በልጆቹ ላይ ያላት ሥልጣን ፥ የሃብት ተጋሪነት ፥ በደሞዝዋ የማዘዝ ሥልጣን ፥ የተለየ ሃብት ማበጀት ፥ ትምሕርት ማግኘት ፥ የመንግሥት ሥራ እኩል ለመያዝና ፥ የመምረጥና የመመረጥ መብት (ፖለቲካዊ ኑሮ) በነዚህ ውስጥ ይቆጠራሉ ። በመሠረቱ የሴትን መብት መጠበቁ ጠቃሚ ድርጊት ሆኖ ተገኝቷል ።

ወንድ ጉልበት አለውና ብዙ ሺ ዘመን ሲያደርግ እንደኖረው ሁሉ ፥ ሴትን እንዳያጉላላና ሞራላዊ መብቷን እንዲጠብቅ ግዳጅ ነው ። ይህም ሆኖ ሴት የተቀደሰ ተግባርዋ

እናትነት መሆኑን መዘንጋትና በሕብረሰብ ኑሮ ከወንድ ጋር በመፎካከር ቤቷንና ትዳርዋን መርሳት የለባትም ። ልጆቿን ማሳደግ ፥ ቤቷን መጠበቅ ፥ ክብርዋንና ስሟን ከፍ ማድረግ የማይሠረዝ ተግባርዋ ነው ። በሥርዓትና በቁጠባ በመኖር የቤተሰብ ሃብትና ተድላ እንዲያድግና እንዲስፋፋ ለማድረግ የምትችል እሷ ነች ፤ ቤት የሚፈርስም ፥ የሚለማም በሴት ነው ።

ልጅና ቤተሰብ ፡—

የቤተሰብ ዋና ዓላማ ልጆች መውለድ ነው ፤ እዚህም ላይ ሞራል ተፈጥሮን ይከተላል ። የቤተሰብ ተግባር ፥ ሕይወትን ማስተላለፍ ፥ በጊዜ ውስጥ የሰው ዘር እንዲዘልቅ ማድረግ ፤ ሕብረሰብን ማደራጀት ነው ። ልጆች የሌሉት ቤተሰብ ፥ ሰብዓዊና ሕብረሰባዊ ተግባሩን አልፈጸመም ፤ በአካልም በሞራልም ጐዶሎ ነው ። ሰው አንድ ልጅ ሲወልድ ሕሊናው ይለዋወጣል ፤ ግለሰብ አለመሆኑንና ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ እስኪያልፍ ድረስ አብሮት የሚኖረው ሰንሰለት አንዱ ቀለበት እሱ መሆኑ ይሰማዋል ። በቤተሰብ ውስጥ አዲስ ስሜቶች ፥ አባታዊ ፍቅርና በተለይም ግሩም የሆነው የእናት ፍቅር ይፈጠራል ። ሴቲቱም በፍጹም መንፈሷ ይቀየራል ፤ ባለፉት ገጾች እንዳልነውም ሰው የሚሰዋው ለሚወደውና ለሚያፈቅረው ነገር ነው ። ሕብረሰብ ሊኖር የሚችለው ፥ ልጆቻቸውን ለመመገብ ፥ ለማልበስ ፥ ለማባበል ፥ በየቀኑ እናቶች የሚያደርጉት መስዋእትነት ፥ በሚያበረክተው ጸጋ ነው ። የነዚህ የአዲስ ስሜቶች መፈጠር ቤተሰብን ይበልጥ ያስተሳስራል ። ቀድሞ የነበሩትንም ስሜቶች

ያጠነክራል ። ሚስቲዮዋም ባልዋን የሕይወት ጓደኛው ብቻ ላይሆን የልጆችዋ አባትም አድርጋ ትመለከተዋለች ። እንዲወዱ ፡ ለጤናቸውና ላስተዳደጋቸው እንዲያስቡ ፤ በየደቂቃው ለነሱ እንዲጨነቁላቸው ልጆች አባትና እና ትን ስለሚያስገድዱ በግዴታ ያቀራርቧቸዋል ።

የልደት ሁኔታ ፡—

ዳሩ ግን የቤተሰብ ተግባሮች በብዙዎች ዘንድ ባለመ ፈጸማቸው ፡ በሰብዓዊ ፡ በሕብረሰባዊ ፡ በሕዝባዊና በሞራ ላዊ ረገድ ከፍ ያለ ጉዳት ያስከትላል ። አገራችን ኢትዮጵያ የሕዝቧ ቍጥር አነስተኛ መሆኑን በመጽሐፉ በመጀመሪያ ው ክፍል ገልጨዋለሁ ። ይህን ሁኔታም የሚያስከትሉት አብዛኛውን ጊዜ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ናቸው ፤

1. ሰው ባለገሩን እየተወ ወደ ከተማ በመሰብሰቡ ፡ የከተማም ኑሮ ቍጥሩ በዛ ላለ ቤተሰብ ስለማይመች ፡ በባላ ገሩም ልጆች ለቤተሰብ ረዳት ሲሆኑ በከተማ ግን ለቤተ ሰብ ሸክም ስለሆኑ ፡—

2. የጨዋታና የቅብጠት ስፍራዎች ብዛት ሕዝቡን ከቤተሰባዊ ኑሮ ስለሚያርቀው ፤

3. በመጭው ላይ እምነት በማጣት የተነሣ ለረጅም ጊዜ አስቦ ከመነሣት ይልቅ ሕዝቡ ለዛሬ ብቻ ስለሚያስብ ፤

4. የሕይወትን ከባድ ተግባሮች ከመፈጸም ይልቅ የሚመችንና የሚያስደስትን ኑሮ ብቻ በመምረጥ ፡ ለዚህም ዓይነት ኑሮ የልጆች መኖር እንቅፋት ስለሚሆን ፤ እነዚህ ሁኔታዎች በአገር ላይ ብዙ ጉዳቶች ያስከትላሉ ፡ ለምሳሌ ፤

1. የሕዝብ ማነስ ከሌላ አገር ጋር በማንኛውም ጊዜ እኩል ለመቋቋም ያስቸግራል ፤

2. የባላገሩ መሬት እዳሪ ሆኖ በመቅረቱና መንደሩ ባዶ በመሆኑ የምድሪቱ ሃብት ተቀብሮ ይቀራል ።

3. በሕዝቡ መካከል ከወጣቱ ይልቅ የሽማግሌው ቍጥር ስለሚበዛ ሕዝባዊ ድልድልና የአገር ኃይል ይጠፋል ።

4. የቤተሰብ መንፈስ ይፈጥረውና ይጠብቀው የነበረው የጸጋ ባሕርይ ይቀነሳል ።

ለዚህ መድኃኒቱ ፡—

1. ልጆችን የሚገድሉትን ጠንቆች በማጥፋት የሚወለዱት ሕጻናት ሁሉ በሕይወት እንዲቆዩ ማድረግ ፤ (የሕጻናት ጽዳት ጥበቃ ፡ አመጋገብ ፡ ወተት)

2. የቤተሰብን አካላዊ ኑሮ ማቃለል ፡ ልጅ መውለድ ሸክም እንዳይሆን በሚገባ መርዳት ፡ በተለይም በአዲስ ትዳር ላይ የልጆች መወለድ ከባድ የገንዘብ ሸክም እንዳያመጣ ማድረግ ፡ የመገላገያና የመታከሚያ ሆፒታሎች በር ካሽ ዋጋ ማቋቋም ።

3. ኤሌትሪክ ፡ መገናኛና የመሳሰለውንም በማስገኘት የባላገርን ኑሮ ተወዳጅ ማድረግ ፤

4. በሕዝቡ መንፈስ ብዙ ልጆች ያሉት ቤተሰብ ክብር እንዲያገኝ ማድረግ ፤ ለምሳሌ ፡ ብዙ ልጆች ላሏቸው ቤተሰቦች ቤት አናከራይም የሚሉትን መምከር ፤

5. የሞራልን መንገድ በመከተል ደግሞ ፥ ሰው የሕይ ወትን ተግባር በሙሉ እንዲቀበል እንጂ የሚመቸውን ብቻ ወደመሳተፉ እንዳያደላ በትምሕርት ማሳመን ።

ስለምድር ልግሥና ፥ ስለባላገር ቤተሰብ ቴሌማክ ከተ ባለው ድርሰት የተቀዱ ጥቂት መስመሮች እናንብብ ።

«ምድር የሚኖሩባትን ሰዎች ለማበልጸግ የምትመኝ እናት ናት ፥ ጭንቀቷ ሰው ስታጣ ብቻ ነው ። ምድር መ ቼም ቢሆን ውለታቢስ አይደለችም ፤ በጥንቃቄና በትጋት ለኰተኰቷት ፍሬዎችዋን ትመግባለች ፥ ሥራን ለሚጠ ሉና ከድካም ለሚርቁ ግን ሃብቷን ትነፍጋለች ።»

«ባላገር ልጆቹ እየበዙ ሲሄዱ ፥ ሃብቱም በዚሁ መጠ ንይበዛል ፤ ልጆቹ ከሕጻንነት ጀምሮ ይረዱታልና ፥ ትንን ሾቹ በጐችን ያሰማራሉ ፥ ከፍ ያሉትን መንጋ ያግዳሉ ፤ ትል ልቆቹ ደግሞ አባታቸውን ፥ በእርሻ ይረዱታል ።»

የባላገር ቤተሰብ ልጆቹ አይከብዱትም የተባለው ስለ ዚህ ነው ።

<u>ወላጆች ስለልጆቻቸው ያላቸው ተግባር ፤</u>

በምድር ላይ ከሚገኙት ተግባሮች ከዋናዎቹ አንዱ ወላጆች በልጆቻቸው ረገድ ያላቸው ተግባር ነው ። የመጪ ውን ጊዜ ሰዎች ማዘጋጀት ስለሆነም የአላፊነት ስሜት ከፍ ብሎ ይሰማል ። ልጅ መውለድ ወዲያውኑ ግዴታ ያስከ ትላል ። ቤተ ሰብም የሕብረሰብ ምንጭ ስለሆነ ሕዝባዊ ሥልጣኖች ባላቸው አቅም እንዲረዱት ያስፈልጋል ። ወላ

ጆች የልጆቻቸውን ሞራላዊ ጤና ማደርጀት ስላለባቸው ፥ ዘወትር የሕጻናትን አነጋገርና ድርጊት መከታተልና መጠ ባበቅ ዓይነተኛ ተግባር ነው ፤ ሰዎችን ፤ በተለይም ሕጻናትን ለመምራት ደግሞ ለነሱ በፍጹም የታረመ ጠባይ ማሳየት ያስፈልጋል ። ምሳሌነትን የመሰለ ብርቱ ነገር የለም ፤ ያለ ምሳሌም ትምሕርት ሊኖር አይችልም ፤ የመልካም ምግባር ደንቦች ምቹና ወጣቶችም በቀላሉ ሊቀበሏቸው እንደሚ ችሉ ሆነው የተሠሩ ናቸው ፤ ነገር ግን አስገዳጅ ካልሆኑ ዋጋ የላቸውም ። አስገዳጅም ለመሆን ፤ በአእምሮ ውስጥ እንዲቀረጹ ያስፈልጋል ። አንዲት ቅድስት እንዲህ ብላ ለች ፥

«የእናታቸውን ምሳሌ በመከተል ጸጋንና ጨዋነትን ለመሸመት የቻሉ ልጆች የታደሉ ናቸው ። ፍቹም ከጨዋ እናት የመወለድ እድል የገጠማቸው ማለት ነው ።»

የዚህን ዓለም ኑሮ ጥሩ መንገድ ለማሲያዝ የሚቻለው እንደዚህ ያሉትን ምሳሌዎች በማውረስ ነው ፤ በልጆች መን ፈስ ውስጥ የመምሰል ባሕርይ እጅግ የተዘረጋ ስለሆነ ፥ እን ደፈጣሪ ከሚቆጥርዋቸው ከወላጆቻቸው የሚወስዱት ም ሳሌ ፥ የሞራላዊ ሕይወታቸው መመሪያ ይሆናል ።

ሕጻናቶች ከጥቂት ጊዜ በኋላ ፥ ከሕይወት ችግሮች ጋር የሚጋፈጡ ሰዎች እንደሚሆኑ በመገንዘብ ፥ ወላጆች የልጆ ቻቸውን አስተዳደግ መጠበቅና ፥ ስሜትና ጠባያቸውን መ ልክ መስጠት ከተግባራቸው አንዱ ነው ። ከሁሉም ይልቅ በልጅ ዘንድ የአላፊነትን ስሜት ማስፋፋትና የእለት ጉዳ

ዮቹን ሁሉ ራሱ እንዲፈታቸው ማድረግ አስፈላጊ ነው ። ልጅ ለራሱ አገልጋይ መሆን ፥ ማለትም አልጋውን ማን ጠፍ ፥ ዕቃውን መደርደር ፥ በቤት ሥራ መካፈል ማጥናት አለበት ፤ ራሱን በመጠበቅ ፥ ጠንቃቃነትንና ትክክለኝነ ትን ከመልመዱም በላይ እያንዳንዱ ሰው ያንድ ሰው ሥራ ሊያፈራ ከሚችለው በላይ ፈላጊ መሆን እንደማይገባው ይረዳል ።

በተረፈ ወላጆች ልጆቻቸው እንዲማሩ ማድረግ ታላቅ ግዳጃቸው ነው ። አንዳንዶቹ ልጆቻቸውን ራሳቸው ለማስተ ማር ይፈቅዳሉ ። ነገር ግን የወለደ አንጀት በርሕራሄና በአ ድላዊነት እየተመራ ለልጁ ችሎታ ትክክለኛውን ፥ ግምት መስጠት ስለማይችል የማያውቀውን አወቀ እስከ ማለት ስለሚያሳስት ፥ የማስተማርን ሥራ ለአስተማሪዎች መተው የተሻለ ነው ። በመሠረቱ የወላጆች ተግባር ሥርዓት ማስያ ዝና መጠባበቅ መሆኑ ነው ፤ የቤተሰብን ኑሮ ለልጆች ትም ሕርት እንደማያውክ አድርጐ ማደራጀት ፥ ልጆች በተወ ሰነ ሰዓት እንዲሠሩና ወላጆች አስተማሪዎችን ለመርዳት ፤

1. የልጆቹን ጤና መጠበቅ ፥ 2. በጸጥታ ለመሥራትና ለማጥናት የሚችሉበት ጊዜና ሥፍራ በቤት ውስጥ ማዘጋ ጀት 3. በእረፍት ሰዓት እንዲያርፉ ፥ በሥራ ሰዓት እንዲ ሠሩ ማድረግ ፥ 4. ተግባራቸውን ወዲያውኑ እንዲፈጽሙ እንጂ ለነገ እያሉ እንዳያሳደሩ መከልከል ፥ ለዚህም የሚያ ቀርቡትን ምክንያት አለመቀበልና ተግባራቸውን እስኪፈ ጽሙ ድረስ መጠበቅ ነው እንጂ መቆጣት አይጠቅምም ። 5. ለሥራ በተወሰነላቸው ሰዓት እንዲሠሩና ይህም ሁኔታ

ልማድ ሆኖ እንዲቀር ሰዓቱን በየጊዜው አለመለዋወጥ ፥ በጠቅላላው እነዚህ አምስት ነገሮች ይጠቅማሉ ።

ልጆች በወላጆቻቸው ረገድ ያላቸው ተግባር ፤

ልጆች የቤተሰቡ አላፊ ለሆኑት ለወላጆቻቸው (ለዘመ ዶቻቸው) ፍጹም ታዛዥ መሆን አለባቸው ። ከወላጆቻ ቸው ለሚቀበሉት ፍቅርና ጥበቃ መልስ ፥ ወላጆቻቸውን መውደድና ውለታቸውን ማስታወስ አለባቸው ። ልጆች ወላጆቻቸውን በማፍቀርና ከልክ በላይ ባለማስቸገር ፥ የኑ ሮን ፈተናዎች እንዲያሸንፉ ሊረዷቸው ይችላሉ ። በተለ ይም ወላጆች ባረጁ ጊዜ መጠበቅ ፥ መጦርና የሚያስፈልጋ ቸውን ነገር ሁሉ እንዲያገኙ ማድረግ የልጆች ቅዱስ ተግ ባር ነው ።

ልጆች እርስ በርሳቸው ያላቸው ተግባር ፤

መልካም አስተዳደግ የሚገኝ ልጆች በበዙበት ቤተ ሰብ ነው ። አንድ ልጅ ለቤተሰብ ኦይበቃም አስተዳደጉም ሞልቃቃ መሆኑ አይጠረጠርም ፥ የወንድማማቾችና የእሕ ትማማቾች ማሕበር እንዲኖር ፍጹም አስፈላጊ ነው ። በዚህ ኦኳኋን ሕጻኑ እኔ ብቻ ነኝ ፥ ሁሉም ለኔ ይገባኛል ማለትን ይተውና የትክክለኝነትና የመረዳዳት መንፈስ በልቡ ያድ ራል ። በተሰይም አባት ወይም እናት የሞቱ እንደሆነ ታላ ቆች ለታናሾቻቸው የሚሆኑት ነገር ይጠፋቸዋል ። የአላ ፊነት ኦሜት በልባቸው ይፈካል ።

የሚያስታውሱት አንድ ዓይነት ነገር ፥ አንድ ዓይነት ሰዎች ፥ አንድ ዓይነት ታሪክ ፥ ኦለሆነ ፥ ያንድ ቤተሰብ ል ጆች በዘመነ ሕይወታቸው በሙሉ ሊለያዩ አይችሉም ።

የወንድማማችነት ጠባይ የሚጠናው ብዙ ልጆች ባሉት ቤተሰብ ነው ፤ ቀጥሎም የሰውን ዘር ሁሉ ወንድም ለማድረግ የሚችሉት በቤተሰብ ባገኙት ትምሕርት ነው።

ስለሁለት ወንድማማቾች ንግግር አንድ ደራሲ የጻፈውን እንመልከት ።

—«እጅ ለእጅና ልብ ለልብ ተያይዘን አብረን አደግን ፥ አብረን አረጀን ፥ ዛሬ አዋቂ ሰዎች ሆነናል ፤ ነገር ግን ፥ ክብሩ ይሰፋ የልጅነት ባሕሪያችን አለቀቀንም ። ምሳችን ባንድ አገልግል ይዘን ፥ ወደተማሪቤት እንጓዝ የነበረው እነዚያው ወንደ ማማቾች ነን ፤ ችግራችንም ፥ አሳባችንም ፥ ደስታችንም የሚይለያዩ ነበሩ ። ያንዳችን ሐዘን አንደኛችንን ያስለቅሰዋል ፥ ያንዳችን ደስታ አንደኛውን ያስፈነድቀዋል ፤ ተለያይተን ማንኛውንም ነገር ፥ እድልንም ቢሆን ፥ ሞክረን አናውቅም ፥ ጠባዮቻችን ምንም እንኳን የተለያዩ ቢሆኑ ፥ ተሳሳሪና ተሶማሚ እንጂ ተቃዋሚ ሆነው አያውቁም ። ፍላጐታችን ፥ ምኞታችን ፥ አምሮታችን ዘወትር ተመሳሳይ ነበሩ ። እሱ ለኔ መካሪዬ ነው ፤ እኔንም እንደመሪው ይቆጥረኛል ፤ ጉድለቶቹን ያውቃቸዋል ፥ ግን አይቶብኝ አያውቅም ፤ ዮሕተቶቼን እንዳርም ይረዳኛል ፥ ተሳስተሃል ብሎኝ አያውቅም ።

ስለዚህ በሰዎች ፊት የሚረዳኝ ፥ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚጸልይልኝ ወዳጅ እንዳለኝ ይሰማኛል ። ምኞቱ ሁሉ እኔን ደስ እንዲለኝ ነው ፤ እኔን ደስ እንዲለኝ መስዋዕት ለመሆን አይመለስም ። ብልጽግናዬን ሲያይ ትፍስሕት ይሰማዋል ፤ እድል ባጣሁም ጊዜ አይለየኝም ። ለጥፋቴ ሁሉ ይቅርታ ያደርግልኛል ። በተጐዳሁም ጊዜ ያስተዛዝነኛል ፤ እሱ የወንድም ጓዴ ነው ፥ እኔም ለሱ እንደዚሁ ነኝ ፤ ይህ ታላቅ ጌትነት በልባችን ሙሉ ይሰማናል ። የትም ብንሄድ ተለያይተን ደስ ሊለን አይችልምና እግዚአብሔርንም የምንለምነው ፥ አብረን እንድንኖር ፥ አብረን እንድንሠራ ፥ መከራንም አብረን እንድንችል ነው ። አንድ ዓይነት ደም ፥ አንድ ዓይነት ልብ ፥ አንድ ዓይነት ተግባር የሰጠን አምላክ ፥ እረፍታችንንም ባንድ ስፍራ እንዲያደርግልን ለማያልቀው ርሕራሄው ጸሎታችንን እናደርሳለን» ።

እነዚህ መስመሮች የወንደ ማማችነትን ስሜት እከፍ ተኛው የፍቅር ደረጃ አድርሰው አሳይተውናልና ምሳሌ እንዲሆኑን ተሶፋ እናደርጋለን ።

<u>ቤተሰብ ፥ በሕብረሰባዊና በሞራላዊ ኑሮ ፡—</u>

ታላቅ መብትና ታላቅ ዋጋ ያለው የቤተሰብ ኑሮ በሕብረሰባዊና በሞራላዊ ሕይወት ላይ ከባድ አመዛኝነት አለው ። የሕብረሰብን አባሎች (ሰዎችን) የሚመለምልና ላቅመ ኦዳምም እሶ ኪደርሱ ድረስ የሚጠብቅና የሚያሳደግ እሱ ነው ፤ የሃይማኖትን ፥ የአኗኗርን ልማዶች ኦቆይቶ ለመጭዎች በማስተላለፍ የአገር ባሕል እንዳይጠፉ የሚያደርግ ቤተሰብ ነው ። ያንድ ሕዝብ የሥልጣኔ ደረጀና ኦረማመዱ የሚገመተው የቤተሰቦቹ የመንፈስ ጥንካሬና የሕዝቡም በዚህ ረገድ ያለው ጽኑ እምነት ፥ የቱን ያህል እንደሆነ በመገንዘብ ነው ። ተፈጥሮና ሞራል የሚዋሃዱበት ፥ ሰብዓዊ ፍቅር የሚጠቃለልበት ፥ ተስፋን የሚቀሰቅሱት ስሜቶች የሚፈልቁ

ብት በቤተሰብ ኑሮ ነው ። በነዚህ ስሜቶች ገፋፊነት ፥ ሕይ ወት በየጊዜው በሚጠይቀው ግዳጅ ፥ በአላፊነት ጐትጓችነ ትና በየቀኑ የሚፈጸመውን ሁሉ በማስተዋል ፥ ተግባር ወሬ መሆኑ ይቀርና ተፈጻሚነትን ያገኛል ።

ሰው ጥልቅ በሆነ በዝምድና ፍቅር ተከቦ ፥ ሳያስብ በት ሳይቸገር ጨዋነትንና ጸጋን የሚያጠናና የሚማረው በቤተሰብ መካከል ነው ።

<u>ቤተሰባዊ ስሜትን ስለመኰትኰት ፡—</u>

በቤተሰብ ውስጥ በሚገኘው ዕለታዊ ትምሕርት እየተ ጠቀመ ሰው ቀስ በቀስ ለሕብረሰባዊ አባልነት ይዘጋጃል ። መጀመሪያ ከቤተሰቡ አባሎች ጋር በመለማመድና በመተ ባበር የሚሸምተው ስሜት በዝግታ እየተዛመተና እየተስ ፋፋ በጠቅላላ ከሰው ዘር ጋር ለሚያደርገው ግንኙነት በሚ ጠቅም ስሜት ይለወጣል ።

የአባትን የበላይነት መብት በመቀበል ፥ መታዘዝን ይማራል ፤ በወንድሞቹና በሕቶቹ ላይ ያለው ስሜት ወደ አገሩ ልጆች ይተላለፋል ። ነገር ግን የነዚህን ስሜቶች ጣዕ ምና መልክ ለይቶ ለማወቅ ፥ አስቀድሞ ልጆቹንና ወንድሞ ቹን እየወደደ መማር አለበት ፤ ያንድ ቤተሰብ አስተዋይ ነት በልጆቹ ጠባይ ይገመታል ይባላል ። ቤተሰብ ለሞራላዊ ግብርና ከሁሉ የተመቸ ሥፍራ ነው ። ሆኖም ሞራላዊ ግብ ርና አውቆ ሊፈጸምና ሊከናወን ኦይችልም ። ተፈጥሮ የተ ከለው ችግኝ በመልካም ፈቃድ ካልተኰተኰተ ሊያብብ አይችልም ፤ በቤተሰብም ሆነ በሕይወት ገበታ ሰው ለማ

ምረት የሚችለው በዘራው መጠን ነው ። ቤተሰብ ሊኖር የሚችለውም በጨዋነትና በጸጋ ላይ ሲመሠረት ነው ። ቤተ ሰባዊ ስሜቶች የሚያስከትሉትን ተግባር መፈጸም ያሻል ፥ አለዚያ የእናት ፍቅርም ጠቃሚ ሊሆን አይችልም ። መው ደድ ራሱ ብቻውን በቂ አይሆንም ፤ ሰዎች ሊረዳዱ የሚች ሉበት ከቤተሰብ የተሻለ ቦታ በምድር አይገኝም ፤ ነገር ግን የቤተሰብ አባሎች በኃጢአትና በመጥፎ ጠባይ የተመሩ እንደሆነ የመከራና የጥፋት ስፍራ ሊሆንም ይችላል ።

እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል አድራጐቱ የሚያስከትለ ውን ነገር ሁሉ አስቀድሞ ማወቅ አለበት ፤ በዙሪያው የሚ ያጋጥሙትን የኑሮ እሾኾች ዕለት በዕለት መንቀል ይገባ ዋል ። ሕብረሰብም ደግሞ ፥ ቤተሰብን መጠበቅ ፥ ሕሊናው ውን ፥ እድገቱንና ሰላሙን ማረጋገጥና እንደዚሁም ለማሕ በራዊ ኑሮ አስፈላጊ ስለሆነ የቤተሰባዊነትን መንፈስ በማን ኛውም አኳኋን ማነቃቃት አለበት ። ቤተሰብ ለማለሰብ ሞራላዊ አስተዳደግ ፥ አስፈላጊ ጣቢያ ነው ። ጣቢያ ነው ስንልም ግብ አይደለም ማለታችን ነው ። ምክንያቱም ከቤ ተሰብ በላይ ከሱ የሰፉ አቅዋሞች ስላሉና ቤተሰብ ለነዚህ አቅዋሞች ተገቢ ሆኖ ለመገኘት የሚያዘጋጅ ስፍራ ስለ ሆነ ነው ። በቤተሰብ ኑሮ የተገኘ ማንኛውም ፍሬ ነገር ለማ ሕበራዊ ኑሮ እንዲውል ካልተደረገ ደግሞ ፍሬ ነገሮቹ ለእ ውነተኛው ዓላማ ዋሉ ለማለት በፍጹም አስቸጋሪ ነው ።

ም ዕ ራ ፍ 6

ሞራልና ፖለቲካዊ ኑሮ አገር ፡—

ባለፉት ገጾች እንዳልነው ሁሉ ፣ ቤተሰብ ያንድ ሰፊ የሆነ ማሕበራዊ ድርጅት ክፍል ነው ። የሕብረሰብ እውነ ተኛው ሕይወታዊ ሕዋስ ፣ ስለሆነም ፣ እንደማንኛውም ሕይ ወታዊ ሕዋስ ቅስቃሴና ሕይወት ከሚሰጠው አካል ተነ ጥሎ ሊኖር አይችልም ።

ሁላችንም ኢትዮጵያውያን መሆናችን ይሰማናል ፣ በዚህም የተነሣ ከባዕድ አካል ፣ በአሐዱነት በሚከላከል ባንድ አካል መዋሃዳችንና ተባባሪዎች መሆናችን ይታወቀ ናል ።

ሰዎች ከሚያቋቁሟቸው ሕብረቶች ሁሉ ዋናቹ ቤተ ሰብና አገር መሆናቸው በአዋቂዎች ዘንድ ብዙ ጊዜ ተነግ ርዋል ።

አገር ማለት ምንድነው ? ኢትዮጵያ ለኛ ምናችን ናት ? አገር መጀመሪያ የተመሰረተችው ዘላን የነበሩ ሕዝቦች ባንድ ስፍራ ላይ መቀመጥን ለምደው መኖሪያ ያደረጉትን ምድር መውደደና ፍቅሩም በመሬትዋና በልብ ውስጥ ስር መስደድ ከጀመረ በኋላ ነው ።

መሬቷ ፡—

አገር ፣ ከሁሉ አስቀድሞ ፣ በመወለድና በተፈጥሮ ተሳ

ሳሪያችን የሆነው የምድር ቁራሽ ነው ። ስደተኞች አለመሆ ናችን የሚሰማንም ፣ በአገር ውስጥ በምንኖርበት ጊዜ ብቻ ነው ። አገር ማለት ፣ እንደምንተነፍሰው አየር አስፈላጊያ ችን የሆኑት ፣ የሰማይ ክልልና የፀሐይ ብርሃን የሚገኙባት ስፍራ ነች ። በተለይም ከሥጋችንና ከአካላችን ጋር የተዛመ ደው መሬቷና አፈርዋ ወደ ሌላ ስፍራ ሊያዛውሩት የማይ ቻል በአገር ብቻ የሚገኝ ሃብት ነው ። አስቀድሞ በመንደር ቀጥሎም በአውራጃ የተዘረጋው የመውደድ ስሜት ፣ ቅር ጽና ድንበርዋ በማይደመሰስ አኳኋን በካርታ የተመዘገበ ውን አገርን ወደመውደዱ ይለወጣል ።

የተፈጥሮ ድንበሮች ፡—

አገር በመሠረቱ ከተፈጥሮ በመነጩ በወንዞች ፣ በተ ራሮች ፣ በባሕሮች ድንበርዋ የተወሰነ ነው ። አንድ አንድ ጊዜም በማይታይ መስመር ብቻ ከሌላው አገር የምትለይበ ትም ጊዜ አለ ። ነገር ግን ይበልጥ የሚያጋንኗትና ተወዳጅ የሚያደርጓት በተፈጥሮ ድንበሮች ተከልላ ፣ እስከ እገሌ ባሕር ድረስ ፣ ከእገሌ ወንዝ ፣ ከእንደዚህ ያለው ተራራ ወ ዲህ ሲባልና ፣ ለክብርዋና ለነጻነቷ በነዚህ ወሰኖች ላይ የተ ፈጸሙት ታሪካዊ ድርጊቶች ሲታወሱ ነው ።

ኤኮኖሚካዊ ሁኔታዎች ፡—

አገር መኖሪያ ስፍራ ብቻ አይደለችም ። አንድ ሕዝብ ለሕይወቱ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ሁሉ እንዲያገኝባት የተመደበች የጋራ ንብረት ነች ፤ ንብረት የተባለውም በም ድሩና በታሕተ ምድሩ ፣ የሚገኙት ሰብሎችና ማዕድኖች ፣

በሕግ የተመሠረቱት ንግዶችና እንዱስትሪዎች የሚያስገኙ አቸው ሃብቶች ናቸው ። እነዚህ ሃብቶች ለሁሉም እኩል እኩል ባይደርሱ ቅሉም ፣ በጠቅላላው ለመላው ሕዝብ ጥ ቅም መዋላቸው አይቀርምና የመሥራት መብት ፣ አንድ ዓይነት የኑሮ ደረጃ ፣ የተወሰነ የኑሮ መተማመኛ ፣ አስፈ ላጊ የሆኑት መቅኖች ፣ አንድ ደንበኛ መገበያያ ገንዘብ እን ዲኖረው ያሻል ፤ (በመሠረቱ ገንዘብ ልዩ ክብር የተሰጠው ሸቀጥ ነው ።)

የአንድ አገር ኤኮኖሚካዊ ሁኔታ በየጊዜው እያደገ የሚሄድና ከፍ ያለ ግምት የሚሰጠው ነው ፤ ኑሮዋቸውንና ቅርሶቸውን ለማመዛዘን ባላቸው ችሎታ መሠረት ሰዎች አገራቸው እያደረ ይበልጥ እንድትሰጣቸው መጠየቃቸው አይቀርም ።

ቋንቋ ፡—

ከዘር ጋር ተመሳሳይነት ያለው ፣ ያንድ አገር ታላቅ አብነት ቋንቋ ነው ። አገር ፤ አባሎቹ በሙሉ መግባባት እንደሚችሉበት ፣ እንደአንድ ቤተሰብ ትቆጠራለች ፤ የቋ ንቋ መለያየት በሕዝብ መካከል ፣ አለመመሳሰልን ያስከት ላል ፤ የቋንቋ አሐዱነት ግን የሕዝብን አንድነትና የአገርን ፍቅር ያጠነክራል ። ስሜቶችን መልክና ባሕርይ ሰጥቶ ለሰ ዎች ሕሊና የሚገልጽላቸው ቋንቋ ነው ፤ በትርጉምና ባስተ ርጓሚ መግባባት የቱን ያህል እንደሚያስቸግር የማይገነ ዘብ ሰው የለም ። የአንድ አገር ታላቅ ሃብት የሆኑት የታላ ላቅ ጸሐፊዎች ድርሰቶች ዋጋቸውን የሚያገኙት በቋንቋ

ምክንያት ነው ። ያባቶቻችን መታሰቢያዎችና ያለፈውን የምናስታውሰው በቋንቋ እየተሸጋገረልን ነው ።

በተከታታይ ትውልዶች መካከል መያያዣ ስለሆነ ፣ ታላላቅ ድርጊቶችን ፣ ታላላቅ ሰዎችን ፣ ባሕልን ፣ ዜማን ፣ ታሪክን ፣ በማስታወስ ነዋሪ የሚያደርጋቸውና አገርን ከ ስር ጀምሮ የሚያሳውቅ ቋንቋ ነው ። ቋንቋ ባንድ ዘመን በሚኖሩ ሰዎች መካከል መገናኛ ከመሆኑ ይልቅ በተከታ ታይ ትውልዶች መካከል መተሳሰቢያ መስመርነቱ ይበል ጣል ለማለት ይቻላል ።

ስለዚህ ያንድ አገር ቋንቋ በተቻለ መጠን አንድ ዓይነ ትና ባንድ ዓይነት ደንቦች የሚመራ ሲሆን ለሕዝቡ ከፍ ያለ ጥቅም የሚሰጥ መሆኑ የታመነ ነው ።

እራስ ዘንድ የመኖር ስሜት ፡—

እራስ ዘንድ መኖር ፣ በለመዷቸው ነገሮች መካከል መገኘት ብቻ ሳይሆን ፣ የራስ ባለቤት መሆንንና በባእድ ሕግ ስር አለመተዳደርን ለሕሊና የሚገልጽ ሁኔታ ነው ። ኢትዮጵያዊ መሆን ፣ ኢትዮጵያ የኛ መሆኗን የሚያረጋግጥ ልን ፣ በዚህም የተነሣ አቅዋሞቹና ሕጐቿ ፣ ማለት ያስተ ዳደር ድንጋጌዎችዋ ፣ ከባዕድ ያልመነጩና ፣ ከሕዝቡ ፍላ ጐት ፈልቀው ፣ ሕዝቡ የፈቀዳቸው እንዲሆኑ ግዴታ መ ሆኑ ግልጽ ነው ። ሕጐቿ ዘወትር የሚጠብቁን ደንቦች እ ንጂ የሚጨቁኑ ግዴታዎች ሆነው የማይሰሙን በዚህ ዓይ ነት መንገድ ሲወጡ ብቻ ነው ።

የሕዝብ እንደራሴዎች በምክር ቤቱ ውስጥ እንዲገቡና የሕግ አውጭነት ሥልጣን ፥ እንዲያገኙ ፥ በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ከተወሰነ በኋላ ፥ ሕዝቡ በአገሩ አስተዳደር ፥ ተካፋይ በመሆኑ የአላፊነት ስሜት በዚሁ መጠን ያደገ ሆንዋል ።

የትውስትና የምኞት ተመሳሳይነት ፡—

የጋራ ታሪኮች ባንድ ትውስት ሲጠቀለሉ አገር ይሆናሉ ፤ በነዚህ ትውስቶች የተነሣ የዘመናችን ስር እስከ ጥንታዊ ጊዜዎች ይዘልቅና ከኛ በፊት የኖሩትን ሁሉ ያስታውሰናል ።

አንድ ታላቅ ደራሲ እንዳለውም ሁሉ ፥ ካንድ አገር ሕዝብ በሕይወት ካሉት ይልቅ የሞቱት መብዛታቸውን ያስታውሰናል ። እነዚህ ትውስቶች አገራችን ያሳለፈቻቸውን የድልም ሆነ የሐዘን ጊዜዎች በመንፈሳችን በመቀስቀስ ፥ በልብ ውስጥ ኃይለኛ ስሜቶች ይፈጥራሉ ። ያለፉትንም ጊዜዎች ሲያስታውሱ ፥ በጋራ ምኞታችን ደጋፊነት ዘላቂነቱ የማያቋርጥ መጭ ጊዜ ወደፊታችን እንዳለ ይሰማናል ።

አገር የምታሳድርብን ስሜቶች ፡—

አገርን መውደድ አንድ የተፈጥሮ ባሕርይና ኃይለኛም ስሜት ነው ። በሰውም መንፈስ ላይ ያለው ኃይል ከቤተሰባዊ ስሜት የማያንስና በስፋት እንዲያውም የበለጠ ነው ።

የሃይማኖትና የሳይንስ ጉዳዮች ፥ በዘለዓለማዊነት ባሕርይና ባከናወናቸውም ከሰብዓዊ ፈቃድ በላይ ሲሆኑ ፥ አገር ምድራዊና ታሪካዊ ባሕርይ ያላት ግምቷ ከሰው ሥልጣን በላይ ያልሆነ ድርጅት ነች ። እርግጥ ነው ፤ በጊዜም ሆነ በስፍራ ከኛ የቀደመች ናት ፥ ቢሆንም በኛ ነው የምትኖረው ፤ ከኛ በፊት ትኖር ስለነበረ ከኛም በኋላ ትኖራለች ፥ ዘላለማዊት ነች ፥ ብለን በከንቱ ማመን የለብንም ።

የሕዝቡ አንድነት ፥ ንቃታና የመሥዋትነት መንፈስ ፥ አንድ ቀን ላላ ያለ እንደሆነ ልትሞትም የምትችል ናት ። አገርን ልጆቿ ያለማቋረጥ በሕይወት እንዲጠብቋት ያስፈልጋል ። እያንዳንዱ ሰው ስለሷ ያለውን አላፊነት በማንኛውም ሰዓት ለመገንዘብና ለመረዳት ይችላል ። ከዚያ በኋላ ቢያደክማትም ቢያድናትም የሱ ፈንታ ይሆናል ።

አገርና ተግባር ፡—

አገር የምታሳድርብን ስሜቶች ስለሷ ልንፈጽማቸው የሚገባንን ተግባሮች የሚያስታውሱናን የሚጠሩን ናቸው። ግን ብዙዎች ሰዎች ስሜቱ ስላደረባቸው ብቻ ተግባራቸውን የፈጸሙ ስለሚመስላቸው ለዚህ ጥሪ አብዛኛውን ጊዜ አቤት ሳይሉ ይቀራሉ ። ሆኖም የጉዳዩ ከባድነት ማንኛውም ቢሆን ፥ የሚያፈልቃቸው ስሜቶች ፥ በሚያስከትሏቸው ተግባሮች ካልተሟሉ ፥ የስሜቱ መመንጨት ራሱ ምክንያትም ፥ ዋጋም የለውም ። ስለአገር የሚያድሩብን ስሜቶች

ብርቱና የሚነሽጡ ቢሆኑም ፥ እንድንፈጽማቸው የሚጠይቁን ተግባሮች የማይዘለሉና እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ፥ ሕይወታችንንም አሳልፈን እንድንሰጥ የሚጠይቁ ናቸው ።

ማንም ሰው ይህን መሥዋዕትነት ያለማመንታት ፈቅዶ መቀበል አለበት ። ዞሮ ዞሮ ሞት አይቀርምና ፥ ሕዝባዊ ተግባርን ሲፈጽሙ ፥ ግንባርና ደረትን በአገር ላይ በተነሳው መከራ ፊት ደቅኖ ከመሞት የተሻለ ሌላ አሟሟት ልንመኝ አንችልም ። በዚህ ዓይነት አሟሟት ሕይወታቸውን ያሳለፈው የሰጡት ወንደሞቻችንና አባቶቻችን ፥ በስጋቸውና በደማቸው ኢትዮጵያን ስለገነቧት ዛሬም በሕሊናችን ሕያው ለመሆን ችለዋል ። ድንበር አናስደፍርም ሲሉ አጥንታቸውን በመከስከስ ፥ ወሰኖቻችንን በአጽማቸው ክበዋል ፤ ሕይወታቸውን ኦሳልፎ በመስጠት ፥ ከሃብቶች ሁሉ የላቀ በሆነው በመሥዋዕትነት ጽዋችን ውስጥ ደማቸውን አንቆርቁረዋል ፤ ጀግንነታቸውም ለሌሎቹ አርዓያና መሰቢያ ሆነ ። እንደዚህ ያለው የመሥዋዕትነት መንፈስ እስካለ ድረስ አገር በሕይወት ትኖራለች ። ነገር ግን ልጆቿ ሕይወታችንን አናሳልፍላትም ያሉ ዕለትና ከነሱ በፊት መሥዋዕት የሆኑትንም መታሰቢያቸውን አናከብርም ብለው የናቁ ዕለት ኦገር ትጠፋለች ። ሕይወትን አሳልፎ ከመስጠት ተግባሩ የሚሸሽ ከአላፊነት ሁሉ ፥ የተቀደሰና ከፍ ያለ ዋጋ ያለውን ግዳጁን መክዳቱ ነው ። ባገሩም ላይ የማይጠፋ ጉድፍ አሰፈረባት ፤ ሕይወቴን አላሳልፋትም ሲልም ፥ በኔ ምትክ እሷ ትሙት ማለቱ ነውና ባገሩ ላይ ሞት ፈረደባት ማለት ነው ።

አገርን በመከላከል ጊዜ ፥ ሕይወታችንን እንደ መዋጮ መስጠት እንዳለብንና ፥ በምትኩም የምናቀርበው ምንም ዓይነት ነገር ፥ ምንም ዓይነት ምክንያት እንደሌለ መርሳት የለብንም ። አገር ከተወረረች ፥ ነጻነት ከተደመሰሰ ፥ ሁሉም ጠፋ ፥ ምንም ቀሪ ነገር የለም ማለት ነው ።

ከዚህም በቀር ስለአገራችን በየቀኑ ልንፈጽማቸው የሚገባ ዝቅተኛ ተግባሮች አሉ ። በዚህም ረገድ አጉድሎ መገኘት ትልቅ ጥፋት ነው ። ሥራውን በሚገባ የማያከናውን መንግሥታዊ ሠራተኛ ፥ ሕግን የሚጥስ አገረሰብ ፥ ትምሕርቱን ችላ የሚል ተማሪ ፥ መሬቱን የማያርስ ገበሬ ፥ የተበላሸ ዕቃ የሚሠራ ባለፋብሪካ ፥ መጥፎ ሸቀጥ የሚያቀርብ ነጋዴ ፥ የብጥብጥ መንፈስ የሚነዛና የተባባሪነትን መንፈስ የማይቀበል ሰው ፥ ሁሉም በየበኩላቸውና እንደየዓይነታቸው ኢትዮጵያን ያቆስላታል ።

አንድ አገር የሚሰጣት ግምት በውስጧ በሚኖረው ሕዝብ ባሕርይ ፥ ማለትም በሥራ ሕሊናው መጠን ነው ፤ አቅዋሞችና አገሮች ሊኖሩ የሚችሉበት የጸጋ ኃይል ፥ የሚገኘው ፥ እያንዳንዱ ሰው ተግባሩን በደንበኛው መንገድ ሲፈጽም ነው ።

ያገር ፍቅርና ኃይሉ ፡—

በሰው ልብ ውስጥ ስር ከያዙት ስሜቶች አንዱ የአገር ፍቅር ነው ። የሚጠይቀው ተግባር ግን እጅግ ከባድ ስለሆነ፥ አንድ አንድ ጊዜ ልንረሳው ወይም ልናፍነው እንሞክራለን፤ ነገር ግን በተለይም በመከራ ጊዜ ፥ ተመልሶ በኃይል ይገለ

ጻል ። ከብርቱዎቹ ስሜቶች አንዱ እንደመሆኑ መጠን ፥ ሰው ተግባሩን እንዲፈጽም የሚያነቃውና ከተፈጥሮ ስስታምነቱ የሚያርቀው እሱ ነው ። ላገር መታመንን ፥ ለራስና ለወገን አለማድላትን ፥ ድፍረትን ፥ ጽናትን ፥ እንዲሁም ችግርን ፥ ሕመምንና ሞትን መናቅን ያስተምራል ። የሰዎችን ተባባሪነት በብርቱ አኳኋን በማሰማቱ ባንዳንድ በታላቅ ታሪካዊ ሰዓቶች ጊዜ ፥ በምር የተለያዩን ወገኖች እንዲያ ብሩ ያደርጋል ።

የአገር ፍቅርና የሰው ዘር ፡—

እንደቤተሰብ ስሜቶች ሁሉ የአገርም ፍቅር በሞራል እንዲገራ ያስፈልጋል ። ሳይጠበቅ ሲቀርና እንዲያውም ያለልክ ሲያነቃቁት ፥ ሰውን እውር ያደርገዋል ። የውጭ አገርን ሰው ጥላቻ ያሳድርበታል ፥ ሰብዓዊ ስሜቶችን ያስንቀዋል ። በሥርዓት በተያዘ ጊዜ ግን ሰላማዊና ሰብዓዊ ስሜቶቻችን በበለጠ አኳኋን እንዲገለጹ ይረዳናል ። በዚህም የሌሎቹን አገር ክብር መጠበቅ እንማራለን ። አገርም የሰብዓዊ ስሜት የትምሕርት ገበታ ትሆንና በጐ ፈቃዳችንና የፍቅር መንፈሳችን ከድንበርዋም አልፎ እንዲስፋፋ ታደርጋለች ። የሰውን ዘር በመላው ለመውደድ የሚቻለው አስቀድሞ ያገርን ልጅ በመውደድ እየተማሩ ነው ፤ ነጻና ሃብታም በሆነች አገር ነዋሪ የመሆኑ ስሜት የሰው ኑሮ መሠረት ነው ፥ ለማለት እንችላለን ፤ አገር ከጠፋች ሁሉም ጠፋ ማለት ነው ። ካገር ፍቅር ተመሳሳይ የሆነ ሌላ ስሜት ሊኖር አይችልም ። ቢኖሩም ጥቂቶች ናቸው ።

ም ዕ ራ ፍ 7

ሕዝብ ፡—

ሕዝብ አንድ ነፍስ ነው ፤ ከጊዜ ብዛት ያንድ አገር ልጆች ሕብረት እየጠነከረ መሄዱ ይሰማቸዋል ። በስሜትም በትዝታም ፥ በተስፋም ፥ ይመሳሰላሉ ፥ አብሮ የመኖር ፍላጐትም ያድርባቸዋል ። ከዚህም በኋላ መንፈሳቸውም አካላቸውም አንድ ሆኖ ይታያቸዋል ፥ ማለትም አንድ ሕዝብ ይሆናሉ ።

ስለሕዝብ የተጻፈ ያንድ ደራሲ ገጽ ፡—

—አንድ ሕዝብ አንድ አካል ፥ አንድ የመንፈስ መሠረት ነው ። ይህም ሁኔታ ከሁለት ነገሮች የተገኘ ነው ፤ አንደኛው ፥ ያለፈው ጊዜ ፥ ሁለተኛው ያለንበት ጊዜ ነው ። ያለፈውን ጊዜ መለስ ብለው ሲመለከቱት አንድ ዓይነት ታሪክ ፥ ተመሳሳይ ደስታና አንድ ዓይነት ሐዘን የሚያስታውሱ ፥ በዛሬው ጊዜ ፥ አብሮ ለመኖር ፥ የወረሱትንም ሃብት ዋጋ ለማስገኘት ፈቅደው የተቀበሉና ግባቸው አንድ ዓይነት የሆነ ሰዎች ፥ አንድ ሕዝብ ይባላሉ ።

ካለፈው ጊዜ የጋራ ትውስትና ክብር መውረስ ፥ በዛሬ ጊዜ ባንድ ዓይነት ዓላማ መመራት ፥ አብሮ ታላላቅ ሥራዎች የፈጸሙ መሆን ፥ ወደፊትም አብሮ ሌሎች ተግባሮች ለመፈጸም ፈቃደኛ መሆን ፥ አንድ ሕዝብ ለመባል ተገቢ ሆነው የሚያስገኙ ስሜቶች ናቸው ። በተቀበሉት መሥ

ዋዕትነት ፥ በተቀበሉት ሥቃይመጠንይወዱአል፤የስፓርት ሰዎች መዝሙር፤ ጥንት እንደኛ ነበራችሁ ወደፊት እንደና ንተ እንሆናለን ይል ነበረ ፤ ፍቹም ፥ ጥንት ሕያው እንደነበ ራችሁ ዛሬ እኛም ሕያው ነን ፥ ዛሬ ሙታን እንደሆናችሁ እኛም ወደፊት ሙታን እንሆናለን ፤ ስለዚህ መጀመሪያች ንም ፍጻሜያችንም አንድ ነው ማለት ነው ።

ስለዚህ ሕዝብ ማለት ፥ አብረን በተቀበልናቸውና ወ ደፊትም ልንቀበላቸው በምንፈቅደው ፈተናዎች ላይ የተመ ሠረተ አንድ ሕብረት ነው ። በጤናማ መንፈስና በጽኑ ልብ ላይ የተመረኰዘ ታላቅ የሰዎች አንድነት ፥ ሕዝብ ተብሎ የሚጠራ አንድ ሞራላዊ ሕልውና ይፈጥራል ። ይህም ሞራ ላዊ ሕልውና የሚደርስበትን ፈተናና ሥቃይ ለመቀበል ኃ ይል ሲኖረውና እያንዳንዱም ሰው ፥ የግል ጥቅሙን ለሕብ ረቱ ጥቅም አሳልፎ ከሰጠ ሕዝብ ሕጋዊ አቅዋም ይሆናልና ለመኖር መብት አለው ።

ሕዝብና ግለሰብ ተመሳሳይ ባሕርይ አላቸው ፦—

ዞሮ ዞሮ ሕዝብ ማለት ፥ በተፈጥሮም ሕግ ሆነ በፈቃደ ኛነት ፥ ለመኖርም ፥ ለመሞትም ተዘጋጅቶው የገቡበት አንድ ታላቅ ቤተሰብ ነው ። ሕዝብ ፥ አንድና ሊነጣጠል የማይችል ነገር ነው ። ዋናው ባሕርዩም አሐዱነት ስለ ሆነ፥ እንደማንኛውም ሕይወታዊ አካል ሁሉ እንነጣጥልህ ቢሉት ይሞታል ። ሕዝብ እንደ አንድ ሰው አሐዱነት ፥ ሕ ሊና ፥ ስሜትና ፍላጐት አለው ። ለመኖርም መብት ስላለው ሕይወቱን ለማጥፋት መሞከር አይገባም ፤ በወረሰው መ

ሬት ላይ የባለቤትነት መብት አለው ። እንዲሁም በሌሎቹ ላይ ጉዳት አያምጣ እንጂ ኑሮውን በፈቀደው መንገድ ለመ ምራት መብት አለው ። የሰዎቹ ቍጥርና የመሬቱ ሰፊነት ሳይታይ አንድ ሕዝብ ነጻና በራሱ ተዳዳሪ የመሆን መብት አለው ። ይህም መብት ሊሸጥና ሊለወጥ የማይቻል ነው ።

የሕዝብ አላፊነትና ተግባር ፦—

ሕዝብ እንደ አንድ ግለሰብ በጐና ክፉ ለመሥራት ይች ላል ። ስለዚህ አላፊነትና መብት አለው ። አንደኛ ፥ በራሱ ረገድ ፥ የመኖር ፍላጐቱን ማጠንከርና ይህንን ምኞቱን ለመ ፈጸም አስፈላጊ የሆነውን የመሥዋዕትነት መንፈስ ከጫን ቃው ማፍለቅ አለበት ፤ እንዲሁም ከውጭ የሚመጣውን ችግርና ከውስጥም ሊላላ የሚሞክረውን ነገር ሁሉ አስቀ ድሞ ማየትና መድኃኒት ማበጀት አለበት ። ሕዝብ የአባሎ ቹን ሰላም ፥ ጸጥታና ሕልውና የመጠበቅ ፥ ሕዝባዊ ግልጋሎ ትና ያስተዳደሩ ሥራ በሥርዓት እንዲከናወን ማድረግ ፥ የያ ንዳንዱ ሰው ኑሮ በተቻለ መጠን ምቹ እንዲሆን የመጣር ፤ በሰዎቹም መካከል የተባባሪነት መንፈስ እንዲኖርና እንዲ ደረጅ ኃላፊነት አለበት ። በተረፈም የሌላውን አገር ሕዝብ፥ ነጻነቱን ማክበር ፥ አለማዋረድና በሚችግረውም ጊዜ የመር ዳት ተግባር በሕዝቦች ኃላፊነት ውስጥ ይቆጠራል ።

የሕዝቦች ማሕበር ፦—

ዛሬ የመንግሥታት ማሕበር እየተባለ የሚጠራው ፥ አቅዋም ፥ የአንጋገር ልምድ ነው እንጂ መባል የሚገባው የሕዝቦች ማሕበር ነው ። ተጠንቅቀንም ብናስተውል ይህ

ድርጅት በውነትም የዓለም ሕዝቦች ሕብረት ነው ። የተቋ
ቋመው በመንግሥታት መሪዎች ትጋት ቢሆንም ፥ መሪ
ዎቹ የተባበሩት በየአገራቸው ሕዝብ ስም ነው ። የሕዝቦ
ችን መኖር አምነን ከተቀበልን ፥ ሕዝቦች እርስ በርሳቸው
እንዲከባበሩ ፥ በመካከላቸው እኩልነት እንዲኖር ፥ አንዱ
ሌላውን የማጥቃትና የመውረር አሳብ እንዳያድርበት አስፈ
ላጊ ነው ። ይህ ዓለማ እንዲፈጸም ፥ የሕዝቦች ማሕበር
ማቋቋም ዓይነተኛው መድኃኒት ሆኖ ተገኘ ። የዚህ አሳብ
አመንጭዎች የተቀደሰ ግባቸው ፥ ሕዝቦችን በማስተባበር ፥
ወንድማማችነትን በሕዝቦች መካከል በመፍጠር በሕዝ
ቦች መካከል የሚነሳውን ጦርነትና ነፍስ መጣፋት ከተፈ
ጥሮ ሕግ ውጭ ለማድረግና ፥ በአጥፊውም ሕዝብ ላይ ነው
ርና ውርደትን የሚዘረጋ መሆኑን ለማሳመን ነበረ ። ከሁለ
ተኛው የዓለም ጦርነት በፊት የሕዝቦች ማሕበር ተብሎ
የሚጠራ ፥ ሕብረት በጄኔቭ ላይ ተቋቁሞ ነበረ ። ነገር ግን
በውስጡ ማሕበረተኛ ከነበሩት ሕዝቦች መካከል መሠረ
ታዊ ዓላማቸውን ማለትም ፥ እያንዳንዱ የሌላውን ሕዝብ
ነጻነትና ክብር መጠበቅ የሚለውን አንቀጽ አናከብርም
ስላሉና በተለይም ፥ በአገራችን በኢትዮጵያ ላይ ፋሽስታ
ዊት ኢጣሊያ ፥ በሙሶሊኒ እየተመራች የፈጸመችውን የዓ
መጽና የወረራ ተግባር ፥ በመቃወም ፈንታ ሌሎቹ ሕዝቦች
ፈርተውና ራሳቸውን ለማዳን ብቻ በማሰብ ዝም ብለው
በማየት ፥ ሌላው ሕዝብ ሁሉ ቅጣት ሳይፈራ የወረራ
ተግባር ሊፈጽም የሚችል መሆኑን ስላስረዱት ፥ ሂትለር
ተነስቶ ዓለምን ለመበጥበጥና በኢትዮጵያ መከራ ጊዜ እ

ዳር ቆመው ያዩትን ሁሉ በተራቸው አሳራቸውን ሊያበላ
ቸው ቻለ ፥ ዛሬም የተባበሩት ሕዝቦች ተብሎ በአሜሪካ አ
ገር በዚሁ መልክ ተቋቁሟል ። በኰሪያ በደረሰው ግጭት
ጊዜ ፥ በእሥራኤልና በግብጽ በስዊዝ ካናል ውጊያ ጊዜና
በኰንጐም ብጥብጥ ፥ ኃይሉን አግብቶ ለመዳኘት ሞክር
ዋል ፤ ነገር ግን በተለይ ፥ አገራችን ኢትዮጵያ የምታምን
በት የጋራ ጸጥታ ጠባቂ የሆነው የሕዝቦች ማሕበር የራሱ
ጦር ስለሌላው ፥ ዳኝነቱን የሚያስከብረው ቃላቸውን በመ
ጠበቅ አንድ አንድ አገሮች በሚያቀርቡለት ጦር ስለሆነና
እነርሱም ለግል ፖለቲካቸው ሳይስማማቸው ሲቀርፈያቀረቡ
ላትን ጦር መልሰው ስለሚነጥቁት ፥ የሕዝቦች ሰላምና ጸጥ
ታ በሱ ብቻ ሊጠበቅ የሚችልበት ጊዜ እስኪመጣ ድረስ ፥
የሕዝቦችን ግንኙት ሥርዓት ሊያስይዘው በሚችለው ፥ በሞ
ራል ደንቦች ላይ እምነታችንን ብንጥል የተሻለ ነው ።

<u>በሕዝቦች መካከል የሞራል አስፈላጊነት ፤</u>

ሕዝቦችም እንደ እያንዳንዱ ግለሰብ አንዱ የሌላውን
መኖር ፈቅደው የተቀበሉት መሆናቸውን አምነናል ፥ በኢ
ንተርናሺናልም ሆነ በግለሰባዊ ሞራል ፥ ዓይነተኛው ሥር
ዓት አንዱ ሌላው እንዲኖር መፍቀድ ፥ አሐዱነቱን ፈቅዶ
መቀበል ፥ ማንኛቸውንም ልዩነት ግምት ሳያገቡ እንደ
እኩያ ማክበር ነው ። እንዲሁም በሰፊው ደግሞ የሕዝቦችን
ሕልውና ማክበርን ያሳስባል ። ግብረ ኃይልንና ግፍን ፥
የመውረርና የመግዛትን መንፈስ ፥ በሕዝቦች መካከል የሚ
ፈጥሩትን ጉዳት በማመዛዘን ጨርሶ ከሕግ ውጭ ያደርጋ
ቸዋል ። አንዱን ሕዝብ ለማጥፋት ወይም ጐዶሎ ለማድ

ረግ ፣ ነጻነቱንና ሃብቱን ለመግፈፍ ፣ በኃይልና በብልጠት መጠቀም በታሪክ ውስጥ በሰፊው የተመዘገበ ቢሆንም ፣ በሰው ዘር ፊት አንድም ጊዜ ይቅርታና ስርየትን አግኝቶ አያውቅም ።

ኢንተርናሺናላዊ ሞራል እየተስፋፋ ይሄዳል ፡—

ምንም እንኳ አልፎ አልፎ አንዳንድ ብጥብጥ መፈጠሩ ባይቀርም ኢንተርናሺናላዊ ግንኙነቶች ወደሞራላዊ አመራር እያዘነበሉ መሄዳቸው አልቀረም ። ዛሬ ሠለጠኑ በሚባሉት አገሮች ሁሉ ባገራቸው ለሚኖሩት ለውጭ አገር ሰዎች የእንግድነትና የጥገኝነት መብት ይሰጣሉ ፤ የነዚህን ሰዎች ብሔራዊና ንግዳዊ ጥቅም የሚጠብቁላቸው ፣ ቆንስላዎች ፖለቲካዊ መብታቸውን የሚጠብቁ ኤምባሲዮች ፣ እንዲቋቋሙ ይፈቅዳሉ ። በተረፈም የኤምባሲዮቹ ግቢዎች እንደመልክተኛው አገር ምድር ተቆጥረው እንዳይደፈሩ ያደርጋሉ ።

የጋራ ሕግን የጣሱ (ሕዝባዊ ሕግን ፡) ወንጀለኞች ተይዘው ለባለጉዳዩ አገር እንዲሰጡ የሚያዘውን ስምምነት ያከብራሉ ። ኢንተርናሺናል የንግድ ውሎች ፣ የፖስታና የቴሌግራፍ ስምምነቶች ፣ ኢንተርናሺናል የምድር ባቡር መስመሮች ፣ የባሕርና የአየር መንገድ ውሎች እንዲከበሩ ያደርጋሉ ።

ጦርነት ፡—

በሕዝቦች መካከል ያሉት ግንኙነቶች ብዙ ጊዜ እጦርነት ላይ ያደርሱና ሞትንና ጥፋትን አሰቃቂ በሆነ መንገድ

ስለሚያስከትሉ ፣ አንዳንድ ጊዜ ፣ የሰው ዘር ፣ ሰው መሆኑን የከዳ ፣ በመንፈሱም ማመኑን የተወ ያስመስለዋል ።

በኃይል ፈንታ መብትን መተካት ተገቢ የነበረውን ሁሉ ይዘነጋዋል ። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ሰው ግብርናው ከራሱ በላይ ስለሚውልና ሊቆጣጠረው ስለሚሳነው ፣ ሕዝቦች ለጦርነት ምቹ ሆነው ይገኛሉ ። የፈተናውም ቀን ሲደርስ አንድ ሕዝብ ሕጋዊ ከሆነው ከመከላከል መብቱ ሊያፈገፍግ አይችልም ፤ ቢያፈገፍግ ግን ፣ ወደባርነት ውስጥ ይወድቃል ። ባርነትም ሕይወትንና ሕይወትን የሚያስመኙትን ነገሮች ሁሉ የሚያስጠላ ስለሆነ ያው እንደመሞት የሚቆጠር ነው ። ሆኖም ሰው የጦርነትን አጥፊነት ለመቀነስ በየጊዜው ስምምነቶች ሲያደርግ ጦርነት የማይቀር ነገር መሆኑን ያመነ ይመስላል ። ለምሳሌ ፣ ገለልተኞች አገሮች እንዳይነኩ ፣ ዘማቹ የሠለጠነ ወታደር እንዲሆን ፣ ሲቪሎች በተለይም ፣ ሽማግሌዎች ፣ ሴቶች ፣ ሕጻናቶች እንዳይነኩ ፣ ንብረት ያለሕግ እንዳይወረስ ፣ ክፍት ከተሞች በቦምብ እንዳይደበደቡ ፣ ወንዞችና የውሃ ጉድጓዶች መርዝ እንዳይጠበጥባቸው ፤ የመርዝ ጭስና አካል የሚበጣጥሱ ጥይቶች እንዳይሠራባቸው ፣ ቁስለኛን ፤ ጠላትም ቢሆን ፤ እንዲረዳ ፣ የምርኩኞች ሕይወት እንዲጠበቅ ስምምነቶች ስላደረጉ ከጦርነት መቅሰፍትና በዚያን ሰዓት ከሚፈጠረው የሰው መንፈስ ግሎት አንድ አንድ ነገሮችን ለማዳን ተስፋ ነው ።

አንዳንድ ጊዜም እነዚህ ስምምነቶች ይጣሳሉ ፣ ቢሆንም ያብዛኞቹ የሕሊና ምኞት ስምምነቶቹ እንዲጠበቁ ስለ

ሆነ ጥንት እንደሚደረገው ሁሉ ፥ ምርኰኞች ቢታረዱ ፥ አ
ካል የማጉደል ሥራ ቢፈጸም ፤ በዛሬው ጊዜ የማይሳቀቅ
ፍጡር አይገኝምና መሻሻል እንደተደረገ አይጠረጠርም ።

ተስፋ የሚሰጡ ምልክቶች ፡—

በማንኛውም አኳኋን በሕዝቦች መካከል ስላለው ግን
ኙነት የሞራል ሁኔታ እየተሻሻለ መሄዱ አልቀረም ። እንዲ
ያውም የደረሱት ሁከቶችና ችግሮች የሚያስከትሉት ፈተና
ትምሕርት እየሆነና መንፈስን እያብራራ ሰውን ወደሩሕሩ
ሕነት ስለሚገፋው ሞራል እየጠነከረ ይሄዳል ። ይህም እ
ጅግ ተስፋ የሚሰጥ ነገር ነው ።

አንድ ሕዝብ የራሱን ጉዳዮች በአስተዋይነትና በቅን
ነት ሲያከናውን የሌሎችን ነጻነት ሲያከብር ፥ ቃሉን ሲጠ
ብቅ ፥ ትክክለኛ ዳኝነትንና በጐ አድራጐትን ሲያዘወትር ፥
የቀረውን ዓለም ፍቅርና እምነት ይማርካል ፤ በዚህም የተ
ነሳ ለወደፊቱ ኑሮው አጥጋቢ ዋስትና ያገኛል ። ነገር ግን
አገርጋሪና እብሪተኛ የሆነ በተለይም የገባውን ግዴታ የማያ
ከብርና የግብረ ኃይል ፥ የአድልዎና የሽሚያ ፖለቲካ የሚ
ከተል ሕዝብ በሌሎቹ ዘንድ ሞገስ ያጣል ። ከዳኞች ሁሉ
ርሕራሄ የሌለው ጊዜ ነውና ምንም እንኳን ዲፕሎማቶቻ
ቸው ቢያብረቀርቁና ስማቸው ቢገን ፥ ወራሪዎች የተሳተ
ፉት ድል ፥ በግብረኃይልም የነጠቁት ምርኰ ፥ ኗሪ ፍሬ ሊ
ሰጡ እንደማይችሉ የተረጋገጠ ነው ። ወረተኛ በሆነ ድል
ሰዎች ለጥቂት ጊዜ ሊመኩና ሊግደረደሩ ይችሉ ይሆናል ፥
ነገር ግን በፍጥነትም ሆነ ቆይቶ ፥ የሚፋቸውን ዋጋ ሕዝባ
ቸው መክፈሉ አይቀርም ። በግብረኃይልና በግፍ የሚመሩ

ሰዎች ፥ አሻግሮ የሚያይ እውቀት የሌላቸው ናቸው ። የፖለ
ቲካ አመራር የሞራልን መስመር ሲለቅ ፥ ጠፊ መሆኑን ማ
ወቅ አለባቸው ።

ም ዕ ራ ፍ 8—

መንግሥት ፡—

ባለፉት መስመሮች እንደተነገረው ፥ የአንድን ሕዝብ ፥
እንዲያውም የአንድን ሰው ነጻነቱን ለመንሳትና የሚተዳደ
ርበትን ሕግ ከባእድ እንዲቀበል ለማድረግ ፥ መሞከሩም ተ
ገቢ አለመሆኑን ገልጸናል ። ይህንንም ስንል ፥ ሕዝብ እንደ
ግለሰብ ሁሉ በራሱ እንዲተዳደር መብት እንዳለው ማወቃ
ችን ነው ። ሕዝብ ግን ራሱ መንግሥት ሆኖ ራሱን ሊያስተ
ዳድር ስለማይችል ይህን ተግባርና ሥልጣን አሳልፎ ለተወ
ሰኑ ሰዎች ይሰጣል ፤ ማለትም ለመንግሥት ይሰጣል ። መን
ግሥት የሕዝብ ፖለቲካዊ ድርጅት ነውና ፥ በዚህም የአስተ
ዳዳሪና የተዳዳሪ ሁኔታ ስለተፈጠረ ለመጀመሪያዎቹ የማ
ዘዝ ሥልጣን ፥ ለሁለተኞቹ የመታዘዝ ተግባር ተሰጠ ፤ ሥል
ጣን እሶስት ላይ የተከፈለ መሆኑን በመጽሐፉ መጀመሪያ
ክፍል ገልጸናልና መመለሱ ጠቃሚ ሆኖ አላገኘነውም ።

መንግሥትና ግለሰብ የጋራ ተግባር ኦላቸው ፡—

ሕዝብ አንዳንድ ጊዜ መንግሥቱ ለሱ የማይጠቅመው
ወይም ከሱ ሥልጣን ውጭ መሆኑ ሲሰማው እምነት አያሳ

ድርበትም ፥ መጠራጠር ይጀምራል ፤ ነገር ግን መንግሥት የሕዝቡ ሕዋስ ሆኖ በሚፈጽመው ተግባር ለውጥ ከያንዳ ንዱ ሰው ሕጋዊ ተግባር ሊጠይቅ ይችላል ። ሰዎች በመንግ ሥት ረገድ ሊፈጽሟቸው የሚገባ ተግባሮች አሉ ፤ ሕጕ ችን በጠቅላላ የማክበር ተግባር ፥ ግብርን መክፈል ፥ ወታደ ራዊ አገልግሎትን መፈጸም ፥ የሕዝብን ንብረት መጠበቅ ፥ በሕዝባዊ ሥራዎች ተካፋይ መሆን ፥ ለጋራ ሃብት እድገት መሥራት ፥ የመንግሥትን ሠራተኞች በተግባራቸው መር ዳትና በማንኛውም ጊዜ ችግራቸውን ማቃለል ፥ ሕዝባዊ ተግባሮች ናቸው ። በበኩሉ ደግሞ መንግሥት ሥራውን በሚገባ መፈጸም አለበት ፤ በመንግሥቱ አስተዳደር ውስጥ ያሉት ሠራተኞች ተግባራቸውን በትክክልና በንጹሕ ሕ ሊና እንዲፈጽሙ ማድረግ አለበት ። መንግሥት በችሎታው ሕዝባዊ አገልግሎትን ፥ ገንዘብን ፥ የጦር ኃይልን ፥ ፖሊስን፥ ያደከመ እንደሆነ ሕዝብን እንደበደለ ይቆጠራል ።

መንግሥትም በማንኛቸውም ጊዜ ከተሰጠው ሥል ጣን የማለፍ ፍላጐት እንዳይኖረው ያስፈልጋል ፤ ሥልጣን አደገኛ ፈተና ነው ፤ ሰውን ያሰክረዋል ፥ እንዲያውም ይመር ዘዋል ። እብሪት ሊያሳድርበት በሥልጣኑም ከተፈቀደለት በላይ እንዲሠራበት ሊገፋፋውና ራሱን ከመጠን በላይ እን ዲገምት ሊያደርገው ይችላል ፤ ስለዚህ ሥልጣን ማለት አስፈላጊ ሲሆን ማዘዝና መከልከል ነውና ፥ ትእዛዙም ሆነ ክልክሉ ከሕዝብ ጥቅም ጋር የተመጣጠኑ እንዲሆኑ መጠ በቅ ነው ።

የሥልጣን ጉዳይ ፡—

በሥልጣን መሥራት የሰውን ነጻነት መወሰን አይደ ለምን ? የመንግሥት ሥልጣን ተገቢ ነውን ? ወሰኑስ ምንድ ነው ? ለግለሰብ የሚሰጠው ነጻነት እስከየት ነው ? ለነዚህ ጥያቄዎች ሁሉ መልስ ለመስጠት ፥ የኃላፊነትን ሁኔታ ጠን ቅቆ ማየት ያስፈልጋል ። መንግሥት የሚያዘውም ፥ የሚያ ስገደድ ውም ፥ ለሕዝቡ ሕይወትና ለአገሪቱ ነዋሪ ጥቅሞች አላፊ እንደመሆኑ መጠን ነው ። ይህ አላፊነቱ የኛን ተግ ባር ያስተምረናል ። የፖለቲካ ዝንባሌዬ ማንኛውም ቢሆን ፥ የሚያስተዳድረኝ መንግሥት የሚሰጠኝን ትእዛዝ መፈጸ ምና እነዚህ ግዴታዎች የሚወስኑትን ሕጕች ማክበር አለ ብኝ ። እነዚህን ትእዛዞች የጣስን እንደሆነ ፥ ሕዝባዊ አገል ግሎትን መጉዳታችን ነው ። በዚህም የተነሳ በጊዜው በዚህ መንግሥት ጠባቂነት ሥር ያለውን ያገሪቱን ሕልውና በአ ደጋ እንጨምራለን ። እንደዚሁም ፥ ለምሳሌ ፥ አገር በጦር አደጋ ውስጥ በምትሆንበት ጊዜ የመንግሥት አላፊነት እየበዛ እንደመሄዱ መጠን ፥ የኛም ተግባር ስለሚበዛ ትእዛ ዞችም የበለጡ ስለሚሆኑ ወደን መቀበል አለብን ።

• መንግሥትና ግለሰብ ፡—

በመንግሥትና በግለሰብ መካከል ያሉትን ግንኙነቶች ሕብረሰባዊ ሊቃውንት አብራርተውታል ። ሰው እውቀቱና ችሎታው ማንኛውም ቢሆን የብቸኝነት አሳብ ሊኖረው ኦይገባም ። ተባባሪነት ፥ ከተፈጥሮ የመጣ ባሕርይ ስለሆነ ሰው በግዴታ ሊቀበለው የሚገባና የማያሻማ ሁኔታ ነው ። ማንኛውንም ነገር ስናደርግ ፥ ባንድ ትንሽ መሣሪያ ስንገለ

ገል ፥ በጋራ ሃብት በመጠቀም መሆኑን አለመዘንጋት ነው ። እያንዳንዱ መብት ተመሳሳይ ተግባር አለው ። ማሕበራዊ ሃብት የጠፋ እንደሆነ ችግርና ባርነት ይመጣሉ ።

መንግሥት በተቻለው መጠን በግለሰብ መንፈስ የአላፊነት ስሜት እንዲኖረውና ፥ እንዲዳብር ማድረግ አለበት ፤ የተባባሪነት ስሜት ከአላፊነት ስሜት ጋር የተያያዘ ስለሆነ አንዱ አንዱን ያዳብረዋል ።

በኤኮኖሚ ረገድ ሰው ከመንግሥት ጠባቂነትና ተቆጣጣሪነት ሊወጣ አይችልም ፤ የራሱንና የቤተሰቡን ኑሮ ማረጋገጥ ግን የሱ ፋንታ ነው ። ብዙዎች ሰዎች መንግሥት እንዲያኖራቸው ይፈልጋሉ ፤ ተገቢውን ወሰን እያደረገ መንግሥት ለግለሰብ ሰፋ ያለ የሥራ ነጻነት እንዲሰጠው ያሻል። የመንግሥት ተግባር ዋናው መቆጣጠር እንጂ እራሱ መሥራት አይደለም ። በትምሕርትም ረገድ ቢሆን መንግሥት ብዙ ለመሥራት ይችላል ፤ ነገር ግን በተማሪዎቹ አንጐል ላይ ትምሕርትን ለማተም ስለማይችል ፥ ተማሪው በራሱ ትጋት እውቀቱን በመንፈሱ ማሳደር አለበት ። በዚህ አኳኋን ሰው ለመማር የሚችለው በነጻ ኃይሉ መሆኑ ከታመነ ፥ የሥራን ፥ የማሰብን ፥ የሃሳብ መግለጽን ነጻነት እንዲተወ ለት ያስፈልጋል ። ይህም ሲሆን የሃሳቡ አገላለጽ ሕዝባዊ ጥቅምን ቢጐዳ ተጠያቂና አላፊው ራሱ መሆኑን ተገንዝቦ ነው ።

በሞራል ረገድ ደግሞ የአላፊነትን ስሜት ማዳበር ከማንኛውም ይልቅ አስፈላጊ ነው ። በሞራል ረገድ ሰው የራሱ

ሃብት ነው ። ሞራላዊ ውጤት ለያንዳንዱ ሰው ከተሰጠው የሕሊና ነጻነት ጋር የተያያዘ ነው ። መዳን ፥ ለሰው ብቻ ሳይሆን ለመንግሥትም ከውስጥ ነው የሚመጣው ። መንግሥት የሚፈልቀው የያንዳንዱ ሰው ጉልበት ሲደመር ነው ። ሕጐችም ፥ ደንቦችም ዋጋ የሚኖራቸው እንደተቀባዮቹ ሰዎች መጠን ነው ።

ምዕራፍ ፱—

ሞራልና ኤኮኖሚካዊ ኑሮ ፡—

የሰው ችግር ፡—

ሰው በመሠረቱ ችግር ያጣደፈው ፍጡር ነው ። ለምሳሌ ፥ ምግብ ያጣ እንደሆነ ይሰቃያል ፥ ይከሳል ፥ ይሞታል ። እንደ እንስሳም ያሁኑን ችግሩን በመወጣት አይደሰትም ፤ በልቶ እንደገና እንደሚርበው ያውቃልና ያለ ስጋት ለመኖር ለወደፊቱ ማሰብና ማዘጋጀት አለበት ። የሥልጣኔ መጀመሪያ ዓላማ ከችግር የሚያድኑትን ፥ መተማመኛዎች ማዘጋጀት ነው ።

የሥራ አስፈላጊነት ፡—

እነዚህን መተማመኛዎች ማዘጋጀት ድካም ይጠይቃል ። ምድር የሚያስፈልገንን ሁሉ ይዛለች ፥ ግን በሥራ ላይ እንዲውልና ለጥቅማችን እንዲሆን ለማድረግ ብዙ ልፋት ያስፈልጋል ፤ በብላሽ ተሰጠን ለማለት የምንችለው

የምንተነፍሰውን አየር ብቻ ነው ። ውሃን እንኳን ንጹሕ ለማድረግና ለማምጣት ድካም ይጠይቃል ። ሁሉንም ነገር ሰው በግንባሩ ወዝ ማግኘት አለበት ። ምድርን ትኩር ብለን ስንመለከት የሰው ሥራ በላይዋ ተጽፎ እናያለን ። ከሁሉም አስደናቂ የሆነው ደግሞ ሥራ ሌላውን ሥራ መጥራቱ ነው። አንድ እርሻ የተተወ እንደሆነ አረም ይወረዋል ፤ ሐዲድ እንኳን ካልተጠበቀ ባቡር አያስኬድም ። የሥልጣኔ እርምጃ ትክክለኛና አለታዊ በሆነ ሥራ ካልተደገፈ ሊገፋ አይችልም ። እድሚያችንን ሙሉ የማይለየን አለታዊ ሥራ ፥ ታላቅ አብነት ነው ። የምንኖረው በዕለታዊ ሥራ ነው ። አስፈላጊነቱም ተግባራችንን ያስተምረናል ። ሰው ማንኛውንም እንቅስቃሴ ሲያደርግ ፥ ቁራሽ ዳቦ ሲጐርስ ፥ አንድ ጉንጭ ውሃ ሲጠጣ ፥ መብራት ሲለኩስ ፥ በሌላው ሰው ድካም መጠቀሙ ነውና ዕዳ መግባቱ ነው ። ሥራ የሕይወትን ዋጋ ፥ ራሱን ሕይወትን የምንሸምትበት ገንዘብ ነው ። ሰነፍ ሰው በመኖሩ ብቻ የሰውን ተባባሪነት አንካሳ ያደርገዋል ።

የተፈጥሮ ስንፍና ፡—

ሰው በተፈጥሮው ሥራን እጅግም እንደሚይደፍር ማመን ይኖርብናል ። በተለይም በልጆች ዘንድ ይህ ጠባይ ይገኛል ፤ በአንድ አገር ላይ ፥ የሥራ ፈትነትንና የግዴለሽነትን ሁኔታ የሚያስፋፋ ስንፍና ነው ። ስለዚህ ሰው ተፈጥሮን በማሸነፍ ወደተግባሩ እንዲያመራና ሕይወትና ተድላን ፥ ቀድሞ ይጠላ ከነበረው ፥ ከሥራ እንዲያገኝ ሞራል እንዲመራው ለማድረግ እንሞክራለን ።

የሥራ በጐ አድራጊነት ፡—

ሥራ ለሰው ምቾትንና ተድላን ያበረክታል ፤ ሥራን የሚጠሉ የተሳሳተ መንገድ የያዙ ናቸው ። ምቾትና ተድላ ከውጭ የሚመጣና ለያንዳንዱ እንደዕጣ የሚደርሰው ነገር ይመስላቸዋል ። በእውነቱ ግን ደስታ ከገዛ ሥራችን የምናፈልቀው አብነት ነውና ለሕይወት ጣዕም የሚሰጠው እሱ ነው ። ሰው ሥራ በፈታ ጊዜ መሰልቸት ይሰማዋል ፤ የሚያደርገውም ሲያጣ ጊዜውን የሚያሳልፍበት ቀልድና ፈንጠዝያ ይፈልጋል ። በዚህም የተነሣ ዓመል ይሆንበትና የስሜትና የሥጋ ባሪያ ስለሚሆን ፥ አንድም ከፍ ያለና የተቀደሰ ዓላማ ሊኖረው አይችልም ። ብዙ ሰዎች ከሥራቸው ላይ ፈቃድ አግኝተው እረፍት ለማድረግ ያለልክ ሲጥሩ ይገኛሉ ፤ ግን ፈቃዱ ከተሰጣቸውና ጥቂት ጊዜ ከቆዩ በኋላ ቀኑ አልመሽ ስለሚላቸው እንዲያውም የፈቃዱ ጊዜ ሳያልቅ ወደሥራቸው ይመለሳሉ ። ተማሪዎች ተማሪ ቤት በተዘጋ ጊዜ የሚያደርጉት ይጠፋቸዋል ፤ ይህ ሁሉ ሰው ሳይሠራ ደስ ብሎት ሊኖር እንደማይችል ያስረዳናል ። ስንፍና የኃጢያቶች ሁሉ እናት ነች የሚባለውን ተረት በማረጋገጥ ፥ አብዛኞቹ ወንጀለኞች ፥ በስንፍናም ሆነ ፥ የሚቀጡበት በማጣት ፥ ሥራ ከፈቱ ሰዎች መካከል ነው የሚገኙት ።

ሥራ መንፈስን በማነቃቃት ፥ ፈቃደኝነትንና እውቀትን ያስፋፋል ። ማንኛውም ሥራ ከዕለት ወደዕለት እየተሻሻለ ስለሚሄድ ፈቃደኝነትና እውቀት ዘወትር የአዲስ አሳብ ምንጭ ያደርገዋል ። በተለይም እጅ ሥራ ሰውን ወደታላቅ ትጋት ይማርከዋል ። እጅሥራ የሚማር ሕጻን ፥ የሰውን መ

ሠረታዊ ባሕርይ ማለትም እጅችን የማሠራት ልምድ ይወር ሳል ። ዛሬ መኪና ምድርን ቢወራትም ፥ የሰው እጅ አስቀ ድሞ ካልሠራውና በየቀኑ ካላስተካከለው ማንኛውም ሥራ ፍጹምነትን አያገኝም ።

እጅችን ሲሠሩ ማየት እውቀትን በግብርና ላይ እንደማ ስተዋል ነው ። ሰዓት ሠራተኛ ፥ አናጢ ፥ መኪና ሰፊ ፥ ይህን የመሳሰሉት ሁሉ ምንም ቢሆን ጠማቸውን አያድሩም ፤ በጠቅላላው ሥራ በብቸኝነት መቼም ቢሆን ሊያከናውኑት የሚቻል ነገር ስላልሆነ ፤ ሰዎችን ከሁሉ ይበልጥ የሚያስ ተሳስራቸውን የግብርና ተባባሪነት መንፈስ ያሳድርባቸ ዋል ።

ሞያ ፡—

መሥራት ብቻውን በቂ አይደለም ፤ እያንዳንዱ ሰው አንድ የተወሰነ ሞያ እንዲኖረውና እስከ መጨረሻው እንዲ ገፋበት ያስፈልጋል ። ለሕብረሰብም ይበልጥ ጠቃሚ ለመ ሆን ፥ የሚችለው በዚህ ነው ።

የሞያ ሕሊና ፡—

የሞያ ሕሊና ፥ ከተፈጥሮ ጋር የተያያዘ ቢሆንም ፥ ሞራ ላዊ ኃይል የሚጠይቅ ነገር ነው ። ሕብረሰብ የሞያ ሕሊናን ማስፋፋትና መጠበቅ ከታላላቆቹ ተግባሮቹ አንዱ ነው ። የሞያ ሕሊና የሞራላዊነትና የሕብረ ሰብ ድጋፍ ስለሆነ በማንኛቸውም ሥራ ላይ አስፈላጊ ነው ። ታላላቆች ጀብዱ ዎች የሚፈጸሙት በዚህ ባሕርይ ዋጋ ነው ። የሞያ ሕሊና ልዩ ልዩ መሠረቶች አሉት ።

ሀ. ሥራን ለሥራ ሲሉ ማክበር ፡—

ይህ ሁኔታ ታላቅ ስሜትን ይጠይቃል ፤ ለምሳሌ ፥ የሠ ራተኛ እጅ ፥ ቤተ መቅደስ ሲሠራ ፥ ወይም አንድ ወንበር ሲሠራ ፥ ጥንቃቄው ፥ ትጋቱ እኩል መሆን አለበት ።

ለ. በሥራ ራስን ማክበር ፡—

ሰው ራሱን ለመግመት የሚችለው በሥራው ነው ። የመንፈስ እርጋታ ለማግኘትም የሚችለው ሌሎቹ ለሥራው በሚሰጡለት ግምት መሠረት ነው ።

መ. የኃላፊነታችን ስሜት ፡—

እያንዳንዱ ሰው ለሕብረሰብ አገልጋይ መሆኑን አምነ ናል ፤ ስለዚህ ሕብረሰብ በኛ ላይ የጣለብንን አደራና እም ነት ማክበራችን የሚሰማንና የምናውቀው ፥ የተሰጠንን ሥራ በሚገባ ፈጽመን ስንገኝ ነው ። አለዚያ የሕሊና እረ ፍት አናገኝም ፤ የሞያ ሕሊና በሰብዓዊ ተባባሪነት ውስጥ ትክክለኛ ዳኝነት ያስገባል ። አለዚያ ተባባሪነት ዋጋ ያ ጣል ። በያለበት ያነክሳል ፥ እያንዳንዱም ሰው በሌላው ላይ እምነት ስለማይኖረው ተባባሪነት መኖሩም አይሰማንም ።

ስለዚህ የሞያ ሕሊና ከታላላቆቹ ሞራላዊ ተግባሮች አንዱ ነው ። የሞያ ሕሊና የሌለው ሠራተኛ ሌሎቹ የጣሉ በትን እምነት ማጉደሉ ነው ፤ እንዲያውም በጥፋት ውስጥ ሊጨምራቸው ይችላል ። ለምሳሌ ያህል ፥ መድኃኒቱን በጥንቃቄ የማይቀምም መድኃኒት ሻጭ ፥ በሥርዓት የማይ መረምር ኃኪም ፥ በአድልዎ የሚፈርድ ዳኛ ፥ እንድን ሕዝ ብ ጨርሰው ሊያጠፉት ይችላሉ ። ከሁሉም ይልቅ የሚያሳ

ዝነው በዚህ ሁኔታ የተበደለ ሰው ፥ በሌላ ሰው ላይ ለወደፊቱ እምነት ስለሚያጣ ተባባሪነትን ይጠላና ወደብቸኝነት ስለሚያዘነብል ፥ ከቀን ብዛት መተማመንና መረዳዳት ይጠፋና ሰው ሁሉ እንደ አውሬና እንደ አዳኝ ሲፈላለግና ሲደባበቅ ሊኖር የሚችልበት ሁኔታ ሊፈጠር መቻሉ ነው ።

የሞያ ሕሊና የሚገጥመው ችግር ፡—

የሞያ ሕሊና ጉድለት ባገራችን ብዙ ችግር ይፈጥራል። ለምሳሌ ፥ የፖስታ ቤት ሠራተኞች ፥ ግዴለሽነት ሕዝብ በፖስታ አገልግሎት ከመጠቀም ይልቅ አሁንም በሰው መላላኩን ይመርጣል ። የትራፊክ ፖሊስ ቸልተኝነት ብዙ አደጋዎች ሊያስከትል ይችላል ፤ የሞያ ሕሊና ከሌለ ማንኛውም ሥራ በሰው ፊት ሞገስና ጠቃሚነት ሊያገኝ አይችልም ።

ሰው ብቸኝነት እንዲሰማው አያስፈልግም ፡—

ከሁሉ አስቀድሞ ሰው ብቸኝነት እንዲሰማው አያስፈልግም ፥ በሥራውም በጓደኞቹ መካከል መገኘቱና እነርሱም ለሞያው ተገቢውን ግምት እንደሚሰጡለት ማወቅ አለበት፤ ስለዚህ የጠበቆች ሕብረት ፥ የሐኪሞች ሕብረት ፥ በጠቅላላው አንድ ዓይነት ሥራ የሚሠሩ ሰዎች ሕብረቶች መኖራቸው ፥ እያንዳንዱ ሰው ብቸኛ አለመሆኑ ስለሚሰማውና የሞያ ሕሊናውንም የሚቆጣጠሩት የሥራ ጓደኞች እንዳሉት ሲያውቅ ይበልጥ ይጠነቀቃል ።

ሰው በሥራው መናቅ የለበትም ፡—

ደግሞም እያንዳንዱ ሰው በሚሠራው ሥራ ዝቅተኝነት መናቅ የለበትም ። ባገራችን ይህ ሁኔታ የሚፈጥረውን

ችግር ሁላችንም እናውቀዋለን ፤ በአዲሱ ዘመን በሕግ ረገድ ከፍተኛና ዝቅተኛ ሥራ አለመኖሩ የታወቀ ነው ። ነገር ግን የቀድሞ ጊዜዎች ቅሪት ሆኖ በተለይ እጀሠሪዎችን የመናቅ ስሜት ጨርሶ አልጠፋም ፤ የሠራተኞቻችን ድርጅት በሁለት ታላላቅ ክፍሎች የተለየ ይመስላል ።

ባለአእምሮዎችና እጀሠሪዎች ፥ የጽሕፈት ሥራ ከሌሎቹ ሥራዎች በለጥ ተደርጐ ይገመታል ። የጸሐፊው ሚስት ፥ ላም የምታልበውን የገበሬ ሚስት ትንቃለች ፥ ከሁሉም የሚያሳዝነው የእጀሠሪ ልጅ ፥ አባቱ ምንም እንኳን በሥራው በቂ ገንዘብ ቢያገኝበት ፥ ወደፊት ያባቱን ሥራ ወርሶ ለመቀበል ያለው ጥላቻ ነው ። በዚህም የተነሣ በየትም ሕርት ቤቱ የሚገኙት ወጣቶች ፥ ትምሕርታቸውን ጨር ሰው የመንግሥት ባለሥልጣን ፥ የጽሕፈት ቤት ሹም ለመሆን በመጣራቸው የአስተዳደር ሥራ ተጨንቆና ተጠቦ ሲገኝ እጀሥራ ሰው አጥቶ ባዕዶች ለመቅጠር ይገደዳል ። የእርሻ ትምሕርት ተምሮ ከኰሌጅ የወጣው ገበሬ ሆኖ በዘመናዊ ዘዴ በመሥራት ፈንታ እርሻ ሚኒስቴር ውስጥ መቀጠር ይፈልጋል ። ስለዚህ ማንኛቸውንም ዓይነት ሥራ የሚሠሩ ሰዎች እኩያ መሆናቸውን ያመኑ ዕለትና እጀሠሪ በጨዋነት ተግባሩን ካከናወነ ከማንም የማያንስ ሰው መሆኑን ሲረዱ ፥ አገር ታላቅ እርምጃ አደረገች ለማለት ይቻላል ። ነገር ግን አንድ ሰው በተናቀው ክፍል ውስጥ መገኘቱ በስሜቱ ውስጥ እስካለ ድረስ እውነተኛ መሻሻል ሊገኝ አይችልም ።

ሥራና ኤኮኖሚካዊ ድርጅት ፡—

በኤኮኖሚካዊ ድርጅት ውስጥ ዳኝነት እንዲኖር ያስ ፈልጋል ። ከሁሉም የባሰው የዳኝነት ጉድለት ፣ በሃብት መከ ፋፈል ላይ ያለው ነው ። የሰውን ሕይወት ያበላሻል፤ከማበሳ ጨቱም በቀር የሚያስከትለው ችግርና እጦት ፣ የሚያሰቃ ይና የሚገድልም ነው ። ሥራ የመንፈስም የሞራልም ዳኝ ነት ይጠይቃል ። በመንፈስ ረገድ አንድ ሰው የሚሰጠው አበል ከሚሠራው ሥራ ጋር ያልተመጣጠነና አነስተኛ ሲሆ ንበት ሥራውን በእውነተኛ ሕሊናና ጥሞት ሊያከናውን አይችልም ። በሞራል ረገድ ደግሞ አንድ ሰው ሕብረሰብን ለማኖርና የጋራ ሃብትን ለማደርጀት ፋንታውን መሥራት ሲኖርበት ፣ በአገልግሎቱ መጠን መብት አለው ። (ድርሻ እንዲሰጠው)

በሥራው የሚያስገኘውንም ፍሬ ባለቤት የመሆን ወ ይም ተመዛዛኙን ዋጋ የማግኘት መብት አለው ። ነገር ግን አብዛኛውን ጊዜ ንብረትና ሥራ እኩል ተደላድለው አይገ ኙም ። ምንም የሌላቸው ሰዎች ሥራ አጥተው ይቸገራሉ ፤ ደግሞ ሥራ እያላቸው ለመተዳደሪያቸው በቂ አበል የማያ ገኙ አሉ ፤ እንዲሁም ሃብት ያላቸውና ሳይሠሩ ሊኖሩ የሚ ችሉ ደግሞ ይገኛሉ ። ይህ ሁኔታ ለሞራል ተስማሚ አይደ ለምና ሥርዓት ያስፈልገዋል ።

ንብረት ፡—

ንብረት ማለት ፣ ንብረቱን መያዝ ብቻ አይደለም ፣ ሕ ጋዊ ይዞታን ይጠይቃል ። ባለንብረቱ ፣ በንብረቱ እንደፈ

ቀደ እንዲያዝበት በሕግ ተፈቅዶለታል ። በዚህም መብቱ የተነሣ ንብረቱ የሆነውን ነገር ሌላ እንዳይወስደው ወይም እንዳይጠቀምበት ሊከለክል ፣ እንዲሁም ሊወስደው ወይም ሊጠቀምበት ከሚፈልገው ሰው ዋጋ ሊጠይቅ ይችላል ማ ለት ነው ።

የንብረት ሕጋዊነትና ወሰኑ ፡—

ንብረት ማበጀት ከሰው ተፈጥሮ ጋር በጣም የተሳሰረ ስሜት ነው ፤ እያንዳንዱ ሰው የራሱ የሆነ ነገር እንዲኖረው ይሻል ። ንብረት ከሥራ የተገኘ ፍሬ ሲሆን ሕጋዊ ነው ። የወንዝ ውሃ የሁሉ ነው ፤ ነገር ግን በእንሥራዬ ከቀዳሁት በኋላ የኔ ነው ። እንዲሁም ባሕር የሁሉም ቢሆን የተጠመ ደው አሣ የአጥማጁ ንብረት ነው ። ስለዚህ ከሥራ ፍሬ የመ ነጨ ነገር ባለንብረቱን አያሳፍረውም ። የመሬት ይዞታም እንዲሁ ነው ። የመሬቱ ባለቤት መሬቱን ካረሰና ከተጠቀ መበት ይዞታው ተገቢ ሊሆን ይችላል ። መሬቱን ያለሥራ ሲተወው ግን በባለቤቱና በመሬቱ መካከል ያለውን ግንኙ ነት መቋረጡ ነውና ባለቤትነቱ መሠረት አይኖረውም ።

ውርስ ፡—

የውርስ ነገርም በጣም አከራካሪ ነው ። በምን የተነሣ አንድ ሕጻን ሲወለድ የብዙ ንብረት ባለቤት ሲሆን ሌሎቹ ሕጻናቶች አንድም ነገር ሳይኖራቸው ይቀራሉ ? በዚህ ምክ ንያት የሚፈጠረው ልዩነት መንፈስን ይገጫል ፤ ያለአንድ ሃብት መወለድም በሕይወት ጉዳና ለመግፋት ታላቅ እንቅ ፋት ስለሆነ ፣ ብዙዎቹ አቅቷቸው እመንገድ ይቀራሉ ። በሰው ሕይወት ታላቁ ችግር ፣ ረኃብ ቀን አለመስጠቱ

ነው ። ባንድ በኩል ደግሞ ፥ ውርስን መከልከል ንብረት የያዘው ሰው በንብረቱ እንዳያዝበት መከልከል ነውና የንብረት ይዞታ መብት ሊፈርስ ነው ።

ደግሞም በጠቅላላው ሰው የሚለፋው ላቤተ ሰቦቹና ለልጆቹ ጥቂት ቅርስ ልተውላቸው በማለት ተስፋ ስለሆነ ፥ ውርስን መከልከል የቤተሰብን ተባባሪነት ሊጐዳም ይች ላል ። ነገር ግን መካከለኛ መንገድ ሊያረግለት ይቻላል ። ከብዙ ዘመን ጀምሮ እንዳየነው እጅግ ከፍ ያለ ንብረት የወ ረሱ ፥ ልጆች ሳይሠሩ ሊኖሩ ይችላሉና ባለፉት ገጾች እንዳ ተትነው ሁሉ ያለ ሥራ መኖር ደግሞ ሌላ ጊዜ ማሳለፊያ ዘዴ ስለሚጠይቅ ወደጨዋታና ወደፈንጠዝያ ያመራሉ ። ዕ ድል የገጠማቸው የወረሱትን ሳይጨርሱ እድሚያቸውን ይፈጃሉ ። ነገር ግን ለሕብረሰብ አንድም እርዳታ ሳያደርጉ ለትና አንድም ጠቃሚ ነገር ሳይሠሩላት ያልፋሉ ። ያልታ ደሉት ደግሞ የወረሱትን ሻሽጠው ሲደሰቱና ገንዘባቸውን ሲበትኑ ይቆዩና ንብረታቸውን ጨርሰው ችግር ውስጥ ይገ ባሉ ። በዚያን ጊዜ እንሥራም ቢሉ ወትሮ ያልተለመደ ነ ገር ስለሆነ ያቅታቸዋልና በክንቱ ወድቀው እንደገና ለሰው ዘር ሸክም ሆነው ይገኛሉ ።

ስለዚህ መድኃኒቱ ወላጆች ምንም ሃብት ቢኖራቸው ፥ ልጆቻቸውን ሳያሞላቅቁና ሥራን እያስተማሩ ማሳደግና ከዚህ ዓለም ሲለዩም የኑሮን ትግል ለማሸነፍ የሚችሉበት ሃብት አውርሰው የቀረውን ሠርተው እንዲያገኙ ማድረግ ነው ። እጅግ ንብረት ያበጁት ወላጆች ደግሞ ትርፉን ለበጐ

አድራጐት ድርጅቶች ቢያወርሱ ለሕብረሰብ ብቻ ሳይሆን ለልጆቻቸውም ከፍ ያለ ውለታ ይውሉላቸዋል ።

<u>የሃብትና የሥራ ሙግት ፡—</u>

በኤኮኖሚ ረገድ እጅግ አስቸጋሪ የሆነው ቀጥሎ የተ መለከተው ሁኔታ ነው ። በመሠረቱ ንብረት ሁሉ ሊሸጥ ሊለወጥ የሚቻል ነገር ነው ። ነገር ግን የመለዋወጥና የመሸ ሻጥ ሥራ ፥ በአጋጣሚም የተነሣ እንዲሁም በሽሚያና በስ ስት ምክንያት ፥ አንዳንዶቹን ሲያከስር አንዳንዶቹን ደ ግሞ ያበለጽጋል ። ሃብትም በነዚህ ዘንድ ሲጠራቀም ከቀን ብዛት ካፒታሊስቶች (ባለዋናዎች) ይሆናሉ ። በድሆች ሥራ ላይም መብትን ይይዛሉ ፥ ሥልጣናቸውም ከእውነተኛ ንግ ሥና አያንስም ። በሥራው ብቻ የሚተዳደረውና ሳይሠራ ለመቆየት የማይችለው ሰው መቆየት የሚችለውን የካፒታ ሊስቱን ፍላጐት መቀበል ግዴታ ስለሚሆንበት በችግር ሁኔታ ውስጥ ይገኛል ። በዚህ አኳኋን ሃብትና ሥራ ይለያ ዩና ተቃራኒ መሆን ይጀምራሉ ፤ ይህ መለያየትና ተቃራኒ ነት በተለይ በኢንዱስትሪ ረገድ ከክንዳቸው በቀር ሌላ ኃይል የሌላቸውን ሠራተኞችን የጥቂት ካፒታሊስቶች ንብ ረት ያደርጋቸውና አቅማቸውን በወራዳ ዋጋ ማከራየት ግ ዴታ ይሆንባቸዋል ።

በሃብትና በሥራ መካከል ያለው ተቃራኒነት እንዲ ጠፋ በመሞከር ብዙ ዓይነት የኤኮኖሚ አስተዳደር ዘዴ ዎች በየጊዜው ተፈልስፈዋል ። ቢሆንም በዚች መጽሐፍ ስለያንዳንዱ ለመናገር ስፍራው ስላልሆነ ፥ ባጭሩ በሞራ

ል ረገድ በኤኮኖሚካዊ ኑሮ ዳኝነት ሊፈጽም የሚገባውን ለመዘርዘር እንሞክራለን ።

1. ለሰብዓዊ ሕይወት መተማመኛ መስጠት ፥ የሥራው ፍሬ ለሱ እንደሚሆን ማረጋገጥ ፥ ላንድ ሰብዓዊ ሕይወት ሕልውናና ለሞራላዊ ኑሮው በጥቂቱ አስፈላጊ የሚሆነውን ሃብት እንዲያገኝ ማድረግ ።

2. ነጻነቱን ማክበር ፥ ማለትም እንደሸቀጥ ሊቆጠር የማይቻለውን ሰውነቱንና ሥራውን ከካፒታሊስቶች እብሪት መጠበቅ ፤ የጋራ ሕይወትን በሚመሩት ሕጐችተካፋይ እንዲሆን ማድረግ ።

3. ሰብዓዊነቱ እያደገ እንዲሄድ ማድረግ ፤ የተመቻቸው ሰዎች ሠራተኛን እንዳይንቁ ፥ ሠራተኛ በተመቻቸው እንዳይቀና አስፈላጊውን ትምሕርት በሰፊው መስጠት ።

በምድር ላይ ማናቸውም መሻሻል ቢደረግ በሰዎች መካከል የኤኮኖሚካዊ ኑሮ ልዩነት አይቀርም ። ነገር ግን አንድ አንድ ዓላማዎች ፍጻሜ ቢያገኙ እነዚህ ልዩነቶች በጣም እየተቃለሉ እንደሚሄዱ እናምናለን ።

1. የእኩልነት መንፈስ ፡— ሰዎች አንዱ ባንዱ ላይ ያላቸውን የመናናቅ ስሜት ለማስወገድ ፈቃደኛ እንዲሆኑና ሥራቸውን ፥ ማሕበራዊ ደረጃቸውን ሳይመለከቱ እኩል መሆናቸውን እንዲገነዘቡ ።

2. መጠነኛነት ፡— የእኩልነት መንፈስ ላንድ ሰው ሕይወት አስፈላጊና በቂ የሆነውን ብቻ ወደመገመት ስሜት

ይመራል ፤ የያንዳንዶችንም ፍላጐት አንድ ሰው ሊያፈራ ከሚችለው በላይ እንዳይሄድ ይገታናል ፤ ሞራላዊ ሕይወት እንዲፈካ ፥ የምኞት አነስተኛው መጠን አስፈላጊ መሆኑን ገልጸናል ። ፍላጐትን መግታትም በዚሁ መጠን አስፈላጊ ነው ። ጸጋ ፥ ከደስታ ፍላጐትና ከልክ በላይ ከሆነ የገንዘብ አምሮት ጋር አብሮ ለመኖር አይችልም ። የዚህ ዓለም ደስታ በመጠን ላይ የተመሠረተ መሆኑን በማስረዳትና በማስተማር ልጆች እንዲገነዘቡ ማድረግ ይቻላል ።

3. ዳኝነትና ሞራልን በማክበር ተባባሪነት ቋሚ እንዲሆንና ዋጋ እንዲኖረው ማድረግ ፤

4. እንደ ተባባሪነት መንፈስ ንፉግነትን ለማስታገስ የሚችል ነገር የለምና ይህን መንፈስ በተቻለ ማስፋፋትና ማጠንከር ፥ ያስፈልጋል ። ሰው ለዚህ ዓለም ሃብት ከልክ በላይ የሚጓጓው ባንድ በኩል በስስት ሲሆን ባንድ በኩል ደግሞ ለኑሮው በመስጋት ነው ። የሌሎቹን ሰዎች ተባባሪነት ካላገኘ ብቸኝነት ይሰማዋልና መድሕኑ ሃብት ብቻ ሆኖ ያገኘዋል ። የሌሎቹን ተባባሪነት ሲያገኝ ግን ንፉግነትን ከራሱ ለማስወገድ አይመለስም ፤ ይህ ሁሉ የሰው ዘር ፈቃደኛ ከሆነ በደስታና በሰላም ለመኖር የሚችል መሆኑን ይገልጽልናልና እንደዚህ ያለ ቀላል መንገድ ሲኖር ለምን እንለያያለን ፥ ለምንስ እንጣላለን ብለን መደነቃችን አይቀርም ።

— ማሳሪጊያ —

ይህች መጽሐፍ እዚህ ላይ ተፈጽማለች ፤ በመጀመሪ ያው ክፍል እንዳያችሁት ፣ ሰው እንደምን በማሕበር እንደ ሚኖርና እንደሚተዳደር ባጭሩ ገልጫለሁ በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ስለሞራል ጥቂት ገጾች ጽፌያለሁ ።

ሞራል በጐና ክፉን ለይቶ ለማወቅና ለያንዳንዱ ነ ገር ትክክለኛውን ግምት እንድንሰጥ ፣ ለአምሮታችን ፣ ለስ ጋችንና ለኃዘናችን መጠን እንድናበጅ ፣ የመንፈስ ኃይላ ችንን እንድናጠነክርና በሕይወታችን ጊዜ ሁሉ የሚደርሱ ብንን ፈተናዎች ሰብዓዊ ክብራችንን ፣ ሳናዋርድ እንድንች ላቸው የሚያስተምረን ጥበብ ነውና ፣ በአዲሱ ዘመን ው ስጥ ለሚጓዘው የኢትዮጵያ ሕዝብ መጽሐፉ በቂ መግለጫ እንዲሆን እመኛለሁ ።

የሥልጣኔ እርምጃ ፣ የአካላዊና የማሕበራዊ ኑሮ መለ ዋወጥ ፣ ለደካማው ተፈጥሮአችን የቀረበውን ጥያቄ እጅ ግም መስመር አላስለቀቁትም ። ዞሮ ዞሮ መኖርን ማወቅ ፣ መከራን መቻል ፣ ሞትን መቻልና ፣ በማሕበር ስለምንኖ ርም የጋራ ሕይወታችንን ጥቅም ከግላዊ ኑሮአችን ጋር ማስ ማማትን ይጠይቃል ። የዚህ ጉዳይ ከፍተኛነት እውቀቱን ፣ ኃይሉንና ሃብቱን ፣ ብዙ ጊዜ ለራሱ መጥፊያ ሲያደርገው በምናየው በሰው ዘር አድራጐት ግልጽ ሆኖ ይታየናል ። የሞራል ግዳጆችን ማወቅ ከዚህ ሁሉ ሊያስጥለንና ወደ ደህናው መንገድ ሊመራን ይችላል ።

— ተ ፈ ጸ መ —